በ ኢትዮጵያ ምድር የተከናወነ ዘግናኝ ታሪክ

# ኤፍ...!



ከዚርግ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ምድር የተከናወነ ዘግናኝ ታሪክ!!

# ኤጭ....!

አዘርግ

2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ይህን አዝናኝ አስተማሪ መፅሐፍ መልሶ ለማሳተም

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

ኮፒራይት © 2010 አዘርግ

## ቀደምት ስራዎች

1. የሆነ የሆነ ነገር ይሠማኛል 2003
2. ኢያሪኮ 777 2004
3. ኢያሪኮ 888 2004
4. ኢያሪኮ 999 2005
5. አዳምና ሄዋን 2005
6. አቢሲኒያ 24 2005
7. አ ... ዘንደኪ 2006
8. አ ... ያያያ 2006
9. በኢያሪኮ ከተማ 2007
10. ሹካ ቱስ 2007
11. ሽርብትን 2008
12. ቋ (አንድ) 2008
13. ለሚስቴ ባል ፍለጋ 2009
14. በኢያሪኮም ጩኸት በዛ! 2009

## አጭር ማስታወሻ

## ለውድ ተደራሲያን!!

ይህ ኤጭ የተሰኘው ዘግናኝ በኢትዮጵያ ምድር እየተከናወነ ያለ እነሆ 30% እውነተኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይህን ታሪክ ስነጽሁፋዊ ለዛ እና ጣዕም እንዲኖረው 70% ምናባዊ ትዕይንቶች አብረውት እንዲፈሱ ተደርጓል፡፡

በተረፈ ጀማሪ ፀሐፊዎች ምንም ይፈጠር ምንም ሳትሰላቹ እና ሳታወላውሉ እንዲሁም “ኤጭ ምንም ላደርግ አልችልም ብላችሁ” ሞራላችሁን ዝቅ ሳታደርጉ ታገሉ! ታገሉ! ... በብዙ ትግል በእርግጠኝነት ስኬታማ ትሆናላችሁ!!

አዘርግ - 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ፡፡

# ማስታወሻነት

ለቅን ኢትዮጵያዊያን በሙሉ!!

# 1

## ደብረ ማርቆስ

(ከ1988 እስከ 2000 ዓ.ም)

ማን ነው ተጠያቂው? ህይወት? ሴይጣን? አጋጣሚ? ዕጣፋንታ? ወይስ ታላቁ ፈጣሪ? ወይስ ሁሉም ተጠያቂዎች አይደሉም? ወይስ ተጠያቂ የሚባል ነገር የለም? አልያስ ከፀሐይ በታች ያለው ሁሉ ከንቱ ንፋስን እንደመከተል ነው የተባለው እውነት ይሆን? እውን ከጸሐይ በታች ያለው ሁሉ የከንቱ ከንቱ ነው? የከንቱ ከንቱ ለሆነ ነገርስ መጨነቅስ አስፈላጊ ነው? የከንቱ ከንቱ ከሆነስ ስለምን ከጸሐይ በታች ያለው ሁሉ ተፈጠረ? ስለምን የምድር ነዋሪዎች ከእነ ግሳንግሷ ተፈጠሩ? ወይስ ከንቱ መሆን ራሱ ከንቱ አለመሆን ነው ? ወይስ መሆን አለመሆን! አለመሆን መሆን! መሆን መሆን! አለመሆን አለመሆን! አለመሆን መሆን ነውን? ለነገሩ አለማሰብ፣ አለመጨነቅ ፣ አለሙብሰልሰል፣ በዝምታ ያለ አንዳች የጥያቄ ናዳ መቀመጥስ ይቻላል? ከተቻለስ ይህስ ከንቱ አይደለም? ከንቱ ባይሆን እንኳ ከንቱ አለመሆን ራሱ ከንቱ አይደለም?

ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ? ስለምንስ ይህን ያህል ስለከንቱ መሆንና አለመሆን ተወጥሬ አብሰለስላለሁ? ስለምንስ ብቻዬን እቆዝማለሁ? ለመሆኑ እንደው ለአባባል ካልሆነስ ሰው ብቻውን መቀመጥ ይችላልን? አጠገቡ ሴይጣን የለም? አጠገቡ መላዕክት የሉም? አጠገቡ የሚያብሰለስለው ሀሳብ የለም? እንኪያስ እኔ ብቻዬን ተቀምጬ እውን ብቸኛ ነኝ ማለት ይቻላልን? ፈጣሪ እንኳ ብቻውን መሆን ይችላል? ፈጣሪ እንኳ ሰማይና ምድርን ሲፈጥር መች ብቻውን ነበር? እውን ከፀሐይ በታች ይሁን ከፀሐይ በላይ ብቸኝነት የሚባል ነገር አለን? ስለምንስ ውስጤ በአንዳች የባዶነት ስሜት ይናወጣል? ስለምንስ ዘወትር ቀይና ጥቁር

በሆነ በማያልቅ ጥያቄ እናጣለሁ? ስለምንስ በግዴለሽነት ወንዝ አብዝቼ እንቦራጨቃለሁ? ስለምንስ ስለ ህይወት ከንቱነት አብዝቼ አውጠነጥናለሁ? ስለምንስ ሁሉ ነገር የከንቱ ከንቱ ንፋስን የመከተል ያህል ነው እላለሁ? ስለምንስ በከፍተኛ የተስፋ መቁረጥ ማዕበል ውስጥ እዋኝቃለሁ? ስለምንስ ስለዓለም በግዴለሽነት ማዕበል ተሞልቼ አውጠነጥናለሁ? ስለምንስ መጀመሪያም መጨረሻም በሌላቸው የጥያቄ እና የሀሳብ እንቆቅልሾች እያውጠነጠንኩ ራሴን እጀዝባለሁ? ስለምንስ በፍልስፍና መንገድ ለመኳተን እታትራለሁ? እንደፋደፋለሁ?

ማን ነኝ? መጨረሻዬስ ምንድ ነው? ለመሆኑ መጨረሻውን የሚያውቅስ አለ? እንኳን እኔ ያለ ፍላጎታቸው ከፀሐይ በታችም ሳይሆን ወይም ከፀሐይ በላይም ሳይሆን "ገነት" በምትባለው የሀሳብ መንደር የተፈጠሩት ሁለቱ ሚስኪኖች ቀዳማይ አባታችን አዳም ሆነ እናታችን ሄዋን መጨረሻቸውን ያውቁ ነበር? መንገዱን ከፈጣሪ ጋር ያደረገው ታላቁ ሙሴ መጨረሻውን ያውቅ ነበር? ታላላቅ የዓለማችን ነገስታት መጨረሻቸውን ያውቁ ነበር? አያውቁም!! እና እኔ አንዲት ሚስኪን እንዴት የመጨረሻዬን ላውቅ እችላለሁ?

እ

ና

ም

ስለ መጨረሻዬ መናገር አልችልም:: አለመቻሌ ከንቱ ነው:: በእርግጥ ስለ መጨረሻዬ መናገር ብችልም እንኳ ከንቱ ነው:: በዚች በከንቱ የተወጠረች ዓለም ውስጥ የሰው ልጅ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ስለሚሆነው ነገር በእርግጠኝነት መናገር አይችልም:: መገመት መብቱ ነው:: መመኘት መብቱ ነው:: ተስፋ ማድረግ መብቱ ነው:: ሂሳባዊ ቀመር መስራት መብቱ ነው:: ይህን ማን ይከለክለዋል? ለማንኛውም ስለመጨረሻዬ መናገር ባልችልም ስለተወለድኩባት ቀን... አሁን እስካለሁበት ቀን ድረስ ያለውን መናገር እችላለሁ! መተርተር እችላለሁ! መቀባጠር እችላለሁ! በእርግጥ ይህም ከንቱ ነው! ንፋስን የመጨበጥ ያህል ነው::

እዚች ግራ አጋቢ የሆነች ቁሌታም የሴይጣን ምድር ላይ የመጣሁት በግዕዝ አቆጣጠር ሚያዚያ 25፤1988 ነበር:: እኔ በእርግጥ ምድር የሴይጣን መሆኗን አምናለሁ:: ይህን ያመንኩት ደግሞ ቀዳማዊት እናታችንን ሚስኪኗን ሄዋንን ጉድ የሠራት ሴይጣን ... በእባብ ተመስሎ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ባደረጉት ግልፅ ውይይት ነው::

"… ዲያብሎስም እጅግ ረጅም ወደሆነ ተራራ ወሰደው ፤ የዓለምንም መንግስታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው…" ተብሎ ተፅፏል፤ እናም ይቺ የሴይጣን ምድር ላይ የመጣሁት ሚያዚያ 25፣ 1988 ዓ.ም ከአዲስ አበባ 299 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው በደብረማርቆስ ከተማ ነው:: በፍቅር አስጨርስ መንገድ ላይ ከሚገኙት ቤቶች በአንደኛው የሀብታም ግቢ ውስጥ በታላቅ እልልታ ተወለድኩ:: ከታሪካዊው መንቆረር ት/ቤት ወደታች በሚገኘው ቤታችን ውስጥ ያለፍላጎቴ ይቺን ምድር እኔም እንደ አዳምና ሄዋን ተቀላቀልኩ::

አባቴ 140 ኪሎ የሚመዝን ፤ ጥቁር፣ መልከ መልካም ፤ በኩራት መራመድ የሚወድ ግዙፍ ሰው ነው:: ስሙ ፍቅር አብርሃም ይባላል:: በእርግጥ ስሙን ፍቅር አብርሃም ከሚሉት ሴይጣን አበረ ቢሉት ምርጥ እና ድንቅም ይሆን ነበር:: ስለ አባቴ ብዙ ማውራት መሻቱ ስለሌለኝ ይህ ዐ/ነገር በቂ ነው:: ሚስኪኗ እናቴ ቀይ ፤ ቀጠን ያለች፣ ፈገግታ የማይለያት፣ ወላዋይ ፀባይ ያላት ስትሆን አስቴር ሳምሶን ትባላለች:: 55 ኪሎ የምትመዝነዋ እናቴ ለአባቴ የበኩር ልጇን እዩኤል የተባለ ልጅ የወለደችለት ቢሆንም የተወለደው ልጅ አንድ ዓመት ሳይሞላው ሞተ:: ይህ አሳዛኝ ገጠመኝ በሆነ በሁለተኛው ዓመት እኔ ተወለድኩ:: እንደተነገረኝ የእናቴ እና አባቴ ደስታ በቃላት የማይገለፅ ነበር አሉ… ታላቅ ፌሽታ ነበር አሉ… ታላቅ ድግስ ነበር አሉ… 12 ግዙፍ በሬዎች ታርደው ነበር አሉ… 12 ግዙፍ በሬዎችን ማረድ ለእናቴ እና አባቴ ተራ ነገር ነች፤ ምክንያቱም አባቴ የገንዘብ ችግር የለበትም:: የናጠጠ ሀብታም ነው:: ሁለት ከፍተኛ ገበያ ያላቸው ሆቴሎች፣ ወርቅ ቤት ፤ ጅቡቲ የሚመላለሱ በርካታ የጭነት መኪናዎች ፤ ግዙፍ ብረት መሸጫ፣ ብሎኬት ማምረቻ ፤ ሁለት ዘመናዊ የቤትና የመኪና ዕቃዎችን ከጣሊያን እና ዱባይ እያስመጣ የሚሸጥባቸው ግዙፍ የንግድ ድርጅቶች ያሉት… በደብረማርቆስ ብቻ ሳይሆን እስከ አዲስ አበባ ፤ ባህር ዳር ፤ ሞያሌ፣ መቀሌ እና ጅቡቲ ድረስ በሀብት ላይ ሀብት በማከማቸት ስሙን ለመትከል የቻለ ዝነኛ ግለሰብ ነው:: እናም የተወለድኩት እብድ ያለ ሀብት ካላቸው ቤተሰብ ውስጥ ነው:: በእርግጥ ይህም ከንቱ ነው:: ውሃን የመጨበጥ ያህል ነው:: ንፋስን አቅፎ የመያዝ ያህል ነው::

እነሆ ይቺም ትሞትብን ይሆን የሚል ፍራቻ ነበራቸው አሉ፤ እናም በስስት ይከታተሉኝ ነበር:: አልሞትኩም:: የመጀመሪያ ዓመት ልደቴ በታላቅ ፌሽታ ተከበረ:: ሁለተኛውም በታላቅ ኳኳታ ተከበረ:: ሶስተኛውም በታላቅ ዳንኪራ ተከበረ:: አራተኛውም

በታላቅ ፈንጠዚያ ተከበረ፡፡ በዚህ መሀከል ሌላም ታላቅ ደስታ በቤታችን ሆነ፡፡ እናቴ ሌላ ልጅ አረገዘች! ምንዋጋ አለው? እኔ ዝርዝር ጉዳዩን ባላውቅም ስምንተኛው ወር ሲሆናት ተጨናገፈ፡፡ እናቴ በሀዘን ልቧ ተሰበረ አሉ፡፡ ይበልጥ ሌላም ሀዘን ጨመሩላት! እናቴ በድጋሚ መውለድ እንደማትችል ቅስሟን የሚሰብር መርዶ ተነገራት! ትልቅ ሆኘ ጉዳዩን ሳጣራ እናቴ በወጣትነቷ በዚያ በፍንዳታ ዘመኗ ሁለት ጊዜያት ተማሪ እያለች አስወርዳ ነበር፡፡ ያ ትልቅ ሴት ስትሆን ችግር እንደፈጠረባት ሰማሁኝ፡፡ ማስወረድ የኋላ የኋላ ከፍተኛ ጣጣ እንደሚያመጣ እና ምነው ያን ጊዜ ባላደረኩት በሚል ፀፀት ህሊናችን እንደሚወጠር አወኩ፡፡

ት/ቤት ገባሁ፡፡ የዚያን ሰዓት አብዝቶ ውብ መሆኔን አወኩ፡፡ ትንሹም ትልቁም የሚያወራው ስለእኔ ውበት ነበር፡፡ በመልክ ዳይኖሰር የሚያክለውን አባቴን ቁርጥ ነኝ፡፡ ፀጉሬ እንደ አባቴ የሚያምር ሉጫ እና ደማቅ ጥቁር ነው፡፡ መልካችን ቁርጥ አንድ ዓይነት ነው፡፡ አወራራችን ቁርጥ ተመሳሳይ ነው፡፡ ሳይንስ ውሸት መሆኑን አሳብቄ ነበር፡፡ ሳይንሱ እንደሚቀደደው ከሆነ “ማንኛውም ልጅ ከእናቱ 23 ክሮሞዞም፣ ከአባቱ 23 ክሮሞዞም ባንድነት 46 ይዞ ይወለዳል” የሚለው ለእኔ የሰራ አይመስለኝም ፤ እናቴን በምንም መልኩ አልመስላትም ነበር፤ ምናልባት ቅጥነትን የወረስኩት ከእናቴ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ይበልጥ ቤተሰቡ ግራ የተጋባው በእውቀቴ ነበር፡፡ በእርግጥ አባቴ የናጠጠ ሀብታም ቢሆንም ሀብቱን ያገኘው ባልታወቀ መንገድ ለዚያውም በትንሽ ዓመት ውስጥ ተነስቶ መሆኑን እንጂ ትምህርት ያልተማረ ምርጥ ደነዝ ነው ሲሉ ሠምቻለሁ፡፡ እንደ ቀድሞ በኢትዮጵያዊነት ፍቅር ያበደው ግን ጨካኝ እንደነበረው መንግስቱ ኃ/ማርያም እየወደቀ እየተነሣ እስከ ስድስተኛ ክፍል የተማረ መሆኑን ሰምቻለሁ፡፡ እናቴም ከአባቴ ባነሰ ከእውቀት ነፃ ነች፡፡ ትምህርት ጭራቅ እና ተራራ ሲሆንባት ያቋረጠችው አራተኛ ክፍልን በሁሉም የትምህርት ዓይነት ፈርጣ መሆኑን ሰምቻለሁ፡፡ እኔ ግን በጣም አወዛገብኩ፡፡ እኔ ግን ይህ እንዴት ይሆናል አስባልኩ! እውቀት ከቤተሰብ ሊተላለፍ እንደማይችል በአራት ነጥብ አስመሰከርኩ!!

በደብረማርቆስ በሚገኘው የሀብታም ልጆች ይማሩበታል በሚባለው እና የካቶሊኮች

ትምህርት ቤት እንደሆነ በሚታመነው ስሙ በመልካም የገነነው ት/ቤት ውስጥ እየተማርኩ አስገራሚ የሆንኩት በውበቴ ብቻ አልነበረም:: ሀቅ ነው ምንም እንኳ ውብ መሆን አልያም መልከ ጥፉም መሆን እኩል ከንቱ ቢሆኑም ሁለቱም አንፃራዊ ቢሆኑም ሁለቱም የተፈጥሮ ስጦታ ቢሆኑም እኔን በተመለከተ ግን ትንሹም ትልቁም ውብ መሆኔን ያወራሉ:: አንዳንቿ ያለች ጣጣዋን የጨረሰች ውብ እስከዛሬ አይተን አናውቅም ይሉኛል:: በቃላት ክምር ከፍ ከፍ ሊያደርጉኝ ይጥራሉ! በግርምት እየመነጠሩ ይመለከቱኛል! አይናቸው እስከሚጎለጉል ያዩኛል! ይህ ብቻ ሳይሆን "ውብ ሴቶች ደደብ ጭንቅላት አላቸው! በውበታቸው ስለሚቆለሉ በብዛት ትምህርት ላይ ዜሮ ናቸው" የሚባለውን አባባል እውነትነቱን አረከስኩት! እርግጥ አባባሉ 90% ሀቅ ቢሆንም ለእኔ አልሰራም ነበር:: "ውብ ሴቶች ሁሉ ት/ት ላይ ደደብ ናቸው" የሚለው ሀሳብ ማወዛገቡን ይቀጥላል:: ልክ "ለመሆኑ ውበት ራሱ ምንድነው?" የሚለው ሀሳብ ራሱ እንደሚያወዛግበው ማለት ነው:: ለማንኛውም አንደኛ ክፍልን 999/1000 በማምጣት አንደኛ ወጣሁ:: ሁለተኛ ክፍልንም በተመሳሳይ 999/1000 በማምጣት አንደኛ ወጣሁ:: ሶስተኛ ክፍል ሁሉንም ጉድ ያሰኘ ውጤት በማምጣት 1000/1000 በማምጣት አንደኛ ወጣሁ:: በዚህ ጉዳይ አስተማሪዎች እንዴት ለተማሪ 1000/1000 ውጤት ይሰጣል ? እያሉ ከፍተኛ ውዝግብ ተነስቶ ነበር:: አራተኛ ክፍል አስረኛ የልደት ቀኔን በትልቁ አከበርኩ፤ በዚህ ዓመትም 998/1000 በማምጣት አንደኛ ወጣሁ:: በሚቀጥለው ዓመት 1998 ዓ.ም አስራ አንደኛ ዓመቴን ሳከብርም አምስተኛ ክፍልንም 999/1000 በማምጣት አንደኛ ወጣሁ:: አንደኛ መውጣት ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የት/ቤታችንን የመልካም ሥነምግባር የጸባይ ዋንጫ ተሸላሚም ሁሉ ሆንኩ:: እውነቱን ለመናገር የፀባይ ዋንጫ ተሸላሚ በመሆኔ በጣም ሀሴት አድርጌ ነበር::

በት/ቤታችን ውስጥ በውበቴ ዝነኛ ሆንኩ:: በት/ቤታችን ውስጥ በጉብዝናዬ ዝነኛ ሆንኩ:: በት/ቤታችን ውስጥ የመልካም ሥነምግባር ዋንጫ ተሸላሚ ሆንኩ፤ በዚህ የተነሣ ዝነኛ ሆንኩ! ምን ሙቀት ትፈጥሪያለሽ የሀብታም ልጅ እንደመሆንሽ የግል አስጠኚ አለሽ ትሉ ይሆናል፤ ቅሉ ግን እውነታው አስጠኚ የሚባል አልነበረኝም! ራሴ ነበርኩ የማጠናው! አባቴ ከእውቀት ነፃ ነው:: እናቴም ከእውቀት ነፃ ነች! በሌላ በኩል እኔ ደግሞ መጠየቅ እወዳለሁ!! የማወቅ ጉጉት በጣም አለብኝ! የማወቅ ጥማት አለብኝ! እናቴ ጥያቄ አትወድም! አባቴም ጥያቄ አይወድም:: እንደማይመልሱልኝ እያወኩ ተስፋ ባለመቁረጥ እጠይቃለሁ:: "ስለዚህ

ጉዳይ አትጨነቂ ትልቅ ስትሆኚ ትደርሺበታለሽ" ይሉኛል፡፡ በሌላ በኩል ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ የእኔን መሻት እና ለማወቅ ያለኝን ቀናኢነት ታላቁ ፈጣሪ አውቆ የእናቴ ወንድም የሆነውን አጎቴን ሶቅራጥስ ሳምሶንን ሰጠኝ!! የእኔ ትልቅ ስጦታ፡፡ አ ሶቅራጥስ! አ አጎቴ! ስለ እውነት ስለ አባቴ እና እናቴ ከማወራ ስለ ሶቅራጥስ ባወራ ሀሴት አደርጋለሁ፡፡ እርካታ ይሰማኛል፡፡ ሶቅራጥስ ለእኔ ብርሃኔ ነበር! ሶቅራጥስ ለእኔ ፀሐዬ ነበር! ሶቅራጥስ ለእኔ የእውቀት አባቴ ነበር! ሶቅራጥስ ለእኔ የደስታዬ ምንጭ ነበር! ሶቅራጥስ ለእኔ የእ/ር ስጦታ ነበር!

አጎቴ ሶቅራጥስ አጭር፣ ወፍራም፣ ፈገግታ የማይለየው እንደ ህፃን ልጅ ድንቡሽቡሽ ያለ መልከ ያለው ፣ መሀከል ጭንቅላቱ ውስጥ መላጣ ያለው፣ ሳይናገር በምልክት ብቻ ማሣቅ የሚችል ለየት ያለ ሰው ነበር፡፡ እናም አጎቴ እናቴና አባቴ ያልሰጡኝን ፍቅር ሰጠኝ! እውቀት ሰጠኝ! ማስተዋል ሰጠኝ! የአጎቴ አስተሳሰብ ከእናቴና አባቴ የሰማይ እና የምድር ያህል ይራራቃል፡፡ ለምሳሌ አንድ ወቅት ሠርግ ወሰዱኝና ሙሽሪት እና ሙሽራውን በጥሞና ስመለከት ሙሽሪት በቀኝ ተቀምጣ አየሁኝ፡፡ ሌላ ጊዜ በሌላ ሠርግ ላይም ሙሽሪት እንዲሁ በቀኝ ተቀምጣ አየሁኝ፡፡ ይህ ነገር ደንብ ነውን? ወይስ አጋጣሚ? የሚለው እኔን ሳበኝና እናቴን "እናቴ ሴት ሙሽሪት በቀኝ ለምን ትቀመጣለች?" አልኳት፡፡ እናቴ እንደተለመደው "ምን ያደርግልሻል ስለዚህ ነገር አትጨነቂ ትልቅ ስትሆኚ ትደርሺበታለሽ" አለች፡፡ ይህን ጉዳይ ለማወቅ አጎቴ ሶቅራጥስ ጋር አመራሁ፡፡

"አቤት!" አለኝ በፍቅር ዓይን እየተመለከተኝ፡፡

"አጎቴ ለምን ሴት ሙሽራ ከወንድ ሙሽራ ቀኝ ትሆናለች?" አልኩት፡፡

"በእርግጥ የመጀመሪያዋ ሴት ሄዋን ከአዳም የግራ ጎን አጥንት ነበር የተፈበረከችው ቢሆንም አሁን በዘመናችን አንዲት ሴት ስታገባ በቀኝ ትቆማለች፡፡ የቀኝ ውክልና የመልካም ምሳሌ ነው፡፡ በግራ ከቆሙት ይፋታሉ የሚል ባህልም አለ፡፡ አየሽ በተምሳሌት ዘይቤ ቀኝ የፈጣሪ ነው፡፡ ግራ የሴይጣን ነው፤ ስለዚህ አንቺም ፀሎት የምታደርጊ ከሆነ ሁልጊዜ በቀኝህ አድርገኝ እያልሽ መፀለይ ነው" በማለት አስረዳኝ፡፡

ከአባቴ ጋር አስቦበት ሳይሆን እንደው ድንገት አንዳንዴ በመኪና ሳይሆን በእግራችን መንገድ ስንሄድ አባቴ ለማኝ ሲያገኝ አስር አስር ብር እያወጣ በታላቅ መኮፈስ ይሰጣቸዋል፡፡ በጣም አሮጊቶች ከሆኑ ደግሞ 50 ብር የሚሰጥበት ጊዜም አለ፡፡ ይህ ጉዳይ ግራ ስለሚገባኝ

አባቴን መጠየቅ ፈለኩ፡፡

"አባቴ ለለማኝ ገንዘብ መስጠት አስፈላጊ ነው? ስራ እንዳይሰሩ ማስነፍ አይሆንም?"

"ችግረኛን መርዳት ያፀድቃል! አየሽ ገነት መግባት ከፈለግሽ ለማኝና ችግረኛን መርዳት አለብሽ!"

"ህግ ነው?"

"ነገርኩሽ እንግዲህ!" በማለት ይቆጣል፡፡ ቁጣው በጥያቄ ላይ ጥያቄ ስለምከምርበት ነው፡፡ በሌላ በኩል በእግር በጣም መጓዝ ከሚወደው ምርጥ ከሆነው ከአጎቴ ጋር መንገድ ላይ እየሄድን ስንዝናና እንደ አባቴ ሁልጊዜ ሳይሆን አጎቴ ለተወሰኑ ሰዎች በተለይ የአካል ጉዳተኛ ብቻ ሲመለከት አስር ሳይሆን ሀያ አምስት ብር ጥቅልል አድርጎ በእጃቸው ላይ ያስቀምጣል፡፡

"አጎቴ" እለዋለሁ፡፡

"አቤት" ይለኛል፡፡ በፈገግታ ተሞልቶ፡፡

"ለለማኝ እና ችግረኛ መስጠት ያጸድቃል?"

"ማን አለሽ?"

"አባቴ"

"የእኔ ልጅ አያፀድቅም፡፡ በእርግጥ በአባባል ደረጃ ለለማኝ እና ችግረኛ መስጠት ለእ/ር ማበደር ነው ይባላል፡፡ አየሽ ሰማይ ላይ ያለው ታላቁ አባታችን መልካም ነገር እንድንሠራ ፣ የተቸገረን እንድንረዳ፣ ደግ እንድንሆን ፣ እንድንፋቀር፣ እንድንረዳዳ ይፈልጋል፤ ምክንያቱም ለሰዎች ቅን ስትሆኚ ፣ ደግ ነገር ስትሰሪ፣ ለሰዎች ጥሩ ነገር ስትሰሪ በምላሹ ለአንቺም አንቺ የማታውቂያቸው ሰዎችም እንኳ አንቺ እርዳታ ስትፈልጊ ላንቺ ደግ እና ጥሩ ነገር ይሠሩልሻል እንጂ ለለማኝ እና ችግረኛ ስለሰጠሽ መፅደቅ ወይም ገነት መግባት የሚባል ነገር የለም!! እርዳታ የምታደርጊው ነገ ፈጣሪ ይህን በማድረጌ ይህን ይሰጠኛል እና መስጠት ያጸድቃል ብለሽ በማመን እና በማሰብ ከሆነ ይህ ራሱ ሀጢያት ነው፡፡ በራስ ላይ መርገምትን መጥራት ነው፡፡ አየሽ አንቺ ጥሩ ስታደርጊ ላንቺም ምድር ላይ ጥሩ የሚያደርጉ ያጋጥሙሻል! የዘራሽውን መልሰሽ ታጭጂያለሽ ማለት ነው፡፡ ታዲያ ለሰዎች ስትሰጪ ያለ አንዳች ስስት መሆን አለበት! በስስት ከሰጠሽ እንዳልሰጠሽ ይቆጠራል! በስስት ከሰጠሽ ላንቺ እርግማን ነው! በስስት ተሞልተሽ ከምትሰጪ አለመስጠት የበለጠ ዋጋ አለው፡፡ በዚያ ላይ መልካም ነገር ስታደርጊ አንዳችም ምላሽ መጠበቅ የለብሽም፡፡ ይህን በማድረጌ ይህን አገኛለሁ ብለሽ ማሰብ

የለብሽም፡፡ ለማኝ እና ችግረኛን ስለረዳሽ ነጥብ የሚቆጥር ተራ አምላክ የለንም! መስጠት ያለብሽ መስጠት ስለሚያጸድቅ ሳይሆን ላንቺም እንዲሰጥሽ ብቻ ነው! መልካም ማድረግ ያላብሽ መልካምነት ስለሚያፀድቅ ሳይሆን ጥሩ ስነምግባር ስለሆነ ብቻ ነው! የኢትዮጵያ ህዝብ ለማኝ ሆኖ የቀረው ልመና እና ለለማኝ መስጠት ያፀድቃል ብሎ በከንቱ አስተሳሰብ ስለተሞላ ነው" በማለት ነገረኝ፡፡ እንዲገባኝ በምሳሌዎች ጭምር አስረዳኝ፡፡ ምክንያቱን ባላውቅም እናቴ እና አባቴ ከሚነግሩኝ ይልቅ አጎቴ የሚነግረኝ መስማት ያስደስተኝ ነበር፡፡ ከእናቴና አባቴ ይልቅ የአጎቴ ምክር ይበልጥብኝ ነበር፡፡ በጣም ያረካኝ ነበር፡፡ ለውስጤ ደስታ ይፈጥርልኝ ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ቀስ በቀስ ከእናቴና አባቴ ይልቅ አጎቴን ይበልጥ መቅረብ ጀመርኩ፡፡ አጎቴም እውቀቴ እንዲሰፋ የተለያዩ ነገሮችን ይነግረኝ ነበር፡፡ በርካታ የተረት መጽሐፍትን እየገዛ ያመጣልኝ ነበር ፡፡ ይንከባከበኝ ነበር፡፡ ፍቅር ይሰጠኝ ነበር... ይህ ነገሩ በጣም ስለሚገርመኝ አንድ ጊዜ

"አጎቴ" አልኩት፡፡

"አቤት"

"እድሜህ እኮ ትልቅ ነው አይደለም?"

"የእናትሽ ታላቅ እኮ ነኝ!"

"የራስህ ቤት አለህ?"

"አለኝ"

"ሥራም አለህ?"

"አለኝ"

"ታዲያ ሚስት ለምን የለህም? ልጅ ለምን አትወልድም?"

"አይ የኔ ልጅ ለዚህ አልታደልኩም"

"አልታደልኩም ማለት?"

"መውለድ አልችልም፡፡ መሀን ነኝ፡፡ አየሽ ስፈጠር ጀምሮ መውለድ አልችልም"

"መሀን ማለት አጎቴ? አብራራው?" አልኩት አጎቴ በሚገባኝ ቋንቋ አስረዳኝ፡፡ አዘንኩለት፡፡ የእውነት በጣም ነበር ያዘንኩለት ከዚያ ጠየኩት

"አጎቴ"

"አቤት"

"ግን አምላክ ለምን መሀን አደረገህ?"

"አየሽ ዓምላክ የራሱ ፍቃድ አለው፤ ምናልባት ለእኔ የተሻለውን ሰጥቶኝ ይሆናል፤ በዚህ አምላኬን አላማርርም" አለኝ:: አጎቴ የገንዘብ ችግር ባይኖርበትም ከእኛ ዘመናዊ ቤት አንፃር የአጎቴ ቤት ትንሽ ናት፤ ግን ታምራለች፤ በተለይ አንደኛው ክፍል ውስጥ መፅሐፍት ለጉድ ተከምረዋል:: የታሪክ... የሀይማኖት የፍልስፍና... የቦለቲካ .. በሽ ናቸው :: በትንሹ 3,000 ሺ ይጠጋሉ:: አጎቴ ይሠራል:: ቤቱ ይገባል:: ያነባል:: እኔ ቤት ካለው ብቻ ይመጣል:: ይጫወታል:: ይሄዳል:: ስለ አጎቴ የበዛ እውቀት ስገረም በሌላ በኩል ታናሽ እህቱ እናቴ ከእውቀት ነፃ መሆኗን ሳስብ ደግሞ ያስገርመኛል:: ወይ ተፈጥሮ እላለሁ:: የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው የሚለውን አስታውሳለሁ::

እሁድ ጠዋት ጠዋት እናቴ ቤተክርስቲያን ቀርታ አታውቅም:: አንዳንዴ እኔንም ይዛኝ ትሄዳለች:: በእርግጥ በጥያቄ ስለምወተውታት ይዛኝ ከመሄድ ጥላኝ መሄዱን ትመርጣለች:: አንድ ጊዜ ቤተክርስቲያን ስንሄድ አንድ ወጣት ቄስ ወደ እናቴ መጣና ትንሽ ካወሩ በኋላ እናቴን በትኩረት እያያት "ከኢየሩሳሌም ድረስ ተባርኮ የመጣ ነው 235 ብር" በማለት አንገት ላይ የሚታሠር መስቀል ያለው ማተብ ሰጣት:: ገዛች:: ወዲያው እሰሪው አለችኝ:: በእሺታ ተቀብዬ አሠርኩት:: ከዚያ ወደ ቤት ፀሎት ጨርሰን ስንመለስ

"እናቴ ስለገዛሽልኝ አመሠግናለሁ ግን ለምንድነው ማተብ አንገት ላይ የሚታሰረው?" አልኳት::

"መታሰር ስላለበት ነዋ!"

"ለምን?"

"እንግዲህ አትጨቅጭቂኝ" አለች:: እኔ ግን ማታ አጎቴ ሲመጣ ጠየኩት::

"አጎቴ"

"አቤት"

"አንተ ለምን ማተብ አላሰርክም? አባቴም አለው፣ እናቴም አላት፣ ዘመዶቻችን ሁሉ አላቸው እኮ?"

"አየሽ ልጄ ማተብ መታሰር የተጀመረው በ400 ክፍለ ዘመን ያዕቆብ ዘዕቢረዳዒ በተባለ አንድ ጳጳስ ጊዜ ነበር:: እርሱም ክርስቲያኖች አንዴ ለራሳቸው ከተጠመቁ በኋላ ለሞቱት ዘመዶቻቸው በድጋሚ እየተጠመቁ ሲያስቸግሩት ለመለያ እንዲያገለግለው

የዘየደው መላ ነበር፡፡ በአገራችን ደግሞ ወደፊት ታሪኩን ት/ቤት በምትማሪው በዘርዓ ያዕቆብ ጉባኤ ንጉስ ዘርዓያዕቆብ መስቀልን በአንገት ማሠር ይገባል፤ በመስቀል ምልክት ማማተብ ሴይጣንን ያርቃል፣ መንፈስ ቅዱስን ያቀርባል፤ የሚል ህግ ለወቅቱ ለነበሩት ኢትዮጵያዊያን የክርስትና እምነት ተከታዮች ስለደነገገባቸው ከዚያን ዘመን አንስቶ መታሰር ተጀመረ፡፡ እኔ ግን እውነተኛ ክርስትና አንገት ላይ ገመድም ሆነ ማተብም ሆነ መስቀልም ስለታሰረ ይገለጣል የሚል ወንዝ የማያሻግር እምነት ስለሌለኝ አላስርም፡፡ ሰዎች በሚያወጡት የህግ ኮተቶች መመራት አልፈልግም፤ በዚያ ዘመን በዘርዓያዕቆብ ጊዜ አንገትሽ ላይ ክር ከሌለ ትገደይ ነበር ፤ እናም ወደሽ በግድ ታስሪያት ነበር ፤ አሁን ዘመነ ዲሞክራሲ ነው! በዚያ ላይ እውነተኛ ክርስትና ማለት አንገት ላይ መስቀል ማንጠልጠል አይደለም!!" አለኝ፡፡

"አጎቴ መንፈስ ቅዱስ ምንድ ነው?" አልኩት፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማውት ቃል ስለነበር፡፡

"ሌላ ጊዜ አስረዳሻለሁ" አለኝ፡፡ አጎቴ ሌላ ጊዜ አስረዳሻለሁ ካለኝ የጠየኩት ጥያቄ ከእኔ የማስተዋል ደረጃ በላይ እንደሆነ ስለሚገባኝ ዝም እላለሁ፡፡

ለህፃናት ተረት መንገር ከምግብ በላይ ጣፋጭ ነው፡፡ ህፃናት ተረት ይወዳሉ፡፡ ተረት ያንፃቸዋል፡፡ ተረት የማስተዋል ችሎታቸውን ይጨምርላቸዋል፡፡ ተረት ደስተኛ ያደርጋቸዋል፡፡ ተረት የህፃናትን ሥነ ምግባር መቅረጫ ጭምር ነው፡፡ ተረት ለህፃናት ህልመኛ የሚያደርጋቸው መንገድ ነው፡፡ ተረት ህፃናትን አንባቢ የሚያደርጋቸው ማነቃቂያ ነው... አባቴ ተረት መናገር አይችልም፡፡ እናቴም ተረት መናገር አትችልም፡፡ አጎቴ ግን ድንቅ ነው፡፡ ልክ እንደ አባባ ተስፋዬ ተረት ይነግረኝ ነበር፡፡ የመናገር ችሎታዬን እንዳዳሻሽል እኔ ሳወራም ከልቡ ያዳምጠኝም ነበር፤ በተለይ አጎቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የነገረኝ ቁም ነገር ቀመስ ሁለት ቀዳሚ ተረቶችን መቼም ልረሳቸው አልችልም፡፡

"አጎቴ ተረት ንገረኝ"

"ተረት ተረት"

"የመሠረት"

"አራት ሰዎች ነበሩ"

"እሺ"

"እነዚህ አራት ሰዎች በትንሿ አውሮፕላን ሲበሩ አውሮፕላኑ ድንገት አየር ላይ ይበላሽና በፍጥነት ሰዎቹ ወደ ምድር በፓራሹት ጃኬት እንዲዘሉ ይታዘዛሉ፤ ግን የነበረው ፓራሹት ጃኬት ብዛት ሶስት ብቻ ነበር፤ ስለዚህ ከአራቱ አንደኛው መሞቱ የግድ ነበር:: በዚህ መሀከል ከአራቱ አንደኛው ዶክተር ነበር "እኔ እውቅ ዶ/ር ነኝ! የማከማቸው በርካታ በሽተኞች ስላሉብኝ በህይወት መኖር አለብኝ" በማለት ምላሻቸውን ሳይጠብቅ አንደኛውን ፓራሹት በፍጥነት በማንሳት ዘለለ:: ሁለተኛው አንድ ዝነኛ ቦለቲከኛ ነበር እሱም በፍጥነት "እኔ ለዚች ምስኪን አገር ኢትዮጵያ በጣም ወሳኝ የሆንኩ ሰው ነኝና አስፈልጋታለሁ! አስራ ሰባት ዓመት ጫካ የታገልኩት እንዲሁ በዋዛ ልሞት አይደለም ፤ በዚያ ላይ የጀመርኳቸው ዘጠኝ ሰማይጠቀስ ፎቆች ስላሉኝ እነሱን መጨረስ አለብኝ" በማለት እሱም ምላሻቸውን ሳይጠብቅ አንደኛውን ፓራሹት በፍጥነት አንስቶ ወደ ምድር ዘለለ:: አንድ ሽማግሌ እና ትንሽ ልጅ ቀሩ:: ሽማግሌው ልጁን እየተመለከቱ "የእኔ ልጅ አምላኬ የተመሰገነ ይሁን እኔ ብዙ ዓመት ኖሬያለሁ! አንተ ገና ልጅ ነህ! የኢትዮጵያ ተስፋ ነህ፤ ስለዚህ በህይወት ቆይ! አደራ ለአገርህ ኢትዮጵያ መልካም ነገር አድርግ! በጭራሽ ሙስና አትብላ! ሰዎችን አታዛዝን! ኢትዮጵያን አፍቅር! ዘረኝነትን ተዋጋ! ፍቅርን ስበክ! አረንጓዴ ፣ ቢጫ ቀዩን ባንዲራ አክብር! አገርህን በደግነት እና በቅንነት አገልግል! ብታጣም ፈጣሪህን እንዳታማርር ብታገኝም እንዳትታበይ ቸሩ ፈጣሪ ይርዳህ! በል በፍጥነት ፓራሹቱን በመያዝ ውረድ" አሉት:: ልጁ በፈገግታ ሽማግሌውን እየተመለከተ "አባባ ከልብ አመሠግናለሁ፤ ግን ሁለታችንም አንሞትም! በህይወት እንተርፋለን፤ ምክንያቱም ቦለቲከኛው ፓራሹት መስሎት ይዞ የዘለለው የእኔን የት/ቤት ቦርሳዬን ነው" አላቸው:: አየሽ ስግብግብ እና ራስ ወዳድ ሰው ችኩል ስለሆነ ምንጊዜም መጨረሻው አያምርም ፤ ስለዚህ የእኔ ልጅ አንቺ መቼም ስግብግብ እና ራስ ወዳድ መሆን የለብሽም:: መኖር ማለት ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች መኖርንም የሚያጠቃልል ነው" አለኝ:: ሁለተኛውንም ሁልጊዜ የማስታውሰውን አሪፍ ተረት የነገረኝ የዚያኑ ዕለት ነበር:: ለዚያው ትልቅ ቁም ነገር ያለው ተረት ነበር::

"ተረት ተረት!"

"የመሠረት"

"የገደል ማሚቶን በተመለከተ ት/ቤት ተምረሻል?"

"ተምረናል አጎቴ"

"ጥሩ አንድ የህንድ ጥበበኛ አባት ነበር"

"እሺ"

" ያ ህንዳዊ ጥበበኛ አባት ልጁን ተራራ ላይ እያንሸራሸረው የገደል ማሚቶ ጋር ሲደርስ `ልጄ ይህ የገደል ማሚቶ ይባላል:: የገደል ማሚቶ ማለት አንተነትህ የሚቀረፅበት መንገድ ነው:: ለምሳሌ የእኔ ልጅ እስቲ ሌባነኝ በል:: ልጁ ወዲያው ሌባ ነኝ አለ:: የገደል ማሚቶውም መልሶ ሌባ ነኝ አለ:: እስቲ እኔ ድንቅ ነኝ በል አለው:: ልጁ በጩኸት እኔ ድንቅ ነኝ አለ:: የገደል ማሚቶውም መልሶ እኔ ድንቅ ነኝ አለ:: እስቲ የእኔ ልጅ እኔ የማልረባ ነኝ በል:: አለው:: ልጁም አለ:: የገደል ማሚቶውም መልሶ እኔ የማልረሳ ነኝ አለ:: ከዚያ አባት ልጁን በትኩረት እየተመለከተው የኔ ልጅ ሰዎች ስላንተ የፈለጉትን ይበሉህ አንተ ግን ሁልጊዜ ለራስህ ውድቀትን መናገር የለብህም:: ሰዎች ያሉህን በውስጥህ ጨርሶ ማስተጋባት የለብህም፤ ምንጊዜም በውስጥህ መቻልህን መናገር አለብህ! ውስጥህን አለመቻልህን የምትነግረው ከሆነ ውስጥህ መልሶ አለመቻልህን ይነግርሃል:: ይህ ትልቁ ወርቅማ ህግ ነው:: ለውስጥህ ምንጊዜም አሸናፊነትህን የምትሰብከው ከሆነ ታሸንፋለህ በማለት ነገሩት፤ ስለዚህ አንቺም ይህን ወርቅማ ህግ በጭራሽ እንዳትረሺ! ለውስጥሽ መጥፎ ነገር እንዳታስገቢበት! ቀናውን ነገር ብቻ ለውስጥሽ መግቢው! ይህን ካደረግሽ በምንም ሁኔታ እና ፈተና ውስጥ ብትዘፈቂ እንኳ አሸናፊ መሆንሽ አይቀርም:: በተለይ በኢትዮጵያዊያን ህዝቦች ሥነልቦና ላይ በተደረገ ጥናት 88.5% የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚያበረታታሽ ይልቅ እንደማይቻል የሚነግርሽ እና ተስፋ ቆርጠሽ እንድትቀመጪ የሚያደርጉሽ ህዝቦች መሆናቸው ስለታወቀ ይህን አስቸጋሪ የህዝባችንን ጎታች ባህሪ አውቀሽ ሁልጊዜ ሰዎች ተስፋ ቢያስቆርጡሽም አንቺ ግን በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ የለብሽም!!" በማለት ነበር አጎቴ የነገረኝ... ብቻ አጎቴ በዓለም ላይ ካሉት ሰዎች የእኔ ቁጥር አንድ ተወዳጅ ሰው ነበር... በእውቀት የሞላኝ ቅን ሰው ነበር... መዳፈር ካልሆነብኝ አጎቴ የእኔ መላዕክ ነበር::

ዘመን ንፋስ ነው:: በፍጥነት ይነጉዳል:: ዘመን ሻማ ነው በፍጥነት ይቀልጣል:: ዘመን ወንዝ ነው በፍጥነት ይፈሳል... እነሆ 1999 ዓ.ም መጣ:: በዚህ ዓመትም እንደኛ ከመውጣት ማንም ያገደኝ አልነበረም:: በእርግጥ ያመጣሁት 995/1000 ሺ ነበር:: የአስራ ሁለተኛ የልደት በዓሌንም በደማቁ ነበር ያከበሩልኝ:: ከማክበር እና ድግስ ጋር በተገናኘ ቤታችን ውስጥ ከእንቁጣጣሽ ፣ ከፋሲካ እና ከገና በላይም በታላቅ ድምቀት እጅግ ብዙ ሰው ተጠርቶ በታላቅ ፈሽታ ውስኪ እንደውሃ እየተጠጣ ፣ ቁርጥ ለጉድ እየተቆረጠ፣ የሙዚቃ ባንድ መጥቶ እየተሞዘቀ የሚከበረው የመላዕክት አለቃ እንደሆነ በሚነገረው እና በኢብራይስጥ ቋንቋ ፍቺው እንደጌታ ያለማን ነው? የሚል ፍቺ ባለው የዓመቱ የቅዱስ ሚካኤል ቀን ነው:: በተጨማሪ እናቴ መጋቢት አምስትን እና ግንቦት አንድን ከበርካታ ሴቶች ጋር ታከብራለች፤ ታዲያ በእነዚህ ቀናት አንድም ቀን የምወደው አጎቴ እኛ ቤት መጥቶ አያውቅም:: ለምን አትመጣም ስለው " ወዳጅሽም ቤት ቢሆን እንኳ እግር ማብዛት ጥሩ አይደለም:: እኔ እዚህ ቤት የምመጣው ላንቺ ስል ነው እንጂ..." ይልና ዝም ይለኛል:: የሆነ መናገር የሚፈልገው ነገር እንዳለ ያሳብቅበት ነበር፤ ግን እንዳልወተውተው ሌላ ርዕስ ያነሳል:: ከእነዚህ ቀናት በተጨማሪም የልደቴም ቀን አይመጣም:: በነጋታው ግን የተለመደውን ስጦታ ይዞልኝ ይመጣል:: የአጎቴ ስጦታ መፅሐፍ ነው:: እናትና አባቴ እጅግ ውድ ስጦታዎችን ይሰጡኛል:: የሚገርመው የእኔ ጉጉት ግን በልደቴ ቀን ማግስት የአጎቴን ስጦታ መቀበል ነበር:: በዚህ ሁኔታ እናቴና አባቴ ባይናገሩም ውስጥ ውስጡን ይበሳጩብኝ ነበር:: ለአጎቴ በምሰጠው ፍቅር ይቀኑ ነበር:: ይንጨረጨሩ ነበር::

"እንኳን ለአስራ ሁለተኛ ዓመትሽ አደረሰሽ! ትልቅ ሆነሽ አገርሽን ኢትዮጵያን የምታገለግይ ትሆኚ ዘንድ ፈጣሪ ይርዳሽ!!" በማለት እንደተለመደው አጎቴ የቀኝ እጄን ሳመኝ:: እንደሌ ስለመሳም ከተነሣ አባቴ ጠዋት ሲወጣ ሆነ ማታ ሲመለስ "የእኔ ውብ ልጅ!" በማለት ከንፈሬን ይስመኛል:: እናቴ "ኧረ እባክህ አንተ ሰው ከንፈሯን አትሳማት !" ትለዋለች:: "ምን ችግር አለው አባቷ እኮ ነኝ" ይላታል... አባቴ ቢባል ቢባል ከንፈሬን መሳሙን ስላልተወ እናቴ ታከታትና ተወችው:: እናም አባቴ ጠዋትና ማታ ከንፈሬን ምጥጥ እያደረገ ይስመኛል ... ወደ አጎቴ ልመለስና የልደት ስጦታዬን ተቀብዬ አጎቴን በፍቅር አይን እያየሁት

"አንተ ግን ስንት ዓመት መኖር ትፈልጋለህ?" አልኩት::

"የእኔ ልጅ እድሜ የፈጣሪ ስጦታ ነው፡፡ ሀጢያት ካበዛሽ ግን ቶሎ ትሞቻለሽ"

" እና ህጻናት የሚሞቱት ምን ሀጢያት ሠርተው ነው?"

"እናትና አባታቸው ሀጢያት ሠርተው ከሆነ በልጃቸው ይቀጣሉ"

"ግን ይህ ተገቢ ነው? እናትና አባት ባጠፉት ፈጣሪ ለምን ምንም የማያውቁትን ህፃናትን ይቀጣቸዋል?"

"የእኔ ልጅ ይህ የፈጣሪ ጉዳይ ነው፡፡ ከእኔና አንቺ አዕምሮ በላይ ነው፡፡ ስለ እድሜ ካነሳሽ ግን በፈጣሪ ዘንድ አንድ ሺ ዓመት አንድ ቀን ናት፤ አንድ ቀንም አንድ ሺ ዓመት ናት፤ ይህ እንዴት ይሆናል ካልሽ የፈጣሪ ጥበብ ነው፡፡ የፈጣሪ ጥበብ ደግሞ ከእኔና አንቺ ማስተዋል በላይ ነው፡፡ እኛ የፈጣሪ ፍጡራን ነን፤ ፍጡራን እንዴት በኢምንት እውቀታቸው የፈጣሪያቸውን የጥበብ እና የእውቀት ደረጃ ሊያውቁ ይችላሉ? አይችሉም!!"

"ታዲያ ትልቅ እድሜ የኖረው ማን ነው?"

"እንግዲህ መፅሐፍ ቅዱስን በሚገባ ተመልከተናል በሚሉ ምሁራን መሠረት አባታችን አዳም 930 ዓመት፣ የአዳም ልጅ ሴት የሚባለው 912 ዓመት፣ ያሬድ 962 ዓመት፣ ማቱሳላ 969 ዓመት፣ በሰው ልጆች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት ሚስቶች ያገባው አመንዝራው የኖህ አባት ላሜክ 777 ዓመት ፣ አብረሃም 175 ዓመት፣ ሚስቱ ሣራ 127 ዓመት ፣ ታላቁ አምስቱን ቅዱሳን መፅሐፍት የፃፈው ሙሴ 120 ዓመት ፣ እንደኖሩ ይነገራል፤ ታዲያ የሚገርምሽ ሙሴ ሲሞት ህዝቡ ከልቡ በማዘን ለ30 ቀናት ነበር አንድም ቀን ሳያቋርጥ ያለቀሰለት፡፡ እስከ ዛሬ በታሪክ በምድር ላይ ለሰላሳ ቀናት ያህል የተለቀሰለት እስካሁን ያለ አይመስለኝም፡፡ በሌላ በኩል ሞትን ሳይቀምሱ በእ/ር ኃይል ወደ ሰማይ የወጡም አሉ፡፡ ኢልያስ እና ሄኖክ ናቸው፡፡ በእርግጥ ሄኖክን ሁሉም አያምኑበትም፡፡ እንግዲህ የሰው ልጅ እድሜ ከዘመን ዘመን እየቀነሰ የመጣው የሰው ልጅ ሀጢያት እየበዛ በመምጣቱ ነው፡፡ በ2929 ዓ.ም የሰው ልጅ ትልቁ የእድሜ ጣሪያ 25 ብቻ ይሆናል የሚል አወዛጋቢ ትንቢት አለ፡፡"

"2929 ምንድ ነው?"

"666 ዓለምን መግዛት ሙሉ ለሙሉ የሚጀምርበት ዓመት ነው"

"እና ዓለም ፍፃሜስ መቼ ነው?"

"የእኔ ልጅ አይታወቅም! ይህን በተመለከተ መፅሐፍ ቅዱስ በማርቆስ 13፡22 ላይ ያለውን ልንገርሽ? `ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላዕክት ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም' ይላል፤ ስለዚህ ስለዓለም መጨረሻ ማንም መናገር አይችልም! ትንቢት እንኳ አየሁኝ ብሎ መናገር አይቻልም"

"እሺ እስቲ ዛሬም ስለ ሴይጣን ንገረኝ"

"ከዚህ በፊት ነግሬሽ ነበር እንዴ?"

"አይ አጎቴ ትረሳለህ ማለት ነው? አንድ ጊዜ ሴይጣን የዕብራይስጥ ቃል ነው ትርጉሙ ባላጋራ፣ ጠላት፣ተቃዋሚ፣ አሰናካይ ማለት ሲሆን ዲያቢሎስ ግሪክኛ ቃል ሲሆን ፍቺው ከሳሽ፣ ሰውን በእ/ር ፊት የሚከስ፣ የሴይጣን አለቃቸው መሆኑን እና ሴይጣን መጀመሪያ ሲፈጠር ቅዱስ መላዕክ እንደነበር ከዚያ ከፈጣሪ ጋር ስልጣን መሻማት ፈልጎ እኔ ፈጣሪ ነኝ ኃይል እና ስልጣን የእኔ ነው በማለቱ ቅድስናው ተነጥቆ እርኩስ መላዕክ በመሆን ወደ ምድር ተከሰከሰ አልከኝ"

"ጎበዝ አስታዋሽ ነሽ!"

"አመሠግናለሁ! ታዲያ ሴይጣን ምድር ላይ ከተከሰከሰ በኋላ ከነገርከኝ ሌላ በተጨማሪ አሁን ምን ይሠራል?"

"ብዙ ስራ አለው:: የእ/ርን ቃል ከሰው ልብ መስረቅ ፣ ክፋትን ማስፋፋት፣ ሰዎችን በራስ ወዳድነት አጥር ማጠር፣ ሰዎች በቶሎ ተስፋ ቆርጠው ተሸመድምደው እንዲቀመጡ ማድረግ ፣ ሰዎችን ሊወጡበት በማይችሉበት የተለያዩ ሱሶች አስሮ ማስቀመጥ፣ ጦርነትን እና ግጭትን ማስፋፋት፣ የማያምኑትን ሰዎችን አዕምሮ ማሳወር፣ ቅዱሳንን መክሰስ፣ እምነትን ማባዛት፣ የእ/ር ስራን ማኮላሸት ፣ ጨለማን ማስፋፋት፣ እ/ር የለም ማስባል፣ ፈርሐ እ/ርን ከሰዎች ልብ ውስጥ ማጥፋት ፣ ሰዎችን በተንኮል መመረዝ... ወዘተ ይሠራል... አንዲት ሴኮንድ እንኳ ከስራው ደከመኝ ብሎ አርፎ አያውቅም! ሴይጣን ሲበዛ በጣም ታታሪ ሰራተኛ ነው:: የሚገርምሽ ሴይጣን ስለመጨረሻው ያውቃል፤ ፈጣሪ ይቅር እንደማይለው በሚገባ ያውቃል ግን እስከዓለም መጨረሻ ከፈጣሪ ጋር እየታገለ እና እየተፃረረ ይኖራል:: ይህ ነገር እኔን ያስቀኛል"

"እናቴ ከሴት ማህበርተኞቿ ጋር ስለ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ሲያወሩ እንደሰማሁት እኚህ ታላቅ ሰው 700,200 ሴይጣኖችን ገድለዋል ሲባባሉ ሰማሁ:: እውነት

ነው?"

አጎቴ ደስ የሚለውን ፈገግታውን ለገሰኝ:: ከዚያ ዝም አለ:: እኔም እስከሚያወራ በትዕግስት ጠበኩት::

"ሌላስ ምን ሲያወሩ ሰማሽ?"

"የጎጃምን ህዝብ ማርልኝ ብለው ጣና ሐይቅ ውስጥ ገብተው በእናታቸው ተዘቅዝቀው መቶ ዓመት እንደፀለዩ! የገረመኝ ግን መቶ ዓመት በፀሎት ብቻ ካሳለፉ ስንት ዓመት ኖረው ነበር?" አልኩኝ ግራ ስለገባኝ::

"የእኔ ልጅ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ በላሊበላ ዘመን ኢትዮጵያ የመጡ ግብፃዊ ናቸው:: አየሽ እንደሚወራው ለዘመናት እየተቀነባበረ የመጣው እውነት መሰል ተረት ውስጠ ሚስጢሩ መቼም ቢሆን ለአገራችን ኢትዮጵያ እንቅልፍ በማይኖራት የሸር እናት በሆነችው በተንኮለኛዋ ግብፅ በረቂቅ የተዘጋጁ የግብፅ ጉዳይ ገዳይ ነበሩ:: ኢትዮጵያ አገራችን የአባይ ወንዝን እንዳትጠቀምበት የግብፅ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊያንን ለማደንዘዝ የላኩዋቸው ነበሩ:: ሰውየው በዚያን ዘመን ለነበሩ ኢትዮጵያዊያን የጎጃም ህዝቦች የአባይ ወንዝ ገነትን የሚያጠጣ ቅዱስ ወንዝ በመሆኑ የገነት አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች እንዳይደርቁ ከአባይ ወንዝ አንዲት ጭልፋ ውሃ እንኳ እንዳትቀዱ እ/ር የጣናን ሐይቅ እና የአባይ ወንዝን አጠገባችሁ ያስቀመጠው ሊፈትናችሁ ነውና ፈተናውን ለማለፍ ከፈለጋችሁ እንዳትነኩ! እያሉ ህዝቡን የሚያስቦኩ ነበሩ:: አየሽ እኛ የምንገኝበት ክልል ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ ከፋት! የተለየ ተንኮል! የተለየ አረመኔነት የጎጃም ህዝብ ሰፍኖበት ሳይሆን የአባይ ወንዝ የሚገኘው ጎጃም ላይ ስለሆነ የተጠቀሙበት ረቂቅ ሴራና ደባ ነበር:: አየሽ ይቺ አሲዳም ግብፅ ከ323 ዓ.ም እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መሪዎችን እየሾመች የምትሰጠን እሷ ነበረች ታዲያ ተሹመው የሚመጡት የሃይማኖት መሪዎች ዋነኛ ስራቸው የግብፅን ጥቅም ማስጠበቅ ስለሆነ ለሚስኪኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ከስራ ይልቅ የተለያዩ በዓላትን እንዲያከብሩ 30 ቀናቱንም በዓላትን በመሰየም ለህዝቡ ከስራ ይልቅ መቀመጥን ሲሰብኩ ፣ ወግ አጥባቂነትን ሲሰብኩ፣ ፈሪሳዊነትን ሲሰብኩ፣ ድንዛዜን ሲሰብኩ ነበር:: በዚህ የተነካ ህዝቡ ዛሬ ሚካኤል ነው፣ ዛሬ ገብርኤል ነው፣ ዛሬ ኡራኤል ነው... ወዘተ... እያለ ዛሬ ድረስ የአጉል በዓላት እስረኛ ሆኖ በግብፆች ሴራ ታስሮ ለምድራዊውም ለሰማያዊውም ሳይሆን መሀከል ቤት ደንዝዞ እንዲቀመጥ አድርገውታል:: የውሸት ክርስትናን ለህዝቡ ሰብከዋል! እስራኤል ውስጥ

ፈሪሳዊነትን በድጋሚ ኢትዮጵያ ወስጥ እንዲነግስ አድርገዋል፤ ስለዚህ የእኔ ልጅ ይህም ሰውዬ አንደኛው የተንኮለኛዋ ግብፅ ሴራ አራጋቢ ነበር!!" በማለት አጎቴ አስረዳኝ። አነጋገሩ ውስጥ ቁጣ ነበር። ንዴት ነበር። ለግብጾች ጥላቻ እንዳለው ያሳብቅበት ነበር። ፈሪሳዊነት የምትለዋን ቃል እና ፍቺ የዚያን ጊዜ ነበር ያወኩት። እርግጥም ዘመናዊ ፈሪሳዊያን ማን ናቸው? ከተባለ ምላሹ እኛ የኢትዮጵያ ህዝቦች መሆናችንን ዛሬ ላይ አውቄያለሁ።

አጎቴ ባይኖር ምን እንደሚውጠኝ አንዳንዴ ሳስበው ይጨንቀኛል። አባቴ እና እናቴ ገንዘብ አፍቃሪዎች ናቸው። ወሬያቸው ሁሉ ዘወትር ስለገንዘብ ነው። እንዴት ሀብታቸው ይበልጥ እንደሚጨምር ሰርክ ማውራት ነው። ለእኔ በቂ ጊዜ አልሰጡኝም። ለእኔ በቂ ፍቅር አልሰጡኝም። በእርግጥ የጠየኩትን አንዳችም ነገር ከልክለውኝ አያውቁም። ፍቅር ግን አልሰጡኝም ፍቅርን የተቀበልኩት ከአጎቴ ነው። አጎቴ የእኔ ብርሃን ነው። አጎቴ የእኔ መርከብ ነው። አጎቴ የእኔ ጨለማን የምዋጋበት ፀሐይ ነው። አጎቴ የእኔ አውሮፕላን ነው።

የተወለድኩባትን ከተማ ደብረማርቆስን እያንዳንዱን ቦታ ያሳወቀኝ አጎቴ ነው። በምዕራብ ኢትዮጵያ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከአዲስ አበባ 299 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ደብረማርቆስ የተቆረቆረችው የጎጃም ገዥ በነበሩት ደጃዝማች ተድላ ጓሉ በ1845 ዓ.ም ነበር። በዚያን ወቅት የከተማዋ መጠሪያ መንቆረር ነበር፣ ቆሎ ግን በ1872 ወደ ስልጣን የመጡት ንጉስ ተክለሃይማኖት ከታላቁ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ምስረታ ጋር በማያያዝ መንቆረር የሚለውን ስያሜ በመሠረዝ ደብረማርቆስ የሚል ስያሜ በመስጠት የከተማዋ መጠሪያ ይሆን ዘንድ አሳወጁ። ከፍታ እና ዝቅታ ፣ ወጣ ገባ በሆነችው ማርቆስ ከተማ ውስጥ ከማንም በላይ የፍቅር አስጨርስ መንገድ ላይ መሄድ ደስ ይለኝ ነበር። ከቤተመንግስቱ ፊትለፊት የተሰራው እያንዳንዱን የደብረማርቆስ ቦታን ማሳየት በሚያስችለው አህዱ መናፈሻ ላይ በመቀመጥ ከተማዋን ወደታች ቁልቁለት መመልከት ያረካኝ ነበር... መናሐሪያ ውስጥ በመቆም ያለውን ጫጫታ እና ግርግር መመልከት ያዝናናኝ ነበር... በከተማዋ ውስጥ

ያሉትን የደህ ሰፈሮች ፣ ቪዲዮ ቤቶች፣ ጉራንጉሮች፣ እሪ በከንቱዎች መመልከት የምችለው ከአጎቴ ጋር ብቻ ነበር፡፡ አባቴ እንኳን ሊወስደኝ ከደሀ ልጆች ጋር ሳወራ ካየኝ ራሱ ይቆጣኛል፡፡ ትላንትና አባቴ ራሱ ሙልጭ ያለ ደሀ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ደሀ ማየት አይሻም፡፡ አጎቴ ግን ነፃነት ሰጠኝ! አጎቴ ነፃ እና ደግሰው ነው፡፡ እናቴና አባቴ ድብቅ ናቸው፡፡ በተለይ አባቴ ድብቅ ነው፡፡ አንዳንዴ የአባቴ ሁኔታ ግራ ያጋባኛል... ብቻውን የራሱ መኝታ ቤት ይቀመጣል... ብቻውን ያወራል... በተለይ እኔ የማላውቀውን ቋንቋ እየተጠቀመ ፀሎት ያደርጋል፡፡ አንድ ጊዜ በጠዋት ሲነሣ ሳያየኝ ተከተልኩት፡፡ ሳሎን ውስጥ ተንበረከከ፡፡ መብራቱን ሳያበራ ድምፁን መጠነኛ አድርጎ መጸለይ ገባ፡፡ እኔ ሰምቼ የማላውቀውን ቋንቋ እያወጣ ነበር

"... ቅርጭናኤል ክፍትናኤል አስታስቅፎል ኪራቆስኤል ሐበርጅን ሐበርጅን ጅን ሐበርጅ ደምርታዳ ደምርታዳ አከሎክ አከሎክ ኤፌርዜዛዋን ኤፌርዜዛዋን ሐድርጅ ፍትሐ ዘኮነ በእስላም ወዘክርስቲያን በቀሲስ ወዲያቆን በመኃይምነት ፍታሕ ሐርጅዋን ሥራዬ እምላዕለ አመትከ..." ምናምን ነገር አለ፡፡ ከዚያ ዝም አለ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ሌላ ፀሎት ያደርግ ገባ፡፡

"... ሽዊራ ሽሽዊራ ጎጎላሽ ጨርጨርሺበ ዝመዓቱን ፈጨፈጨ ዘቆርዐ ይስጥቆ ያመሽብር ያመሽብር ዮሰሜር አድሜሽ ድቸር አዶናዊሮስ ሰራሥቅሰሬል ቶቤል አሽማሽል አሽማሽል ጀቃሽ ማሽል ጀቃሽ ማሽል በውላላኤል በውላላ ኤል አጀረማን አጀረማን አጥዮንስ አጥዮንዮስ..." ምናምን የሚሉ እኔ ትርጉማቸውን የማላውቃቸው ቃላት ነበር፡፡ ድንገት ካየኝ ይጮህብኛል ብዬ ስለፈራሁ ተመልሼ ተኛሁ፡፡ ሌላ ጊዜም መኝታ ቤት ጆሮዬን ደቅኜ ሳዳምጥ አባቴ ፀሎት ያደርሳል፤ ግን የሚጠቀማቸው ቃላት ለእኔ የማልረዳቸው ባዕድ እና በብዛት በቃሌ ልይዛቸው እንኳ የሚያስቸግሩኝ ናቸው፡፡ በዚህ ነገር ግራ ተጋባሁ፡፡ ስለ አባቴ ፀሎት አጎቴን ልጠይቀው አስብና "ፀሎት የግል ጉዳይ እና ሚስጢር" ነው ሲሉ ስለሰማሁኝ ፈራሁ፡፡ ውስጤ ጠይቂ ፣ ጠይቂ ይለኛል፡፡ አንድ ቀን መጠየቄ አይቀርም በማለት ወሰንኩ፡፡ አባቴ ሌላም ግራ የሚያጋባኝ ነገር አለው፡፡ አንዳንዴ በተለይ እሁድ ጠዋት

"የኔ ውብ ልጅ ከፍተኛ እንግዳ ስለሚመጣ ከመኝታ ቤትሽ እንዳትወጪ!!" በማለት ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ትዕዛዝ ያዘኛል፡፡ ከዚያ እንዳልወጣ የመኝታ ቤቱን በር ይቆልፈዋል፡፡ ይህ የከፍተኛ እንግዳ ጉዳይ ሁሌ ግራ ያጋባኝ ነበር፤ ምናልባት ልጅ ፊት የማይወራ ጉዳይ እንደሆነ እገምታለሁ፤ ግን የዚህ የከፍተኛ እንግዳ ጉዳይ ይገርመኝ ነበር.... ዘወትር ለማወቅ

አጓጓ ነበር፡፡ ይህ ከፍተኛ እንግዳ እንዴት ያለ ይሆን እያልኩ ከራሴ ጋር እወያይ ነበር፡፡ ለመሆኑ ይህን ከፍተኛ እንግዳ ለማየት የማይፈቀድልኝስ ለምንድነው እያልኩ ራሴን በጥያቄ አወጥር ነበር፡፡

እነሆ 2000 ሺ ዓመተ ምህረት ባጀ፡፡ ጉድ ነው! ጊዜ እሳት ነው! ይንበለበላል፡፡ ጊዜ ክንፍ አለው ይከንፋል፡፡ እኛ ማለት ጊዜ ነን! እኛ ማለት የጊዜ እስረኛ ነን! እድሜያችን እሳት ነው፡፡ እድሜያችን ይንበለበላል፡፡ እድሜያችን ይከንፋል፡፡ አስራ ሶስተኛ ዓመቴ እንደተለመደው በታላቅ ድምቀት ተከበረ፡፡ የእኔም ውጪያዊ ውበቴ ይበልጥ ጨመረ፡፡ እንደፀሐይ አበራሁ፡፡ ሁለቱ ጡቶቼ ውበታቸውን ለማሳበቅ ጉችጉች አሉ፡፡ ዳሌዬ ውበቱን ለማሳበቅ ይበልጥ ፈነዳ፡፡ መንገድ ላይ የሚመለከተኝ ሁሉ ሲቋምጡብኝ፣ ከንፈራቸውን ሲነክሱ፣ በግርምት ሲመነጥሩኝ ተመለከትኩ፡፡ ለወሲብ ሲመኙኝ ታዘብኩ፡፡ በዓይናቸው ከእኔ ጋር ዝሙት ሲፈፅሙ ታዘብኩ፡፡ እኔ ግን በውጪያዊ ውበቴ ከመመጻደቅ እና እዩኝ ከማለት ይልቅ በትምህርቴ እና እውቀትን መሸመትን በማስቀደም ት/ት ላይ ትኩረቴን አደረኩ፡፡ እናም በት/ቤት እንደተለመደው የመጀመሪያው ግማሽ መንፈቀ አመት 994/1000 ሺ በማምጣት ሰባተኛ ክፍልንም አንደኛ ወጣሁ፡፡

ሚያዚያ 25 የልደት በዓሌ በተከበረ ሶስተኛው ቀን ሚያዚያ 28 ዕለቱ ቅዳሜ ስለነበር ተኝቼ ነበር፡፡ አባቴ ገና በጠዋቱ እኔ ጋር በመምጣት ቀሰቀሰኝ፡፡ እንደተለመደው "የእኔ ውብ ልጅ" በማለት የሚያምሩትን ውብ ከንፈሮቼን ገመጣቸው፡፡ ከዚያ በፍቅር ዓይን እየተመለከተኝ "የእኔ ውብ ልጅ በፍጥነት ተነሺና ሰውነትሽን ታጥበሽ ለልደትሽ ያመጣሁልሽን ያን ውብ ልብስሽን ልበሺና ተዘጋጂ" አለኝ፡፡ በሚያወዛግብ ፈገግታ ተሞልቶ እየተመለከተኝ፡፡

"ሽርሽር ነገር ልንሄድ ነው?"

"አይደለም የኔ ውብ! አንድ ከፍተኛ እንግዳ ይመጣል"

"እና?"

"አስተዋውቅሻለሁ"

"ለእኔ?"

"በሚገባ"

ያን ከፍተኛ የሚባለውን እንግዳ ለማየት በጣም ፈለኩ። ምን ዓይነት ሰው ይሆን? እናም በፍጥነት

"እሺ" አልኩ። አባቴ በደስታ በድጋሚ የሚያምሩትን ውብ ከንፈሮቼን በመሳም ከክፍሌ ወጣ። እኔም በፍጥነት በመነሳት ሰውነቴን ታጠብኩ። ቁርሴን በላሁኝ። አዲስ ልብሴን በመልበስ የሚያምረው ትልቅ ሳሎናችን በመሄድ ያን ከፍተኛ እንግዳ መጠበቅ ያዝኩ። እናቴ በጠዋት ዕለቱ የመዳኒኃለም ቀን ስለነበር ቤተክርስቲያን ሄዳለች። ድንገት አባቴን ሳየው የሆነ የመቁነጥነጥ ነገር አነበብኩበት። ይህን የመሰለ ከፍተኛ የመቁነጥነጥ ስሜት ደግሞ እስከዛሬ ያላየሁበት ስለነበር በመጠኑ ግር ብሎኛል። ጥያቄ አነሣሁ።

"አባቴ" አልኩት።

" እህ" አለኝ። በቀስታ አነጋገር።

"እስቲ ስለ ከፍተኛው እንግዳ ንገረኝ"

"የእኔ ውብ ልጅ መሪጌታ እንዳለ ዋሲሁን ይባላል። እባክሽ ምንም ነገር እንዳትጨቀጭቂው የሚያዝሽን ብቻ እሺ ብለሽ አድርጊ ፤ ይህን ካደረግሽ ከረምት ትምህርት ስትጨርሺ ባህርዳር፣ አዲስ አበባ ፤ ሀዋሳ እና ዱባይ ሽርሽር እወስድሻለሁ"

"እውነት?"

"እውነት!"

"እስቲ ማል!"

"የዲማው ጊዮርጊስን እወስድሻለሁ!!" አለኝ።

" መሪጌታ ግን ምን ማለት ነው?"

" የዲቁና የቅስና የመዘምርነት ሙያን የሚያውቅ ዲያቆናትን፣ ቀሳውስትን፣ መዘምርነት ሙያን የሚያውቅ፣ ዲያቆናትን፣ ቀሳውስትን፣ መዘምራንን ሁሉ የሚያዝ ትልቅ ስልጣን ያለው ነው፤ በዚህ ላይ ስለ ነገ የሚያውቅ አዋቂ ነው"

"አባቴ ስለ ነገ ማወቅ ይቻላል እንዴ? አንቴ ስለ ነገ የሚያውቀው ታላቁ ፈጣሪ ብቻ እንደሆነ ነግሮኛል"

"እውነቱን ነው ፤ ግን ስለ ነገ የማወቅ ስልጣን የተሰጣቸው የተወሰኑ ሰዎች ምድር ላይ አሉ። አየሽ መሪጌታም ስለ ነገ ያውቃል"

"ግን እኮ አንቴ እን..." ከማለቴ አባቴ በፍጥነት

"እባክሽ ዝም በይ! ሌላ ጥያቄ አትጠይቂኝ" በማለት ተማፀነኝ:: ዝምታ ነገስ:: ዝ... ም...ታ... :: አባቴ የሚያስበውን አላውቅም:: እንዴት ሌላ ሰው በልቡ የሚያውጠነጥነውን ማወቅስ ይቻላል? እኔ ግን ስለ መሪጌታ እያሰብኩ ነበር:: እንዴት ስለ ነገ እንደሚያውቅ እያውጠነጠንኩ... ሳይታሰብ ከፍተኛ እንግዳ የተባለው መሪጌታ ከሳሎን ገባ :: ግዙፍ ረጅም ሰው ነው:: ደማቅ ጥቁር ጢም የወረረው ፊት ያለው ፣ ትላልቅ ዓይኖች ያሉት፣ ትላልቅ ከንፈሮች ያሉት ግዙፍ ሰው ነው:: አባቴ በፍጥነት ዘሎ የመሪጌታውን እግር ሳመ:: በአባቴ ሁኔታ አፈርኩ:: ተሸማቀቀኩኝ:: እንዴት ያለ ከአባቴ የበለጠ የናጠጠ ሀብታም ቢሆን ነው? ሀብታሙ አባቴ የመሪጌታውን እግር የሚስመው? አልኩኝ:: እንዴትስ የሰው ልጅ ለሰው ልጅ ይህን ያህል ይሰግዳል? አልኩኝ፡ ምክንያቱም አባቴ ውስጥ ያነበብኩት የአክብሮት ሳይሆን ከአክብሮትም የዘለለ የስግደት ነውና!

መሪጌታው ከትልቁ ሶፋ ወንበር ላይ በእርጋታ ተቀመጠ:: በእነዚያ ግዙፍ አይኖቹ በትኩረት ተመለከተኝ:: እጁን ዘረጋልኝ:: ውስጤ እና ስድስተኛው ስሜቴ ይህን አላስፈላጊ ሰው እባክሽ አትጨብጪው አለኝ:: ሳየው ሁሉ በማላውቀው ስሜት አስጠላኝ ፤ ግን ለአባቴ ቃል ስለገባሁለት እጄን ዘረጋሁለት:: አንዳች አይነ ምድር እንደሚነካ ሰው እየቀፈፈኝ- በጣም አጥብቆ ጨበጠኝ::

"በጣም የምታምሪ ቆንጆ ልጅ ነሽ!"

"ይሆናል"

"ማን ነው ስምሽ?"

"እሌኒ" አልኩ:: ግንባሬን ቋጥሬ::

"በትምህርትሽ ጎበዝ እንደሆንሽ ሰማው"

"የሰማኸው ልክ ይሆናል"

"እስቲ የግራ እጅሽን አምጪ"

"ለምን?"

አባቴ ወዲያው በዓይኑ እና በግንባሩ ተቆጣኝ:: ከዚያ እኔም በዝምታ ለመሪጌታው የግራ እጄን ሰጠሁት:: መሪጌታው የግራ እጄን ለተወሰኑ ሴኮንዶች ጨመቃቸው:: ከዚያ እጄን ለቀቀኝና ከተቀመጠበት በመነሳት እንደ አባቴ በማላውቀው ቋንቋ ይፀልይ ገባ...

"ጀጀሀሜ ጀጀሀሜ ጸጸርኤል ጸጸርኤል ጸጸርኤል አጥዮንዮስ አጥዮንዮስ አጥዮንዮስ ሐርጀምን ሐርጀምን ሐርጀምን..." ወዘተ ምናምን አለ። ከዚያ በትኩረት እያየኝ ተመልሶ ተቀመጠ። አባቴን እየተመለከተው

"በጣም ትክክለኛው ሰዓት ነው። ከሶስት ቀን በኋላ የወር አበባዋን ታያለች ! እንኳን ደስ አለህ" አለው። ከዚያ እኔን በተንኮለኛ የሚመስል ፈገግታ እያቃኘኝ

"የወር አበባሽ ከሶስት ቀን በኋላ ይመጣል! እንዳትፈሪ እሺ" አለኝና አባቴን እየተመለከተው "ቢቃ ደሙን ይዘህ ና!" በማለት በፍጥነት ተነሣ። አባቴ ሊሸኘው ወጣ። ምን እየተከናወነ ነው? ይህ መሪጌታ ምን እያደረገ ነው? ስለምን የወር አበባ እያወራ ነው? በእርግጥ ስለ ወር አበባ ት/ቤት ተምሬያለሁ! እንዴት የ13 ዓመት ሴት እንደመሆኔም ስለ ወር አበባ አውቃለሁ፤ ግን ይህ መሪጌታ እንዴት የእኔ የወር አበባ ስለሚመጣበት ቀን ሊያውቅ ይችላል? አባቴንስ የምን ደም ነው ይዘህ ና ያለው? ይህን መሰል ነገር እያውጠነጠንኩ አባቴ ተመልሶ መጣ።

"አባቴ የምን የወር አበባ ነው?" አልኩት።

"የመጀመሪያ የወር አበባሽን ማየት የምትጀምሪው ከሶስት ቀናት በኋላ ነው። አየሽ ወደፊት የተቃና ህይወት እንዲኖርሽ የመጀመሪያው የወር አበባሽ ላይ ጸሎት መደረግ አለበት ፤ ስለዚህ እኔ ደሙን ለመሪጌታ እወስድለትና ፀሎት ያደርግልሻል። ይህን የምናደርገው በዚህ ድንቅ ውበትሽ የተነሣ እጅግ በርካታ ፈተና እንዳያጋጥምሽ ነው። ቀሪውን ሌላ ጊዜ እነግርሻለሁ፤ ስለዚህ ጉዳይ ለማንም እንዳትናገሪ! በተለይ ለአንትሽ እንኳ እንዳትነግሪው! ብትነግሪው ዋ! የገባሁልሽን ቃል አፈርሰዋለሁ!!" በማለት ባለሁበት ጥሎኝ ወጣ። ይህ በሆነ ምሽት በጣም የሚያምረው የግሌ መኝታ ቤት ገብቼ ተኛሁ፤ ግን በህይወቴ በጣም አስቀያሚ ሌሊት ነበር። በጣም አስፈሪ ሌሊት ነበር። አራት ህልሞችን አየሁ። አራት አስፈሪ ህልሞች። አስጨናቂ ህልሞች... በነጋታው እሁድ ስለህልም ከዚህ በፊት አንቴ ነግሮኝ ስለነበር እናቴና አባቴ ጠዋት ቤት ስላልነበሩ ለሰራተኞችን ነግሬያት ከቤታችን ብዙ የማይርቀው መንቆረር ት/ቤት ዝቅ ብሎ በስተቀኝ ያለው የአንቴ ቤት እየበረርኩ ሄድኩኝ።

"ምነው በጠዋት የኔ ልጅ" አለኝ አንቴ ደንግጦ።

"አራት አስፈሪ ህልሞች አየሁኝ! ትላንት ሙሉውን ሌሊት አልተኛሁም ነበር አንቴ"

"እሺ ተረጋጊ የኔ ልጅ! ለመሆኑ ቁርስ በላሽ?"

"አልበላሁም! እንደተነሳሁ አንተ ጋር ነው የመጣሁት"

"ጥሩ! አሪፍ ቁርስ እሰራልሻለሁ! አብረን እንበላለን:: ምርጥ ሻይ አፈላልሻለሁ:: እንጠጣለን! ከዚያ ህልምሽን ትነግሪኛለሽ እሺ!"

"እሺ" አልኩኝ::

አጎቴ የምግብ ባለሙያም ጭምር ነው:: ይህን እናቴ ስትመሰክርለት ሰምቻለሁ:: እንዳለው እጅ የሚያስቆረጥም ቁርስ አበላኝ:: ምርጥ ሻይም አጠጣኝ:: ስንጨርስ

"እንዴት ነው?"

"ምርጥ ነው! አመሠግናለሁ!!"

"ጥሩ! በይ አሁን የምታስታውሺውን ህልም ንገሪኝ"

"አራት ናቸው:: ትልቅ መጥረቢያ፣ ሙዝ፣ ብስክሌት እና መስቀል ናቸው"

"ቆይ የእኔ ልጅ! ተራ በተራ እንያቸው መጥረቢያው ምን ዓይነት ነበር?"

"የሆነ አስፈሪ ሰው በደም የተነከረ ትልቅ መጥረቢያ ይዞ እኔን እየከተፈኝ ነበር በጣም እያስካካ ይስቅም ነበር:: አሁን ተሳካልኝ እያለ ይጮህም ነበር በቃ ስለመጥረቢያው ይህን ብቻ ነው ያየሁት"

"የእኔ ልጅ መጥረቢያን በህልም ማየት ሁለት ፍቺ አለው:: የተስፋ መቁረጥ፣ ያለመረጋጋት፣ ትዕግስት ማጣት፣ በቀል እና የውስጥ መረበሽ ሲሆን በህልም የታየው መጥረቢያው በደም የተጨማለቀ ከሆነ ሴይጣናዊ ንኪኪ ያለው ነው:: ይህ ማለት አንድ ሰው ሴይጣናዊ ስራ ሊሠራ እየተዘጋጀ መሆኑን የሚያመለክት ነው"

"እና አጎቴ?"

"ቆይ ሁሉንም ለመረዳት የተቀሩትንም መጀመሪያ ንገሪኝ እስቲ ስለ ሙዙ ንገሪኝ?"

"አባቴ በሀብት ላይ ሀብት እንጨምራለን! ኢትዮጵያ ውስጥ ስማችን የሚጠራ ትልቅ ሀብታም እንሆናለን! የኔ ውብ ልጅ እንኳን ደስ አለሽ በማለት ተለቅ ያለ ሙዝ በግድ እየታገለ ብልቴ ውስጥ ሲጨምርብኝ አየሁ"

"በቃ"

"በቃ አጎቴ!"

"ግራ የሚያጋባ ነው እኔ እንደማውቀው ሙዝ አንዲት ሴት በህልሟ ካየች የወሲብ ስሜት፣ ስለወሲብ ማሰብ፣ የወሲብ ስሜትን መጨቆን ነው:: እስቲ ሌላውን ህልምሽን

ንገሪኝ"

"መንገድ ላይ እየሄድኩ አንዲት ሰው ሳይሆን በራሷ ጊዜ የምትሄድ ያረጀች ሳይክል ወደ እኔ እየበረረች በመምጣት ላመልጣት ብሞክርም እያሯሯጠች ገጭታኝ ትሰወራለች"

"እህ... ምን ዓይነት ህልሞችን ነው ያየሽው? ግራ ያጋባል በህልም ብስክሌት ማየት በተለይ በብስክሌት ሲገጩ ማየት ችግር እና መሰናከል እንዳለ ጠቋሚ ነው:: በተለይ በወሲብ የሚመጣ ችግር እንዳለ ያመለክታል እስቲ ሌላውን ህልምሽን ንገሪኝ?"

"የማላውቃቸው በርከት ያሉ ሰዎች መጀመሪያ በጣም የሚያስጠላ ጥቁር እሾክ ያለበት መስቀል ላይ ሰቀሉኝ ከዚያ አንድ ፊቱን ማየት ያልቻልኩት በብርሃን የተከበበ ሰው 'አትፍሪ ሁሉ ነገር ሰላም ይሆናል! ሁሉ ነገር የምስራች ይሆናል!' በማለት ደም ያለው መስቀል ላይ ሠቀለኝ... በቃ ይህ ነው"

"መስቀል? እህ... አየሽ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው መስቀል በህልሙ ከተመለከተ ክርስትናን እንዲቀበል መለኮታዊ ጥሪ እየተደረገለት ነው፣ ግን ክርስቲያን የሆነሰው መስቀል በህልሙ ካየ እርዳታ መሻት፣ መከራን መቀበል፣ ስቃይን መዋጀት ነው:: በቀይ ደም ያለው መስቀል ላይ መሠቀል ደግሞ ፍቺው ህይወትሽ ብርሃን የሚያገኘው በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስትቀበይ ብቻ መሆኑን የሚጠቁም ነው ፤ ግን አየሽ አንዳንዴ ህልም ቅዥት ሊሆንም ይችላል ወይም ቀን ላይ የሚያስፈራ ነገር ስታከናውኚ ከነበርሽ አልያም አስፈሪ ሆረር ፊልም ካየሽ ያንን ማታ በህልምሽ የማየት ነገር ሊከሰት ይችላል፣ ስለዚህ እስቲ ትላንት ቀን ላይ ያደረግሽውን በእርጋታ አስታውሺና ንገሪኝ"

"አጎቴ የተለየ ነገር አልነበረም"

"ለምሳሌ የሆረር ፊልም አይተሽ ነበር?"

"በጭራሽ"

"የብልግና ፊልም አይተሽ ነበር?"

"በጭራሽ!"

"የኢየሱስን ፊልም አይተሽ ነበር?"

"በጭራሽ!"

አጎቴ በዝምታ ያብሰለስል ገባ:: ግራ መጋባት ይነበብበት ነበር:: በህልሞቹ ሳይጨነቅ አልቀረም:: እኔ ደግሞ ከራሴ ጋር እየተወያየሁ ነበርኩ:: ለእኔ ከአባቴም ከእናቴም

አንቴ በጣም ይበልጥብኛልና በመጨረሻ ወሰንኩ፡፡ እናም...

"ግን አንቴ" አልኩት፡፡ አንቴ በትኩረት ተመለከተኝ፡፡ በዝምታ፡፡

"በእርግጥ አባቴ ለማንም እንዳትናገሪ ብሎ አስጠንቅቆኛል ለምን እንደሆነ አላውቅም፡፡ ይህን ጉዳይ በተለይ ላንተም መንገር እንደሌለብኝም ጭምር አስጠንቅቆኛል ቢሆንም ልንገርህ ግን አደራ ነገረችኝ ማለት የለብህም"

"እሺ የእኔ ልጅ"

ለአንቴ የሆነውን እና ቤታችን መጥቶ ስለነበረው ከፍተኛ እንግዳ ነገርኩት፡፡ አንቴ ፊት ላይ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ድንጋጤ እና ንዴት አየሁበት፡፡ ከዚያ በንዴት ከንፈሩን ይበልጥ ነክሶ በለሆሳስ

"አሀ... የሚወራው እውነት ነው ማለት ነዋ?" ሲል ሰማሁት፡፡

"ምኑ አንቴ?"

"እህ ... የእኔ ልጅ እስቲ ይህን ጉዳይ በሚገባ እውነቱን ከሀሰቱ መርምሬ ላጣራ! እርግጠኛ ነሽ ግን ቤታችሁ ትላንት የመጣው ከፍተኛ እንግዳ የተባለው ስሙ መሪጌታ እንዳለ ዋሲሁን ነው?"

"ሺ ፐርሰንት እመነኝ አንቴ! እርግጠኛ ነኝ ስሙ መሪጌታ እንዳለ ዋሲሁን ነው!!"

"በቃ የእኔ ልጅ እኔ ሁሉን ነገር አጣራለሁ አንቺ በታላቁ ፈጣሪ እምነት ይኑርሽ አንዳችም ባንቺ ላይ አይሆንም ፤ ስለዚህ አሁን ወደ ቤት ተመልሰሽ ሂጂና የበላሽው ምግብ ሲረጋጋ ከአንድ ሰዓት በኋላ ገላሽን ታጠቢ፡፡ እኔ ስለህልምሽ ከእኔ የተሻሉ ህልም የሚፈቱ ሽማግሌ ስላሉ እሳቸው ጋር ሄጄ ልከኛውን ትርጉሙን አጣራለሁ፡፡ ተረጋጊ እሺ" በማለት የቀኝ እጄን በመሳም ወደ ቤት እንድሄድ ነገረኝ ፤ ቅሉ ግን አንቴ ላይ የተደበላለቀ ስሜት ይነበብ ነበር፡፡ አንቴ ተረጋጊ ቢለኝም ምክንያቱን በግልፅ ባልረዳውም ውስጤ ግን ለመረጋጋት አልቻለም ነበር፡፡ ሰባተኛው ስሜቴ አንዳች አስቀያሚ ነገር እንዳለ ሹክ እያለኝ ነበር፡፡ በጣም ቀፎኝ ነበር፡፡ "የአንቴ ተረጋጊ እሺ" የሚለው ቃል እርጋታን አልሰጠኝም ነበር፡፡ አንዳች አስቀያሚ ነገር ይፈጠራል ይለኝ ነበር፡፡ ሰባተኛው ስሜቴ፡፡ ውስጤ፡፡ እኛ ሰዎች የደመነፍሳችንን መልዕክት አንረዳውም እንጂ አንዳች አስቀያሚ ነገር ሲፈጠር ሲል በእርግጠኝነት ሹክ እንደሚለን ዛሬ ላይ በሚገባ መናገር እችላለሁ፡፡

እንደሰማሁት የወር አበባ የደህ ቤት በአስራ ስድስት ዓመት ትገባለች:: የወር አበባ እንኳ ሙሰኛ ሆና ሀብታምን ከደሀ በመለየት የሀብታም ቤት በ12 ዓመት ትገባለች:: እኔ ጋር ደግሞ በ13 ዓመቴ መጣች:: እነሆ በህይወቴ የመጀመሪያውን የወር አበባ አየሁ:: ት/ቤት በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ቁርጥማት እና ቁርጠት ሆዴ እና ወገቤን አንቀጠቀጠኝ፣ ቆራረጠኝ፣ ፈጀኝ እንዳች እሳት ውስጤ እየነደደ ያለ መሰለኝ:: እነዚህ ምልክቶች የወር አበባ መሆናቸውን አውቅ ስለነበር ጥርሴን ነክሼ የመጨረሻው ክፍለ ጊዜ እስከሚያልቅ ጠበኩ:: ሌላ ጊዜ ከት/ቤት ቤታችን የሚወስደኝ ምስኪኑ ካላናገሩት የማይናገረው ሚስቱ እና ልጁ በመኪና አደጋ አባይ በረሃ ውስጥ በምትገኘው ፍልቅልቅ በምትባለው ትንሽ ከተማ የሞቱበት ራሱም የፍልቅልቅ ተወላጅ የሆነው ሁልጊዜ ሳየው አንጀቴን የሚበላው ሹፌራችን ነበር:: ዛሬ ግን አባቴ የራሱን ቪ8 የምትባለውን መኪና ይዞ ነበር የመጣው:: ገና እንዳየኝ በደስታ እየተፍለቀለቀ መጣና ከንፈሬን ምጥጥ አድርጎ ሊስመኝ ሲል ተማሪዎች ፊት እንዳይስመኝ በዘዴ ሸውጄው መኪናው ውስጥ ገባሁ::

"እሺ የእኔ ውብ ልጅ ቀኑ እንዴት ነበር?"

"እያመመኝ ነው እባክህ አባቴ በፍጥነት ወደ ቤት እንሂድ!" አልኩት::

"አይዞሽ የኔ ውብ ልጅ ዛሬ በህይወትሽ የመጀመሪያዋን የወር አበባ ያየሽባት ልዩ ቀን ናት"

"መሪጌታው ግን የወር አበባዬ ዛሬ እንደሚመጣ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?"

"ስለ ነገ ያውቃል፤ አዋቂ ነው ብዬሽ አልነበርን አሁን አመንሽኝ አይደለም?"

ዝም አልኩት:: አባቴን መጠራጠር ጀምሬያለሁ:: በተለይ ከአጎቴ ላይ ያን ፍራቻ እና ያን ግራ መጋባት ካየሁበት በኋላ አባቴን ሰባተኛው ስሜቴ እየተጠራጠረው ይገኛል:: አባቴ ምንም ሳይናገር መኪናውን እያበረረ ይከንፍ ጀመር:: ታሪካዊው መንቆረር ት/ቤት አቅራቢያ የሚገኘው ቤታችን ሳይሆን ወደ ስታዲየውም ይበር ጀመር:: ግራ ሲገባኝ

"ቤት አንሄድም እንዴ?" አልኩት::

"የኔ ውብ አንድ ቦታ ደርሰን እንመለሳለን" አለኝና በድጋሚ እያየኝ

"አንቀይም የኔ ውብ ልጅ" በማለት መኪናዋን ይበልጥ ያከንፉት ጀመር:: ከደብረማርቆስ ስታዲየውም በስተግራ በሚገኘው መንገድ ታጠፈ:: አንድ በጣም የሚያምር ቪላ ቤት ውስጥ መኪናዋ ገባችና ቆመች:: አባቴ በፍጥነት ወረደ:: እኔ የተቀመጥኩበት

ወንበር ጋር መጣና "ውረጂ የእኔ ውብ ልጅ ሶስት ደቂቃ ያህል ብቻ ነው የምንቆየው! ነይ ውረጂ የኔ ልጅ!" በማለት እያጣደፈኝ ከመኪናዋ አስወረደኝ፡፡ እጄን በመያዝ ወደ ሚያምረው ሳሎን ይዞኝ ሄደ፡፡ እየፈራሁ፤ ውስጤ እየተጨነቀ ስድስተኛው ስሜቴ እየተጨነቀ፣ ሰባተኛው ስሜቴ ተይ ይቅርብሽ እያለኝ፤ እንደበግ እየተነዳሁ ገባሁ፡፡ ልክ ቤቱ ውስጥ ስገባ ከትንሿ ብልቴ ድንገት ደም ጠብ... ጠብ... ሲል ተሰማኝ፡፡ ጥርሴን ነከስኩ፡፡ ቤቱ ውስጥ በርከት ያሉ ሰዎች ፊታቸው እንዳይታይ ተሸፍነው መሬት ላይ የተዘረጋው ፍራሽ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ አባቴ እጄን ጭምቅ አድርጎ በመያዝ ወደ ግራ የሚገኘው ክፍል ውስጥ ይዞኝ ገባ... በጣም ሰፊ ክፍል ነው፡፡ ትልቅ ነጭ ፍራሽ አለ፡፡ አንድ ሳህንም አለ፡፡ በቃ ሌላ ምንም የለም ፤ ወዲያው ያ እኛ ቤት የመጣው አስፈሪው መሪጌታ መጣ፡፡ ከአባቴ ጋር እኔ በማላውቀው ቋንቋ ያወሩ ጀመር

"ኩቢኮንታቼ?"

"እንጥኪዮቼታ!"

"ማንቴቲያ?"

"ማንቴቲያኪ!"

ይህን ትርጉሙን ያላወኩትን ንግግር አውርተው ዝም ዝም ተባባሉ፡፡ ከዚያ ሁለት ጠብደል ሰዎች ድንገት በመምጣት አጣድፈው ያዙኝ! ትልቁ ነጭ ፍራሽ ላይ አጋደሙኝ፡፡ በፍጥነት ልብሴን አወለቁት... እንዳልጮህ አንደኛው አፌን ያዘው፡፡ መሪጌታው የማላውቀውን ቋንቋ በመጠቀም ፀሎት ያደርግ ጀመር "ደናይል ሸላሹ ወሼይፌ እምህራ ሐጂጂሐ ሐርጅምን ነዓሼፈ አጀረማን አጀረማን ዮናኬል ዮናኬል ዮናኬል ፐፐርያል ፐፐርያል ቃብላጣኤል ቃብላጣኤል ..." ምናም የሚሉ ነበሩ፡፡ ይህን በመሰለ አስደንጋጭ ደቂቃ እንዴትስ ሁሉንም ቃላት ለማስታወስ ይቻለኛል? ከዚያ በእጁ ይዞ የነበረውን ስኒ ውስጡ ምን እንዳለ ባላውቅም ቀመሰና እኔ ላይ እንትፍ እንትፍ አለብኝ፡፡ አባቴ በፍጥነት አልባሳቱን አወለቀና የመሪጌታን እግር ሳመ፡፡

ከ...

ዘ...

ያ... የፈጣሪ ያለ! ? ይህን እኔ ማመን

አልቻልኩም... ይህን እኔ በህልሜ እንኳ ማየት አልቻልም... ይህን ለሰዎች ሳወራ እንዴት ሊያምኑኝስ ይችላሉ? ከ... ዘ... ያ... አባቴ... በመልከ ቁርጥ እኔን የሆነው የገዛ እውነተኛው

አ... ባ... ቴ... በጣም ወፍራም እና ትልቅ ብልቱን አቁሞ ወደ እኔ መጣ... ይህን ሰቅጣጭ ትዕይንት ለማየት ስላልቻልኩኝ አይኔን ጨፈንኩ... ጥርሴን ነከስኩ:: የተወለድኩበትን ቀን ረገምኩ::

የአባቴ በጣም ወፍራም እና ትልቅ ቁላ የእኔ ትንሿ ያልተዘጋጀች እምስ ውስጥ ለመግባት ያደርግ የነበረውን ጥረት... ከዚያ ሲገባ የነበረውን ስቃይ፣ የነበረውን በቃላት ሊገለፅ የማይችል ህመም... የተሰማኝን ቃጠሎ፣ ያደረኩትን ጩኸት ... እንዴት በቃላት ማስቀመጥ እችላለሁ? እንዴትስ ይህን ዘግናኝ ትዕይንት ለመናገርስ እችላለሁ? የማስታውሰው ነገር አባቴ ስሜቱን ሲጨርስ መሪጌታው እየሣቀ እኔ ላይ ሲወጣ ነበር... በቃ ከዚህ በኋላ ያለውን አላስታውስም... ማስታወስም አልፈልግም... ብፈልግም አልችልም... ብቻ ይህ ዘግናኝ ትዕይንት ከተፈፀመ ሀያሶስት ሰዓት በኋላ በመጠኑ ስነቃ ራሴን ያገኘሁት ሆስፒታል ውስጥ ነበር:: አጠገቤ የእናቴ ዓይኖች ቀልተው እና አብጠው ነበር:: ከአጠገቧ የምወደው አጎቴ በከፍተኛ ሀዘን ተውጦ ተቀምጦ ነበር...

ሁለቱን ሳይ አለቀስኩ? አላለቀስኩም:: እንባ ጨርሻለሁ! እንባስ ከየት አባቱ ይምጣ? ተናገርኩ? አልተናገርኩም! ቃላትን ጨርሻለሁ እናም በዝምታ አይኔን ወደግራ ወደቀኝ በማድረግ እያፈራረኩ ሁለቱንም አየዋቸው:: በዚያች ሴኮንድ አባቴን ባለማየቴ ቢያንስ ተረጋግቻለሁ:: እናቴ ወዲያው ጉሉኮስ ያልተሰካበትን እጄን ያዘችኝ:: ከቀሉት ዓይኖቿ እንባ ዱብ ዱብ እያደረገች "አይዞሽ የኔ ውድ! ይህ ሁሉ የሚሆን አልመሰለኝም ነበር፤ እኔንም አባትሽንም ይቅር በይን! ይቅርታ አድርጊልኝ! አባክሽ ይቅርታ አድርጊለት!" በማለት አይኔን፣ ግንባሬን፣ እግሬን በመሳም ወዲያው ተፈትልካ ወጣች:: ይህ ትዕይንት እናቴን ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁበት ነበር:: ከዚያ በኋላ በድጋሚ በህይወት አላየዋትም:: በኋላ እንደተነገረኝ ይቅርታን ለምናኝ ከሆስፒታል የተሰናበተችኝ ሚስኪኗ እናቴ እኔ ከተኛሁበት ሆስፒታል ከወጣች በኋላ እንደ አሜሪካ የሆሊውድ የፊልም አክተሮች አክሽን ፊልም ሠርታ ሞተች አሉኝ:: ቤታችን ውስጥ ያለውን የአባቴን መሣሪያ በመጠቀም መጀመሪያ አባቴን ግንባሩን በማለት ገደለችው:: ያ አላረካትም መሰለኝ ከሞተ በኋላ ጋዝ አርከፍክፋበት በእሳት አቃጠለችው ከዚያ በቀጥታ የመሪጌታው ቤት በማምራት ቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሁሉ በሽጉጥ እየበረቀሰች ጨረሰቻቸው:: ይህም አላረካትም መሰለኝ ቤቱን በእሳት አቃጠለችው! የጀግናው በላይ ዘለቀ መንፈስ እንዳለባት አስመስከረች! በመጨረሻ እንደ ንጉስ አፄ ቴዎድሮስ ራሷን ገደለች! ይህ የእናቴ

ታሪክ ነው... በኩራት የማላወራው አስቀያሚ ታሪክ:: የመደፈር እና የመግደል ታሪክ::

እርግጥ ዛሬ ሁሉን ነገር አውቄያለሁ:: ይህ ሁሉ የሆነው እናቴም በተለይ አባቴ ከመሬት ተነስተው በአንድ ጀንበር ሀብታም የሆኑት ጠንቋይ ቤት እየተመላለሱ ስለነበር ነው:: የመጀመሪያ ልጃቸውንም ለሰፈሩ ሰዎች እና ለቤተዘመድ ሞተ ብለው አስወሩ እንጂ ለጠንቋይ ቤት ደሙን ገና በጨቅላነቱ ቀልበውት ነበር:: ይህም አልበቃቸውም ነበርና በተለይ አባቴ የሀብት መጠኑ እንዲጨምር እና ያለው ሀብትም እንዳይባክን እኔንም ለጠንቋይ ቤት የደም ትስስር ለመፍጠር የመስዋዕት በግ አድርጎ መቀለብ ነበረበት:: ገና ስወለድ እየተቀለብኩ ያደኩ የመስዋዕት በጊት ነበርኩ:: የሰው ልጅ በግን የሚንከባከበው አስብቶ ለመሸጥ አልያም አስብቶ ለመብላት ነው የሚባለው ትንቢት በእኔ ላይ ተፈፀመ:: የገንዘብ አምልኮ የሀጢያት ሁሉ የደም ስር ነው:: አዕምሮን አውሮ የማይደረገውን ሁሉ ያስደርጋል የሚባለው ትንቢት በእኔ ላይ ተፈፀመ ፤ እናም የእኔ ደም በጠንቋይ ቤት መፍሰስ ለአባቴ የሀብቱ ማሰሪያ ውል ነበር:: ያ ያየሁት አስፈሪ ህልም እውነት ነበር:: አባቴ ለገንዘብ ሲል አዕምሮው ታውሮ ነበር ... ለገንዘብ ሲል ከገዛ ልጁ ጋር ወሲብ ማድረግ ፣ የገዛ ልጁን መድፈር፣ የገዛ ልጁን ማስደፈር ነበረበት! ይህ የእኔ የእሌኒ አስቀያሚ ታሪክ ነው:: ይህ የእኔ የእሌኒ ፍቅር አብርሃም እውነተኛ አስቀያሚ እና ሊታመን የማይችል በኢትዮጵያ መሬት ላይ የሆነ እውነተኛ ታሪክ ነው:: አባቴን ለዚህ ነው ፍቅር አብርሃም ከሚሉት ይልቅ ሴይጣን አበረ የሚል ስም ቢሰጡት ይሻለዋል ያልኩት:: አንዳንዴ በሀበሻ ምድር ስምን መላዕክ ያወጣዋል የሚባለው ፍፁም ሀሰት ነው! በዚህ አባቴ ምርጥ ምሳሌ ነውና!!

እነሆ የፌስቱላ ችግር አልደረሰብኝም:: ቢሆንም ለስምንት ቀናት ያህል በሆስፒታል ውስጥ ህክምና እና የስነልቦና ምክር ተደረገልኝ:: ዘጠነኛው ቀን ከአጎቴ ጋር እኛ ቤት በጭራሽ መሄድ ስላልፈለኩ አጎቴ ቤት ነበር በቀጥታ ያመራሁት:: ከአጎቴ ፊት ላይ በቃላት ሊመነዘር እና በሐረጋት ሊተነተን ከቶ የማይችል ሀዘን፣ ጭንቀት፣ ቁጭት ይነበብ ነበር:: ውስጡ በንዴት እንደቆሰለ ያስታውቅ ነበር::

“የእኔ ልጅ ህልምሽን ነግረሽኝ ልደርስልሽ ባለመቻሌ በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ!

ይህ ይሆናል የሚል ግምት ጨርሶ አልነበረኝም፤ ለማንኛውም የእኔ ልጅ ነገሌላ ቀን ነው:: አዲስ ህይወት እንጀምራለን! እኔ አባትሽ እሆናለሁ! ምንም እንዳትጨነቂ ፈጣሪ ካንቺ ጋር ነው" አለኝ::

"እናቴ! ፈጣሪ ከእኔ ጋር ቢሆን ኖሮ ያ ሁሉ ዘግናኝ መከራ ሲደርስብኝ ለምን ዝም አለ? ለምን አይፈጃቸውም ነበር? ለምን ህልሙን አስቀድሞ አሳይቶ ዝም አለኝ? እውነት ፈጣሪ በሁሉም ቦታ እና በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ከሆነ ያን የመሰለ መቼም ልረሳው የማልችለው ድርጊት እየተፈፀመብኝ እያየ ለምን ዝም አለኝ? ለምን እኛን ይጠብቁ ዘንድ የፈጠራቸውን መላዕክትን አላስጠበቀኝም ነበር? ለምን እውነት ፈጣሪ ካለ ያ ሁሉ ስቃይ ሲደርስብኝ ፣ ያ ነጭ ፍራሽ በደም ተጨማልቆ ቀይ ሲሆን እንዳችም ነገር ማድረግ ተሳነው? እውነት ፈጣሪ ከዙፋኑ አለ?" ይህን ለእናቴ ስናገር እና ስጠይቅ በታላቅ ቁጣ ውስጤ እየነደደ ነበር::

"የእኔ ልጅ ፈጣሪ ድንቅ ነው:: የፈጣሪን ፀጋ መመርመር አይቻልም:: የፈጣሪን እቅድ ማወቅ አይቻልም:: ፈጣሪን ይህን ለምን አደረክ? ይህ ሲሆን ለምን ዝም አልከኝ? እውን ከዙፋንህ አለህ ወይ? አይባልም:: በእርግጥ በእኔ ግንዛቤ እና እይታ ሁሉ ነገር የሚሆነው ለበጎ ነው የሚል እምነት ባይኖረኝም ሁሉ ነገር የሚሆነው ግን ለምክንያት እንደ ሆነ አውቃለሁ:: ለምሳሌ አንቺ ላይ ይህ ነገር ተፈጠረ፡፡ እናትሽ በንዴት አባትሽን እና እነዚያን ጠንቋዮች እና ደብተራዎች በመሳሪያ እና በእሳት ፈጀቻቸው:: አየሽ እነዚያ የሴይጣን አጨብጫቢዎች እና ተላላኪዎች የሌሎች ሰዎችን ወይም እንዳንቺ ያሉ ህፃናትን ህይወት ማጨማለቃቸውን ሳይቀጥሉበት ባንቺ የተነሣ በእናትሽ እጅ ህይወታቸው ጠፋ! ገና ወደፊት ደግሞ ፈጣሪ በሰሩት ሀጢያት የማይጠፋ የዘላለም እሳት ውስጥ ይጨምራቸዋል!! አየሽ አንቺ ምንጊዜም ማስታወስ ያለብሽ አራተኛውን ህልምሽን ነው:: ፈጣሪ ላንቺ የወደፊቱን አሳይቶሻል!! ስለ መስቀሉ አስታወሽ?

"እህ"

"እስቲ በድጋሚ ንገሪኝ?"

"የማላውቃቸው በርከት ያሉ ሰዎች መጀመሪያ በጣም የሚያስጠላ ጥቁር መስቀል ላይ ሰቀሉኝ፤ ከዚያ አንድ ፊቱን ማየት ያልቻልኩት ሰው 'አትፍሪ ሁሉ ነገር ሠላም ይሆናል! ሁሉ ነገር የምስራች ይሆናል' በማለት ደም ያለው መስቀል ላይ ሠቀለኝ"

"ልክነሽ! አየሽ ይህ ተራ ህልም አይደለም፡፡ የእኔ ልጅ ተደግሶልሽ ከነበረው ከቤተሰቦችሽ የጥንቁልና ዛር እና መንፈስ አሠራር ነፃ እንደምትወጪ የተነገረሽ የምስራች ነው፡፡ ነፃ የሚያወጣሽ ደግሞ መስቀሉ ላይ ለሰው ልጆች ስለፍቅር ሲባል ቤዛ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ነው፤ ስለዚህ አትጨነቂ ነገ ሁሉ ነገር ይስተካከላል፤ እናም ለአንዲት ሴኮንድም ብትሆን ታላቁን ፈጣሪን በጭራሽ እንዳትወቅሺ! ቸሩ መድኃኒዓለም አንቺን ድቅድቅ ጨለማ እና በረሐ ላይ ጥሎሽ በጭራሽ ዝም አይልሽም ፤ ምክንያቱም ይህ የታላቁ ፈጣሪያችን ባህሪ አይደለምና!!"

"እንዳልክ አጎቴ"

"የእኔ ልጅ አሁን አንድ ሀሳብ ነበረኝ"

"ምን?"

"ከዚህ በኋላ አባትሽ ነኝ! አንቺን ከማንኛውም ነገር መጠበቅ አለብኝ፤ በዚያ ላይ የተረጋጋ ህይወት እንድትኖሪ ማድረግ አለብኝ፤ ስለዚህ ትምህርትሽን ለመጨረስ ትንሽ ቀናት ይቀራሉ፤ ስለዚህ ፈተናሽን እንደምንም ተፈተኚና ስትጨርሺ እዚህ ያለውን ጣጣ ጨርሰን በቀጥታ ደብረማርቆስን በመሰናበት ወደ ሰፊዋ አዲስ አበባ እናመራለን ምን ይመስልሻል?"

"አዲስ አበባ ለመኖር?"

"አዎ!"

"ያንተ ስራስ?"

"አዲስ አበባ ስራ እፈልጋለሁ፡፡ አሳማኝ ሙያም ስላለኝ በእርግጠኝነት አላጣም፤ በዚያ ላይ ለራሴ የሚሆን በቂ ገንዘብ አለኝ፤ ያው የምሰራው መስራት ስላለብኝ እና በተጨማሪ ያለአንዳች ስራ የሚቀመጥ አዕምሮ የሴይጣን እና የስንፍና እስረኛ ስለሚሆን ማንም ሰው ያለ አንዳች ስራ በጭራሽ መቀመጥ ስለሌለበትም ነው"

"ግን ለእኔ ስትል እንጂ አዲስ አበባ ለመኖር ህልም አልነበረህም?"

"እውነቱን ለመናገር አዎ"

"አጎቴ!"

"አቤት!!"

"ውስጤን ስላነበብከው አመሠግናለሁ፡፡ ሆስፒታል እያለሁ የማስበው ሁሉ ከተወለድኩበት ደብረማርቆስ ራቅ ያለ ቦታ ሄዶ መኖርን ነበር፤ ስለዚህ በደስታ እስማማለሁ!!"

"ግን የእኔ ልጅ"

"ግን ምን ?"

"እያንዳንዱን ዝርዝር መረጃ ባይሆንም እንደምታውቂው ከተማችን ትንሽ ስለሆነች ወሬ በፍጥነት ይዳረሳል፤ ስለዚህ ት/ቤት ያንቺን ጉዳይ ሰምተው ልጆች ሆን ብለው ሊተናኮሉሽ ይችሉ ይሆናል:: እባክሽ የእኔ ልጅ ሀዘን እንዳይሰማሽ እሺ!! ካልሆነ ትምህርትሽን አቋርጪና አዲስ አበባ ትቀጥያለሽ ወይ ፈተናውን ብቻ ሄደሽ መፈተን ይሻላል? ምን ይመስልሻል የእኔ ልጅ?"

"አትጨነቅ አጎቴ! በቀላሉ አልሰበርም:: ምሳሌ መሆን እፈልጋለሁ! በዚያ ላይ ስለዚህ ጉዳይ ሆስፒታል እያለሁ ምን ማድረግ እንዳለብኝ የሥነልቦና አማካሪዋ ነግራኛለች:: እኔም ተዘጋጅቻለሁ! አደርገዋለሁ! ሰባተኛ ክፍልን በድጋሚ መማር አልፈልግም! ችግሬን ለማሸነፍ እንጂ ችግሬ እንዲያሸንፈኝ አልፈቅድለትም" አልኩት:: ቁርጥ ባለ አቋም::

"ጎበዝ ኢትዮጵያዊት!!" በማለት እንደተለመደው የቀኝ እጄን ሳመኝ:: በነጋታው ጥርሴን ነክሼ እና ውስጤን አጀግኜ የሚመጣውን ፈተና ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ሚስኪኑ ሹፌሬ ከአደጋው በኋላ መኪናዋን ይዞ መጥፋቱን አጎቴ ስለነገረኝ ለአጭር ቀናት ት/ቤት የምታመላልሰኝ ሴትዮ ስላገኘው በእርሷ መኪና ት/ቤት አመራሁ:: እንደጠበኩት ነበር:: ት/ቤት በመምጣቴ ብዙዎች በግርምት ከሌላ ዓለም እንደ መጣች ዮፎ ሲመለከቱኝ ነበር:: ብዙዎች ተማሪዎች እና አስተማሪዎች የሆነውን ነገር በተለይ የእናት እና አባቴን ሞት በተለይ አባቴ በከተማዋ ታዋቂ ስለሆነ በእርግጠኝነት መስማታቸው ከአይታቸው ላይ ያሳብቅ ነበር:: ከብዙ አስተማሪዎችም ሆኑ ተማሪዎችም የፊት ገፅታ ላይ የሚነበበው ለእኔ ያላቸው ሀዘኔታ ነበር:: በጣም ደስ ያለኝ ግን ማንም ደፍሮ በመምጣት ያናገረኝ አለመኖሩ ነበር:: በእርግጥ በተማሪዎች ሆነም አስተማሪዎችም ሁኔታ ብዙም አልተገረምኩም ፤ ምክንያቱም እነርሱ ምን አጠፉ? አስቀያሚውን ታሪክ የጻፉት ቤተሰቦቼ አይደሉም? እና ቢያንሾካሽኩብኝ ልገረም ይገባልን? በውስጣቸው እንዴት አይነት ጨካኝ ሴት ናት እናትና አባቷን በሞት አጥታ አርባቸው እንኳን ሳይወጣ? ሰማኒያቸው ሳይወጣ፣ እንዴት ት/ቤት ትመጣለች? ይሉ ይሆናል አልያም ደግሞ እናትና አባቷን ቀብራ በቀናት ውስጥ ለት/ት መመለሷ እንዴት ያለ የአዕምሮ ጥንካሬ ያላት ቆራጥ ሴት ናት ይሉ ይሆናል :: አልያም እውን የእኔ እናትና አባት ሞተው ቢሆን ኖሮ በስንት ቀናት ት/ቤት እመለስ ነበር? እያሉ ራሳቸውን በጥያቄ ይወጥሩ ይሆናል...

ብቻ ይህ ሁሉ እንዳለ በዚች ምድር ላይ ያለው ትልቁ እውነታ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ከስተቱ ምንም ይሁን ምንም "በምድር ላይ ከ72 ሰዓት በላይ የሚያስገርም አንዳችም ነገር የለም" ይላሉ የሰዎችን ስሜት እና የሥነልቦና ሁኔታ አጥንተናል የሚሉት ባለሙያዎች ፤ ይህ እውነት መሆኑን ለማመን በመጠኑ ችያለሁ:: እርግጥም ት/ቤት ውስጥ እኔ ላይ የነበራቸውን እይታ ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎችም የነቀሉት በሶስተኛው ቀን ላይ ነበር:: እኔም እንደ ወግ አጥባቂዎች እና የአሮጊት ተረት እንደሚወዱ ሰነፎች ሀዘንተኛ መሆኔን ለማሳበቅ ፀጉሬን አልተላጨሁትም! እንዴትስ ለደፈረኝ አባቴ ሞት እላጫለሁ? ጥቁር ልብስም አለበስኩም! እንዴትስ ለደፈረኝ እና ላስደፈረኝ አባቴ ጥቁር ልብስ እለብሳለሁ? እናም ትኩረት አልሳብኩም:: ሁሉም የእኔን ጉዳይ ረስተው ወደራሳቸው ዓለም ዞረው ነበር፤ ይመስለናል እንጂ በዚች ከንቱ የሆነች ዓለም ውስጥ ሁላችንም ራስ ወዳድ ነን! ሁላችንም 24 ሰዓት 99% በቀኝም ይሁን በግራ የምናውጠነጥነው ስለራሳችን ነው:: ይህ ድብቅ የማንነታችን መገለጫ ነው:: ይመስለናል እንጂ እኛ ሰዎች በዓለም ላይ በቁጥር አንድ የምናውጠነጥነው ስለራሳችን ነው:: ይህ የተዳፈነ ግን ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው:: ለዚያ ነው ግልፅ ማውራት የሚወዱት ነጮች በዓለም ላይ በጣም አስፈላጊዋ እና ቀዳሚዋ ቃል "እኔ" የምትለዋ ነች የሚሉት::

እነሆ ቀናት በፍጥነት ቀለጡ:: እኔም ሙሉ ትኩረቴን በትምህርት ላይ ብቻ ለማድረግ ወሰንኩ:: በራሴ ጥንካሬ እና ውሳኔ ተደሰትኩ:: በተለይ አጎቴ በጣም እንደተገረመብኝ ያስታውቅበት ነበር:: እስከዛሬ አስቀያሚው ትዕይንት እስከሚፈጠር ድረስ የሌላ ሰው ቤት እንዳድር በጭራሽ ስለማይፈቀድልኝ አጎቴ ቤት እንኳ አድሬ አላውቅም ነበር:: አሁን ግን አጎቴ ቤት አብሬው መኖር ከጀመርኩ አስራ አምስተኛ ቀን ሆነኝ:: አንድ ቀን ድንገት አጎቴ ከሰጠኝ መኝታ ቤት ተኝቼ ያን አስቀያሚ ትዕይንት አስታወስኩና እንቅልፍ አጥቼ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ተነሣሁ:: የሳሎን መብራት እንደበራ ነበር:: አጎቴ ረስቶት ተኝቶ ይሆናል በማለት ወደ ሳሎን ሳመራ አጎቴ ተቀምጦ እያነበበ አየሁት:: ገና ሲመለከተኝ በጣም ደነገጠ:: ከወንበሩ በፍጥነት ተነሣ

" ምነው የእኔ ልጅ?"

ልነግረው አሰብኩና እንዳልረብሸው ስለፈለኩ ዋሸሁት " ብዙ ውሃ ጠጣሁ መሰለኝ ሽንቴ ወጥሮኝ ተነስቼ ነው"

"ጥሩ! አየሽ ከምሽቱ 2 ሰዓት በኋላ ብዙ ውሃ አትጠጡ የሚባለው ለዚህ ነው::

ለብዙ ሰዎች ማታ ላይ ቡና ፣ ኮካም ሆነ ብዙ ውሃም መጠጣት እንቅልፍ ይነሣል፤ ይህ ሳይንስ ያረጋገጠው ነው"

"አንተ ግን ለምን እስካሁን አልተኛህም?"

"የእኔ ልጅ እስካሁን በህይወቴ በጣም ተኛሁ ከተባለ ረጅሙ ለአምስት ሰዓት ብቻ ነው፤ በእርግጥ አንድ ሰው ጤነኛ ለመሆን በቀን ውስጥ ቢያንስ ለስምንት ሰዓት መተኛት ግዴታው ነው:: ይህን ሳይንስ ያወራል፤ እኔ ግን አልቻልኩም፤ ስለዚህ አምስት ሰዓት ብቻ ነው የምተኛው:: ለነገሩ ለእኔ አሪፍ ነው እነብበታለሁ! መተኛት ሲበዛ ትልቅ ስንፍና ነው:: በዚያ ላይ እንደኛችንን ስንሞት እንተኛለን፤ በእርግጥ ሞት ማለት መተኛት ባይሆንም" አለኝ:: አጎቴ ሲያነበው የነበረውን መፅሐፍ ርዕስ አየሁት:: "ሴቶችና መፅሐፍ ቅዱስ" የሚል ርዕስ ያለው ነው::

"ሴቶችና መፅሐፍ ቅዱስ?" አልኩት::

"እህ"

"ሚስት የማታገባ ከሆነ ስለሴቶች ለምን ታነባለህ?"

"የእኔ ልጅ እውቀት እኮ ጠቃሚ ነው:: እኔ ባልጠቀምበት ለሌላ ሰው መረጃውን አስተላልፍ ይሆናል:: የዚህ መፅሐፍ ፀሐፊ እንኳ ዋነኛ ዓላማው ሴቶችን ማናናቅ፣ ሴቶችን ማጥላሸት ፣ ሴቶችን የስህተት ሁሉ ጀማሪ፣ ሴቶችን ግንባር ቀደም የሴይጣን ተላላኪ አድርጎ ለማቅረብ እየጣረ ነው:: ይህን ደግሞ ይበልጥ ለማሳካት ዋነኛ ማጣቀሻውን የሚያደርገው መፅሐፍ ቅዱስን ነው"

"ለምሳሌ?" አልኩትና አጠገቡ ሄጄ ቁጥጥ በማለት ተቀመጥኩ::

"ለምሳሌ ለታላቁ አብርሃም አምላክ ብዙ ልጆች እንደሚሰጠው እና ትውልዱ እንደ ከዋክብት እና የምድር አሸዋ እንደሚበዛ ተነግሮት እና የትንቢት ተስፋ ተደርጎለት እየጠበቀ ነበር:: ይህን በታላቅ ተስፋም ይጠብቁ ነበር፤ ቅሉ ግን አብርሃም እና ሚስቱ ሣራ እስከ እርጅናቸው ልጅ መውለድ ስላልቻሉ ሚስቱ ሣራ አብርሃምን ከቤታቸው ሠራተኛ አጋር ጋር እንዲተኛ እና ልጅ እንዲያፈራ ስለ ቀሰቀሰችው ሚስኪኑ አብርሃም የእ/ር ቃልን በመጠራጠር እና ቸል በማለት ከሠራተኛቸው አጋር ጋር ወሲብ በማድረግ እስማኤል እንዲወለድ በር ከፈተች:: ይህ ደግሞ እ/ር ለአብርሃም ከገባለት ቃል ውጪ ስለነበር ሣራ በአብርሃም ላይ ትልቅ ችግር ይዛ መጣች"

"እንዴ አንቴ እኛ አገር ሠርግ ላይ የአብርሃምና የሣራ ሠርጋችሁ ይሁን የሚባለው እስከ አርጅናችሁ ድረስ ልጅ አትውለዱ አልያም ልጅ ካጣችሁ ከሠራተኛችሁ ጋር ዝሙት ፈፅሙ ማለት ነው?"

አንቴ ሣቀ:: አንቴ ብዙ ጊዜ ስለማይስቅ ሣቁ ይማርካል:: ያልተለመደ ደስ የሚል ሣቅ አለው::

"የእኔ ልጅ ምንም አሳማኝ ባይሆንም ለማለት የተፈለገው ትዳራችሁ ይመር፣ ዘራችሁ ይብዛ፣ ፍቅራችሁ ረጅም ይሁን፣ ትዳራችሁ ችግር እና ፈተና ቢኖረው እንኳ ፈጣሪ ይመልከተው ለማለት ፈልገው ነው:: ለእኔ ግን ሠርጋችሁ የአብርሃምና የሣራ ይሁን ሲባል ከምርቃት ይልቅ መርገም በትዳራቸው ውስጥ እንዲዘልቅ የሚጠሩ ይመስለኛል"

"እሺ ያቋረጥከውን ቀጥል አንቴ"

"እህ... ሚስኪኑ ሎጥ በሚስቱ ቆስቋሽነት ወደ ተረገመችው የዝሙት ባንዲራ ከሚውለበለብባት የሰዶም ከተማ ከአብርሃም ተለይቶ እንዲያመራ አደረገችው"

"የዝሙት ባንዲራ ማለት አንቴ?"

"የእኔ ልጅ ዝሙት ማለት ከጋብቻ ውጪ ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ መፈፀም ብቻ ማለት አይደለም:: ፈጣሪን መርሳትም ዝሙት ነው:: ፈጣሪ የለም ማለት ራሱ ዝሙት ነው:: ሴይጣንን ማምለክ ዝሙት ነው:: ባጣኦት ማምለክ ዝሙት ነው:: በገንዘብ፣ በዝና፣ በስልጣን መመካት እና መታበይ ዝሙት ነው:: አዕምሮን በታላቅ ፈንጠዚያ ውስጥ መዝፈቅ ዝሙት ነው:: በዘር እና በዘረኝነት አጥር መታጠር ዝሙት ነው:: በዚህ መሠረት አሁን ወደ ሙት ባህር የተለወጠችው የበፊቷ የሰዶም ከተማ ዝሙተኛ ነበረች:: ነዋሪዎቿ ፈጣሪን ረስተው ነበር:: ነዋሪዎቿ ወንድ ከወንድ ወሲብ ያደርጉ ነበር:: ሴት ለሴት ፍቅር ይሠሩ ነበር:: 24 ሰዓታት ይጠጡ፣ ይዘፍኑ፣ ዳንኪራ ይመቱ! ብቻ ፈጣሪን ረስተው የዝሙት ባንዲራ ያውለበልቡ ነበር:: ወደዚች በዝሙት የጨሰች ከተማ ነው የሎጥ ሚስት ባሏን የወሰደችም፤ ታዲያ የሰዶም ህዝብ ሀጢያቱ ሲበዛ፣ የዝሙት ባንዲራቸው እጅግ በጣም ሲውለበለብ ፈጣሪ ሰይፍ አነሳባቸው! በከተማዋ ውስጥ አስር የሚደርሱ ፃዲቅ ሰዎች እንኳ በመጥፋታቸው ፈጣሪ አጠፋቸው! ከተማዋን ዶግ አመድ አደረጋት"

"ታዲያ በዚያን ሰዓት ወንድ ለወንድ እና ሴት ለሴት ወሲብ የሚያደርጉ በፈጣሪ ቁጣ ከምድር ላይ ጠፍተው ከነበረ አሁን በድጋሚ ከየት መጡ?"

"እንደኛ የሰው ልጅ ከታሪክ ሳይማር ሲቀር ታሪክ ራሱን ይደግማል:: ሁለተኛ መንፈስ ነው:: እየሽ የእኔ ልጅ በእርግጥ በዚያን ዘመን ሰዎቿ ጠፍተው ከተማዋ አሁን ሙት ባህር እየተባለ የሚጠራውን ሆናለች፤ ግን መንፈሱ አልጠፋም! ይህ እኮ የሴይጣን ስራ ነው:: ሴይጣን እኮ ያለም ፍጻሜ መጥቶ በአርማጌዲዮን ጦርነት ምድር ዶግ አመድ ስትሆን ወይም በመጨረሻው ሰዓት ሙሉ ለሙሉ የሽንፈት ፅዋን ቢከናነብም ለራሱ የተዘጋጀለት ስፍራ ውስጥ በእሳት እየተቃጠለ ይኖራል እንጂ እስከ መጨረሻው እኮ አይጠፋም፤ ስለዚህ የሰው ልጆችን በድጋሚ የአርማጌዲዮን ጦርነት እስከሚደርስ የዝሙት ባንዲራ እንዲያውለበልቡ እያስደረገ ምድር እንድትጠፋ በትጋት እየሠራ ይገኛል:: መሸነፉ ባይቀርም ከመሸነፉ በፊት ግን የሰው ልጆችን ከእ/ር መንግስት ማራቅ አላማው ነው! ሰዎች የነፍስ እርካታ ሳያገኙ እንዲኳትኑ ማድረግ ተልዕኮው ነው"

"ገባኝ ! ሌላውን ቀጥልልኝ አንቴ"

"የሰው ዘር መነሻ አዳም በሚስቱ ሄዋን ቆስቋሽነት የተከለከለችውን ፍሬ በላና ሞት እንዲመጣብን አስደረገችው:: ምስኪኑ ኢዮብን ሚስቱ ታላቁን ፈጣሪ እንዲሰድብ ቆሰቆሰችው:: ስለታላቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰብክ የነበረውን መጥምቁ ዮሐንስን ሄሮድያዳ የተባለችው ሴት በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበረውን ንጉሱን ቆስቁሳው አንገቱ በዘግናኝ ሁኔታ እንዲቆረጥ ምክንያት ሆነች ... ደሊላ የተባለችው ሴት 'እኛ ለድካምሽ ገንዘብ እንሰጥሻለን አንቺ የጠላታችንን ሳምሶምን ሀይል ያለበትን ንገሪን" ሲሏት ደሊላ የፍቅረኛዋን ሳምሶምን ሚስጥር ጀንጅናው አወቀችና የሳምሶን ሀይል ያለበት ጸጉሩን ላጨችውና የሳምሶም ሀይል ተነጠቀበት... የኦርቶዶክሶቹ ጸበል ቦታዎችም ሆነ የፕሮቴስታንቶቹም ፀሎት ላይ ሴይጣን እና ኢጋንንት ከውስጣችን ወጣልን ከሚሉት አንድ ሺ ሰዎች 997ቱ ሴቶች ናቸው:: ቅዱሳንን ሰዎች በዝሙት እያረከሱ ከመስመር የሚያስወጡዋቸው ሴቶች ናቸው:: ሴይጣን በዋነኝነት በተላላኪነት የሚጠቀምባቸው አያሌዎች ሴቶች ናቸው:: ሴቶች የማሰብ ችሎታቸው ጠባብና ልክስክስ፣ በስሜት የሚነዱ ገልቱ ፍጡሮች በመሆናቸው ሴይጣን በቀላሉ እንዳሻው የሚያሾራቸው እና የሚጠቀምባቸው መገልገያ ዕቃዎቹ ናቸው... ወዘተ እያለ ሴቶችን ተጠያቂ ለማድረግ ይጥራል:: በእርግጥ ጸሐፊው የሴቶች ጥላቻ ይኖርበት ይሆናል እንጂ ለምሳሌ ያህል የሳምሶም ታሪክ እኮ የሚደንቅ ነው:: ሳምሶን መጀመሪያ ጸጉሩን ሳይላጭ እና ሀይሉ ሳይነጠቅ በአህያ ውርንጭላ ጭንቅላት በአንድ ጊዜ ብቻ አንድ ሺ ሰው ፈጀ:: በነገራችን ላይ አንድ

የጎንደር የኢንፍራንዝ ወጣት አስገራሚውን የሳምሶምን አንበሳ በእጁ መግደል እና በአህያ ውርንጭላ ጭንቅላት ብቻውን በመሆን አንድ ሺ ሰው መፍጀት ታሪክ ያነበበ ወጣት በታሪኩ ተወስውሶ እና ተነሽጦ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ሰዓት በታላቅ ጀግንነት ተሞልቶ `እንኳን ለእናት አገር እንኳን ለእናት ምድር ሰው ይሞት የለም ወይ በአልባሌ ነገር` በማለት የነበረችውን ውርንጭላ አህያ ገድሎ ጭንቅላቷን በመያዝ አዲስ አበባ በማምራት የጠላታችንን ወራሪዎች ጣሊያኖችን ጭንቅላት በሚገርም ብቃት እንደንብ ዘሎ እየተከመረባቸው 22 ጣሊያኖችን ከገደለ በኋላ መስዋዕት ሆኗል! የዚህ የጎንደር ወጣት አርበኛ ገድል እና ታሪክ ግን አልተፃፈም:: ለህዝቡ ሳይነገር ተዳፍኖ ቀረ፡፡ ወደ ሳምሶን ስንመለስ ፍልስጥኤማዊያን ሳምሶምን ያዙት፡፡ ጸጉሩን ይበልጥ መላጣ አድርገው ላጩት፡፡ ይህም አልበቃ ብሎዋቸው እንዳያይ ሁለቱን ዓይኖቹን ወግተው አፈሰሱት፡፡ የጨለማ እስር ቤት ውስጥ ጣሉት፤ ግን አንድ ቀን ፍልስጥኤማዊያን ዳጎን በተባለው የጣኦታቸው ቤተመቅደስ ውስጥ ትልቅ በዓል ለማከበር ሶስትሺ እንግዶች በግዙፉ ቤተመቅደስ ውስጥ ተገኙ፤ ታዲያ በሳምሶም ላይ ለማፌዝ ወደ ግዙፉ ቤተመንግስት አስገቡት፡፡ ማየት በማይችለው ሳምሶም ተሣለቁበት `እውን አንተ የምትሰው ፈጣሪ ካለ እስቲ ሳምሶን የአንተ ፈጣሪ ይምጣ! እስቲ ሀይል በፀጉርህ ላይ የሰጠህ ፈጣሪ እውን ካለ ይምጣና አሁን ያድንህ!" እያሉ አፌዙበት! አስካኩበት! አሽሟጠጡበት! ተሣለቁበት! ምራቃቸውን ተፉበት! በዚህን ሰዓት ሶምሶን በልቡ ለታላቁ ፈጣሪ ፀሎት አደረገ `አምላኬ ሆይ ህይወቴ ከፍልስጥኤማዊያን ጋር ትጥፋ!' በማለት ፀለየ፡፡ ከዚያ ሲያንገላቱት የነበሩትን ሰዎች `እባካችሁ የህንፃው ምሰሶ ጋር አስጠጉኝ` አላቸው፡፡ ያሰበውን አላወቁምና አስጠጉት፡፡ ሳምሶም ሀይሉን በመጠቀም ሁለቱን የግዙፉን ቤተመቅደስ ምሰሶዎች ሳያስቡት ናዳቸው፡፡ ታላቁ ግዙፍ ቤተመቅደስ ፈረሰ፡፡ ሰው በሰው ላይ ተደራረበ፡፡ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተደራረበ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተጠሩት እና ውስጡ የነበሩት 3000ሺ ሰዎች በአንድ ጊዜ ሞቱ፡፡ እየሽ ሁሉ ነገር ለበጎ ባይሆንም ለምክንያት ነውና እነዚያ በአምላክ የማያምኑ ጣኦት አምላኪ ጨካኝ ፍልስጥኤማዊያን 3000 ሺ ጠላቶች ይሞቱ ዘንድ ደሊላ ሳምሶምን ማታለል ነበረባት፡፡ የሳምሶም ዓይኖች መፍሰስ ነበረባቸው... በዚያ ላይ ፀሐፊው ያልገባው አንድ ግዙፍ እውነት ታላቁ ፈጣሪያችን ዓለምን ያዳናት በሴት የመጣውን ሀጢያት በሴት አማካኝነት ነው፡፡ ሄዋን ያመጣችው የሀጢያት ጣጣ ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ በተወለደው ኢየሱስ አማካኝነት ለማዳን ችሏል፡፡ ይህን እውነታ ሳይገነዘብ ፀሐፊው ዙሪያ

ጥምጥም እየሄደ ሴቶችን ቀንደኛ እና ብቸኛ የሴይጣን ተላላኪ ናቸው ለማለት እየዳዳው ነው፤ ለማንኛውም የእኔ ልጅ በዚህ ጉዳይ ሌላ ጊዜ በስፋት እናወራለን፤ አሁን ነገ ተማሪ ስለሆንሽ ሽንት ቤትሽ ግቢና ተመልሰሽ ተኚ"

"እሺ!" አልኩት አጎቴን:: ከዚያ ሽንቴ ባይመጣም ሽንት ቤት ለወጉ ያህል በማምራት እና ትንሽ ቆይቼ በመመለስ አጎቴን ተሰናብቼው ወደ መኝታ ቤቴ ገባሁኝ:: እንቅልፍ የለም:: ያን አስቀያሚ ትዕይንት እያስታወስኩ ነበር:: በመጨረሻ ቢያንስ አዕምሮዬን ዘና ለማድረግ ሙዚቃ ለማዳመጥ ፈለኩና ጆሮዬ ላይ ማዳመጫ ሰካሁ:: ምናልባት ይህ ሀሳቤን ይበትንልኝ ይሆናል... ሙዚቃውን ከፈትኩት:: የመጀመሪያው ሙዚቃ በጣም የምወዳት የበዓሉ ግርማ ፍቅረኛ የነበረችው የብዙነሽ በቀለ ነበር:: በዚያ በሚያምረው ተስረቅራቂ ድምፅ እያዜመች ነበር

.... አዲስ ፍቅር እኔን ይዞኛል

የማደርገው ሁሉ ጠፍቶኛል

ጨነቀኝ ጠበበኝ እኔን

ማሰብ አቃተኝ ሰሞኑን...

በእርግጥ ስለሴትና ወንድ ፍቅር አላውቅም ፤ ወደ ፊት እድሜዬ እና አጋጣሚ ቁርኝት ፈጥረው ለዘመነ ማፍቀር እና መፈቀር ስደርስ ማወቄ አይቀርም:: ለሁሉም ጊዜ አለው ይባል የለም? ስለ ፍቅር ሆነ እሮጌ ፍቅር አልያም አዲስ ፍቅር አሁን የማውቀው ነባራዊ እና ተጨባጭ ግንዛቤ ባይኖረኝም የብዙነሽ በቀለ መረዋ ድምፅ ዘና አደረገኝ:: አዕምሮዬን ወደ አንዳች የማላውቀው ዓለም ወስዶ መለሰኝ... የብዙነሽ እንዳለቀ ቀጥሎ የመጣው የሙዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሰሰ ዘመን የማይሽረው ሙዚቃ ነበር

ቃላቶች ያጥሩኛል ምን ብዬ ላድንቅሽ

እንዲያው በደፈናው ሞናሊዛዬ ነሽ!...

ጠቢባን ሊያደንቁሽ ቢፈልጉ ቃላት

ፍጹም አቃታቸው አልቻሉም ለማግኘት...

እንዳንቺ ውብ የለም በምድሪቱ ላይ

ብዬ ባደንቅሽ ይበቃሻል ወይ...?

የሚገርም እኮ ነው!? አሁን እንደዚህ የሚባልላት ድንቅ ሴት? እንከን አልባ ሴት? አመለሿ

ሴት! በውበት የተንቆጠቆጠች ሴት? በመልካም ሥነምግባር የተንቆጠቆጠች ሴት? በቀናነት ውስጧ የሸበረቀ ሴት? ታላቁን እ/ርን የምትሰማ ሴት? ከአሮጊት ተረት ራሷን የጠበቀች ሴት? ባልተኛ ፣ ፈዘኛ፣ ልግመኛ እና የወሬ ሱሰኛ ያልሆነች ሴት? ህልሚ እንደ ሸንቷ አጭር ያልሆነች ሴት? እውነት በምድር ላይ ትኖራለች? ወይስ የሆነች ምናባዊት ሴት ናት? እንደዚች አይነት ንጽህት ሴት ምድር ላይ ትኖር ይሆን? እንደዚች ዓይነት ዕንቁ የሆነች ሴት እውነት ትኖር ይሆን? እኔንጃ! ብቻ ሙዚቃው እንድፈላሰፍ፣ እንድመራመር፣ ሀሳቤን ብትን እንዳደርግ ረዳኝ፡፡ ከዚው ከጥላሁን ሞናሊዛዬ ሙዚቃ ካዳመጥኩ ከዘመናት በኋላ በወጣትነት ዘመኔ በሰማሁት በአብዱኪያር የኔማር ሙዚቃ ስለዚያች በምሽት አለች ወይ ብዬ ያሰብኳት እና ከራሴ ጋር አሰጥ አገባ ውስጥ እንድዘፈቅ ያደረገችኝ ምናባዊት ሴት በድጋሚ ለማሰብ ተገድጄ ነበር

... ውበት ቁንጅናሽን በቃል ለማስረዳት

የቋንቋ እውቀት ያለው ያስፈልጋል ረዳት...

ቃላት ላይ ፊደል ላይ ስልጣን የሌለው ሰው

አይችልም! አይችልም! ውበትሽን ሊገልጸው...

ጉድ እኮ ነው! ጋሽ ጥላሁን ገሰሰ ጠቢባን ሊያደንቁሽ ፈልገው ቃላት አጡ ከቶ አልቻሉም እያለ ነው፡፡ በሌላ በኩል አብዱኪያር ደግሞ በሌላ እይታ የቋንቋ እውቀት ያለው ባለሙያ ካለ አንቺን መግለፅ አያቅተውም ይላል... ብቻ በዚያች ምሽት ሙዚቃ ማዳመጤ ያን አስቀያሚ የመደፈር ትዕይንትን እንድዘነጋው ረድቶኝ ነበር፡፡ ዛሬም ድንገት ያ አስቀያሚ ትዕይንት ትዝ ካለኝ ትርኪምርኪ የሆኑ ሙዚቃዎችን ሳይሆን አሪፍ የሚባሉትን እየመረጥኩ አዳምጣለሁ፡፡ ይህ ለእኔ መረጋጋት ይሰጠኛል፡፡ ሀሳቤን ብትን ያደርግልኛል፡፡ ሙዚቃውን እያዳመጥኩ አብሬው መዝፈን ሳይሆን ሀሳቡን ማጣጣል እና መሰነጣጠቅ ሀሳቤን ይበትንልኛል፡፡ ምንም እንኳ የደረሰብኝ ጠባሳ ለዘለዓለም ከአዕምሮዬ ውስጥ ጨርሶ የማይበተን ቢሆንም... ለጊዜው ግን ያስረሳኛል፡፡

ያ አስቀያሚ ትዕይንት ከሆነ 24 ቀናት በኋላ ቅሌት እና ጅራት ከወደኋላ ነው

የሚባለው አባባል ሀቅ ነውና በቤተሰቦቼ ቅሌት እገረም እና እሸማቀቅ ጀመርኩ:: ከምን ዓይነት የተረገመ ቤተሰብ እንደ ተወለድኩ ራሴን በግርምት ጠየኩት? ከምን ዓይነት ድብቅ ቤተሰቦች ነው የተወለድኩት? ምን ዓይነት ጥልቅ ድብቅ ቤተሰቦች ነበሩኝ? እናም የቤተሰቦቼ ጣጣ እና ገመና ተጀመረ:: በእርግጥ አስቀድሞ አንቴ በጣም እንዳልገረም እና ግር እንዳይለኝ ነግሮኝ ነበር

"የእኔ ልጅ ስለውርስ መቼም ታውቂያለሽ?"

"ትምህርት ቤት ተምረናል"

"አየሽ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የውርስ ስርዓቶች ሁለት ናቸው:: በኑዛዜ እና ያለ ኑዛዛ የሚከናወኑ ሲሆኑ በኑዛዜ ማለት በግልፅ ቀበሌ ወይም ፍርድ ቤት በውልና ማስረጃ በሚደረግ ማረጋገጫ፣ በጽሁፍ በሚደረግ ማረጋገጫ፣ አልያም በሽማግሌዎች እና ምስክሮች ፊት በሚደረግ ማረጋገጫ፣ አልያም በሽማግሌዎች እና ምስክሮች ፊት በሚደረግ የቃል ንግግር ሊሆን ይችላል:: የአንቺ ቤተሰቦች አንዳችም በኑዛዜ ያስቀመጡት ነገር ስለሌላ ውርስ የሚከናወነው ያለ ኑዛዜ ነው፤ በዚህ መሠረት ህግ በተቀመጠው ስርዓት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል ማለት ነው፤ ስለዚህ ህግ ማን ወራሽ እንደሆነ ያጣራል:: ህግ የውርሱ ተቀባይ ማን እንደሆነ ይለያል ፣ ያለውን የሀብት መጠን ይለያል፣ የጥሬ ገንዘብ ብዛት ፣ የንብረት ብዛት ይለያል:: ከዚው ጋር እናትሽ እና አባትሽ የሚከፍሉት እዳ እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው በጥንቃቄ ያጣራል፣ የመንግስት ዕዳ እንዳለባቸው ፣ ብድር እንዳለባቸው፣ የኢንሹራንስ እዳ እንዳለባቸው፣ መዘጋት ያለባቸው እዳዎች እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው ወዘተ ያጣራል፤ በተለይ እናትሽ እና አባትሽ ያስቀመጡትን ሀብት በቀጥታ ወራሽ አንቺ ብቻ ነሽ? አልያስ ሌላም ወራሽ እንዳላቸው እና እንደሌላቸው ያጣራል:: የተደበቀም ጉድካለ በቅርቡ የእናትሽንና አባትሽን የሞት ዜናቸውን ስለሚሰሙ ከያሉበት እየተከለፈለፉ ይመጣሉ"

"የተደበቀ ጉድ ማለት አንቴ?"

"ዲቃላዎች ካሉ በኢትዮጵያ ህግ ልጆችም ሆኑ ዲቃላዎችም ሀብትን እኩል ይካፈላሉ፤ በተጨማሪ የጉዲፈቻ ልጅም በአዲሱ የቤተሰብ ህግ ህጋዊ ወራሽ ይሆናል፤ በእርግጥ እኔ እስከማውቀው ድረስ እናንተ ቤተሰብ ውስጥ የጉዲፈቻ ልጅ የለም"

"እንዴ አንቴ?"

"አቤት"

"ዲቃላ እኮ ማለት በዝሙት የተወለደ ማለት ነው"

"ልክ ነሽ!"

"ታዲያ የኢትዮጵያ ህግ ለዲቃላ ውርስ እኩል መስጠት አለበት ሲል ዝሙትን ማስፋፋት አይሆንም? ዝሙት ሀጢያት ነው ከተባለ ለምሳሌ ሚስት ሳታውቅ ባል ዝሙት ሲፈፅም በወለደው ልጅ ሚስት ለምን የባሏን ንብረት ትጠየቃለች? ከህጋዊ ሚስት ልጆች እኩል ዲቃላዎች እንዴት ይወርሳሉ? ህጋችን እንዴት ለዝሙት እውቅና ይሠጣል? ይህ ከሆነ እኮ አንዲት ብልጥ ሴት ገንዘብ የምትፈልግ ከሆነ ካንድ ሀብታም ሆን ብላ ጠጋ ብላ ብትወልድ ገንዘብ ታገኛለች ማለት ነው? ህጉ ለዝሙት መስፋፋት ህጋዊ እውቅና በመስጠት ዝሙትን ይበልጥ አያንረውም?"

"እየሽ ትልቅ ሆነሽ ዩኒቨርሲቲ ገብተሽ ይህን መሰል ጥልፍልፍ የሆኑ ህጎች መቅረት አለባቸው እያልሽ በመከራከር፣ ሀሳብ በመስጠት ወይም ማሻሻያ እንዲደረግባቸው መቆስቆስ ትችያለሽ ማለት ነው የእኔ ልጅ"

"ግን አጎቴ አባቴ ዲቃላ ይኖረዋል?"

"እውነቱን ለመናገር ሰሞኑን ይህን ጉዳይ ለማጣራት ላይታች ስል እኔ ራሴ ከው ብያለሁ! አባትሽም ዲቃላዎች አሉት:: አውቃታለሁ ከእኔ የተደበቀ ሚስጢር ሊኖራት አይችልም የምላት እህቴ ራሱ ጉድ አላት"

"የምርህን ነው አጎቴ?"

"የምሬን ነው"

"ምን?"

"ከመጀመሪያዋ ደህ ፍቅረኛዋ የወለደችው ልጅ አላት:: ያን ልጇን ፍቅረኛዋ ላይ ጥላው እንደመጣች፣ ህጋዊ የጋብቻ ወረቀት እና የእሷ ልጅ እንደሆነ ማስረጃ እንዳለው የቀድሞ ፍቅረኛዋ ይዞ መጥቷል:: በዚህ በጣም ተገርሜያለሁ፤ ስለዚህ ነገር በጭራሽ አውርታኝ አታውቅም ነበር:: ይህ የሆነው እናትሽ ማንኩሳ እያለች ነበር፤ ስለዚህ ይህ ልጅ ከእናትሽ ሀብት ወራሽ የመሆን ህጋዊ መብት አለው ፤ እንዲሁ እስካሁን ባለኝ እና በደረሰኝ መረጃ አባትሽ ቡሬ፣ ፍኖተሠላም፣ ኮሶበር እና አርሲ ነገሌ አራት ዲቃላዎች እንዳሉት ሠምቻለሁ:: ሰሞኑን ሁሉም ይመጡ ይሆናል፤ በዚህ ምንም ሀዘን እንዳይሰማሽ የእኔ ልጅ" በማለት ነበር አጎቴ የነገረኝ:: በዚው የውርስ ጣጣ አጎቴ የእኔ ህጋዊ ወኪል መሆኑን እና ለእኔ

መብት እንደሚከራከር ለማሳወቅ ስራውን በመተው ቀበሌ እና ፍርድ ቤት ሁለት ቀናትን ት/ ቤት ቀርቼ ስንከራተት ነበር። አጎቴ እንዳለው የእናቴ ዲቃላ ልጅ አባት እንዲሁም የአባቴ አራት ዲቃላ ልጆች እናቶች የውርስ መብት ተካፋይ መሆናቸውን ለእኔና አጎቴ በአካል በመምጣት አስረግጠው አሳወቁን። በሚቀጥለው ቀንም አጎቴ ቤት ተቀምጠን እኔ የቤት ስራዬን እየሰራሁ አንዲት የምታምር በተለይ የሚያምር ዓይን እና አርቴፊሻል ሳይሆን እውነተኛ ጥቁር ረጅም ጸጉር ያላት ሴት ከአንድ ትልቅ ሴትዮ ጋር መጡ። በተፈጠረው ነገር ማዘናቸውን ገለፁ። እስከዛሬም ያልመጡት ለቅሶ ባለመቀመጣችን እንደሆነ ገለፁ። እርግጥ አጎቴ ምንም እንኳ አንዲ ሟች የገዛ እህቱ ብትሆንም ለእድር ማንም ለለቅሶ እና ለማስተዛዘን ቤት እንዳይመጣ ብሎ በመናገሩ ማንም አልመጣም ነበር። ከዚያ ወደመጡበት ጉዳይ ዘው ብለው ገቡ።

"አርሴማ መኮንን እባላለሁ። ባህር ዳር ቀበሌ ስምንት ነዋሪ ነኝ። የአምስት ዓመት ልጅ አለኝ። አሁን እንደምታዩኝ የስምንት ወር እርጉዝ ነኝ። የህግ አዋቂዎች ጋር በመሄድ እንዳጣራሁት በእናቱ ማህጸን ያለ ልጅም የመውረስ መብት አለው፤ እንዳሉኝ ከሆነ በማህጸን ያለ ልጅ የሚወርሰው ተወልዶ አርባ ስምንት ሰዓት ሲሞላው ነው፤ ምናልባት ግን ሲወለድ ከሞተ አይወርስም ብለውኛል! እኔ በእመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም እምነት ስላለኝ እና ልጄም እንዳጣራሁት ሙሉ ጤነኛ ስለሆነ ከወር በኋላ እገላገለዋለሁ፤ ስለዚህ ህጋዊ የጋብቻ ወረቀትም ሆነ ምስክሮችም አሉኝ በመሆኑም እነዚህ ሁለቱም የፍቅር አብርሃም ልጆች ናቸው፤ ስለዚህ የውርስ መብት እንዳለኝ እንድታውቁልኝ ልነግራችሁ ነው" በማለት ኮስተር ባለንግግር ተናገረች። ምላሰኛ ሴት እንደሆነች ያሳብቅባታል።

"የእኔ እህት ስለ ገንዘብ ወይም ውርሱ አትጨነቂ! እውነተኛ መረጃ ከሆነ በህጉ መሠረት ተገቢውን ሁሉ በእርግጠኝነት ትወስጂያለሽ! በዚህ እርግጠኛ መሆን ትችያለሽ! ልጅሽን በሰላም እንድትገላገይ ፈጣሪ ይርዳሽ" በማለት ጀምሮ መወያየት ያለባቸውን ተወያይተው በሰላም ልጅቷ እና ሴትዬዋ ከቤታችን ወጡ። በጣም የሚገርመው የተማከሩ ይመስል ይህ ከሆነ አንድ ሰዓት በኋላ አንዲት ጉሬዛ የመሰለች የማታምር ግን የሚያምር ግዙፍ ዳሌ እና ቀጭን ወገብ ያላት ጥቁር ሴት አንዲት ሴት ይዛ ገባች። በእርግጥ ይቺ ሴት ሳትናገርም 100% በትንሿ ልጅ መልከ ብቻ አይቶ መመስከር ይቻላል! ቁርጥ አባቴን የመሰለች ናት!!

"ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም" አለች፡፡ ወዲያው አትቴ በፍጥነት ምንም ሳታወራ በመቅደም "አትቸገሪ..." በማለት መንገር ያለበትን ጉዳይ ነገራት፡፡ ሁሉ ነገር በህግ መሠረት እንደሚያልቅ እና ፍርድ ቤት ማድረግ ስላለባት ጉዳይ አወሩ፡፡ እሷም በሰላም ወጣች፡፡

በነጋታው የ22 ዓመት ወጣት መጣ፡፡ ይህም ወጣት ደግሞ 1000% ፐርሰንት አባቴን ቁርጥ የመሰለ ነው፡፡ ገና ቤት ውስጥ ሲገባ በጣም ነበር ክው ያልኩት፡፡ ወዲያው ነበር ያን አስቀያሚ ትዕይንት ለሴኮንዶች እንዳስታውስ ያደረገኝ ፤ እናም ይህን ቁርጥ አባቴን የመሰለ ወጣት ምንም ይፈጠር ምንም በድጋሚ ላለማየት ወዲያው ወሰንኩ፡፡ ከዚህ ቁርጥ አባቴን ከሚመስለው ዲቃላው ወንድሜ ለመራቅ በድጋሚ ከራሴ ጋር ተወያይቼ ወሰንኩ፡፡ እሱን ባየሁ ቁጥር ያን አስቀያሚ ትዕይንት ማን እያስታወሰ ይሰቃያል?

"ሻሸመኔ ነዋሪ ነኝ፡፡ ይስሀቅ ፍቅር እባላለሁ፡፡ ብዙ ማውራት አልፈልግም፡፡ የአቶ ፍቅር የመጀመሪያ ልጅ እንደሆንኩ እገምታለሁ፤ ይህን እናቴ ነግራኛለች፡፡ ዛሬ ከሻሸመኔ እዚህ ድረስ የመጣሁት ከውርስ ጋር በተያያዘ ሀብት ለመካፈል አይደለም፡፡ እኔ በጭራሽ የካደኝን አባቴን ገንዘብ አልፈልግም፤ በዚያ ላይ ገንዘቡ በቀና መንገድ እንዳልመጣ አውቃለሁ፡፡ ዛሬ እዚህ የመጣሁት ለሁለት ነገር ነው፡፡ አንደኛ የውርስ ህግን ለማጣራት እንደሞከርኩት አንድ ሰው የውርስ መብት ኖሮት አልፈልግም ካለ የሚያስገድደው ሁኔታ የለም፤ እንዲሁ ወራሽ ሆኖ ወራሽነትን አልፈልግም ባለሰው በምትኩ ሌላ ተተኪ ገብቶ መውረስ እንደማይችልም ለማወቅ ችያለሁ፤ በእርግጥ በህይወት ባይኖር ግን ሌላ ሰው ድርሻውን መውረስ እንደሚችል አውቄያለሁ፤ ያው አንድ ወራሽ ወርሱን አልቀበልም ማለት ቢችልም እና መብቱ የሚከበርለት ቢሆንም ውርሱን የማይቀበለው ወራሹ ላይ የገንዘብ ዕዳ ኖሮበት ብወርስም ያን ገንዘብ ሰዎች ይወስዱታል በሚል ሰበብ አለመሆኑን ማስረዳት እንዳለበት የህግ ሰዎች ነግረውኛል፤ ስለዚህ እኔ ምንም ዕዳ እንደሌለብኝ እና ውርሱን እንደማልፈልግ ለህግ አሳውቃለሁ፡፡ ቃሌንም ፍርድ ቤት እሰጣለሁ፤ ይህ አንደኛው ምክንያት ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የተፈጠረው አስቀያሚ ነገር እንዳለ ሆኖ እህቴ እሌኒ እኔን እንደ ወንድምሽ የምትፈልጊ ከሆነ አጠገብሽ መሆኔን ልነግርሽ ነው፡፡ በጣም ጥሩ ወንድምሽ እንደምሆን ተስፋ አለኝ" አለ፡፡ ከወጣቱ ጋር ማድረግ ስለሚገባቸው ጉዳይ ከአትቴ ጋር አወሩ፡፡ ልጁ ስልኩን እና አድራሻውን ለእኔም ሰጠኝ፡፡ እኔ ግን በጭራሽ በድጋሚ በህይወት አጋጣሚ ድንገት ካልሆነ በስተቀር ላለማየት ወስኛለሁ ... ባጠቃላይ እንግዲህ የአባቴ ዲቃላዎች ስምንት፣ የእናቴ ዲቃላ አንድ ፤ በአንድነት

ዘጠኝ ልጆች ሆኑ:: በሚቀጥሉት ቀናት ተጨማሪ ሰዎች ቢጠበቁም ዝር ያለ አልነበረም:: እኔም እኅቴም ተጨማሪ ዲቃላ ባለመምጣቱ ደስ ብሎን ነበር:: ብዙ ጉድም አስጠሊታ ነገር ነውና!!

ይህን ሁሉ ጉድ ለመርሳትም ሆነ ያን አስቀያሚም ትዕይንት ላለማስታወስም ሀሳቤን ፈተናው ላይ አደረኩ:: ሆን ብዬ ነገሮችን ለመርሳት ትኩረቴን ጥናት ላይ አደረኩ:: በጥናት ውስጥ ራሴን ደበኩት:: የዓመቱን የመጨረሻ ፈተና ተፈተንኩ:: ከቀናት በኋላ ውጤት ተቀበልኩ:: በራሴ ሀሴት አደረኩኝ:: በተለይ አኅቴ ደስ እንደሚለው ሳስብ ይበልጥ ደስ አለኝ:: እጅግ ምርጥ ውጤት ነበር ያመጣሁት፤ እናም እንደተለመደው በእርግጠኝነት የአንደኝነት ደረጃዬን እንደማስጠብቅ ወዲያው ነበር ሰባተኛው ስሜቴ ሹክ ያለኝ:: ያ አስቀያሚ ትዕይንት የት/ት ውጤቴን ባለማበላሸቱ ከልቤ ሀሴት አደረኩኝ:: አስቀያሚ አደጋዎች በህይወቴ ላይ ቢደርሱብኝም መቋቋም የምችል ጠንካራ ሴት መሆኔን ለመገንዘብ ችያለሁኝ:: ለዚህ ደግሞ ሆስፒታል የሥነ ልቦና ምክር የሰጡኝ ሁለት ሰዎች ሊመሰገኑ ይገባል:: በእርግጥ የዓለም ሁለተኛው ጥበብ ስለደረሰብን ችግር ማውጠንጠን ሳይሆን ያን ችግር እንዴት ማሸነፍ እንደምንችል ከራስ ጋር ውይይት ማከናወን ነው::

ቀናት ቀጠሉ:: እጅግ አሰልቺ የነበረው የውርስ ጣጣ በ84ተኛው ቀን ላይ በሠላም ተጠናቀቀ:: የእናቴ እና አባቴ የተለያዩ ባንኮች ውስጥ የተቀመጡ ገንዘቦች፣ በጥሬ የተገኘ ገንዘብ፣ ያላቸው በርካታ ንብረቶች ፣ ሆቴሎች፣ የንግድ ቤቶች ... ወዘተ ወደ ጥሬ ገንዘብ ተለወጡ:: ከአባቴ መሞት ጋር በተያያዘ አብረውን አክሲዮን የነበራቸው ወዲያው ዘዴ ፈጥረው ስሙን በማስወጣት የራሳቸው ንብረት አደረጉት... ይህ እንዳለ የተገኘው ሀብት ውርሱ ይደርሳቸዋል ብሎ ፍርድ ቤት እውቅና የሰጣቸው እኔን ጨምሮ ሁለት ሴቶችና ስምንት ወንዶች በአንድነት አስር ወራሾች ቢሆኑም አንደኛው ወጣት ማለትም የመጀመሪያ

ልጅ የሆነው የሻሽመኔው ይስሀቅ "ከከዳኝ አባቴ የሚደርሰኝ 100 ሚሊየን ብር እንኳ ቢሆን አምስት ሳንቲምም በጭራሽ አልፈልግም" በማለቱ ለተቀሩት እኔን ጨምሮ ተደምሮ፣ ተቀንሶ፣ እዳ ተሰልቶ ለእያንዳንዳችን በጥሬ ገንዘብ የምንቀበልበት የምስክር ወረቀት ከፍርድ ቤት ተሰጠን:: በዚህ መሠረት ለእኔ የተሰጠኝ 24,777,065 ብር ከ45 ሳንቲም ነበር:: የሀያ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ሺ ከስልሳ አምስት ብር ከዜሮ አርባአምስት ሳንቲሙ የምስክር ወረቀቱን የተቀበልን ጊዜ አጎቴ ፊት ላይ አንዳችም ደስታም ይሁን ሀዘንም አላነበብኩበትም ነበር:: ይልቅስ ማታ እራት በልተን ስንጨርስ

"የእኔ ልጅ ይህን ገንዘብ ስንቀበል በቀጥታ ባንክ ቤት በስምሽ እናስቀምጠዋለን:: አስራ ስምንት ዓመት ሲሞላሽ መጠቀም ትጀምሪያለሽ:: አየሽ በርከት ያለ ገንዘብ ስለሆነ ወደፊት በትምህርትሽ ጎበዝ በመሆን ይህን ብር በማባዛት የራስሽን ድርጅት በመክፈት ለሠራተኞች ደሞዝ በመክፈል ሰዎችን መጥቀም እና አገርሽንም መጥቀም ትችያለሽ፤ ስለዚህ አስራ ስምንት ዓመት እስከሚሞላሽ ለእያንዳንዱ ወጪሽ እኔ በቂ ገንዘብ ባንክ ውስጥ አለኝ:: ይህን ቤቱን በአሪፍ ብር የሚገዛም ሰው አግኝቼ ጣጣውን በቅርቡ እጨርሳለሁ:: በዚህ ገንዘብ እና ባንክ ቤት ካተራቀምኩት ገንዘብ በመጨመር አዲስ አበባ ቤት እንገዛበታለን፤ ምናልባት እኔን ለትንሽ ለትልቁ ነገር ገንዘብ መጠየቅ ከደበረሽ የተወሰነውን ገንዘብ በስምሽ በATM ማሽን እንድትጠቀሚ ለብቻው ይቀመጥልሻል፤ ይህ የተሻለው ሀሳብ ይመስለኛል፤ ባጭሩ ይህን ገንዘብ መጠቀም የምትጀምሪው ከአምስት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው"

"አጎቴ የተሻለውን አንተ ነው የምታውቀው እኔ አሁን ደስተኛ የሆንኩት በገንዘቡ ሳይሆን አንተ አጠገቤ ስላለህ ነው! አንተ ለእኔ በጣም መልካም ነህ! አጎቴ በአንተ እንድመካ አድርገህኛል! በጣም አመሠግናለሁ!" በማለት አጎቴን እቅፍ አደረኩት:: አጎቴ ግን ወዲያው መናገር ጀመረ::

"በጭራሽ! የእኔ ልጅ አንድ ነገር ላስጠንቅቅሽ ሁለተኛ በምንም ተዓምር ይህን መመካት የሚለውን ቃል ለሰው ልጅ እንዳትጠቀሚ! መመካት ያለብሽ በታላቁ ፈጣሪ ብቻ ነው! እውነተኛ ሰው መመካት ያለበት በእ/ር ብቻ ነው! ለዚያ ነው የሚመካስ በእ/ር ይመካ! የሚል ወርቅማ አባባል ያለው:: አየሽ በሰው ከተመካሽ የሰው ልቡ እስስት ነው:: አይጨበጥም:: ይወላውላል:: ይወሽከታል:: ጨለማ ውስጥ ጥሎሽ ይሄዳል:: ስለዚህ ምንጊዜም መመካት ካለብሽ ወይም መመኪያ የሚለውን ቃል መጠቀም ያለብሽ ለፈጣሪ ብቻ

መሆን ይኖርብሻል! ይህን መቼም እንዳትረሺ !!"

"እሺ አመሠግናለሁ አጎቴ!"

"የእኔ ልጅ ለአዲስ ህይወትሽ ተዘጋጂ! በቅርቡ ወደ አዲስ አበባ ጣጣችንን ጨርሰን እናመራለን! ሌላ አዲስ ህይወት እንጀምራለን! የእኔ ልጅ በህይወት ውስጥ ስለ ትልቁ እውነታ አወዛጋቢው ደራሲ በዓሉ ግርማ ምን እንዳለ ታውቂያለሽ?"

"ንገረኝ አጎቴ"

"በህይወት ውስጥ ትልቁ ቋሚ ነገር ለውጥ ብቻ ነው"

# 2

# አዲስ - አበባ

(ከ 2001 እስከ 2005 ዓ.ም)

በጣም የሚገርም እና ሊታመን የሚያስቸግር እኮ ነው፡፡ በእርግጥ እብድ ያለ ሀብት ካላቸው ቤተሰቦች የተለወድኩ የሀብታም ልጅ ነኝ፡፡ "ሰው ዓለሙን ሁሉ ወይም ገንዘብ፣ ክብር፣ ዝና እና ስልጣን ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" የሚለውን ወርቃማ የመጽሐፍ ቅዱስ ምክር፡፡ እጅግ ከረሱ ቤተሰቦች የተወለድኩ የቀጭን ጌታ ልጅ ነኝ፡፡ በእርግጥ ነኝ ከማለት ነበርኩ ማለቱ የተሻለ ነው፤ ታዲያ ምንም ከሀብታም ቤተሰቦች የተወለድኩ ቢሆንም እንደ ሀብታም ልጅ የተቀማጠልኩ ፣ እንደ ሀብታም ልጆች ሙልቅቅ ያልኩ... እንደ ሀብታም ልጆች ብዙ ቦታዎችን ያየሁ አይደለሁም፡፡ እናት እና አባቴ ከደብረማርቆስ ውጪ አንዳችም ቦታ አልወሰዱኝም፡፡ በልጅነቴ አሪፍ ትዝታ እንዲኖረኝ ታሪካዊ ቦታዎችን አላሳዩኝም ፣ ታሪካዊ ከተማዎችን አላሳዩኝም፡፡ ከእኔ ጋር ት/ቤት የሚማሩ ሌሎች የሀብታም ልጆች በታላቅ ኩራት ተሞልተው

"ክረምት ከአባቴ ጋር አሜሪካ ለቫኬሽን ሄደን ነበር፣ ክረምት ዱባይ ነበርኩ... ክረምት ሻንጋይ ነበርኩ... ክረምት ስቶኮልም ነበርኩ..." ወዘተ እያሉ ይቀደዱልኝ ነበር፡፡ እኔም መንፈሳዊ ቅናት ይወረኝ ነበር፡፡ ለማንኛውም ከትውልድ ከተማዬ ከደብረማርቆስ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ በዚህ ስሌት መሠረት አዲስ አበባ ለእኔ የመጀመሪያዋ ሌላ ከተማ ሆነችኝ፡፡

አዲስ አበባ ምትሃት የሆነች ከተማ! ዘወትር በግርግር ፣ በጫጫታ፣ በሁካታ፣ በራስ ወዳድነት፣ በግለኝነት፣ በወከባ፣ በእርካታ አልባነት የተሞላች ከተማ! አዲስ አበባ ሊደረስ የማይችልባቸው ጥቂት እብድ ያሉ ሀብታሞች መኖሪያ ከተማ! አዲስ አበባ የሚላስ የሚቀመስ ነገር ያጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምንዱባኖች መኖሪያ ከተማ! አዲስ አበባ የበርካታ ጉላንጆች፣ ፌጠኞች እና አፉኝቶች መኖሪያ ከተማ! አዲስ አበባ የእብብነት እና የበግነት ከተማ! አዲስ አበባ የህልም እና ህልም አልባነት ቅይጥ ግሪንቢጥ ከተማ! በእርግጥ አዲስ አበባ እና የተወለድኩባትን ትንሿን ደብረማርቆስን ማወዳደር ትልቅ ግፍ ይሆንብኛል፡፡ አዲስ አበባ ከተማ ሳትሆን አገር ናት፡፡ በጣም የተለጠጠች አስቀያሚ እና የምታምር ጉራማይሌ የሆነች ከተማ ናት፡፡ ማርቆስ ትንሽ እና ወጣገባናት፡፡ የደብረማርቆስ ድንጋይ ገር ነው፡፡ የአዲስ አበባ ድንጋይ ተንኮለኛ ነው፡፡ የደብረማርቆስ አየር ንፁህ ነው፡፡ የአዲስ አበባ አየር ይወብቃል፡፡ የደብረማርቆስ ህዝብ ፈርሐ እ/ር ያለው ነው፡፡ የአዲስ አበባ ህዝብ ፈርሐ ምንም ነው፡ የደብረማርቆስ ህዝብ በፈጣሪ ይመካል፡፡ የአዲስ አበባ ህዝብ በገንዘብ ይመካል፡፡ የደብረማርቆስ ህዝብ እምነት አለው፡፡ የአዲስ አበባ ህዝብ ፍልስፍና አለው፡፡ የደብረማርቆስ

ህዝብ ልብን ያያል፡፡ የአዲስ አበባ ህዝብ ኪስን ያያል... ብቻ ወደዚች ምትሀት የሆነችው የአዲስ አበባ ከተማ ገባሁ፡፡ እኔን ደግሞ የተቀበለችኝ ያጋጣሚ ሆኖ የሚሊኒየም በዓል እየተከበረ ስለ ነበር በደማቁ ሽርጉድ እያለች ነበር፡፡ ቄጤማ ጎዝጉዛ ነበር፡፡ ባንዲራ እያውለበለበች ነበር... የተቀበለችኝ፡፡

በጀግናው አትሌት አበበ ቢቂላ አዲስ አበባ ላይ ከተሰየመው አበበ ቢቂላ ስታዲየውም 50 ሜትር በስተቀኝ ርቀት ላይ የሚገኝ በጣም የሚያምር እና በተክሎች የተዋበ ግቢ ያለው ቤት ገዝተን ገባን፡፡ አ! የእውነት የቤቱም ሆነ የግቢውም ውበት በጣም የሚያምር ነው፡፡ በአንቴ ምርጫ በጣም ነበር የኮራሁበት፡፡ ይህን የመሰለ ታላቅ ሠላም የሰፈነበት ግቢ ሰዎቹ ራሱ ለምን እንደሸጡት አላውቅም፡፡ ይህ የሚያምረው ግቢ መንፈሴን እንደሚያድሰው ወዲያው ነበር ሰባተኛው ስሜቴ ያንሾካሾከልኝ፡፡ የሚያምረው ግቢ ውስጥ የእንጆሪ ተክል ፣ የኮምጣጤ ተክል እና የብርቱካን ተክል ስላለው ለግቢው የተለየ ደስ የሚል መዓዛ እንዲኖረው አድርገውታል፤ እናም በደስታ ተሞላሁ፡፡

አንቴ ይህን የመሰለ ቤት እንዲገዛ ጣጣውን የጨረሰለት ቅቤ በምላሱ የሚያቀልጠው የድሮ የት/ቤት ጓደኛው እና አሁን ከደብረማርቆስ ኑሮውን አዲስ አበባ ላይ ያደረገው እውቅ ደላላ አማካኝነት ሲሆን ቤቱን ከማጋዛት በተጨማሪ ችግር ድቁስ ያደረጋቸውን አንዲት እናት እና ልጃቸውን ጭምር ግቢው ባዶ እንዳይሆን በሰራተኝነት እንድንቀጥራቸው ስላመጣልን እኛም በሀሳቡ አመስግነን እና ተደስተን ቀጠርናቸው፡፡ ሁለቱም በአጋጣሚው በደስታ ተሞሉ፡፡ በመቀጠል ቀበሌ በማምራት መጨረስ ያለብንን የወረቀት ጣጣዎች በስንት ውጣ ውረድ ጨረስን፡፡ ቀልጣፋ የሚባለው አሠራር ውሸት መሆኑን ቀበሌ ባለው ዝርክርክ አሰራር ለመገንዘብ ቻልኩኝ፡፡ የሆነ ሆኖ ሁሉን ነገር ቀናቶችን ፈጅቶብንም ቢሆን በትዕግስት ጨርሰን አዲሱን የአዲስ አበባ ህይወትን ሀ ብለን ጀመርን፡፡

የት/ቤት ጉዳይ ብዙም አልተቸገርንም፡፡ ባለኝ ምርጥ ውጤት የትኛውም ትምህርት ቤት እጄን ስሞውኝ እንደሚቀበሉኝ እርግጠኛ ነበርኩ እናም “ሊ. ኢትዮጵያ ት/ቤት” ገባሁ፡፡

የአዲሱ የ2001 ዓ.ም ትምህርትን ጀመርኩ:: ስምንተኛ ክፍል... የፈጣሪ ያለህ! እንዴ የደብረማርቆስ ተማሪዎች ሺ እጅ ጨዋ ናቸው! ሥነ ምግባር አላቸው! አስተማሪዎችን ያከብራሉ! ይታዘዛሉ! ከልብ ያዳምጣሉ፣ ፈርሐ ፈጣሪ አላቸው! እነዚህ የአዲስ አበባ ልጆች አይን ያወጡ፣ ፈጣጣዎች ፣ ደፋሮች፣ የብልግና ቃላትን የሚያወሩ፣ አስተማሪዎችን የሚያንጓጥጡ፣ ለአስተማሪዎች አስቀያሚ ቅፅል ስሞችን የሚያወጡላቸው፣ አስተማሪዎችን በንቀት የሚመለከቱ ብቻ ብጥስጥስ የሚሉ በመሆናቸው ይህን የአዲስ አበባ ተማሪዎችን ባህሪ እስከምለምደው ከልቤ ደንግጫለሁ፤ በተለይ አንደኛው ፈጣጣ ተማሪ የዕረፍት ሰዓት የተቀመጥኩበት እንደ ፍሪኮቹ የራፐ ሙዚቀኞች አንገቱ ላይ ረጅም ሰንሰለት ያለው መስቀል እና ግድንግድ ቲምበርላንድ ጫማ አድርጎ እየተጀነነ እየተራመደ በመምጣት

"እንዳንቺ አይነት ቀሽት ጥቁር ሴት በህይወቴ አይቼ አላውቅም! ፍቅረኛ መሆን እንችላለን? ያየሁሽ ዕለት ነው ባንቺ ፍቅር የፈረጥኩት! ከእኔ ጋር ብትሆኚ በደስታ እንደማስከርሽ በእርግጠኝነት እነግርሻለሁ" አለኝ::

"ስንት ዓመትህ ነው እንዴ?" አልኩት:: ገርሞኝ::

"አስራ አምስት ዓመቴ ነው:: እድሜ እና ፍቅር ምን ያገናኘዋል? ፍቅር እኮ ስሜት ነው! ድንገት ነው የምታፈቅሪው፤ በዚያ ላይ ፍቅር እንደማር የሚጣፍጠው አሁን እኔና አንቺ በምንገኝበት ወቅት የሚጀመር ሲሆን ነው"

"ይሆናል፤ ግን ቅድሚያ ለሚገባው ቅድሚያ መስጠት የሚባል ነገር እኮ አለ፤ ስለዚህ ሙሉ ትኩረትህን ለት/ት መስጠት አይሻልህም? ለሁሉም ነገር እኮ ጊዜ አለው የሚለውን ወርቃማ ህግ አታውቀውም?"

"ኧረ ማካበድ! ማዘር ስለምከሮት እናመሰግናለን ፤ ግን በቀላሉ አንፋታም! እየመጣሁ እጀነጅንሻለሁ! በነገራችን ላይ ነገ መኖርሽንም ሆነ መሞትሽንም በማታውቂባት ዓለም ውስጥ እየኖርሽ ለሁሉም ጊዜ አለው በሚለው ህግ ማመን የለብሽም ራስታዎች ምን እንደሚሉ ታውቂያለሽ? ህይወት ዛሬ ነች፤ ስለዚህ በተሰጠሽ ዛሬ መደሰት አለብሽ! ለማንኛውም ማይክ በቀለ እባላለሁ" በማለት ሄደ::

ደብረማርቆስ እያለሁ አስተማሪዎች ክፍል ከመግባታቸው በፊት ለአክብሮት ከወንበራችን ተነስተን ቆመን እንጠብቃለን:: እዚህ አዲስ አበባ አስተማሪው ራሱ መጥቶ ተነሱ ካላለ መነሳት የለም:: ደብረማርቆስ ስለ አስተማሪዎች ጥሩ ይሁን መጥፎ ነገር

አይወራም:: እዚህ አስተማሪዎች ለጉድ ይታማሉ:: ይቦጨቃሉ:: ከፍዝቅ ይላሉ::

"አስተማሪ እከሌ የሴት ቂጥ ማየት ይወዳል... አስተማሪ እከሌ ሴቶችን ያወጣል... አስተማሪ እከሌ ጡት ማየት ይወዳል... አስተማሪ እከሌ ጫማው ይገማል... አስተማሪ እከሌ አፉ ይጠነባል... አስተማሪ እከሌ የኢህአዴግ ሰላይ ስለሆነ እንጂ እውቀት የሚባል ነገር ጨርሶ የለውም... አስተማሪ እከሌ ለቆንጆ ተማሪ ማርክ ያለ ምክንያት ይጨምራል ... አስተማሪ እከሌ ይህን ይወዳል... አስተማሪ እከሌ ይህን ይጠላል..." ኧረ የጉድ ያለህ!? የማይሉት ነገር የለም! ይህ ለእኔ አዲስ ነገር ነው:: በድጋሚ አሁንም እናገራለሁ የእውነት በሥነ ምግባርስ የአዲስ አበባ ተማሪን የደብረማርቆስ ተማሪ በስንት እጅ ያስከነዳል... በተለይ በጣም የደነቀኝ ደብረማርቆስ የባንዲራ ሰዓት ላይ ሬዲዮ ሳይከፈት ተማሪዎች በሀገር ፍቅር ተሞልቶው የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ እየሰቀሉ እጃቸውን ደረታቸው ላይ ለጥፈው በኢትዮጵያዊነት ወኔ ተሞልተው በአንድነት ይዘምራሉ:: እዚህ አዲስ አበባ የሚዘምር የለም:: ሬዲዮ ውስጥ የተከተተው ድምፅ ብቻውን ዘምሮ ይጨርሳል:: ተማሪዎች ለይስሙላ ይቆማሉ:: ይበልጥ በጣም የሚያሳዝነው ሬዲዮ ውስጥ ያለው ካሴት የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር እየዘመረ የሚያወሩ፣ የሚሳሳቁ፣ የሚጎነታተሉ፣ በጥቅሻ የሚጀናጀኑ በሽ ተማሪዎች አሉ... ከሁሉ ያስገረመኝ አጠገቤ የምትቀመጠው ፈገግታ የማይጠፋት ቤተል የተባለችው ተማሪ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር እኔ ከልቤ ስዘምር ስትከታተለኝ ቆየችና የዕረፍት ሠዓት ላይ በትኩረት እና በገረሜታ እያየችኝ

"በነገራችን ላይ ድምጽሽ ደስ ይላል፤ ወደፊት ዘማሪ ብትሆኚ ጥሩ ነው፤ እንደ ኦርቶዶክሷ ዘማሪ ዘርፌ ወይም እንደ ፕሮቴስታንቷ ዘማሪ ሊሊ ማለት ነው:: ዘፋኝነት እንኳ ሀጢያት ስለሆነ ይቅርብሽ!!"

"ዘፋኝነት ሀጢያት ነው?" አልኳት::

"መፅሐፍ ቅዱስ አንባቢዋ እናቴ ሙዚቃ መዳመጥም ሆነ መዝፈንም ሀጢያት ነው የሚል ተቀምጧል ብላኛለች"

"እንጂ አንቺ አላነበብሽም?"

"ማንበብም አልፈልግም:: እናቴ ይህን ትበለኝ እንጂ እኔ ሙዚቃ እወዳለሁ ፤ በተለይ ለስለስ ያሉ ሙዚቃዎችን መስማት ያረካኛል" አለች:: ስለሙዚቃ ከአንቴ ጋር ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ያወራነው:: አንቴን የጠየኩት ስለሙዚቃ ሀጢያት ነው? ሀጢያት አይደለም?

ሰዎች ሲያወሩ እና ሲከራከሩ ሰምቼ ነበር

"እትቴ"

"አቤት"

"ሙዚቃ መስማትም ሆነ መዝፈንም ሀጢያት ነው? ማይከል ጃክሰን ወይም ጥላሁን ገሰሰ በቀጥታ የሚገቡት ዘመናቸውን በሙሉ ሲዘፍኑ ስለነበር ሲኦል ነው ብለው ሲከራከሩ ሰማሁ? በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ትላለህ?"

እትቴ የተለመደችውን ደስ የምትለዋን ሣቋን ሣቀ:: ከዚያ የግራ ቅንድቡን ነካካና እኔን እየተመለከተኝ "የእኔ ልጅ ስለአንድ ነገር አሉታዊ አመለካከት ብቻ ካለን ስለዚያ ነገር አዎንታዊ ነገር ማሰብ ወይም መፃፍ ወይም መናገር አንችልም:: ይህ ብዙዎች ኢትዮጵያዊያን የሚሰቃዩበት በሽታ ነው:: ለማንኛውም ሙዚቃን በተመለከተ ብቸኛው የዓለም ህዝብ የሚግባባበት ዓለም አቀፍ ቋንቋ ነው:: ስለማይከል ወይም ጥላሁን ገነት ይሁን ሲኦል መግባት ብቸኛው አዋቂ ፈጣሪ ብቻ ነው:: መላ ህይወቱን የእ/ር ቃል ሲናገር የነበረ ቄስ አልያም መላ ህይወቱን ሲሰብክ የነበረ ፓስተር ሲኦል ይግባ ገነት በእርግጠኝነት የሚያውቀው የሰው ልጅ ሳይሆን ፈጣሪ ብቻ ነው:: ይህን በድፍረት የሚናገሩት ወይም እከሌ ገነት ይገባል እከሌ ሲኦል ይገባል የሚሉት ተራ ጭንቅላት ያላቸው ሰዎች ናቸው:: ለዚያ ነው ነጋድራስ ገብረሀይወት ባይከዳኝ የሚባሉ ሰው 'አዕምሮ የሌለው ደነዝ ህዝብ ሁሉ የእ/ርን ቃል ሳያውቅ የእ/ር ጠበቃ ሊሆን ይወዳል' የሚል ምርጥ ንግግር ለኢትዮጵያዊያን የተናገሩት:: ለማንኛውም በዓለማችን ላይ 2.18 ቢሊየን ክርስቲያኖች አሉ:: ከዚህ ውስጥ 50% ወይም 1.14 ቢሊየን ካቶሊክ ሲሆኑ 37% ወይም 800 ሚሊየን ፕሮቴስታንት ሲሆኑ 9.12% ወይም 260 ሚሊየን ኦርቶዶክስ ናቸው:: ከእነዚህ ውስጥ ከሁሉም ባፈነገጠ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በገላትያ 5፡21 ላይ ባለው ዘፋኝነት የሚለው ቃል በማከረር የሚወዛገቡት ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያን ነን ባዮች ናቸው:: የዚህ ቃል ፍቺ ጣጣ የመጣው ቅጥ ያጣ አጉል ፈንጠዚያ፣ ድንበር የሳተ አጉል ፈንጠዚያ የሚለውን ቃል የእኛ አገር ተርጓሚዎች "ዘፋኝነት" እና "ሙዚቃ" ብለው በማስቀመጥ የፍቺ ውዝግብ እንዲከሰት በማድረጋቸው ነው"

"ስለዚህ ሙዚቃ ሀጢያት አይደለም?"

"የእኔ ልጅ ሙዚቃ እንደ ስዕል፣ ድርሰት፣ ግንበኝነት ፣ ተናጋሪነት፣ ገጣሚነት፣ ተዋናይነት... ጥበብ ነው:: የተሰጠሽን ጥበብ ለጥሩም ለአጉል ነገርም ልትጠቀሚበት ትችያለሽ

አንድ ሙዚቀኛ በሙዚቃው ስለ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደግነት፣ መልካምነት፣ ኢትዮጵያዊነት ፣ ጠንካራ ሰራተኝነት ሊዘፍን ይችላል:: ይህ እንዴት ሀጢያት ይሆናል? በሌላ በኩል አንድ ሙዚቀኛ በሙዚቃ አማካኝነት ዝሙት ጥሩ እንደሆነ፣ ፈጣሪ እንደሌለ ፣ ማጭበርበር ደግ እንደሆነ፣ ስለዘረኝነት ፣ ስለ ጥላቻ፣ ስለ ባዕድ አምልኮ፣ ሊያቀርብ ይችላል:: በዚህን ሰዓት በተሰጠው የሙዚቃ ጥበብ ሀጢያት ሰራበት ማለት ነው:: በሙዚቃው ውስጥ የተነሣው ሀሳብ ምንድ ነው? እንዴት ተገለፀ? የሚሉት ጥያቄዎች ወሳኝ ናቸው:: ለምሳሌ ኃይለስላሴ ጌታ ነው የሚል የሬጌ ሙዚቃ ብትሰሚ አብረሽ መዝፈንም ሆነ ሙዚቃውንም ማዳመጥ የለብሽም:: ሀጢያት ነው! ኃይለስላሴ ተራ ሰው እንጂ አምላክ አይደለማ! በሌላ በኩል ለምሳሌ እርቆ ማሰቢያ እያለን አዕምሮ ስለምን ተሳነን ለማክበር ቀጠሮ የሚል የጥላሁን ገሰሰን ሙዚቃ ብትሰሚ እንዴት ሀጢያት ይሆናል? ስለዚህ የሙዚቃ ጥበብን ለመልካምም ለሴይጣናዊነትም ልንጠቀምበት እንችላለን እንጂ ሙዚቃ በራሱ ሀጢያት አልያም ፅድቅ ያልሆነ ተሰጥኦ ነው" በማለት ነበር አጎቴ ስለ ሙዚቃ ያጫወተኝ:: ይህን ከአጎቴ ጋር ያወራሁትን ለአፍታ አስታወስኩና ሀሳቤን ወደ ቤተል በመመለስ በትኩረት እያየዋት

"የኦርቶዶክስም የፕሮቴስታንትም መዝሙር ትሰሚያለሽ ማለት ነው" አልኳት::

"እሪ ግራ ነው የገባኝ በእናትሽ" አለች:: ግንባሯን በመቋጠር::

"በምኑ?"

"ቤተሰቦቼ ናቸዋ!"

"አልገባኝም"

"እናቴ አክራሪ ፕሮቴስታንት ናት:: አባቴ አክራሪ ኦርቶዶክስ ነው:: እናቴ ቤት ካለች የፕሮቴስታንት ስብከት እና መዝሙር ትከፍታለች:: አባቴ ደግሞ ድንገት ቀድሞ ቤት ከገባ የኦርቶዶክስ ስብከት እና መዝሙር ይከፍታል:: እንደ ህጻን ልጅ ቅልጥ ያለ ፉክክር ውስጥ ናቸው:: በመሀልቤት እኔ ግራ ገባኝ እኮ"

"እንዴት ተጋቡ?"

"ሲጋቡማ ሁለቱም ካቶሊኮች ነበሩ:: ከዚያ በኋላ ነው ሀይማኖታቸውን የቀየሩት" አለች:: ምንም የምለው ስላልነበረ ዝም አልኩኝ:: ቤተል ግን ቀጠለች::

"እኔም እኮ አንዳንቺ ሙሉውን የኢትዮጵያን ህዝብ መዝሙር አውቃለሁ"

"ሙሉውን?"

"በሚገባ! እንኳን የአገሬን መዝሙር አስር ሰኝኝ ቀርቶ የሰንቱን ሙዚቀኛ መዝሙር ማለቴ ጥቅም ቢቃሌ አይዝ የለም እንዴ?"

"እና አገርሽን ኢትዮጵያን አትወጂም? ታዲያ ለምን ባንዲራ ሲሰቀል አትዘምሪም?"

"በእርግጥ ኢትዮጵያን እወዳታለሁ:: እዚህ የኢትዮጵያ መሬት ላይ ነው የተወለድኩት:: ቤተሰቦቼ ኢትዮጵያዊ ናቸው:: የሚገርምሽ አባቴ እንደነገረኝ የአባቴ ትውልድ መነሻ ከአፄ ቴዎድሮስ ውሽማዎች ከነበሩት አንደኛዋ ወገን የተወለድን የአፄ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ልጅ ነገር ነን:: አባቴ እንደ ነገረኝ የኢትዮጵያ እውነተኛ ባንዲራ አረንጓዴ ፣ ቢጫ፣ ቀይ ነው:: ይቺ መሀከል ላይ ያለችው አንባሻ የኢሉሚናቲዎች መግባቢያ ቋንቋ ነች:: ኢሉሚናቲዎች ደግሞ የሴይጣን ተላላኪዎች ናቸው፤ ስለዚህ ባንዲራ ሲሰቀል እንዳትዘምሪ የብሔር ብሔረሰቦች ምልክት ነው የሚባለው የሸንገላ የዳቦ ስም ነው ስላለኝ የአባቴን ትዕዛዝ በማክበር አልዘምርም" በማለት ነበር ከጀርባዋ ያለውን የግል ምክንያቷን ያጫወተችኝ::

... ብቻ ቀናት እየቀለጡ በመጡ ቁጥር የባንዲራ ሰዓት ቅጥ አልባውን አከባበሩን፣ የአዲስ አበባ ተማሪዎችን በጣም እንዲሻሻል ሊሠራበት የሚገባውን አስነዋሪ ፀባያቸውን፣ የማይጨበጠውን የአዲስ አበባ አስተማሪዎችን ፀባይ ለመልመድ ብዙም አላስቸገረኝም:: በዚያ ላይ አጉል ነገር እኮ በፍጥነት ይለመዳል:: መልካም ነገር ለመማር ነው ጊዜ የሚፈጀው:: እኔ ካለሁበት ክፍልም ሆነ በትምህርት ቤቱም ውስጥ ካሉት የየዓመቱ ምርጥ ቀለሜ የሚባሉ ተማሪዎች ፎቶ ለሌሎች ተማሪዎች መነሳሳትን ይፈጥሩ ዘንድ የሚሰቀልበት ቤተመዛግብት በመሄድ የምርጥ ተማሪዎችን ፎቶዎች አየሁኝ:: በት/ቤቱ ውስጥ በሚደንቅ ሁኔታ አንደኛ ሴት ወጥታ አታውቅም ማለት ነው ፤ ምክንያቱም የተለጠፈው ፎቶ ሁሉ የወንድ ብቻ ነው:: የወንዶች ዓለም! ወንዶች እንደፈለጉ የሚፈነጩበት ዓለም! ወንዶች እንደፈለጉ ህግ የሚያወጡባት እና የሚያሾሩባት ዓለም! የዛሬ ዓመት እዚህ ቦታ እና ክፍል ውስጥ የራሴን ፎቶ እንደማየው ለራሴ ቃል ኪዳን በመግባት እና እርግጠኛ በመሆን ወጣሁ:: በዚህ አጋጣሚ ያልተመለሰልኝ እና በጣም የሚገርመኝ ነገር ከስንት አንድ ጊዜ ነው እንጂ እንደ እኔ ያሉ ውብ ሴት ተማሪዎች ብዙ ጊዜ መከታ የሚያደርጉት ይህን ፈራሽ ውበታቸውን በመሆኑ በክፍል ውስጥ ደካዝ እና ደረጃ መዳቢዎች ናቸው:: ሌላው በጣም የሚገርመኝ ጉዳይ በጣም ድንቅ ጭንቅላት ያላቸው የዓለማችን ሴቶች ውበታቸው የተወቀጠ ነው:: ጭንቅላታቸው ውብ ይሆንና መልካቸው ዝም ይሆናል፤ ይህ ለእኔ የሚያስቀኝ እንቆቅልሽ

ነው! ወይስ ይቺ ጉደኛ ተፈጥሮ አንዱን ባንዱ እያካካሰች ይሆን?? ወይስ ውብት የሚባል የለም? ወይስ ውብት አንፃራዊ ነው? በፍልስፍና ህግ ደግሞ አንፃራዊ የሆነ ነገር እንደሌለ ይቆጠራል፤ ስለዚህ ውብት የለም የሚለው ያስማማል?

ስለ ከፍላችን ተማሪዎች መረመርኩ:: ሰለልኩ:: ግዴለሾች ይበዛሉ:: ለእውቀት ኬረዳሾች ይበዛሉ:: ፊዘኞች ይበዛሉ:: ጎልቶው ለመታየት የሚሯሯጡ ይበዛሉ:: የአፉኝት ልጆች ይበዛሉ:: አንደኛ ሁልጊዜ የሚወጣው ልጅ ከምነግራችሁ በላይ በጣም ጭንቅላቱ ግድንግድ ነው:: ዝምተኛ ነው:: አስተማሪዎችን በትኩረት ያዳምጣል:: በዚያ ግድንግድ ጭንቅላቱ አንድ ጊዜ በቴሲታ ቢለኝ በድጋሚ ህይወት የምዘራ አይመስለኝም ወይም አዲስ አበባ ላይ የመታኝ ደብረማርቆስ ላይ አገኝ ይሆናል:: በህይወቴ እንዲህ ያለ ግድንግድ ጭንቅላት ያለው ሰው በፊልም ላይ እንኳ አይቼ አላውቅም:: ይህ ይገርመኛል ፤ ስለዚህ የተለየ ተፈጥሮ ያለው ልጅ አጠገቤ ያለችው ፈገግተኛ ቤተል እንደነገረችኝ ልጁ አምና አንደኛ ሲወጣ 928/1000 ሺ ነበር ያመጣው:: ይህ ውጤት ከእኔ ጋር ሲነፃፀር ትንሽ ነው:: በእርግጥ በዚህ ዓመት ከከፍል ውጤት ይልቅ ከፍተኛ ዋጋ ያለው የመንግስት ፈተና የሆነው የሚኒስትሪ ፈተና መሆኑን በሚገባ ባውቅም እኔ በከፍልም በሚኒስትሪም ከፍተኛ የሚባለውን ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት አደርጋለሁ:: ያለኝን ጊዜ ሁሉ እጠቀምበታለሁ:: ይቺን የወንዶች ዓለም ለወንዶች ብቻ ሙተው አልፈልግም እናም ወጥሬ እነባለሁ! ያለ እንዳች መሰላቸት እነባለሁ! በትጋት እነባለሁ! ጥረት ካለ በእርግጠኝነት ስኬት አለ! ያለሙትን ህልም እውን ማድረግ በእርግጠኝነት ይቻላል! በዚህ እምነት አለኝ::

ገጠር ቀመስ መልክ እንዳላት በቀላሉ የሚታወቅባት እና እጅግ ከርዳዳ ፀጉር ያላት አማርኛ አስተማሪያችን በጣም ተገርማብኛለች:: ስለንባብ አስፈላጊነት እና መፅሐፍት ማንበብ አስፈላጊነት እያወራች ነበር:: ካለን ሰዓት ላይ አብቃቅተን ያገኘነውን የግጥም፣ የጋዜጣ፣ የመፅሔት፣ የመፅሐፍ፣ የአጭር ልቦለድ... ወዘተ በማንበብ አዕምሮያችንን መመገብ እንዳለብን እየነገረችን እና እየመከረችን ነበር:: ማንበብ የአዕምሮ ምግብ እንደሆነ በብዙ ምሳሌዎች እያጣቀሰች እና እያዋጀች እየነገረችን ነበር፤ ከዚያ ጥያቄ መጠየቅ ጀመረች

“እስቲ የአስገራሚዋን የአና ፍራንክን አስገራሚ እና አሳዛኝ መፅሐፍ ያነበበ?” አለች፡፡ ማንም እጅ አላወጣም፡፡ እኔ ግን አወጣሁ፡፡

“ጎበዝ! እስቲ እሺ ሌላ መፅሐፍ ያነበበ?” አለች በድጋሚ፡፡ ያ ግድንግድ ጭንቅላት ያለው ተማሪ እጁን አወጣ፡፡ እኔም አወጣሁ፡፡ ቅድሚያውን ስባለግድንግዱ ጭንቅላት ተማሪ ሰጠች

“እሺ ልዑል” አለችው፡፡

“በብዛት የተረት መፅሐፍት ናቸው ከዚያ ውጪ እንዳነብ ቤተሰቦቼም መፅሐፍ ማንበብ ጊዜ ማቃጠል እና ትምህርት ላይ ትኩረት እንዳታደርግ ችግር ይፈጥራል ብለው ስለሚያስቡ በጭራሽ እንዳነብ አይፈቅዱልኝም” በማለት ተቀመጠ፡፡

“እሺ እሌኒ” አለች እኔን እየተመለከተች፡፡

“እኔ ያነበብኩት በጣም ብዙ ነው”

“በጣም ብዙ ነው ማለት?”

“አጎቴ በትንሹ 3000 ሺ መጽሐፍት አሉት፡፡ እኔንም እንዳነብ የሚያበረታታኝ አጎቴ ነው፡፡ እስካሁን ከ250 በላይ መፅሐፍትን አንብቤያለሁ እና ማንበብ የአዕምሮ ምግብ መሆኑን አውቄያለሁ” አስተማሪዋ በግርምት ተመለከተችኝ፡፡ ከዚያ በንግግር ሳይሆን በምልክት ቋንቋ ተቀመጪ አለችኝ፡፡ ከፍለ ጊዜዋ አልቆ ሲደወል እኔ ጋር በመምጣት ቢሮዋ እንድመጣ ነገረችኝ፡፡ በዕረፍት ሰዓት ቢሮዋ አመራሁ፡፡ በፈገግታ ተቀበለችኝ፡፡ ስላነበብኳቸው መፅሐፍት አወራን፡፡ ተገረመች፡፡ ከዚያ ልወጣ ስል

“በጣም አሪፍ ነው፤ ቢሆንም በዚህ ለጋ እድሜሽ ከመጠን በላይ ብዙ እና የማይመጥኑሽን መጽሐፍት ሁሉ ማንበብ አደጋ ስላለው ተጠንቀቂ! ያገኘሽውን መፅሐፍት ሁሉ ማንበብ አለብሽ ማለት አይደለም!” በማለት በክብር ከወንበሯ በመነሳት ጨብጣኝ ሸኘችኝ፡፡

በእኔ እይታ አስተማሪዎች መሰደብ የለባቸውም፡፡ አስተማሪዎች የእውቀት አባት ናቸውና ሊከበሩ ይገባል የሚል ግንዛቤ ነበረኝ፡፡ አሁን ግን አንዳንድ አስተማሪዎች መሰደብ

እንዳለባቸው ተገነዘብኩኝ፤ እናም ተሳደብኩኝ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በውስጤ አስተማሪን ተሳደብኩ፡፡ ይህ የማይረባ ባዮሎጂ አስተማሪ አልኩኝ፡፡ እናቱን በድንጋይ ብፈነክተው በጣም ደስ ይለኝ ነበር፡፡ አጋጣሚው ይህ ነበር... ስለተለያዩ በሽታዎች እና ምን ማድረግ እንዳለብን እያስተማረ ነበር፡፡ ከዚያ ባለግድንግድ ጭንቅላቱን ልዑልን በማስነሳት

"ልዑል እስቲ ስለ ስቅታ ንገረኝ?" አለው፡፡ ልዑልም ከተቀመጠበት በመነሳት

"ከሳንባችን በታች የሚገኘው ጡንቻ ሲኮማተር የሚፈጠር የተለየ ድምፅ ነው፡፡ የደረት ንቅናቄ ነው፡፡ ስቅታ የሚከሰትበት ምክንያት የሚያቃጥልና ቅመም የበዛበት ምግብ በመመገብ፣ ምግባችንን ተስገብግበን በፍጥነት በመብላታችን የተነሣ፣ ብዙ አልኮል በመጠጣት፣ በጣም አብዝተን ስንጨነቅ፣ ትኩስ ነገር እና ቀዝቃዛ ነገር አከታትለን ወዲያው ወዲያው በመውሰድ የተነሣ ነው"

"በጣም ጥሩ ልዑል! ስቅታ ሲያስቸግረን በፍጥነት ምን ማድረግ እንዳለብን እስቲ ኩብሳ መልስ" አለው፡፡ ኩብሳ የክፍላችን ረጅሙ እና ከሌሎች ተማሪዎች አንጻር ስነፍ የሚባለው ተማሪ ነው፡፡ አስተማሪ ሲቀር ክፍሉን በሣቅ የሚያንከተክት የክፍላችን ኮሚክ ነው፡፡ በሚናገራቸው ቀልዶች ሁሉም አፋቸውን ከፍተው ሲገለፍጡለት እኔ አልስቅለትም፡፡ ስለማልስቅለት እሱም ይጠላኛል፡፡ ሁሉም ትኩረት ሲሰጡት እኔ ትኩረት ስለነፈኩት በጥላቻ አይን ይመለከተኛል፡፡ ት/ቤት የሚመጣው ለመማር ሳይሆን ተማሪዎችን ለማሣቅ ብቻ ይመስለኛል፡፡ እሱ ያስቃቸዋል እነርሱ ፈተና ሲደርስ ሳይታወቅባቸው በተለያዩ ኮዶች ያስኮርጁታል፡፡ በዚህ ነገር በጣም ስለምበሳጭ የፈለገውን ቢያወራ አልስቅለትም!

"በስመ አብ በስመ ወልድ በስመ መንፈስ ቅዱስ ብለን ማማተብ ነዋ!" አለ፡፡ ክፍሉ በሣቅ አስካካ፡፡ አስተማሪው በንዴት "እያሣካቸው መስሎህ ከሆነ አንተ ደነዝ! የአህያ እር! ቦንቦክላት እየሣቁብህ መሆኑን አትርሣ" በማለት ጥንብ እርኩሱን አወጣው፡፡ በኋላ እንዳጣራሁት ቦንቦክላት የምትለዋ የራስታዎች ስድብ እጅግ አስነዋሪ ፍቺ እንዳላት ነው፡፡ አስተማሪው ይህን በመናገሩ ተሸማቅቄያለሁ፡፡ ከአስቀያሚ ስድብ ይልቅ ምን አለ ቢመታው ነበር ያልኩት! ተማሪ መምታት ደግሞ በት/ቤታችን በጣም አደገኛ ነው፡፡ ተማሪዎችም እንደ ማይመቱ ስለሚያውቁ በአስተማሪዎች ላይ ብጥስጥስ ይላሉ፡፡ በእኔ አይታ ግን ተማሪዎች መጠኑን ያልዘለለ ከሆነ መመታት እንዳለባቸው ውስጤ ያምናል፡፡ ቅጣት ጥሩ ነውና! ጠማማው የሚቃናው በቃል ብቻ ሳይሆን በኩርኩም ጭምር ነውና!

ከዚያ መስቲ የምትባለዋን የክፍላችንን አንደኛ ዘናጭ ተማሪ አስነሣ:: ይቺን መስቲ የተባለችውን የክፍላችንን ዘናጭ በጣም የሚያምር·ጡት እና የሚያምር ቂጥ የመጀመሪያ ጊዜ ስመለከት በተፈጥሮ ድንቅ ስራ ተገርሜ ነበር፤ ግን አጠገቤ የምትቀመጠው ባለፈገግተኛዋ ቤተል ወዲያው ሹክ አለችኝ

"መስቲን ተመልከቺያት የክፍላችን ዘናጭ ነች? ደግሞ ሁሉ ነገር ያምርባታል አይደለምን?"

"በጣም! የሁሉም ትኩረት እሷ ላይ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ"

"ግን ለማንም ካልተናገርሽ የሆነ ነገር ሹክ ልበልሽ?"

"በይኝ!"

"የቻይና ውጤት እኮናት! እኔ የምጠራት መስቲ ቻይና እያልኩ ነው:: ማንም ግን ትርጉሙን አያውቅም"

"አሀ... ክልስ ነች እንዴ?"

"አይ አንቺ! የመስቲ የሚያምር ቂጥ እና ጡት እኮ አርቴፊሻል ነው! ሆንብላ እኮ ነው ያን የምታደርገው! ጎልታ ለመታየት ከፍተኛ ጉጉት አላት እና ቂጧ የውሸት የተለጠፈ እኮ ነው! ጡቷም የውሸት የቻይና ስራ እኮ ነው ይህን የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ"

"አንቺ ግን እንዴት አወቅሽ?"

"የዛሬ ዓመት የቅርብ ጓደኛዬ ነበረች:: እቤቷ ስሄድ ነው ቅሌቷን ያሳየችኝ:: አሁን ተጣላን እንጂ"

"በምን የተነሣ?"

"አንቺ ግን ደራሲ መሆን ነው ምኞትሽ? ሁሉን ነገር በዝርዝር ለማወቅ ትፈልጊያለሽ? በጥያቄ ላይ ሌላ ጥያቄ ታስከትያለሽ?" አለችኝ:: በፈገግታ ዝም አልኳት:: ቤተል ወሬዋን ቀጠለች::

"ሀቁን ለመናገር ጥፋተኛዋ እኔ ነኝ! የሆነ ወሬ ለማንም እንዳትናገሪ ብላ ነገረችኝ እኔ ደግሞ አላስችል አለኝና ያን ወሬ ለሆነ ሰው ሹክ አልኩኝ:: ያ ሰው ደግሞ መልሶ ለራሷ ሹክ አላት! ተጣላችኝ:: ይቅርታ ብላትም በድጋሚ አላምንሽም ብላኝ እንቢ አለች:: በዚያ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (ምሳ 22፡24) ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ የሚለውን ጠቅሳ ተሳለቀችብኝ! ብቻ በጣም ጉራዋን ስትቸረችርብኝ እና ቆዳዋን

ሲታዋድድብኝ ጊዜ ስራ ያውጣሽ አንቺ አርቴፊሻል ቅንብር ብያት ተለያየን" በማለት ጀምረን ስለ ከፍላችን ዘናጭ ተማሪ በመጠኑ ቦጨቅን:: ቡጪቃ የእኛ የሴቶች ምግብ ነው:: መዝናኛችን ነው:: ሲድስተኛ ጣታችን ነው:: ወንዶች ቦለቲካ እና ኳስ እንደሚወዱ እኛ ሴቶች ደግሞ ቡጨቃ እና ወሬ እናፈቅራለን:: የተማረች ትሁን ያልተማረች፣ መንገድ ላይ የምትተኛ ትሁን ቤተመንግስት የምትኖር ሴት ትቦጭቃለች:: ይህ እውነት ነው:: ይህ ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው:: ለማንኛውም የከፍላችን ዘናጭ መስቲ በቁንጠኛ ሁኔታ በመነሳት

"አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውሃ በፍጥነት በአንድ ትንፋሽ ወዲያው መጠጣት አልያም አፍንጫን ለ24 ሴኮንድ አፍኖ መያዝ ችግሩን ይቀርፈዋል" አለችና ተቀመጠች:: ወዲያው ጴጥሮስ የሚሉት እጁን በማውጣት

"አመሠግናለሁ! በተጨማሪ ለስቅታ ሌላው መፍትሔ ወዲያው ሱኳር መላስ እና ሎሚ ማኘክ አሪፍ ሲሆን ስቅታችን ከ40 ሰዓት በላይ እየተደጋገመ ከመጣ ግን ሆስፒታል በማምራት መመርመር ይኖርብናል:: ይህን የነገረኝ የገሊላ ከፍተኛ ሆስፒታል ባለቤት የሆነው ዝነኛው ዶክተር አባቴ ነው" በማለት ስለ አባቱ ዶክተርነት ማስታወቂያ በመስራት ተመልሶ ተቀመጠ::

የባዮሎጂ አስተማሪው ርዕስ ለወጠና ወደ የወር አበባ ገባ:: ወንድ ተማሪዎች ሣቁ:: በእርግጥ ወንዶች ፈጣሪን ሊያመስግኑ ይገባል:: የወር አበባዬ ቀረ ፣ የወር አበባዬ መጣ፣ የወር አበባዬ በዛ፣ የወር አበባዬ አነሠ፣ የወር አበባዬ ሲመጣ ያመኛል፣ ይቆርጠኛል፣ ይወጋኛል፣ የጀርባ ህመም ፣ ራስ ምታት፣ ማቅለሽለሽ ይሠማኛል፣ ይደብተኛል... የመሠሉ ነገሮችን ስለማያውቁ ፈጣሪን ሊያመሠግኑ ይገባል:: የወር አበባ የሴቶች ጸጋ ነው:: እኔ የሚገርመኝ የወር አበባ ላይ የሆነች ሴት ቤተመቅደስ መግባት የለባትም፤ ሀጢያተኛ ስለሆነች ቤተመቅደሱን ታረክሰዋለች የሚባለው የወንዶች ተንኮል የተሞላበት ህጋቸው ነው:: ይህ የፈሪሳዊያን ከንቱ ህግ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ምድር ይከበር ማለታቸው ያስቀኛል:: ስንት የሚያስጨንቅ ጉዳይ እያለ ስለ ሴቶች የወር አበባ ሲጨነቁ ከንቱነታቸውን ያበራልኛል:: ለማንኛውም አስተማሪው ጥያቄውን አስከተለ "እንዲት ሴት የወር አበባ መቼ ታያለች? ለምን ታያለች? ይህን ጥያቄ እስቲ ሔለን መልሺ?" አላት:: ሔለን የከፍላችን በልጣጣ ሴት ናት:: ቁሌታም ሴትናት:: የሚያደርጋትን የሚያሳጣት ሴትናት ፤ ለምን እንደሆነ ባላውቅም ደስ አትለኝም:: ገና ከአሁኑ አርቴፊሻል የዊግ ፀጉር ትጠቀማለች:: አስተማሪ ከፍል ካልመጣ

ከሁሉም ጎልቶ የሚሰማው የእሷ አለብላቢት ምላስ ነው፡፡ እሷ እና ኩብሳ ከፍሉን በአንድ እግሯ ያቆሟታል፤ በተለይ እሷ ማውራት ደከመኝ ፣ መለፍለፍ ደከመኝ የማትል እረፍት አልባ ቀንደኛ ለፍላፊ ናት፡፡ የሆነ የሚያከለፈልፍ፣ ብዙ የሚያስወራ፣ አንድ ቦታ እንዳትቀመጥ የሚያደርጋት አጋንንት ሳይሰፍርባት አይቀርም! በዚያ ላይ ሰውን ሁሉ በንቀት በአይኗ ቂጥ ስለምትመለከት አትመቸኝም

"የወር አበባ ለአንዲት ጤነኛ ሴት ከ28-34 ቀናት ውደት የሚመጣ ከ4-7 ቀናት ሊቆይ የሚችል ሲሆን የወር አበባ ለሴት ልጅ መውለድ ትችላለች ዜና ማብሰሪያ ሲሆን የወር አበባ የሚመጣበት እድሜ ከሴት ሴት ልዩነት ቢኖረውም በብዛት ግን ከ12-16 ዓመት ውስጥ ይመጣል፤ ስለዚህ አንዲት ሴት እስከ 16 ዓመቷ የወር አበባዋ ካልመጣ የጤና ችግር ሊሆን ስለሚችል ምርመራ ማከናወን አለባት፤ ምናልባት አንዲት ሴት ስትወለድ በሚከሰት የልብ በሽታ፣ በጣም ከፍተኛ ውፍረት፣ የብልት ቀዳዳ አለመኖር ፣ ከፍተኛ የምግብ እጥረት፣ የማህፀን አለመኖር፣ በማህፀን አካባቢ የተፈጠረ ዕብጠቶች አልያም የታይሮይድ ዕጢ ችግር የተነሣ የወር አበባ የሚባል እስከመጨረሻው ላታይ ትችላለች፡፡ በሌላ በኩል የወር አበባ ስታይ የነበረች ሴት ደግሞ ድንገት የወር አበባዋ ሊጠፋ ወይም ሊዛባ ይችላል፡፡ የዚህ ምክንያት ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ስትገባ፣ በሚዋጡ መድኃኒቶች፣ አላስፈላጊ ውፍረት የተነሣ ፣ ድንገት ከመጠን በላይ መክሳት፣ የታይሮይድ ዕጢ ችግር ፣ ከመጠን ያለፈ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ ውርጃ ማከናወን ፣ የወር አበባ ሊመጣ ቀናት ሲቀሩ ወሲብ ማድረግ ይጠቀሳሉ፡፡ አንዲት ወሲብ ያልጀመረች ሴት የወር አበባዋ ከ75 ቀናት በላይ ከጠፋ ወዲያው ህክምና ጋር መሄድ ይኖርባታል፤ እንዲሁም ..." ይቺ ለፍላፊ ሒለን አንጄ መናገር ከጀመረች አትፎርሽም! በእርግጥ ምንም ደስ ባትለኝም ፣ ምንም ይህን አርቴፊሻል ፀጉርዋን ብጠላውም፣ ምንም ቆሌዋ ባይስበኝም፣ ምንም ቀልቃላነቷ ባይመስጠኝም ጎበዝ ከሚባሉት ተማሪዎች አንደኛዋ መሆኗን መካድ የለብኝም! ነውጠኛ ጎበዝ ተማሪ! በተለይ ከእኔ ይልቅ እሷ የበለጠ ተናግሮ የማሳመን ችሎታ እንዳላት መካድ የለብኝም፡፡ አንዳችም ነገር የማትፈራ መሆኗን መካድ የለብኝም ፤ እናም ስለ ወር አበባ ኧረ በቃሽ ስላልተባለች ቱልቱሌዋን ቀጠለች

"አንዲት ሴት በወር አበባ ጊዜ የሚመጣውን ሆድ ቁርጠት ፣ ውጋት፣ የጀርባ ህመም፣ ራስምታት፣ ማቅለሽለሽ፣ ድብርት፣ መነጫነጭ እንዴት መቀነስ ትችላለች? ሲጀመር የወር አበባ ደም ነው፡፡ ያደም የወንድ እንቁላል እስከሚያገኝ ይጠብቃል፡፡ የወንድ እንቁላል

ካላገኘ የሴቷ ማህፀን ውስጥ የነበረው የረጋ ደም ተመልሶ ወደ ውጪ መፍሰስ ይኖርበታል:: ያ ቆጮን የነበረው ደም የረጋ ደም ስለሚሆን ያ የረጋ ደም ደግሞ እየተከተፈ፣ እየተሰነጣጠቀ መውጣት ይኖርበታል በዚህን የመከተፍ እና የመሰነጣጠቅ ስራ ሲሰራ ነው እንግዲህ የህመም ስሜት የሚሰማን ፣ ይህን የህመም ስሜት ለመቀነስ አሪፍ ዘዴዎች አሉ:: ለምሳሌ ከእንብርት በታች ያለውን የሆድ ክፍል በስሱ በክብ ቅርፅ የወር አበባችን እስከሚያልቅ በየቀኑ ለ15 ደቂቃ አሸት አሸት ማድረግ፣ ለብ ያለ ውሃ መጠጣት፣ ሙዝ መብላት፣ በጎን ብቻ መተኛት፣ በቀስታ መራመድ፣ በሙቅ ውሃ መታጠብ፣ አስፈሪ የሆኑ ምርጥ ሆረር ፊልሞችን ማየት ይጠቀሳሉ" በማለት ተቀመጠች:: ወንድ ተማሪዎች አጨበጨቡላት:: ወዲያው ያ የዶክተር ልጅ እጁን አወጣ:: አስተማሪው እድሉን በድጋሚ ሰጠው

"አመሠግናለሁ! በእርግጥ ሁሉንም ሄለን ተናግራለች:: የወር አበባን የሴቶች ደስ የሚል ስቃይ ብቻ አድርጋችሁት አታስቡት የገሊላ ከፍተኛ ሆስፒታል ባለቤት የሆነው ዶክተር አባቴ በዝርዝር እንደነገረኝ ወንዶችም የወር አበባ ያያሉ፤ ምናልባት የወንዶች የወር አበባ እንደ ሴቶች ለአራት ቀናት ይሁን እስከ ሰባት ቀናት ደም ባይመለከቱም እንደ ሴቶች ሁሉ ወንዶችም የወር አበባ ሲመጣባቸው ግን ይነጫነጫሉ፣ ይጣላሉ፣ በከፍተኛ ድብርት ይመታሉ፣ ይቆዝማሉ፣ ብቻቸውን ያወራሉ፣ ያልሆነ ዘግናኝ ነገር ያከናውናሉ፣ ዕቃዎችን ይሰብራሉ፣ ከመጠን በላይ ይጠጣሉ፣ ከመጠን በላይ ይዋሻሉ፣ አድርገው የማያውቁትን ነገር እንዲያደርጉ ይገደዳሉ ፤ ስለዚህ ደም ባይመለከቱም ከሴቶች የባሰ የወር አበባ ስቃይ ወንዶችም ጋር እንዳለመርሳት የለብንም! በተረፈ ማስተካከያ ለመስጠት የሆረር ፊልም እንዲመለከቱ የሚፈቀድላቸው እና የሚጠቅማቸው ድንግል የሆኑ ሴቶች የወር አበባ ሲመጣባቸው እንጂ ድንግል ላልሆኑት አደጋ አለው" በማለት ተቀመጠ:: አስተማሪው የዶክተሩ ልጅ ያለውን ነገር ድንግል ላልሆኑት አደጋ አለው" በማለት ተቀመጠ:: አስተማሪው የዶክተሩ ልጅ ያለውን ነገር በተመለከተ ዝም አለ:: አስተማሪው ራሱ ይህን የወንዶች የወር አበባ ይመለከታሉ ሀሳብ አያውቅም አልያም በቂ መረጃ ስለሌለው ለማጣጣልም አልፈለገም፤ ይልቅስ ወሬውን ለማስቀየስ ወዲያው

"ሌላው ጥያቄ የሚሆነው ስለመደፈር ነው:: አንዲት የተደፈረች ሴት ምን የሚባል ህመም ይይዛታል? ይህን ጥያቄ የምትመልስልን አሌኒ ናት ፤ እስቲ አሌኒ ብትደፈሪ ምን ህመም ይይዝሻል?" ብሎኝ እርፍ... እስቲ አንድ አፍታ በእኔ ቦታ ሆናችሁ አስቡት! ምን ዓይነት የተረገመ አስተማሪ ነው? ምን ዓይነት ሥነ ምግባር የሌለው አስተማሪ ነው? እንዴት አይነት

ቀሽም አስተማሪ ነው? እንዴት አስቲ ብትደፈሪ ተብሎ ይጠየቃል? ይህ ከአንድ አስተማሪ አይጠበቅም... አስተማሪዎች ለሚጠቀሙት አያንዳንዱ ቃላት ጠንቃቃ እና መርጠው መሆን ይኖርቢታል፣ ምክንያቱም ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ጀርባ ስንት ጉድ እንዳለ አያውቁም... እናም በንዴት ውስጤ ጨሰ:: ውስጤ ሳላስበው ተንቀጠቀጠ:: አንዳች ነገር ሰውነቴን ውርር አደረገኝ:: ድንገት ያ አስቀያሚ ትዕይንት ትዝ አለኝ:: በንዴት ጥርሴን ነከስኩ፣ ግን ሁሉን ነገር ዋጥ እንዳደርገው ፈጣሪ ፀጋውን ወዲያው ሞላኝ... ዝም አልኩ... ውስጤ አልቅሺ... አልቅሺ... የሆነ ነገር አንስተሽ አስተማሪውን ፈንክቺው! ፈንክቺው! አለኝ... ግን ዋጥ አድርጌ ዝም አልኩኝ... ያ የማይረባ አስተማሪ ስህተቱ ወዲያው ገባውና

"አ! ይቅርታ ይህን የመሰለ አስከፊ ነገር ላንቺ እየተመኘው አይደለሁም፣ በጣም ይቅርታ እሌኒ ምሳሌ ለመስጠት ብቻ ነው..." አለኝ:: እኔ ግን ጥርሴን ነክሼ ዝም አልኩት:: ይቅርታም አንዳንዴ ዋጋ እንደማይኖረው ተረድቻለሁ:: ለምሳሌ አባቴ እና የደፈሩኝ ሰዎች በህይወት ቢኖሩ እና አይናቸውን በጨው አጥበው እኔ ጋር መጥተው "ይህን ያደረግነው ለሀብት ስንል ነው! ሴይጣን አሳስቶን ነው! ይቅርታ አድርጊልን" ቢሉኝ ይዋጥልኛል? ይህ ፌዝ አይሆንም? የአንድን ሰው አይኑን አጥፍታችሁ ይቅርታ ብትሉት ይዋጥለታል? በእ/ር የምናምን ከሆነ ግን ምንም ይደረግብን ምንም ይቅርታ ማድረግ አለብን! ምክንያቱም ይቅርታ የሚያደርግ ይቅርታ ይደረግለታልና! ይህ የፈጣሪ ትዕዛዝ ነው! ይህ የፈጣሪ ትዕዛዝስ ልብ ውስጥ የሚነድ እሳትን ያጠፋዋል?? ጥያቄውን እና መልሱን ለእናንተ ተውኩት...::

ያን ዕለት ት/ቤት አስጠልቶኝ ዋልኩ:: ስመለስ አንቴ ፊቴን እንዴት እንዳነበበው አላውቅም::

"የእኔ ልጅ ዛሬ ት/ቤት የተፈጠረ ነገር ነበር?" አለኝ:: ለአንቴ የተፈጠረውን ብነግረው ት/ቤት በመሄድ አስተማሪው ላይ እንደሚያንቧርቅበት ስለገባኝ አለመናገሩን መረጥኩ:: ሌላ ችግር እና ሌላ ግርግር መፍጠር አልፈልግም::

"ምንም የለም! ያው አንዳንዴ ደርሶ ይደብተን የለም?" አልኩት:: መደበት የምትለዋን ቃል ያወኩት አዲስ አበባ ስመጣ ነው::

"እሺ የእኔ ልጅ ብዙ የቤት ስራ ከሌለብሽ ነይ ወጣ ብለን እንምጣ? አንዳንዴ አየር መቀየር ጥሩ ነው:: ለምሳሌ ግርግር የማይጠፋት ፒያሳ ደርሰን በዚያው አሪፍ ፒዛ በልተን መምጣት እንችላለን?"

"ደስ ይለኛል"

ከአጎቴ ጋር እያወራን ወጣን:: የአጎቴ ነገር ይገርመኛል:: አዲስ አበባ ከመጣን ሀያ ቀን ሳይሞላን ስራ ጀምሯል:: ጠንካራ ሰራተኛ እና ቅን እንደሆነ ደብረማርቆስ በርካቶች ሲያወሩ ሰምቻለሁ:: የአጎቴ ህይወት ሥራ እና ማንበብ ናቸው:: በእርግጥ አጎቴ መሀን መሆኑ ህይወቱን ከሴት ውጪ እንዲሆን አድርጎታል ፤ ግን መሀን መሆኑን አምና የምትቀበል ሴት ኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ትጠፋለች? ይህን ጥያቄ መጠየቅ ፈለኩ:: ይህ ጥያቄ ዘወትር የማብሰለስለው ጉዳይ ነበርና!

"አጎቴ" አልኩት::

"አቤት"

"በቂ ገንዘብ አለን፤ ለምን ለመንቀሳቀሻ መኪና አትገዛም?"

"የእኔ ልጅ ወጣት እያለሁ አንዲት ፊያት መኪና ነበረችኝ:: እዚያች መኪና ውስጥ ስገባ እና መሪዋን ስይዝ በቃ ዓለም የእኔ የሆነች ትመስለኝ ነበር:: የእኛ አገር ሴቶች ደግሞ መኪና የሚነዳ ወንድ ሲመለከቱ አይናቸው ይጎለጎላል! የግራ ቂጣቸው ይንቀጠቀጣል! ሀብታም ወንድ ብቻ መኪና የሚነዳ ይመስላቸዋል እና በዚያች ፊያት መኪና ስንቷን የደብረማርቆስ ቆንጆ ጨረስኩ መሰለሽ? አይ ወጣትነት! ወጣትነት ካላወቅሽበት ሬት ካወቅሽበት ደግሞ ማር ነው እና አንድ ቀን እንደተለመደው እየነዳሁ አንዲት አብዝቶ ውብ የሆነች ሴት ስመለከት እና በአይኔ የዝሙት ባንዲራ ሳውለበልብ ድንገት አንዲት እርጉዝ ሴት ገጨሁኝ:: እናትም ልጇም ወዲያው ሞቱ... በዚህ አሰቃቂ ወንጀል የተነሣ ታሠርኩ:: ታዲያ እስር ቤት እያለሁ ቃል ገባሁ! በህይወቴ በድጋሚ መኪና ላልነዳ! እናም እስከምሞት የመኪና መሪ አልይዝም!! እስር ቤት ትልቁ የጠቀመኝ ነገር ከንባብ ጋር መተዋወቅን ነበር፤ በተለይ በቦለቲካ የተነሣ አብሮኝ የታሰረ አንድ አስደናቂ ጭንቅላት ያለው ምሁር እጅግ በርካታ ነገር እንዳውቅ ረድቶኝ ነበር:: ብቻ የእኔ የህይወት መሠረት እስር ቤት መግባቴ ነበር ለማለት እችላለሁ:: አንቺ ይህን የእኔን ታሪክ አታውቂም፤ ምክንያቱም ገና አልተወለድሽም ነበር"

"አጎቴ"

"አቤት"

"ስለ እስር ቤት ህይወትህ በዝርዝር ሌላ ጊዜ ትነግረኛለህ! አሁን ግን ሌላ የግል ጥያቄ ልጠይቅህ?"

"መብትሽ"

"ግን እንዳትበሳጭ"

"የእኔ ልጅ አትጨነቂ! እኔ በህይወት ውስጥ ሁሉን ነገር ያየው ሰው ነኝ:: ጨለማን አይቻለሁ:: ብርሃንን አይቻለሁ፤ ፍፁም ደስታን አይቻለሁ:: ፍጹም ሀዘንን አይቻለሁ:: ስለዚህ አንቺ የፈለግሽውን ጠይቂኝ"

"ልጅ መውለድ እንደማትችል ይገባኛል፤ ግን ይህን ችግርህን የምታውቅ ሴት ፈልገህ ለምን አታገባም?"

"የእኔ ልጅ በተለያዩ ጊዜያት አምስት ሴቶችን ቀርቤ አምስቱም መሀን መሆኔን ስነግራቸው ሽሽት አድርገዋል! በእርግጥ አልወቅሳቸውም፤ ምክንያቱም የሴት ልጅ ትልቁ ደስታ ልጅ ወልዶ መሳም ነው:: እኔ ደግሞ ያን ትልቅ ደስታ ልሰጣቸው አልችልም፤ ስለዚህ ተጨማሪ ሴት ከመፈለግ ትኩረቴን ስራ እና ንባብ ብቻ ላይ አደረኩኝ:: ደስታ አንጻራዊ ቢሆንም አሁን ባለኝ ህይወት ደስተኛ ነኝ፤ በዚያ ላይ አንቺን የመሰለች አስተዋይ ልጅ አለችኝ! ይህ በቂ ነው"

"ግን አጎቴ እንደው ምናልባት..." አልኩና ዝም አልኩኝ::

"ምናልባት ምን?"

"የምትወድህ ሴት ብታገኝ አታገባም?"

"አላውቅም! ልጅ መውለድ የማትፈልግ ሴት በዓለም ላይ የለችም፤ ምናልባት እንደኔው መሀን ካልሆነች በስተቀር! የእኔ ልጅ ፍፁም እውነተኛ ፍቅር በመሀከላቸው ከሌለ ይዋልይደር እንጂ በልጅ ያልታጀበ ትዳር ይቀዘቅዛል፣ ይፈተናል፣ የግጭት መነሻ ይሆናል"

"እሺ አንድ ልጅ ያላት ባለቤቷን በአደጋ ያጣች መልካም ሴት ብታገኝስ?"

"ፈጣሪ ነው የሚያውቀው"

"አሀ... ብታገኝ ታገባታለህ ማለት ነው?"

አጎቴ ፈገግ አለና ዝም አለ:: ወዲያው ማሰብ የጀመርኩት እንዴት ለአጎቴ ሚስት መፈለግ እንዳለብኝ ነው:: አጎቴ መልካም ብቸኛ ሰው ነው፤ ለዚህ መልካም ሰው አንዲት ጥሩ ሴት ብትገኝለት ደስተኛ የሚሆን ይመስለኛል፤ እናም ለአጎቴ ሚስት ለመፈለግ ለራሴ ቃል ገባሁኝ::

ከአጎቴ ጋር ፒያሳን ዞርናት:: አሪፍ ፒዛ በላን:: ቤት ተመለስን:: በእርግጥ ያን ምሽት የሆነ ሰዓት ላይ ያ አስቀያሚ ትዕይንት ትዝ ብሎኝ ነበር፤ ግን ለአጎቴ የምፈልግለት

ፍቅረኛ ምን አይነት ባህሪ እንደሚኖራት... ወዘተ እያውጠነጠንኩ ያን አስቀያሚ ትዕይንት ላለማሰብ ራሴን በሀሳብ ወጠርኩት፡፡ እናም ተሳካልኝ፡፡ ምሽቱን ሸወድኩት፡፡ በነጋታው ት/ቤት በዕረፍት ሰዓት ባዮሎጂ አስተማሪያችን ቢሮው ጠርቶኝ

"እሌኒ በጣም ይቅርታ ያን አስከፊ ንግግር መናገር አልነበረብኝም፡፡ የአፍ ወለምታ ሆኖብኝ ነው፤ ይህ ጉዳይ ቢሮ ከደረሰ ክስ ይመሠረትብኛል እና እባክሽ ከዚህ በፊት ሌላ ክስ ስላለብኝ..." አለና አይን አይኔን እያየ ዝም አለ፡፡

"መምህር በእኔ በጭራሽ አትስጋ ረስቼዋለሁ" በማለት ነገርኩት፡፡ ቆይቶ የገባኝ አብዛኛው የግል ት/ቤቶች ከአስተማሪዎች ይልቅ ትልቅ ክብር እና ዋጋ የሚሰጡት ለተማሪዎች መሆኑን ነው፡፡ የገንዘብ ምንጭ ናቸውና፡፡ ይህን አስተማሪ ክብሬን ነካው በማለት ሙቀት ብፈጥር ለአስተማሪው አደጋ ይሆን ነበር...

ይገርማል! ቀናት እንዴት ነው የሚነጉዱት? ምንም ሳላውቀው የት/ት ቀናቱ ቀለጡ፡፡ እንዳሰብኩት በአንደኛው መንፈቀ ዓመት ይሁን በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ከክፍል ይሁን ከሴክሽን አንደኛ ወጣሁ፡፡ በእኔ አንደኛ መውጣት ያ ግድንግድ ጭንቅላት ያለው ተማሪ በጣም ነበር የጨሰው፡፡ በንዴት ተንጨረጨረ! እንዴት በሴት እበለጣለሁ? በማለት አንድ ሁለት ቀናት በንዴት ዓይን ሲመለከተኝ ነበር፡፡ ግንቦት መጨረሻ ላይ የመንግስት ፈተና የሆነውን ሚኒስትሪ ወሰድን፡፡ በእርግጥ ለእኔ በጣም ከጠበኩት በላይ ቀላል ነበር፡፡ ክረምት ላይ አንቴ ብዙ ጊዜ ስላለሽ እያነበብሽ ብቻ መቀመጥ የለብሽም በማለቱ ደብረማርቆስ ስማር የነበረውን የፒያኖ እና ካራቴ ትምህርቴን እንድቀጥል አስደረገኝ፡፡ ብቻ ክረምቱ አሪፍ ነበር፡፡ አዲስ አበባንም ከአንቴ ጋር እየተሽከረከርን አየናት፡፡ እርግጥም ከደብረማርቆስ አንፃር አዲስ አበባ እብድ ከተማ ነች! አዲስ አበባ በቀን ይሁን በማታ ሁልጊዜ እንዳበደች ናት፤ በዚህ ትዕይንት በጣም ተገረምኩ፡፡ አዲስ አበባ ገነትም ሲኦልም ናት፡፡

የካራቴ ይሁን የፒያኖ ት/ቤት ሳመራ መንገድ ላይ ወጣት ሴቶችን በተለይ ህጻን ልጅ የያዘች ሴት ስመለከት "ይቺ ለአንቴ ሚስት ትሆን ይሆን?" እያልኩ አውጠነጥናለሁ፡፡ አንድ ጊዜ ግን ፒያኖ ት/ቤት ልገባ ሰዓት እስከሚደርስ አንድ ኬክ ቤት ተቀምጬ ማኪያቶ

እየጠጣሁ ሳለሁ አንዲት በጣም የምታምር ወጣት አንዲት ደስ የምትል በግምት የሰስት ዓመት ፈልፈላ ይዛ ኬክ ቤቱ ውስጥ ስትገባ አየሁኝ:: ያጋጣሚ ሆኖ እኔ ከተቀመጥኩበት ወንበር ብዙም ሳትርቅ ተቀመጠች:: ምክንያት ፈጥሬ አጠገባቸው ሄድኩኝ:: ፈልፈላዋን ሳምኳት::

"ስንት ዓመቷ ነው?"

"በቅርቡ ሶስት ይሞላታል"

"ስሟን ማን አልሻት?"

"ኤልሻዳይ"

"አባቷስ?"

"አሸብር"

ምን አይነት ስም ነው? ኤልሻዳይ ማለት ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ወይም እ/ር ማለት ነው:: ታዲያ ኤልሻዳይ አሸብር የሚለው ሲመነዘር ሁሉን ማድረግ የሚችለው እ/ር አሸባሪ ነው የሚል ቃና የለውም? ይህን ልጠይቃት አሰብኩና በተቃራኒው "ታዲያ አባቷ የት አለ ብቻችሁን?" አልኳት::

"እየመጣ ነው"

በቃ! ከዚህ በላይ የምፈልገው መረጃ የለም፤ ይቺ ሴት ለአጎቴ ሚስት መሆን አትችልም:: ትንሿን ልጅ ትንሽ አጫውቼያት ተለየዋቸው:: ከተለየዋቸው በኋላ በራሴ ድርጊት ፈገግ አልኩኝ::

ከደብረ ማርቆስ ክረምት ይልቅ የአዲስ አበባ ክረምት ፈጣን ነው ልበል? ወይስ ፈጥኖብኝ ነው? ብቻ ክረምቱ በፍጥነት አለቀ:: የሚኒስትሪ ውጤት ወጣ:: ከእኛ ክፍልም ሆነ ከት/ቤቱም ከተፈተኑት የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አንድም የወደቀ ተማሪ አልነበረም:: ሁላችንም አለፍን:: ያ ሰነፍ እንኳ ኮርጆ በከፍተኛ ውጤት አለፈ:: በዚያው ት/ቤት የዘጠነኛ ክፍልን ት/ት ጀመርን:: የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት እንደተለመደው እኔ አንደኛ ወጣሁ:: ያ ትልቅ ጭንቅላት ያለው ተማሪ ሁለተኛ ወጣ:: ሚያዚያ 25 ላይ 15 ዓመት ሞላኝ

አጎቴ የልደት ቀኔን አላከበረልኝም:: እኔም 100% ይህ እንደማይሆን እርግጠኛ ነበርኩ፤ ምክንያቱም እስከዛሬም አስቀድሜ እንደነገርኳችሁ አጎቴ የልደት ቀኔ ሲከበር ስጦታ ይሰጠኛል እንጂ ልደት ሲከበር አይወድም::

"ስንት ህዝብ በሚራብባት ኢትዮጵያ ውስጥ ልደት ማክበር ትልቅ ግፍ ነው" የሚል እምነት እና አባባል አለው፤ እናም የልደቴን ቀን እንደማያከብርልኝ አውቅ ነበር፤ ግን እንደተለመደው በልደቴ ቀን በነጋታው

"አስራ አምስት ዓመት ሞላሽ! አገርሽን ኢትዮጵያ ለማገልገል እየቀረብሽ ነው:: አየሽ የእኔ ልጅ እድሜሽ በጨመረ ቁጥር ትልቅ ሀላፊነት እንደሚጠብቅሽ እየተሰማሽ መምጣት አለበት! አገርሽ ኢትዮጵያ አንቺንም እውቀትሽንም ትፈልጋለች! አምላክሽ እውቀት እና ትልቅ ማስተዋል የሰጠሽ እንዲሁ በዋዛ አይደለም:: ለአገርሽ ኢትዮጵያ አንዳች ቀና ነገር እንድትሰሪበት ነው" በማለት በጣም የምታምር የአንገት ጌጥ እና መጽሐፍ ሰጠኝ::

ምን ዓይነት ነገር ነው እባካችሁ!? ልደቴ ካለፈ በኋላ ያቺን የተረገመች ትዕይንት የተከናወነባትን ቀን ሳልፈልገው ትዝ አለኝና ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ሳልተኛ አደርኩ:: አጎቴ እንዳይጨነቅ ግን አልነገርኩትም:: አጎቴ በጣም ደግ ሰው ነው:: በራሱ ዓለም ውስጥ የሚኖር ገለልተኛ ሰው:: እናም እንዲጨነቅብኝ ጨርሶ አልፈልግም:: ይህ በሆነ በሳምንቱ እሁድ ቀን አጎቴ ቤት ውስጥ አልነበረም:: የቤት ስራዬን ጨርሻለሁ:: ጥናቴንም ጨርሻለሁ:: እናም አጎቴ የመፅሐፍት ክፍል በመግባት የአጎቴን በርካታ መፅሐፍት መበርበር ያዝኩኝ:: ከብዙ ፍለጋ በኋላ አንድ ግድንግድ መፅሐፍ አገኘሁ:: በኢንግሊዘኛ የተጻፈ መፅሐፍ ነው:: አንድ ሺ ዘጠኝ ገፅ ያለው ግዙፍ የኢንግሊዘኛ መፅሐፍ ነው:: ባለማመን ግዙፍ የሆነውን መፅሐፍ ተመለከትኩ:: በእርግጥ ይህ ግዙፍ መፅሐፍ ለእኔ ትልቅ የምስራች ነበር:: በቀጥታ እኔን የሚመለከት ነበር:: የመፅሐፉ ርዕስ "Effects of Rape: Psychological and physical effects of rape" የሚል ነው:: ይህ ስለሚጠቅመኝ በፍጥነት ውስጥ የያዘውን ዝርዝር ርዕሶች ተመለከትኩ:: የተደፈሩ ወንዶች አዕምሮ፣ የተደፈሩ ሴቶች አዕምሮ፣ የተደፈሩ ህፃናት አዕምሮ፣ ለምን ደፋሪዎች ይደፍራሉ፣ መደፈር ምን ማለት ነው? በመደፈር የሚመጣ ሥነልቦናዊ ስብራት፣ በመደፈር የሚመጣ አካላዊ ስብራት... የተደፈሩ ሴቶች ታሪኮች... ወዘተ የሚል በርካታ ርዕሶች አሉት:: በታላቅ ጉጉት ለሁለት ሰዓት ያህል አገላበጥኩት፡ ስለመደፈር ታሪክ የሚጀምረው ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ላይ ካለው የትዕማር

በወንድሚ መደፈር ነው:: በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለችው ትዕማር የተባለች ልጅ በገዛ ወንድሚ ከተደፈረች በኋላ ስላለው ታሪክ ዝርዝር ነገር የለም ወይም መፅሐፍ ቅዱስም በቂ ዝርዝር ነገር አያስቀምጥም:: የመደፈር አደጋ የደረሰባቸው ሴቶች በርካታ ችግሮችን ማለፍ እንደሚጠበቅባቸው ያብራራል፤ በተለይ የተደፈሩ ሴቶች ከተደፈሩ በኋላ የሚከተሉትን ባህሪያት እንደሚያንጸባርቁ አልያም እንደሚከሰትባቸው ያብራራል:: የሥነልቦና ፍራቻ፣ የሥነልቦና ጥላቻ ፣ ምናልባት HIV በሽታ ፣ እርግዝና፣ የፌስቱላ በሽታ፣ በህይወት ቆይታቸው የረጅም እና የአጭር ጊዜ ፀፀት ፣ ይህ ነገር በእኔ ላይ ብቻ የሆነ ነው ብሎ ራስን አርከሶ ማሰብ፣ ከሌላዋ ሴት የእኔ ዋጋ የረከሰ ነው ብሎ ባልተፈላጊነት ስሜት መሞላት፣ ከሌላዋ ሴት አንጻር የመቆሸሽ ስሜት መሰማት፣ እንዴት ይህ ነገር በእኔ ላይ ይደርሳል ብሎ ሰርክ ማብሰልሰል ፣ ለወንዶች በሙሉ ጥላቻ እና እምነት ማጣት፣ በተለይ ህጻናት ከሆኑ የፌስቱላ በሽተኛ መሆን፣ የመነቃቃት ስሜት ማጣት ወይም በግዴለሽነት መሞላት፣ ስሜት አልባነት፣ ብቸኝነትን መምረጥ፣ ቁጠኛ መሆን፣ በቀላሉ መበሳጨት ፣ የሀጢያተኝነት ስሜት፣ የተጠቂነት ስሜት ፣ ራስን ለማጥፋት መነሳሳት፣ የበቀል ስሜት፣ የድብርት በሽታ፣ በተለይ ከወሲብ ጋር በተያያዘ የመደፈር አደጋ የደረሰባቸው ሴቶች በሶስት ምድብ በማስቀመጥ ይዘረዝራቸዋል::

ሀ. ስሜት አልባዎች
ለ. እንከን አልባዎች
ሐ. ዝሙተኞች

በማለት ሲያስቀምጣቸው ስሜት አልባዎች የሚባሉት ወሲብ ለማድረግ በሚዘጋጁበት ጊዜ ያን ትዕይንት ብልጭ አድርጎ አዕምሮያቸው ስለሚያስታውሳቸው ያ አስቀያሚ ድርጊት አሁንም በድጋሚ በህይወታቸው ላይ እየተከናወነ ስለሚመስላቸው ስሜት ውስጥ ጨርሰው ስለማይገቡ እና እምሳቸው እርጥበት ስለሌለው እና ደረቅ ስለሚሆን ከፍተኛ ህመም የሚሰማቸው፣ ወሲብ ቢያደርጉም ምንም ዓይነት የእርካታ ስሜት የሌላቸው አልያም ከማንም ሰው ጋር ወሲብ ለማድረግ የማይፈልጉ ናቸው:: እንከን አልባዎች የሚሰኙት ደግሞ ቀና አዕምሮ ያላቸው እና ሁሉን ነገር ረስተው የተለመደውን ጤናማ ህይወት መኖር የሚችሉ ጠንካራ አዕምሮ ያላቸው እና ይቅር ባይነትን የተላበሱ፣ ልባቸው ውስጥ አስቀያሚውን የመደፈር አደጋ የማያስቀምጡ፣ ሁሉም ወንዶች አንድ አለመሆናቸውን የሚያምኑ ሴቶች ናቸው:: እነዚህ በወሲብ ይሁን በፍቅር ጉዳይ ላይ ምንም የሚደርስባቸው ችግር የለም::

የደረሰባቸውን ነገር አንድ ጊዜ የተከሰተ ኢጋጣሚ ነው በማለት ይረሱታል፤ ባይረሱትም አምነው በመቀበል ህይወታቸውን ያስተካክላሉ:: በምድብ ሶስት የተቀመጡት ዝሙተኞች ሲሆኑ እነዚህ በደረሰባቸው የመደፈር አደጋ ከአንድ ወንድ ጋር መቆየት በጣም ስለሚያንገሽግሻቸው ከብዙ ወንዶች ጋር መማገጥ የሚያረካቸው፣ ለማንም ወንድ በቀላሉ የሚተኙ፣ ራሳቸውን ለመርሳት የሚጠጡ፣ የሚያጨሱ፣ የሚቅሙ፣ ርካሽ ሴት የሚሆኑ፣ ለወሲብ ሲሉ ብቻ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት ውስጥ እንዲገቡ ሴይጣን እና ውስጣቸው የሚገፋፋቸው እና ህይወታቸውን በሙሉ ወንድን ባለማመን የሚኖሩ እንዲሁም መላ ህይወታቸውን በተለያዩ ሱሶች የታጠሩ የሚሆንባቸው ናቸው:: በማለት በዝርዝር ያስቀምጣቸዋል:: ከዚው ከዝሙተኞች ጋር በማያያዝ የተደፈሩ ሴቶችም ሆኑ የተደፈሩ ወንዶችም የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉም በበርካታ ጥናቶች የተደረሰባቸውን ምሳሌዎች እያጣቀሰ ትልቁ የኢንግሊዝኛ መፅሐፍ ያብራራል:: ሴት ከሆነች ሌዚቢያን ወንድ ከሆነ ግብረሰዶም ሊሆኑ እንደሚችሉ በተለይ የተደፈረ ወንድ መልሶ ሊደፍር እንደሚችል በምሳሌዎች ያብራራል፤ እንዲሁም አንዳንድ የተደፈሩ ሴቶች ገንዘብ ካላቸው የደፈራቸውን ወንድ ገንዘብ ከፍለው ግብረሰዶማዊያንን ፈልገው እንደሚያስደፍሩት በምሳሌ ጭምር ያብራራል፤ በተለይ በአንድ ሺ የብራዚል ሴቶች ላይ በተደረገ ጥናት መሠረት ይህ ውጤት መገኘቱን ይጠቁማል:: በጥናቱ ላይ የተመረጡት አንድ ሺ ሴቶች በአንድ ወንድ እና በብዙ ወንዶች የተደፈሩ ሴቶች መሆናቸውን ያብራራል:: የጥናቱ ውጤት የሚከተለውን መሆኑንም ይዘረዝራል:: ከአንድ ሺ ሴቶች:-

- 6% ሴሎችን ለመርዳት ስለመደፈር አስከፊነት ሰባኪ እና አስተማሪዎች ሆነዋል (60 ሴቶች)
- 8% የደፈራቸውን ወንድ ቀን ጠብቀው ገድለውት እስር ቤት ገብተዋል (80 ሴቶች)
- 2% የደፈራቸውን ወንድ በግብረሰዶማዊያን ብር ከፍለው አስደፍረዋል (20 ሴቶች)
- 1% ስለመደፈራቸው ምንም የማያስታውሱ አዕምሮያቸውን የሳቱ እብዶች ሆነዋል (10 ሴቶች)
- 1% ከደፈራቸው ሰው ጋር በፍቅር ወድቀው የደፈራቸውን ወንድ ለማግኘት

ተንከራታች ሆነዋል (10 ሴቶች)

- 3% በሚገርም ሁኔታ በድጋሚ መደፈር የሚፈልጉ እና ያን ስሜት በድጋሚ ለማግኘት መሻት ያላቸው ሆነዋል (30 ሴቶች)
- 24% በጥላቻ የተሞሉ፣ በብቸኝነት የተሞሉ፣ ወንድ ባለማመን የተሞሉ፣ ተጠራጣሪዎች፣ ማንንም ወንድ የማያምኑ ሆነዋል (240 ሴቶች )
- 2% ሌዚቢያን ሆነዋል (20 ሴቶች)
- 40% በሀይማኖታዊና ስነልቦናዊ ምክር ታግዘው ትዳር ይዘው፣ ልጅ ወልደው፣ ጤነኛ ህይወት ለመኖር ችለዋል (400 ሴቶች)
- 7% በከፍተኛ ድብርት ተዘፍቀው ራሳቸውን ገድለዋል (70 ሴቶች)...

በማለት የተገኘውን የጥናት ውጤት ያስቀምጣል:: በዚህ 1000 ሴቶች ላይ የተደረገውን ጥናት አጠቃላይ ውጤት ብንመለከት 46% (460) ሴቶች ህይወታቸው ቀና ሲሆን 54% (540) ሴቶች ህይወታቸው በመደፈር የተነሣ የተበላሸ መሆኑን ጥናቱ ያስገነዝባል ማለት ነው:: በአገራችን ኢትዮጵያ ሴቶች ላይ ይህ ጥናት ቢጠናስ ውጤቱ ምን ይሆን? ለማንኛውም በዚው ግድንግድ መፅሐፍ ውስጥ ከዓለም ዙሪያ የተሰባሰቡ የመደፈር ታሪኮችንም አካቷል:: አንዳንድ ታሪኮች ዘግናኝ ናቸው:: አንዳንድ ታሪኮች ደግሞ አስደሳች ናቸው:: እናም ታሪኮቹ ስለመሰጡኝ ለተጨማሪ ሁለት ሰዓታት አነበብኩ:: የመደፈር አደጋ በማንም ሴት ላይ፣ በማንኛውም አጋጣሚ፣ በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ሊደርስ የሚችል ሀቅ መሆኑን አወኩ:: በዓለማችን ላይ በ29 ደቂቃ ልዩነት ውስጥ አንዲት ሴት ይሁን አንድ ወንድ ላይ የመደፈር አደጋ እንደሚደርስ አሁን ገባኝ:: በዚህ ግዙፍ ጥናታዊ መጽሐፍ ውስጥ ካነበብኳቸው ታሪኮች ውስጥ እንደው ለምሳሌ ያህል ብቻ እነዚህን ታሪኮች ላቋድሳችሁ:-

ኬኒያዊት ወጣት

ኬኒያዊት ውብ ወጣት በ15 ዓመቷ ከት/ቤት ስትመለስ በሰባት ወንዶች ተደፈረች:: የ HIV በሽተኛ ሆነች:: በዚህ የተነሣ በከፍተኛ በቀል እና የወንዶች ጥላቻ ተሞልታ ስለነበር ከ19-28 ዓመቷ በሚያፈዘው ውበቷ በመታገዝ ወንዶችን በማደን 1564 ወንዶችን ያለኮንዶም ወሲብ በማድረግ ሆንበላ በHIV በሽታ ከበከለች በኋላ ራሷን ለህግ አሳልፋ ሰጠች::

ማሊያዊት ወጣት

"... የደፈረኝ ሰውዬ እስር ቤት አስር ዓመት ተፈርዶበት በስድስተኛው ዓመቱ በአመክሮ እና ባሳየው መልካም ጸባይ ተፈታ:: መታሰሩም ሆነ መፈታቱም ምንም ስላላረካኝ ቀን ጠብቄ ሁኔታዎችን አመቻምቼ ገደልኩት:: ብልቱን ቆርጬ ጠብሼ በላሁት:: እጄን ራሴ ለህግ ሰጥቼ አሁን እስር ቤት እገኛለሁ:: በሰራሁት ስራ አሁን ድረስ ፀፀት አላደረብኝም:: በሰራሁት ጠላትን የመበቀል ድርጊት አሁንም ኩራት ይሰማኛል:: ለተደፈሩ ሴቶች የምመክረው የደፈራቸውን ወንድ የገቡበት ገብተው መልሰው እንዲገድሉት ነው:: እንደ እኔ ግን ተሸውደው በገዛ ፍቃዳቸው እጃቸውን ለህግ እንዳይሰጡ..."

ብራዚላዊት ወጣት

በአባቷ እና በወንድሟ እምሷንም ቂጧንም የተደፈረችው የብራዚላዊት ወጣት ታሪክ አስደናቂ ነው:: ይቺ ብራዚላዊት ወጣት ያን የደረሰባትን አስቀያሚ ትዕይንት አሸንፋ የሥነልቦና ዶክተር በመሆን በርካታ ሴቶችን በመርዳት ላይ ትገኛለች:: የደረሰባትን ሊታመን የማይችል ዘግናኝ ታሪክ ሳትፈራ በመናገር ለወጣት ሴቶች "ምንም ይፈጠር ምንም ማሸነፍ ይቻላል" እያለች ትሰብካለች:: አሁን በብራዚል እውቅ ሀኪም እንደሆነች ታሪኳ ያብራራል:: ይቺ ሴት እንግዲህ ከተዘረዘሩት ሶስት ምድቦች ምድብ ሁለት ነች ማለት ነው::

ናይጄሪያዊት ወጣት

"... እንቅልፍ ያለመተኛት እና ማታ የመለፍለፍ ችግር ስላጋጠመኝ ይህ የሴይጣን ሴራ ነው በፀሎት ይከሽፋል በማለት እናቴ ሰፈራችን ውስጥ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ወሰደችኝ:: ከአንድ ዝነኛ ሰባኪ ጋር አወሩ:: ለብቻዬ ፀሎት ሊያደርግልኝ የሆነ ጭር ያለ ክፍል ውስጥ አስገባኝ:: ሰውየው በጣም ታዋቂ ሰባኪ በመሆኑ ይህን ያደርጋል የሚል ግምት ጨርሶ አልነበረኝም፤ ግና ገና የ12 ዓመት ልጅ እያለሁ በግድ ደፈረኝ:: ከዚያ ወንዶች የሚባሉ ሁሉ አስጠሉኝ! ቤተክርስቲያን መሄድ አስጠላኝ፤ በተለይ ሰባኪ የሚባሉ ወንዶችን ማየት አልሻም:: ይህን አስቀያሚ ታሪክ ሰፈር ውስጥ እንዳይወራ ለእናቴ እንኳ አልነገርኳትም፤ በዚያ ላይ ያ ታዋቂ ሰባኪ ብትናገሪ አንቺንም እናትሽንም በእሳት አቃጥላቹዋለሁ!" በማለት በጣም አስቦኩቶኝ ነበር..."

ታንዛንያ

"... ቤታችን እሁድ እሁድ የሚመጣ ቄስ ነበር:: ይህ ቄስ አንድ እሁድ የእናቴን

ቤት አለመኖር አውቆ በ14 ዓመቴ ደፈረኝ:: ይህን ነገር ለእናቴ ብነግራትም ለማንም እንዳልናገር አስገደደችኝ:: እናቴ ለእኔ ሳይሆን ለራሷ ክብር የምትጨነቅ ሴት ነበረች:: እንደ እኔ ብዙዎች የመደፈር አደጋ የደረሰባቸው ሴቶች ዝም እንዲሉ እንደሚደረጉ እገምታለሁ፤ ይህ ግን መሆን የለበትም! ይህን ጉዳይ ለሴቶች ጉዳይ ማሳወቅ ተገቢ ነው:: ማንም ይሁን ማንም ወንጀል የሰራ መቀጣት አለበት:: ዛሬ እኔ ህግ ለጠማቸው ሴቶች ፍርድ ለመስጠት እና እንባቸውን ለማበስ ከአጠገባቸው ለመቆም በአገሬ ታዋቂ ጠበቃ እና የሴቶች መብት ተከራካሪ ሆኛለሁ!!"

ኩዌት

"... እናቴ ዱሪዬ ሴት ናት:: ከአባቴ በተጨማሪ አባቴ ለንግድ ብዙ አገራት እንደሚዘዋወር ስለምታውቅ በርካታ ወንዶችን ታወጣለች:: ለምሳሌ የሙዚቃ አስተማሪዬ ቤት እየመጣ እኔን ሙዚቃ ከማስጠናት በተጨማሪ የእናቴ ቅምጥ እንደሆነ አውቃለሁ:: አንድ ጊዜ እናቴ ቤት ውስጥ አልነበረችም፤ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የ11 ዓመት ልጅ እያለሁ ለነገሩ ለእናቴ ብነግራት ለእናትሽ ብትናገሪ እገልሻለሁ በማለት አስፈራርቶኝ ደፈረኝ፤ አታምነኝም ነበርና ዝም አልኩ:: በሶስተኛው ቀንም ጨንቄ የሚባል ህመም እንዳይዝሽ በማለት የሙዚቃ አስተማሪው በድጋሚ ደፈረኝ:: ትልቅ ሆኜ እገለዋለሁ በማለት ዛትኩ፤ እናም አደኩ:: አጠናሁት:: የሁለት ልጆች አባት ሆኖ ነበር:: ከእነ ቤተሰቡ እሳት ለኮስኩባቸው:: ሁሉም በእሳቱ ተቃጥለው ሞቱ:: አንጀቴ በደስታ ቅቤ ጠጣ:: ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው ግን አዕምሮዬ ሰላም የለውም:: እኔ ለተደፈሩ ሴቶች የምመክረው ጉዳዩን ለህግ ማሳወቅ ይሻላል እንጂ በግል በቀል መፈፀም መጨረሻው የማያልቅ ፀፀት ብቻ መሆኑን እንዲያውቁት ነው"

ህንዳዊት ወጣት

"... ምንም የክርስትና እምነት ተከታዮች ብንሆንም ህይወታችን ግን የቆሸሸ ነበር:: አባቴን አላውቀውም:: እናቴ ሴተኛ አዳሪ ነች:: ገንዘብ ለማግኘት ከተለያዩ ወንዶች ጋር የወሲብ ንግድ ትሰራለች:: አንድ ጊዜ እናቴ ከአንድ ሽማግሌ ጋር ወሲብ ካደረጉ በኋላ ሽማግሌው አለመርካቱን ነገራት:: እናቴ 600 ዶላር የሚከፍል ከሆነ ድንግል ሴት እንደምታመጣለት ነገረችው::

"ስንት ዓመቷ ነው?"

"አስር"

"አትዋሺ!?"

"ሀቂን ነው" አለችው:: ሸማግሌው ተስማማ:: ገንዘቡን ሰጣት:: እናቴ ጠራችኝ:: እጄን በመያዝ መሬት ላይ ጣለችኝ:: የቻልኩትን ያህል በልጅነት ጉልበቴ ራሴን ለማስጣል ተፍጨረጨርኩኝ ፤ ግን አልቻልኩኝም:: እናቴ ለ600 ዶላር ብላ አይኗ እያየ ገና በአስር ዓመቴ አስደፈረችኝ:: የነበረውን ስቃይ እና የነበረውን ህመም እንዴት በቃል ለማስቀመጥ እችላለሁ? እንዴትስ ያን ስቃይ ልረሳው እችላለሁ?"

ኢትዮጵያዊት ወጣት

"... ከልጅነቴ ጀምሮ ፊልም እወድ ነበር:: ወጣት ስሆን ፊልም የመስራት ታላቅ ጉጉት አደረብኝ:: የመጀመሪያ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ ፊልም የመስራት ህልሜን እውን ለማድረግ በሰው በሰው የሞባይል ቁጥሩን አግኝቼ አንድ ዝነኛ ፊልም አሰሪ ታዋቂ ሰው ጋር ደወልኩ

"ስልክህን የሰጠኝ ሰው ነበር"

"እሺ ምን ልርዳሽ?"

"ፊልም ለመስራት ታላቅ ጉጉት አለኝ"

"ስለ አክቲንግ ተምረሻል?"

"አይ እኔ የመጀመሪያ ዓመት የአካውንቲንግ ተማሪ ነኝ፤ ግን ስለ ፊልምም ሆነ አክቲንግም ፍቅሩ ስላለኝ በሚገባ አውቃለሁ! የተለያዩ ትያትሮችን እየሰራሁ ራሴን ፈትሻለሁ"

"እስቲ ለማንኛውም ፊልም ላይ ያለሽን መሻት መነሻ በማድረግ ያለሽን ችሎታ ለማወቅ አጠር ያለ የሙከራ ቀረፃ እናከናውንልሽና እዛ ላይ አሪፍ ከሆንሽ ቀጥለን ለምንሰራው ፊልም ልንመርጥሽ እንችላለን"

"በጣም አመሠግናለሁ እና መቼ ልደውል?"

"የት ነው መኖሪያሽ?"

"አዲስ አበባ ለቡ"

"በጣም ጥሩ! ከአምስት ቀን በኋላ እደውልልሻለሁ" በማለት ተለያየን:: በጣም ነበር የተደሰትኩት:: አራቱ ቀን እስከሚያልፍ ከፍተኛ ልምምድ ሳደርግ ነበር:: እንዳለው ታዋቂው ፊልም አሰሪ በአራተኛው ቀን ቃሉን ጠብቆ ደወለልኝ:: ስሜን ማዘጋጃ ቀጠረኝ:: መኪናው

ውስጥ አስገባኝ፡፡ እኔም በህይወቴ የአገሪቱን ዝነኛ ፊልም አሰሪን በማግኘቴ እና እንዲሁ በቀላሉ አጠገቡ ለመቀመጥ ስለቻልኩ እና አጋጣሚውን ጨርሶ ባለማመን በጣም ደስ አለኝ፡፡ ራሴን እንደ እንዲት እድለኛ ቆጠርኩት፡፡ እያወራን አንድ የሚያምር ግቢ ገባን፡፡ "እንዲት የምትደፈር ሴት ገጸባህሪን ትሰሪያለሽ! ያቺን ሴት ለመሆን የምታሳይው ጥረት ወሳኝ መሆን አለበት! እንዳንቺ በርካታ ፊልም ለመስራት ፍላጎት ያላቸው እያሌ ተወዳዳሪዎች ስላሉብሽ መብለጥ ግድሽ ነው" በማለት እንዳነብ ወረቀት ሰጠኝ፡፡ በሚገባ አጠናሁት፡፡ የሆነ ትልቅ የሚያምር መኝታ ቤት ውስጥ አስገባኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ያጋጠመኝ ግን የሙከራ ቀረፃ አልነበረም፡፡ እውነተኛው የመደፈር አደጋ ነበር፡፡ ድንግሌን በግድ ወሰደብኝ፡፡ ልከሰው ፈልጌ ነበር፤ ግን ለቤተሰቦቼ ጭንቀት ከምፈጥር በማለት ፈራሁ፡፡ "አንቺ ማን ስለሆንሽ ብቻሽን እንደበሬ እየተንተተሽ ሄድሽ ? ባትፈልጊ እየተነዳሽ አልጋ ቤት ውስጥ አትሄጂም ነበር..." ወዘተ እንደምባል ገባኝ፡፡ ተከብሬ በኖርኩበት ሰፈር በታዋቂው ፊልም ሰሪ ተደፈረች የሚባል ወሬ እንዳይወራብኝም ፈራሁ፤ እናም ስሜን ለመጠበቅ ስል በዝምታ ተቀመጥኩ፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ስመረቅ አንድ በጣም የሚወደኝ ፍቅረኛዬ "እስከምትመረቂ ጠብቄሻለሁ አሁን ወሲብ እናድርግ" በማለት የወሲብ ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡ በእኔ ላይ ስለደረሰው የመደፈር አደጋ ምንም ሳልዋሸው ነገርኩት፡፡ ያ ይረዳኛል! ያ ይወደኛል! ያ ማሬ ማሬ! ያ ህይወቴ ህይወቴ! ያ ካንቺ ውጪ መኖር አልችልም! ያ አንቺ የእኔ ብርሃን ነሽ! የሚለው ፍቅረኛዬ የግል ሚስጥሬን ካወቀ በኋላ ሸሸኝ፡፡ በአራት ነጥብ ዘጋኝ፡፡ የእውነት ከደፈረኝ ታዋቂ ሰው ይልቅ ትልቅ ስብራት የደረሰብኝ በፍቅረኛዬ ነበር፡፡ ይወደኛል ያልኩት ፍቅረኛዬ ስላላመነኝ ቅስሜ ይበልጥ ተሰበረ፡፡ ከዚያ በኋላ እንዴት እንደሆነ ባላውቅም በተመረኩበት አካውንቲንግ ሙያ ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳይሆን ራሴን ያገኘሁት ቦሌ ከሚገኝ አንድ ዝነኛ የሴተኛ አዳሪዎች ቤት ውስጥ ነበር..."

ቤልጄሚያዊት ወጣት

"... ከት/ቤት ስመለስ ሶስት ሰዎች በመኪናቸው ጭነው ወስደው ደፈሩኝ፡፡ ሀቁን ለመናገር አሰቃቂ እና መቼም የምረሳው ሁኔታ አይደለም፡፡ ከዚያ በኋላ ወሲብ ሳደርግ ያመኝ ነበር፡፡ ወንዶችን እፈራ ነበር፡፡ ይህን ችግሬን የሚያውቅ መልካም ሰው ወንዶች ሁሉ አንድ አለመሆናቸውን አሳወቀኝ፡፡ ፍቅር ሰጠኝ፡፡ ፍቅር መገበኝ፡፡ ያን መልካም ሰው አገባሁ፡፡ አሁን አራት ልጆች አሉኝ፡፡ በህይወቴም ደስተኛ ነኝ፡፡ እነዚያን ሶስት ሰዎች ይቅር ለእ/ዜር

ብያቸዋለሁኝ፤ ምክንያቱም ቂም መያዝ በራስ ውስጥ የእሳት ቦንብ ማስቀመጥ እና ራስን በምላጭ የመቆራረጥ ያክል ነው፤ በዚያ ላይ እኔ እነዚያን ሰዎች ይቅር ካላልኩኝ እ/ር እንዴት የእኔን ሀጢያት ይቅር ሊለኝ ይችላል? በእርግጥ አስቸጋሪ ቢሆንም ይቅርታን የመሰለ አስደሳች በቀል የለም...!!"

አሜሪካዊት ወጣት

"... የእኔ አጋጣሚ ይገርማል:: ሁለት ሆነው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ደፈሩኝ:: ለምን ይህ ነገር በእኔ ላይ ሆነ በማለት ታላቁ ፈጣሪን ጠየኩት? ለምን እኔ ምስኪኗን ከእነዚያ አውሬዎች አላዳንከኝም በማለት ፈጣሪን ጠየኩት? ታላቁ ፈጣሪ የለህም ማለት ነው? እያልኩ አማርር ነበር ... ቢሆንም ሁሉን ነገር ትቼ ጠንክሬ መማርን መረጥኩ:: ተሳካልኝ:: ሀኪም ሆንኩ:: ዶ/ር ሆኜ ከዘመናት በኋላ በሚደንቅ ገጠመኝ የደፈሩኝ ሰዎች እኔ ህክምና የምሰጥበት ሆስፒታል ውስጥ የመኪና አደጋ ደርሶባቸው ሁለቱም መጡ:: ወዲያው ነበር ያስታወስኳቸው! እንዴትስ ልረሳቸው እችላለሁ? እንዴትስ ልዘነጋቸው እችላለሁ? መጀመሪያ ውስጤ ተፈታተነኝ "ግደያቸው! ግደያቸው! ጨርሺያቸው! ጨርሺያቸው" አለኝ፤ ግን ፈጣሪ ይቅጣቸው! ፈጣሪ የዘሩትን ያሳጭዳቸው በማለት በቀል የፈጣሪ ነውና እኔ የሚጠበቅብኝን ትክክለኛውን ነገር በማድረግ ህክምና ሰጠዋቸውና ድነው ከሆስፒታሉ ወጡ! በጣም የሚደንቀው ግን ሁለቱም ከሰባት ቀናት በኋላ በድንገት በትልቅ መኪና ተገጭተው ተጨፈላልቀው መሞታቸውን ሰማሁኝ:: አይ ፈጣሪ እኔ ጋር ከመሞታቸው በፊት የመጡት ይህን እንዳይልኳቸው ይሆን እያልኩ እገረማለሁ..."

ያን ግድንግድ መፅሐፍ የዚያን ዕለት የቻልኩትን ያህል አገላበጥኩት:: በእርግጥ ግድንግዱ መጽሐፍ የሚሰብከው ስለ ይቅርታ ማድረግ ነው:: የተፈጠረውን እውነታ ስለመጋፈጥ ነው:: እውነታውን ማሸነፍ የሚቻለው ስለ እውነታው ባለማሰብ፣ ስለ እውነታው ባለማወቅ፣ ስለ እውነታው በጭፍን ለመርሳት በመሞከር ሳይሆን እውነታውን ሙሉ ለሙሉ ፊት ለፊት ስለ መጋፈጥ ይመከራል:: ከዚያ ይቅርታ በማድረግ ህይወትን በአዲስ መልኩ ለመጋፈጥ መዘጋጀት ብቸኛው አማራጭ መሆኑን በአብይነት ይሰብካል:: ለምሳሌ ዓለም ላይ

ያሉት ወንዶች ሁሉ ደፋሪዎች አይደሉም:: ዓለም ላይ ያሉት ወንዶች ሁሉ መጥፎዎች አይደሉም:: ዓለም ላይ ምርጥ አፍቃሪ ወንዶችም አሉ:: አለም ላይ ብርሃን እንዳለ ጨለማም አለ:: ይህን ሊደበቅ የማይችል እውነታ በሚገባ በመረዳት ህይወትን መዋጀት ተገቢ መሆኑን ይተነትናል:: አለበለዚያ ስለተፈጠረው አስቀያሚ ትዕይንት ሁልጊዜ ማብሰልሰል መልሶ የሚጎዳው ደፋሪውን ሳይሆን ተደፋሪውን መሆኑን ይናገራል:: እውነታውን መቀበል እና ይቅርታ ማድረግ ምርጥ ቁልፎች መሆናቸውን ይተነትናል... ይህን ግድንግድ መፅሐፍ በሚገባ እንብቤ ለመጨረስ በመወሰን ለጊዜው ከቦታው መልሼ በማስቀመጥ ወደ ሳሎን ተመለስኩ:: ሳሎን ተመልሼ ብዙም ሳልቆይ አጎቴ በፈገግታ ተሞልቶ መጣ::

"የእኔ ልጅ ጥዬሽ ጠፋሁ አይደለም?" አለኝ::

"በጣም" አልኩት:: በእርግጥ አጎቴ ቤት ቢኖር ኖሮ ያን ግድንግድ መፅሐፍ ላላነብ እችል ነበር:: በአጋጣሚዎች መከፋት ሳይሆን በአጋጣሚዎች መጠቀም እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ ::

"አንድ እስር ቤት አብሮኝ ታስሮ የነበረ ወዳጄን አግኝቼ ከእርሱ ጋር ስለ እስር ቤት ትዝታችን ስናወራ ሳናስበው ሰዓቱ ቀለጠ:: አንቺ ውሎሽ እንዴት ነበር?"

"አሪፍ ነው:: በቃ ዛሬ በአጋጣሚው ስለ እስር ቤት ህይወትህ ትነግረኛለህ?"

"እሺ እነግርሻለሁ:: ትንሽ ወክ እናድርግና የሆነ አሪፍ ቤት ተቀምጠን እየበላን እናወራለን መንቀሳቀስ ለጤናም አሪፍ ነው:: አዕምሮንም ፈታ ለማድረግ አሪፍ ነው"

"በጣም ደስ ይለኛል"

ከአጎቴ ጋር ተያይዘን ወጣን:: ህይወት የመግባት እና የመውጣት ቅንብር ነች:: ህይወት የመቀመጥ እና የመነሳት ቅንብር ናት:: ህይወት የመሄድና የመቆም ቅንብር ናት... ህይወት የአንድ ነጠላ ነገር ቅንብር ሆና አታውቅም:: ህይወት ምንጊዜም የሁለት ነገሮች፣ የሁለት ተፃራሪ ፣ የሁለት ተቃራኒ ነገሮች ቅንብር ናት... ይህ የህይወት ትልቁ እውነታ ነው::

የዓመቱ ትምህርት አለቀ:: በክረምት ያን ግድንግድ መፅሐፍ ጨረስኩት:: ብዙ ጠቃሚ ነገሮች አገኘሁበት ፣ በተለይ እውነታውን መጋፈጥን:: ተደፍሬያለሁ:: እርግጥ

መደፈሬ አሰቃቂ ነበር፡፡ ለዚያውም የደፈረኝ የገዛ አባቴ ነው፡፡ ከአባቴ ሌላ ሌሎችም ወንዶች ነበሩ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው አባቴ ለገንዘብ ካለው አምልኮት የተነሣ ራሱን ለአጉል እምነት ጥንቆልና አሳልፎ በመሸጡ ነው፡፡ የአባቴ ሀብት ይበረከትለት ዘንድ የእኔ ደም ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ እኔ ለአባቴ የመስዋዕት በግ ነበርኩ፡፡ አባቴ በመሪጌታው ተተብትቦ ነበር፡፡ በገንዘብ ፍቅር ሰክሮ ነበር፡፡ ልጁን ከገንዘብ አሳንሶ ነበር እና መጨረሻው ምን ሆነ? ያን የተመኘውን ገንዘብ አገኘ? በእናቴ ጥይት ተበረቀሰ.. የአጉል እምነት መጨረሻው ይህ ነው፡፡ ጠንቋይ ዳቦ ይሰጣል ! ሴይጣን ዳቦ ይሰጣል! ዳቦውን ግን እንድትበሉት አያደርግም! እንደውም እንድትበሉት ቢያደርግ ራሱ ዳቦው ውስጥ መርዝ ይከትበታል! ይህ የሴይጣን ባህሪ መሆኑን በአባቴ ድርጊት በሚገባ ለመረዳት ችያለሁ...

በክረምቱ ሌሎች በርከት ያሉ የተለያዩ እውቀቶችን የሚሰጡኝን መፅሐፍትንም ለማንበብ ቻልኩኝ፡፡ ከንባብ በተጨማሪ የጀመርኩትን የፒያኖ ትምህርት እና ካራቴ ትምህርት በሚገባ ቀጠልኩበት፡፡ በዚያው ሂደት ለአንቴ ሚስት መፈለጉን ጨርሶ አልረሳሁትም፡፡ በእርግጥ ይህ በጣም አስቸጋሪው ነገር ነበር፡፡ የሚገርመው ግን አንዷት ሴት ህፃን ይዛ አየሄደች ሳይ በዓይኔ ከእነልጁ እከተላቸው ነበር፡፡ በዚህ ድርጊቴ እኔ ራሱ እንደ እብድ ብቻዬን በሣቅ እንከተከት ነበር... ብቻ ክረምቱም ሳይታሰብ በፍጥነት አለቀ... ህይወታችንም እንደዚህ በቀላል እንደምታልቅ ገባኝ፡፡ ይቺ ከንቱ ህይወት በእርግጥም ከንቱ እንደሆነች በሚገባ ህይወት ራሷ ስለ ከንቱነቷ ሹክ አለችኝ...!!

የአስረኛ ክፍል ትምህርት ተጀመረ፡፡ የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ደረሰ፡፡ ብሔራዊ ፈተና ስለ ነበር በሚገባ ነበር የማጠናው፡፡ ከክፍላችን ያን ግድንግድ ጭንቅላት ያለው ተማሪን በመብለጥ አሁንም አንደኛ ወጣሁ፡፡ ሁለተኛው ሴሚስተር ላይ ግን ያ ግድንግድ ጭንቅላት ያለው ልጅ በደስታ ፊቱ ሲያበራ ልመለከት ፈለኩና ሆን በማለት በሁለት ትምህርቶች ዝቅተኛ ውጤት አመጣሁ፡፡ በእርግጥ እቅዴ ተሳካና ልጁ አንደኛ ይወጣ ዘንድ ከፍተኛ እድል ተመቻቸለት! እናም በጣም ተደስቶ ሲንከተከት አየሁት፡፡ ፊቱ በደስታ ሲያበራ አየሁት፡፡ ይህን ሳይ ሰዎች ደስ እንዲላቸው ማድረግ ራሱን የቻለ ጥበብ እና በዚያ

ሰው ደስታ እኛ ራሱ መልሰን ልንደሰት እንደምችል ለመገንዘብ ቻልኩኝ፡፡ በጣም የደነቀኝ ግን የዚያች የምታስቀኝ ባለፈገግታዋ ጓደኛዬ ቤተል ነገር ነው፡፡ ያቺ ሁሌ በፈገግታ የምታሸበርቅ እና ከድምፄ ውበት የተነሣ ዘማሪ እንድሆን ሁሌ የምታበረታታኝ ቤተል በጣም እየሣቀች

"የእውነት በጣም ቀና ሰው ነሽ" አለች፡፡

"አልገባኝም?" አልኳት

"እኔ ገብቶኛላ! "በማለት ጉንጬን ሳመችኝ፡፡

"ምኑ?"

"ሆን ብለሽ የሆንን ተማሪ ለማስደሰት የሆነ ነገር አድርገሻል"

" ምን እያወራሽ ነው ቤተል?"

"እንደኛ እንዲወጣ እና ደስ እንዲለው ያደረግሽው ሆን ብለሽ ነው፡፡ በእርግጠኝነት እነዚያን ጥያቄዎች እንኳን አንቺ ማንም ቀሽም ተማሪ የማይስታቸው ጥያቄዎች ነበሩ፤ ግን እኔ ማወቅ የፈለኩት እና ሆዴን እየቦረቦረኝ ያለው ለምን የሚለው ነው? ለምን ይህን አደረግሽ? ደስ እንዲለው ብቻ ወይስ ይህን ግድንግድ ጭንቅላት ያለውን ልዑልን ወደሽው ይሆን? መቼም እኛ ሴቶች ምንም ነገር ያለ ምንም ምክንያት አንሰራም? ሳትዋሺ እውነቱን ተናገሪ? ነቅቼብሻለሁ ተናገሪ!" አለች ሁልጊዜ በሚያምረው ፈገግታዋ እያሸበረቀች፡፡

መዋሸት ስላልቻልኩ ዝም አልኩ፡፡ በሁለተኛው ሀሳብ ግን ሣቄ መጣ፡፡ ያን ግድንግድ ጭንቅላት ያለውን ልጅ የምወድበት አንዳችም ምክንያት የለኝም፡፡ ኧረ አስቤ ራሱ አላውቅም፡፡ ኧረ ስለወንድ ልጅ ማፍቀር አስቤ እንኳ አላውቅም፡፡ እንዴት የተደፈረች ሴት እንዲሁ በቀላሉ ስለወንድ ፍቅር ማሰብስ አያስቸግራትም?

"ግድንግድ ጭንቅላቱ ተመቸሽ?"

"በፍፁም! በጭራሽ አልወደድኩትም!" አልኳት፡፡

ቤተል በፈገግታ ተሞላች፡፡ በጣም ከሚገርመኝ የማይለወጥ ጸባይዋ ሁልጊዜ በፈገግታ የተሞላች መሆኗ ነው፡፡ ወደ ጆሮዬ ጠጋ በማለት "የሚገርምሽ አንድ ጊዜ ሽንት ቤት ሲሄድ ሆን በማለት ተከተልኩት፡፡ ሽንት ቤት ሲገባ እኔም የሴቶች ሽንት ቤት በመግባት በሚስጥራዊ ሁኔታ በቦረቦርናት ቀዳዳ ሽንቱን ሲሸና አየሁት! አንቺ የሚገርምሽ ግድንግድ ጭንቅላት ብቻ ሳይሆን ግድንግድ ቁላም ተፈጥሮ አድለዋለች! በጣም ነበር የደነገጥኩት! በሌላ በኩል ያ አንቺን በጣም የሚወድሽ እና የሚጀነጅንሽ ልጅ ደግም ሚጢጢዬ ብልት አለችው፡፡ ይቺን

ሚጢጢዬ ብልት ይዞ እኮ ነው ሴቶችን ለመጀንጀን ደፋ ቀና የሚለው፡፡ በፊት ሽንት ቤት አየገባሁ የወንዶችን ብልት ማየት ደስ ይለኝ ነበር፤ አሁን ግን በጣም አስጠላኝ፤ አንድ ነገር ግን ሹክ ልበልሽ?"

"እሺ"

"እሺ ሳይሆን በይኝ ነው የሚባለው"

"በይኝ"

"ሁልጊዜ የወር አበባዬ ካለቀ አራት ቀናት በኋላ በከፍተኛ የወሲብ ስሜት እናጣለሁ፡፡ ወሲብ አድርጊ! ወሲብ አድርጊ! የሚል ስሜት ይሠማኛል! ውስጤን ይበላኛል! በወሲብ አምሮት እቃጠላለው! ይህ ሀይለኛ ስሜት ሁልጊዜ የወር አበባዬን በጨረስኩ አራተኛው ቀን ይመጣል፤ በዚህ እየተቃጠልኩ ነው፡፡ ዝም ብዬ ሳስበው ግን ወሲብ ሳላደርግ እስከ አስራ ስምንት ዓመቴ ድረስ እንኳ የምቆይ አይመስለኝም፡፡ እቅዴ የነበረው ግን ድንግልናዬን ማስወሰድ የምፈልገው ልክ የ18 ዓመት ልደቴን ሳከብር ነው"

"እስከዛ ፍቅረኛ ባይኖርሽስ?"

"ለአንዱ እድለኛ አበረከትለታለዋ! እያንዳንዱ ድንግል ላይ የሚወስደው ቁላ ስም በጉልህ ተለጥፎበታል የሚል ጥቅስ አንብቤያለሁ፤ በዚህም አምናለሁ" አለች፡፡ ከራሴ ጋር ተነጋገርኩ፡፡ የእኔ ድንግል ላይ የአባቴ ስም ተለጥፎበት ነበር ማለት ነው? ይቺ ባለፈገግታ ሚስኪኗ ልጅ ቤተል በእኔ ላይ የደረሰውን ትእይንት አታውቅም፡፡ ምን አይነት አስቃቂ ሁኔታ ውስጥ ድንግሌን እንዳጣሁ አታውቅም፤ እናም ስለማታውቀው ወሲብ ታወራልኛለች፡፡ ስለወሲብ ሲወራ በተለይ ስለድንግልና ሲወራ ያን ትዕይንት ማስታወሴ አይቀርም፤ ግን መጋፈጥ እንዳለብኝ ውስጤን እያሳመንኩት ነው፡፡ አሜሪካዊ ሮዝ ፔሮት የተባለው ቦለቲከኛ አንዲት ድንቅ አባባል አለችው፡፡ "መናገር ቀላል ነው ቃላትም የተትረፈረፉ ናቸው፤ ተግባር ግን ውድና ብርቅ ነው" የምትል፤ እናም በህይወት ጉዞዬ ስለ ወሲብ ፣ ስለ ድንግል፣ ስለ መደፈር ፣ ብዙ ጊዜያት ይወራል፡፡ በተወራ ቁጥር ያን ትዕይንት እያስታወስኩ በትዝታ እሳት እየተቃጠልኩ ከምጨስ መጋፈጡን መርጬያለሁ፡፡ በእርግጥ እንደ እኔ የተደፈሩ ሴቶች ይህን መሰል ወሬ መስማት ያሳማቸው ይሆናል፡፡ ይዘገንናቸው ይሆናል፡፡ ቃርቃር ሊላቸው ይችል ይሆናል፤ ግን መጋፈጥ ነው፡፡ ከመሸሽ ይልቅ መጋፈጥ የተሻለ ነው፣ እናም የቤተልን ወሬ አላቋረጥኳትም፡፡ ቤተልም ወሬዋን ቀጥላለች፡፡

"ከእኛ ከፍል ወሲብ ማን እንደጀመረ ታውቂያለሽ?"

"አላውቅም!"

"እስቲ ገምቺ?"

"ከወንዶች? ከሴቶች?"

"መጀመሪያ ከሴቶች"

"መስቲ"

"በጭራሽ! ምንም ቀልቃላ እና ዘናጭ ብትሆንም ጠንቃቃ ናት! ምላስ ብቻ ነች!"

"እህ... ናርዶስ"

"አ! በእርግጥ ናርዶስ በጣም ትላልቅ ጡት ስላላት በተለይ ውሎዋ ከወንዶች ጋር ስለሆነ እና ከወንዶች ቂጥ ስር ስለማትጠፋ ወሲብ የጀመረች ብዙዎች ይመስላቸዋል፤ ግን እሷም በጣም ጨዋ ናት! ስለወሲብ እና ብልግና ታወራለች እንጂ አታስነካም፤ ምናልባት እያወራች ትረካ ይሆናል ፤ ያው በማውራት ብቻ የሚረኩ ወንዶችም ሴቶችም እንዳሉ ሳይንስ ስላረጋገጠ..."

"እሺ የመጨረሻ ግምቴ ሊዲያ"

"በቃ እኔ ልንገርሽ! ከእኛ ከፍል እኔ ባለኝ ተጨባጭ መረጃ ሁለት ወሲብ የጀመሩ ሴቶች አሉ:: አንደኛዋ ራሷን አንጀሊና እያለች የምትጠራዋ ከንፈሯ በጣም አስደማሚ ውበት ያለው እየሩስ ከንፈ. ስትሆን ሁለት የአስራ ሁለተኛ ከፍል ተማሪዎች እና ብሎኬት እያልን የምንጠራው ኬሚስትሪ አስተማሪያችን አውጥተዋታል:: ሁለተኛዋ ሴት የከፍላችን የጸባይ ተሸላሚ ቃልኪዳን ነች"

"አትዋሺ? ይህን ለማመን ያስቸግረኛል"

"ቅፅል ስሟ ናፖሊዮን ቦናፓርት ነው:: ዝነኛው ናፖሊዮን ከፍተኛ የሚጥል በሽታ ነበረበት:: ያን የሚጥል በሽታውን ለማስታገስ እና ጉዳቱን ለመቀነስ በብዛት ማሳጅ ይጠቀም ነበር:: የሚጥል በሽታ ያለባቸው ሰዎች ማሳጅ በብዛት መደረግ ለጤናቸው አሪፍ መሆኑን ሳይንስ እውቅና ሰጥቶታል:: ይቺ ቃል ኪዳን ያጋጣሚ ሆኖ የሚጥል በሽታ አለባት፤ በዚያ ላይ የደም ብዛትም ገና በዚህ ልጅነቷ አለባት ፤ በዚህ የተነሣ ገና የ14 ዓመት ልጅ እያለች ነበር ወሲብ የጀመረችው:: የእውነት ቀርበሻት የግል ህይወቷን ብትሰሚያት በጣም ታዝኚላታለሽ:: ገና በልጅነት ህይወቷ የመከራን ሸከም እየተሸከመች ትገኛለች:: እንደ እናቴ ገለፃ የሚጥል

በሽታ የአጋንንት ስራ ነው:: ቤተሰቦች የሚሠሩት ሀጢያት ለልጃቸው ይተርፋል:: በእናት እና በአባት ሀጢያት ልጅ እና የልጅ ልጅ ይቀጣል:: የሚጥል በሽታ የነበረበት ሰው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ አድኖታል:: የሚጥል በሽታ በሳይንስ እና በመድኃኒት ብዛት ሳይሆን በኢየሱስ ይድናል በማለት ነግራኛለች:: በሌላ በኩል ይቺ ልጅ በሽታዋን ለማስታገስ በተደጋጋሚ ወሲብ ታደርጋለች፣ ፀጉሩዋን በየጊዜው ሳያድግ ቶሎ ቶሎ ትቆረጣለች፤ ለዚህ ነው ሁልጊዜ እንደ ወንዶች ፀጉሯን የማታሳድገው ብቻ በጣም ነው የምታሳዝነኝ ፤ ይህ ሁሉ እያለባት በጣም የሚገርም ምርጥ ፀባይ አላት"

"ወሲብ እና የሚጥል በሽታ ግን ምን አገናኘው?"

" ስለዚህ ጉዳይ ለማወቅ ፈልጌ ያን የዶክተር ልጅ ነኝ እያለ ጉራውን የሚቸበችበውን አባቱን ስለዚህ ጉዳይ እስቲ አባትህን ጠይቀህ ና ስለው ዛሬ ነገ ነገ ዛሬ እያለ ጢባሩን ሲነዛብኝ ከፈለከ ተወው አልኩት:: ከዚያ ይህን ጉዳይ ለማወቅ ጉጉት አደረብኝና ሰፈራችን የሚገኝ አንድ መድኃኒት መሸጫ ቤት በመግባት ስለ ወሲብ እና የሚጥል በሽታ ቁርኝት ጠየኩት 'የእኔ ቆንጆ ይህ ለልጅ የሚነገር ጉዳይ አይደለም' በማለት ሳይነግረኝ ቀረ:: እስቲ አንቺ ደግሞ በተራሽ አጣሪ... ከወንዶች ሁለት አሉ እስቲ ገምቺ?"

"አብረሃም እና ገመቹ?"

"እንዴት በአንድ ጊዜ አወቅሽ?"

"ንፁህ ግምት ነው"

ከፈገግተኛዋ ቤተል ጋር ወሬያችንን እንደስቃለን:: ቤተል ነጻ ልጅ ነች:: በሁለት የተለያየ እምነት የሚከተሉ ቤተሰቦች መሀከል በመሆኗ የተነሣ ስለ ሃይማኖት የተወዛገበች እና ግዴለሽ እንድትሆን አድርገዋታል፤ ከዚያ ባለፈ የተረዳሁላት ፀባዩዋ ወሬ በጭራሽ መቋጠር አይሆንላትም፤ በተለይ ለቤተል ሚስጥር ብሎ ምንም ነገር መንገር አስፈላጊ አይደለም:: በእርግጥ ይህን የምታደርገው ማንንም ለመጉዳት ሳይሆን በቃ ወሬ መቋጠር ጣር ስለሚሆንባት ነው፤ በተለይ ሚስጥር መያዝ ጭንቋ ነው፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ስጠይቃት "እንዴ የተነገረኝን ሚስጢር ቢያንስ ለአንድ ሰው ካላወራሁ የወር አበባዬ ይዛባል!" በማለት አስቃኛለች::

እነሆ ዓመቱ አለቀ:: ብሔራዊ ፈተና ተፈተንኩ:: አሪፍ ነበር ፤ በሚገባ ስለተዘጋጀሁ እና ስላጠናሁ በእርግጠኝነት ሁሉንም `A` እንደማመጣ አምናለሁ:: በጣም በጥንቃቄ ነበር የሰራሁት :: ከሌላ ት/ቤት የመጣ አብሮኝ ለፈተና የተቀመጠ እባብ የመሰለ ተማሪ ከእኔ እየኮረጀ ነበር:: እኔ ግን ይህን ልጅ ማስኮረጅ የነገ ህይወቱን ማበላሸት እና አንድ በራሱ ጥረት ስኬታማ መሆን ያልቻለ ሌባ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ማፍራት መሆኑ ስለሚገባኝ እንዳይኮርጅ ግግም አልኩበት:: በዚህ ድርጊቱ በጣም ስለተበሳጨ የመሀል ጣቱን ሶስ ጊዜያት አሳየኝ:: በእጁም እርድሻለሁ እንውጣ የሚል ምልክት ሰጠኝ:: እኔ ግን ዝም አልኩት:: አልፈራሁትም:: የእውነቱን እጠግባለሁ ካለም የካራቴ ትምህርቴን በተግባር የምጠቀምበት አጋጣሚ ስለማገኝ ሊያስቦካኝ ቢያስብም ምንም እንዳልተፈጠረ ቀረቀርኩት:: እናም ፈተናው ሲያልቅ ምንም ሳይፈጠር በሰላም ተለያየን::

ከብሔራዊ ፈተና በኋላ ክረምቱን ከፒያኖ ትምህርት እና የካራቴ ትምህርት በተጨማሪ እውቀቴን ለማበርቀቅ መፅሐፍትን አነበብኩ:: ከአጎቴ ጋር አዲስ አበባን ይበልጥ ለማወቅ ዞርኩ:: በርከት ያሉ አሪፍ ፊልሞችንም አየሁ:: ስለ ፊልም ከተነሣ እስቤው ሳይሆን ሳላስበው የተወሰኑ በመደፈር ላይ የተሠሩ የኢንግሊዝኛ ፊልሞችን አየሁ:: በጣም በሚገርም ሁኔታ በመደፈር ላይ የተሠሩት ሁሉም ፊልሞች በቀጥታ የሚሰብኩት ስለበቀል ብቻ ነው:: የደፈራቸውን ሰው ሲበቀሉ የሚያሳዩ ናቸው:: እኔ ግን ስለበቀል ባየሁ ቁጥር ውስጤ የሚነግረኝ “አንቺም ወንዶችን ተበቀይ!!” ሳይሆን ውስጤ የሚነግረኝ “አንቺ በቀለኛ ሴት ሳትሆኚ ቀና ሴት ነሽ:: ደግ ሴት ነሽ:: ከበቀል ይልቅ ይቅርታ ግዙፍ ዋጋ በፈጣሪ ዘንድ እንዳለው የምታውቂ ሴት ነሽ!” ይለኛል:: ምናልባት በኢንግሊዘኛ ያነበብኩት ምርጥ መጽሐፍ የሆነው የኒኮላስ ሪሰርቸር The power of optimism ለውጦኝ ይሆናል:: በእርግጥ ይህ ምርጥ መፅሐፍ ስለ Optimism እና pessimism ልዩነት የሚያብራራ አሪፍ መጽሐፍ ነው:: Optimism ማለት በቀላል ፍቺ ከማንኛውም አስቀያሚ ነገር አልያም አጋጣሚ ወይም ውድቀት መልካምና ቀናን ነገርን ብቻ የመጠበቅ አዝማሚያ ሲሆን pessimism ደግሞ በተቃራኒው ከእያንዳንዱ አጋጣሚ መጥፎ ነገር ብቻ ይደርሳል፤ ይሆናል ብሎ የማመን ባጠቃላይ ጨለምተኛ እና ከፉ አሳብ ብቻ የማሰብ አዝማሚያ ነው:: በዚው መጽሐፍ ላይ የሁለቱን ምንነት እና ልዩነት በቀላሉ ለማስረዳት የተቀመጠች አንዷት ጥሩ ምሳሌ አለች:: አንድ ብርጭቆ ውስጥ ያለን ግማሽ ውሃ አንድ Optimist እይታ ያለው ግለሰብ ሲመለከት

ውሃውን ግማሽ ሙሉ ብሎ ሲያስብ በሌላ በኩል ይህን ብርጭቆ ውስጥ ያለውን ግማሽ ውሃ ባዶ Pessimist እይታ ያለው ሲመለከተው ደግሞ ግማሽ ባዶ በሚል ምልከታ ይመለከተዋል የምትል ናት፤ በሌላ በኩል Optimism ማለት ከህይወቱ ውስጥ ከሚፈጠርበት ማንኛውም አጋጣሚ መልካም ነገር ይፈጠራል ብሎ የሚያስብ ሲሆን ምንም ሌሎች እንኳ ይህ የተፈጠረበት ነገር ህይወቱን ጨለማ ውስጥ ይከተዋል ብለው ቢያስቡም እርሱ ግን በተቃራኒው ይህ ነገር የተፈጠረው ለበጎ ነው ብሎ የሚያምን ነው፤ በሌላ ቋንቋ Optimism እይታ የሚያራምዱ ሰዎች ከጨለማ ውስጥ ብርሃንን ይፈልጋሉ! ጨለማን በብርሃን ብቻ ያሸንፋሉ! ከማንኛውም ጉዳት ውስጥ ነገ መልካም ነገር ይሆናል ብለው ያስባሉ:: እግራቸው ቢቆረጥ ፣ ሀብታቸው ቢጠፋ፣ ቤተሰባቸው ቢሞትባቸው፣ ዓይናቸው ቢጠፋ፣ በሽተኞች ቢሆኑ የተፈጠረባቸውን አደጋ በጸጋ ይቀበላሉ:: መቀበል ብቻም ሳይሆን ይህ የሆነው ለቀና እና እኔን ጠንካራ ለማድረግ ነው በማለት ያስባሉ:: አሉታዊ ምክርን ያስወግዳሉ:: ከወደቁበት ለመነሳት ብቻ ያውጠነጥናሉ:: ስለ ነገ ቀናውን ብቻ ያስባሉ! ከወደቁበት ለመነሳት ተስፋ ሳይቆርጡ እስከ መጨረሻዋ ጠብታ ይታገላሉ እንጂ ፈጣሪያቸውን፣ ራሳቸውን ፣ ለውድቀት የዳረጋቸውን፣ ጊዜን ፣ ሁኔታን ፣ አጋጣሚን በጭራሽ አያማርሩም ይህ ነገር በእኔ ህይወት ላይ መፈጠር አልነበረበትም ብለው በጭራሽ በትዝታ ራሳቸውን አይወቅሱም !! በተፈጠረባቸው ነገር እስረኛ አይሆኑም! በዚህ እይታ እና ትንታኔ መሠረት ለምሳሌ እኔን አባቴ ለገንዘብ ፍቅር ይሁን የጥንቁልና እምነት ተከታይ በመሆኑ እና አዕምሮው በመታወኩ የመስዋዕት በግ አድርጎ ለአጋንንት በማቅረብ አባቴ እና ሌሎችም አብረው ደፈሩኝ፤ በእርግጥ ይህ ባይሆን ኖሮ የማይባልበት ያፈጠጠ ሀቅ ነው:: ይህ እውነት ነው! ይህ አሰቃቂ ትዝታ ነው! ይህ የማይረሳ ገጠመኝ ነው! ይህ ለወሬ ራሱ የሚያስቸግር ነው፤ ግን እውነታውን ከተቀበልኩ በቃ ይህ ነገር እንዴ ተፈጠረ:: ያን የተፈጠረውን እውነታ ደግሞ መቀየር አልችልም፤ ስለዚህ በዚህ ትዝታ እስረኛ ሳልሆን ያን አስቀያሚ ነገር ማሸነፍ የምችለው ብቸኛ ምርጥ መንገድ ቀናውን ብቻ በማሰብ እና ባለመሸነፍ ብቻ ነው:: በቃ ሆነ! ይህ የሆነው እኔ ጠንካራ ሴት እንድሆን ነው! ከማንኛውም ነገር በመነሳት ህይወትን ማሸነፍ እንደምችል እንዳረጋግጥ የተፈጠረ መልካም አጋጣሚ ነው በማለት ራሴን ማሳመን ከቻልኩ በእርግጥ እኔም Optimist ሆንኩ ማለት ነው ፤ እናም ከ pessimist በትልቁ የእኔ ምርጫ Optimist መሆን ነው:: ህይወት ምርጫ ነች! ምርጫ ካለኝ ደግሞ ምንጊዜም መምረጥ

ያለብኝ ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍለኝ ቢሆንም እንኳ ቀናውን ብቻ መሆን አለበት:: በሌላ በኩል በኢጋጣሚ በመደፈር ላይ የሚሠሩት ፊልሞች ሆኑ የሚጻፉት መጽሐፍትን ስመለከትና ሳነብ ሁሉም ለማለት ይችላል የሚሰብኩት ስለ በቀል ብቻ ነው:: ጨለማን በጨለማ ስለማሸነፍ እንጂ ጨለማን በብርሃን ስለማሸነፍ ከቶ አያወሩም:: እኔ ደግሞ በበቀል ስሜትም ሆነ በጥላቻም ውስጤን መሙላት አልሻም! ጥላቻን በፍቅር ብቻ ማሸነፍ እፈልጋለሁ፤ ስለዚህ እኔ እየጣርኩ ያለሁት እንዴት Optimist ሴት ለመሆን ነው!! ምክንያቱም ምክንያት ውጤት አይለውጥም የሚባል አባባል አለ ወይም በዚች የሩሲያዎች ግሩም አባባል አምናለሁ:: The end does not justify the means በምትለዋ አባባል:: እኔ አዎንታዊት ሴት መሆን እፈልጋለሁ:: ስለ አዎንታዊ ሰዎች ካሊል ጂብራን ምን አለ? "አዎንታዊ ሰው ፅጌሬዳ አበባው ላይ ሲያተኩር አሉታዊ ሰው ፅጌሬዳውን በመዘንጋት እሾሁ ላይ ብቻ ያተኩራል" አሪፍ አባባል አይደለችም? በዚህ ዙሪያ ማርቲን ሉተር ሁለት ምርጥ አባባሎች አሉት "አሉታዊ በእጁ ላይ ስላለው ጥቂት ፍሬ ሲነጫነጭ ይታያል! አዎንታዊ ተነስቶ ይዘራዋል" እና "ነገ ዓለም ያከትምላታል ብባልም እንኳ ዘርን ከመዝራት አልመለስም" የሚሉ ናቸው:: የእውነት ለመናገር በዚች ዓለም ውስጥ ልናሻሽለው እንደምንችል እርግጠኛ የሆንበት ወይም መሆን ያለብን አንድ ነገር ብቻ ነው:: ይህም ራሳችንን ማሻሻል ነው:: በአዎንታዊ አስተሳሰብ መሞላት መቻል ራሱ ትልቅ ጥበብ እና ፀጋ ነው::

እኛ ጊዜ ነን:: የጊዜ ውጤቶች! የጊዜ እስረኞች! የጊዜ ጠብታዎች! እኛ ጊዜ ከሆንን በሌላ ቋንቋ ጊዜ ከንቱ ነው! እኛም ከንቱ ነንና! ምነው አንቺ ልጅ ከንቱ የሚባለውን ቃል አፈቀርሻት? ምነው ደጋግመሻት ልትሉኝ ትችላላችሁ! ያሻችሁኝ በሉኝ ግን የእኔ ምርጥ ቃል ከንቱ የምትለዋ ቃል ነች:: እነሆ! መሬት ላይ ያለው ነገር ሁሉ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው:: ከፀሐይ በታች ያለው ነገር ከንቱ ነው:: ንፋስን የመያዝ ያክል ከንቱ ነው:: ከፀሐይ በታች ያለው እንደ ጠዋት ጤዛ ከንቱ ነው:: ከጸሐይ በታች አዲስ ነገር መች አለና? የሴት ልጅ መደፈር በእኔ አልተጀመረ! ከእኔ በፊት ስንቶች ተደፍረዋል? ከእኔ በኋላስ ስንቶች ይደፈራሉ? ደፋሪ እና የመድፈር መንፈስ እስከመቼም አይጠፋም! በእርግጥ እኔ የተደፈርኩት አካሌን ነው:: ስንቶች አስተሳሰባቸውን ተደፍረው የለም? ስንቶች አመለካከታቸውን ተደፍረው

የለም? ስንቶች ማንነታቸውን ተደፍረው የለም? ስንቶች የመናገር፣ የመፃፍ፣ የማምለክ፣ የመኖር ፣ የመስራት ነፃነታቸውን ተደፍረው የለም? ስንቶች ህልማቸውን ተደፍረው የለም? የቱ ይበልጣል? የሥጋ መደፈር? የአስተሳሰብ መደፈር? ስለ መደፈር ይህን ያህል ትንታኔ ከሰጠነው ዘንድስ ማንስ ነው እኔ አልተደፈርኩም የሚለው? ማንስ ነው ንፁህ? ማንስ ነው ህሊናው ያልቆሸሸ? ማንስ ነው ልቡ እንደ እንቁ ውድ የሆነ? ማንስ ነው ሀጢያት የለብኝም በማለት ሊመፃደቅ የሚችለው? ማንስ ነው እኔ ቆሻሻ አይደለሁም ማለት የሚችለው? ይህን ሁሉ አሰብኩ ፤ በእርግጥ ከጸሐይ በታች ሁሉ ነገር ከንቱ ነው... ሁሉ ነገር ትላንት የነበረ ዛሬ የሚደገም ከንቱ ነው:: ሁሉ ነገር እሽክርክሪት ነው:: ይህ ደግሞ ከንቱ ነው:: አንዳንዴ ስለ ህይወት ሳውጠነጥን ዛሬ እያንዳንዳችን የምንኖረው ትላንት ሌሎች የኖሩትን እየደገምን ይመስለኛል ወይም ይሆናል አልያም ላለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላልን?

አለማሰብ አይቻልም:: የሚገርመው ግን ማሰብም አለማሰብም ከንቱ መሆናቸው ነው:: ፀሐይ ለሚያስበውም ለማያስበውም ትወጣለች:: ፀሐይ ለአረመኔውም ለቅዱሱም ትወጣለች! ዝናብ ለሚያስበውም ለማያስበውም ይዘንባል! ዝናብ ለአረመኔውም ለቅዱሱም ይዘንባል! ከፀሐይ በታች ሁሉ ነገር አስቂኝ ነው... ከፀሐይ በታች የሰው ልጅ የእ/ር ጤዛ ነው! የሰው ልጅ የእ/ር ሽርፍራፊ ሴኮንዶች ውጤት ነው! የሰው ልጅ የእ/ር ቅጠል ነው... ይህን ... ያንን... ከንቱነት... አልከንቱነት... ቅብርጥሶ... አልቅብርጥሶ እያውጠነጠንኩ ከረምቱ አለቀ:: ዘመን ተለወጠ:: አሮጌው በጠረባ ተሸኘ:: አዲሱ መጣ:: ከት/ቤታችንም ሆነ ከክፍላችንም በአስረኛ ክፍል ብሔራዊ የመንግስት ፈተና ሁላችንም አለፍን:: እኔና ያ ግድንግድ ጭንቅላት ያለው ልውል እኩል አመጣን:: የሁለታችንም ኤ ብዛት እኩል ነበር:: ይህን ውጤት በሰማሁኝ ቀን በመጠኑ ግራ ተጋብቼ ስለ ነበር ከአጎቴ ጋር አወራን

"አጎቴ" አልኩት

"አቤት የእኔ ልጅ!"

"በመጠኑ ግራ ተጋብቻለሁ"

"የእኔ ልጅ በህይወትሽ ውስጥ አንዳንዴ ግራ መጋባት በጣም ወሳኝ ነገር ነው:: በግራ መጋባት መሀከል ትክክለኛውን ነገር ለመወሰን በጥንቃቄ ማሰብ ይኖራል:: ለማንኛውም በምን ጉዳይ ግራ ተጋባሽ?"

"አስራ አንደኛ ክፍል ልገባ ነው! ሳይንስ ልግባ? ሶሻል ልግባ? እያልኩ ተወዛገብኩ::

ለሁለቱም እኩል ፍላጎት አለኝ፡፡ ት/ቤት እንዳንቺ ያለች ምርጥ ተማሪ ሳይንስ መግባት አለባት ይሉኛል፤ በሌላ በኩል አማርኛ አስተማሪዬ አንቺ የተደበቀ የሥነ ፅሁፍ ችሎታ ስላለሽ የሥነ ፅሁፍ ተማሪ ሁኚ ይህ ካልሆነ በማንኛውም የት/ት ዘርፍ የአዕምሮ ፈጣንነትሽ የተነሣ ምርጥ አስተማሪ የመሆን እድል ይኖርሻል፤ ስለዚህ ሶሻል ብትገቢስ ትለኛለች... በዚህ ነገር ግራ ተጋባሁ፡፡ በእርግጥ ግራ የተጋባሁት እኔም እንደ ሰነፍ ተማሪዎች አስቀድሜ የወሰንኩት ነገር ባለመኖሩ ነው"

"የእኔ ልጅ ዋናው ቁም ነገር ሳይንስ ግቢ ሶሻል ሁለቱም ጋር መልፋት አለብሽ! ማን ነው ሳይንስን ለጎበዝ ተማሪ ማን ነው ሶሻልን ለመካከለኛ ተማሪ ብሎ ያወጀው? የምርጫ ጉዳይ ነው፡፡ ቁጥር ነክ የማትወጂ ከሆነ በእርግጥ ሶሻል ይሻልሻል አንቺ ግን ቁጥር ነክ ላይም በጣም ጎበዝ ነሽ! ሥነፅሁፍ ላልሽው የሚገርምሽ ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው በሥነፅሁፍ የተሳካላቸውን በሙሉ ታሪካቸውን ብታነቢ አንዳቸውም የሥነፅሁፍ ተማሪ አልነበሩም ለማለት ይቻላል፤ ሁሉም ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁት በሌላ ዘርፍ ነው፤ ስለዚህ ይህን በግልሽ የምታዳብሪው ነው እንጂ በዩኒቨርሲቲ ሥነፅሁፍን ብትማሪ እኔ እንደታዘብኩት ዋጋ የለውም! የሥነጽሁፍ መክሊት ካለሽ ሌላውን በማንበብ በግልሽ ማዳበር ትችያለሽ፤ ስለዚህ ይህን ከግምት በማስገባት የፈለግሽውን መርጠሽ እንድትማሪ እንጂ እኔ አሁንም ዶክተር ሁኚ፣ የህግ ሰው ሁኚ... እያልኩ ልገድብሽ አልችልም፡፡ የእኔ ህይወት የተበላሸው በሞተው አባቴ የተነሣ ነው፡፡ በግድ የማልፈልገውን ትምህርት እንድማር አደረገኝ! ስኬታማ ሳልሆን ቀረሁ፤ ግን አባቴ ሲሞት እና ከእስር ቤት ስፈታ የልጅነት ህልሜን ለማሳካት ችያለሁ፤ ምናልባት ግን እንደ አስተያየት የራስሽንም የሌሎችንም ህይወት ለመጥቀም ከፈለግሽ ዩኒቨርሲቲ ስትገቢ ዋና ምርጫሽን ኢኮኖሚክስ ትንሹ ምርጫሽን ማናጅመንት አድርገሽ መማር ትችይ ይሆናል፤ ይህን ያልኩሽ ባንክ የተቀመጠውን ገንዘብ እንዴት መጠቀም እንዳለብሽ? እንዴት ድርጅት መክፈት እንዳለብሽ? እንዴት ማስተዳደር እንዳለብሽ... ወዘተ ስለ ኢኮኖሚክስ እና ማናጅመንት ሳይንሳዊ እውቀት ትቀስሚያለሽ ብዬ በማሰብ ነው፡፡ ከዚያ የምትፈልጊውን ድርጅት ከፍተሽ በርከት ያሉ ሠራተኞችን ቀጥረሽ ለሌላውም ኢትዮጵያዊ የስራ እድል መፍጠር ትችያለሽ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለመንግስት ሳታጭበረብሪ ልከኛውን ግብር በመክፈል ለአገርሽ ኢትዮጵያም ጠቃሚ ማለት ነው" አለ አጎቴ፡፡ ከአጎቴ ሀሳብ ውስጥ የሚጣል አልነበረበትም፤ እናም ያለ አንዳች ጥያቄ ወዲያው ሶሻል ለመግባት ወሰንኩ፡፡ ለካ ለራሴ

ሳይሆን ለሌሎችም መትረፍ የምችል ሴት ነኝ! በህይወት ጉዞ ላይ ደግሞ ለሌሎች መትረፍን የመሠለ ነገር ምንስ አለና?

ትምህርት ቤት ሶሻል መግባቴን የሰማችው ቤተል አቤት የተደሰተችው ደስታ! የቤተልን ደስታ በቃላት ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ከእኛ ክፍል ሶሻል የመረጡት ተማሪዎች ዘጠኝ ብቻ ነበሩ፡፡ ከዘጠኙ አንደኛው ወንድ ነበር፡፡ ሙክታር የተባለ መነፅር የሚያደርግ የክፍላችን አንደኛ አይን ዓፋር እና ዝምተኛ ተማሪ ነው፡፡

"የእውነት በጣም ጨንቆኝ ነበር፡፡ ሶሻል በመምረጥሽ ከልቤ ነው ደስ ያለኝ ይህን ዜና ለእናቴ ስነግራት በጣም ደስ ይላታል! ካንቺ ጋር በመሆኔ በጣም ደስተኛ ነች" አለች ስሜቷን መቆጣጠር ያቃታት ቤተል እጄን ጭምቅ አድርጋ ይዛኝ፡፡

"ኢኮኖሚክስ እና ማናጅመንት ለማጥናት ወስኛለሁ፡፡ አንቺስ?" አልኳት፡፡

"እኔ አካውንቲንግ እማርና ባንክ ቤት ገብቼ ይህን የሀብታም ብር እቆጥራለሁ፤ ታዲያ ከበድ ያለ ብር ባንክ ቤት ያስቀመጠውን ወይም ሊያስቀምጥ የሚመጣውን አጠናና ጥምጥም እልበትና አግብቼው ቁጭ እላለሁ"

"በቃ"

"ሴት እኮ ነኝ! የሴት ህልም እንደ ሽንቷ አጭር ነው ሲባል አልሰማሽም!? መመረቅ ፣ ማግባት፣ ልጅ መፈልፈል ፣ የባሏ ቋሚ ሠራተኛ መሆን! ቤት ውስጥ ተቀምጣ ፊልም ማየት ፣ ቡና እያፈላች ከጓደኞቿ ጋር በሀሜት መወጠር እና ፣ ባሏ ሲመጣ በነገር መጠቅጠቅ"

"እየቀለድሽ ነው አይደለም?"

"ቀልድም ቁም ነገርም ነው ፤ ምክንያቱ ባይገባኝም ሁልጊዜ የማውጠነጥነው ቶሎ ማግባት እና ልጅ መውለድን በተመለከተ ነው፡፤ እንደተመረኩ ወዲያው ባል የማገባ ነው የሚመስለኝ የእኔ ትልቁ ጉጉት አንዱን ሀብታም አግብቼ የራሴ ትልቅ የሚያምር ቪላ ቤት ውስጥ እየተንደላቀኩ መኖር ነው፡፡

"ቆይ የምታገቢው ቢጠፋስ?"

"እንዴ! እንዳንቺ ልቅም ያልኩ ቆንጆ ባልሆንም የደስ ደስ እኮ አለኝ፡፡ የሚያምር ፈገግታ አለኝ፡፡ የሚያምር ሰውነት አለኝ፡፡ አሁን ይህን ሰውነቴን ይበልጥ ለማሳመር ጂም እየሰራሁ ነኝ፤ ስለዚህ አንዱን ወንድ ጠብ ማድረጌ አይቀርም፡፡ ያው የሚያምር ሰውነት ያለው እና ሀብታም ቢጤ የሆነ ወንድ መሆን አለበት ፤ ምንም ቢፈጠር ቆሜ እቀራለሁ እንጂ

ጅብ መልከ ያለው ወንድ አላገባም"

"ከመናጢ ደሀው ፍቅር ቢይዝሽስ?

"እንደ አከስቴ ልጅ ማርያ? አይ ማርያ ክልስ ነች፡፡ እንዴት እንደምታምር ተያት! ሀብታም ወንድ አገባለሁ እያለች ፓይለት ስታማርጥ፣ መርከበኛ ስታማርጥ፣ ከሀብታሞች የተሻለውን ሀብታም ስታማርጥ፣ ይህ በቂ ገንዘብ አለው ግን ጉቶ ነው፣ ይህ ሽበት አለው፣ ይህ ቦርጭ አለው፣ ይህ ንግግር አያውቅም፣ ይህ እግሩ ሽፋፋ ነው፣ ይህ ዳንስ አይችልም፣ ይህ አይዘንጥም ፣ ይህ አልተማረም፣ ይህ ወሲብ አይችልም... እያለች ሺ ምክንያት እና ሺ አቃቂር ስታወጣ በመጨረሻ ማንን ብታገባ ደስ ይልሻል? መርጦ ለማርያም ከምትባል ቦታ የመጣ የቤታቸውን ዘበኛ! በዘበኛው ፍቅር እብድ አለች! አገባችው፤ ታዲያ ቤተሰቡ እና የሰፈሩ ነዋሪ ምን እንዳለ ታውቂያለሽ? ያ ከመርጦ ለማርያም የምትባል መንደር የመጣ ዘበኛ መቼም መስተፋቅር አሰርቶባት ይሆናል እንጂ እንዲሁ በዋዛ ያቺን የመሰለች ሸበሊት ይህን ብርድ የመታው ዶሮ የመሠለ አታገባም ሲሉ ሌሎች ደግሞ እሰይ! የት አባቷ! ይቺ ኩራተኛ ፣ ይቺ ሰው ጤፉ፣ ይቺ ምድር አልበቃችኝም ባይ፣ ይቺ ራሷን ቆላይ፣ ስንቱን ስታማርጥ፣ ስንቱን በፍቅር እያሽመደመደች ስታባራቸው ፣ ስንቱን ቁምስቅላቸውን ስታሳያቸው፣ የወንድ ልጅ እንባ ጡር አለውና የፍቅር አምላክ ራሷን ቆልላ መሬት ለመርገጥ እየተፀየፈች ሰማይ ሰማይ ስታይ መሬት ላይ አፈረጣት! የስንቱ ወንድ እንባ እና እርግማን ከቤታቸው ዘበኛ ላይ አፈረጣት አሉ አልሻለሁ፡፡ መቼም ይህ በእኔ እንደማይደርስ እገምታለሁ፡፡ ስለ ነገ ማን በእርግጠኝነት መናገር ይችላል?"

"እውነት ነው! ስለ ነገ ማንም በእርግጠኝነት መናገር አይችልም" አልኳት፡፡ ራሴን እየነቀነኩላት፡፡ የተናገረችው ትልቅ እውነትነት ያለው አባባል ነውና፡፡

የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርት ተጀመረ፡፡ 70/30 በሚለው ህግ መሠረት አብዛኛው ተማሪ የሳይንስ ተማሪ ሆነ፡፡ ሶሻል ተማሪዎች በጣም ትንሽ ነን፡፡ ትንሽ በመሆናችን የሳይንስ ተማሪዎች ጉራቸውን ይነዙብናል፡ እኔ ምንም አይመስለኝም፡፡ በሥነልቦና ጥናት እንደተደረሰበት ጉረኛ ሰው ውስጡ የበታችነት ስሜት የሚሰማው ሰው ነው፡፡ ያም ሆኖ

ትምህርት ተጀምሮ ሁለተኛው ወር ላይ ፈተና ሲጀመር እና መጨናነቅ ሲጀምር ሁሉም በራሱ ላይ ተወጠረ:: ሳይንስ ነሽ፣ ሶሻል ነሽ ሁሉ ተረሣ! በዚች ከንቱ በሆነች ዓለም ውስጥ ሁሉ ነገር ወረት ነው:: ሁሉ ነገር በጊዜ ቁጥጥር ስር ነው:: ይህን በዚች ትንሽ የህይወት ቆይታዬ የተገነዘብኩት ሀቅ ነው:: ሁሉ ነገር ጊዜያዊ ነው:: የሞቀ ይቀዘቅዛል! ከፍ ያለ ዝቅ ይላል! ትልቅ ዜና የነበረ ይረሣል! የሣቀ ያለቅሳል! የቆመ ይወድቃል! ይህ የማይሻር የህይወት ህግ ነው! ማንም የቆመ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ የሚል ምርጥ አባባል አለ:: ይህ እውነት ነው::

ከት/ቤት ወደ ቤቴ ስመለስ መንገድ ላይ አንዲት ወጣት ከአንድ ድንቡሽቡሽ ያለ ልጅ ጋር ስትሄድ አየዋት፣ ወዲያው ለአጎቴ ሚስት የመፈለጉ ጉዳይ ትዝ አለኝና በፍጥነት ደረስኩባቸውና ድንቡሽቡሽ ያለውን ልጅ ሳምኩት

"ድንቡሽቡሽ ያለ ደስ የሚል ልጅ አለሽ ስንት ዓመቱ ነው?"

"ሶስተኛ ዓመቱን እየጨረሰ ነው አራተኛውን ሚያዚያ 25 ያከብራል"

"የእውነት ሚያዚያ 25?"

"አዎ!"

"የሚገርም ገጠመኝ ነው! የእኔም ልደት ሚያዚያ 25 ነው!"

"የምርሽን ነው?"

"የእውነት !"

"የሚገርምሽ ሚያዚያ 25 እኔ የተወለድኩባት፣ እናቴ የተወለደችበት፣ ፍቅረኛዬም የተወለደበት፣ ልጄም የተወለደበት አስማተኛ ቀን ነች:: የቀን አምላኪ ብሆን 25 ቁጥርን አመልካት ነበር፤ ልክ ቻይናዎች 8 ቁጥርን እንደሚያመልኩት፤ ግን እንደ ገጠመኝ ብቻ እቆጥረዋለሁ"

"ስለዚህ ከባለቤትሽም ጋር ልደታችሁን በአንድነት በአንድ ቀን ደስ በሚል ሁኔታ ታከብራላችሁ ማለት ነዋ? የእውነት ደስ ይላል! በአንድ ድንጋይ ሶስት ወፍ ማለት ነው"

"እህ... ነበር" አለች:: በትኩረት ልጇን እየተመለከተች:: ወዲያው እኔ ጥያቄዬን

ቀጠልኩ

"ነበር ማለት?"

"ማን ነው ስምሽ?"

"እሌኒ"

"ስንተኛ ክፍል ነሽ?"

"አስራ አንደኛ"

"ፍቅረኛ አለሽ?"

"ኧረ የለኝም"

"አንድ ትልቅ ምክር ልለግስሽ!? በምንም መልኩ ወንድ እንዳታምኚ! በተለይ እወድሻለሁ! ካንቺ ውጪ ህይወቴ ባዶ ነው! አንቺ የእኔ እስትንፋስ ነሽ! አንቺ ከሌለሽ ህይወት ለእኔ ከንቱ ነች! አንቺን የሰጠኝ ፈጣሪ ክብር ይግባው ወዘተ እያለ ፍቅሩን በቃላት ጋጋታ እየቀባጠረ የሚነግርሽን እና እንዲሁ የቅዱሳንን ስሞች እየጠራ፣ በቤተክርስቲያናት ስሞች እየማለ ካንቺ አብድ ያለ ፍቅር እንደያዘው ጠዋትና ማታ የሚተረተርልሽን ወንድ ጨርሶ እንዳታምኚ! ወንዶች ማለት የውሸት ፋብሪካዎች ናቸው፡፡ ማስመሰልን ሁሉም ወንዶች ተክነውበታል፤ ስለዚህ ከቻልሽ ሁሉንም ወንዶች እንዳታምኚ በተለይ ደግሞ ከወንዶች ሁሉ የቃላት ኳኳታ የሚያበዛ ወንድ ከቶውኑ እንዳታምኚ! በህይወቴ አሪፍ ጊዜያት ያሳለፍናቸው እና በጣም ይወደኛል የምለው ፍቅረኛ ነበረኝ፡፡ አምስት ዓመት አብረን ቆይተናል፡፡ ድንገት አረገዝኩ፡፡ ቤተሰብ ጣጣ እንዳያመጣ ቀለል ባለ የቀለበት ሥነ ሥርዓት ተጋባን፡፡ ይህ ልጅ ተወለደ፡፡ ይህ ልጅ ሁለተኛ ዓመት ሲሞላው ባለቤቴ ከአንዲት ሴት ጋር በፍቅር ከንፍ ብለው እና በፍቅር ሰክር ብለው ከኢትዮጵያ ጓዛቸውን ጠቅልለው አሁን ኬኒያ እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ በጣም የሚደንቅሽ ፍቅረኛዬ ያገባት ሴት እኮ የገዛ እናቴን ነው! ቅስሜን ነው የሰበሩት"

"እየቀለድሽ ነው?"

"ለማመን ያስቸግራል አይደለም? ግን ሀቅ ነው! የገዛ እናቴ የእኔ የልጄን ባል ቀምታ አግብታ ኬኒያ አብረው እየኖሩ ናቸው፤ ከዚህ በላይ ልብ የሚሰብር ነገር አለ?"

"በጣም ያሳዝናል!!"

"ወንዶች እንደዚህ ናቸው፡፡ በእርግጥ እናቴም ርካሽ ሴት ናት፡፡ እኔ አሁንም

በአንክሮ የምነግርሽ በጣም አወድሻለሁ፣ ጨረቃን እስጥሻለሁ፣ ጸሐይን እስጥሻለሁ፣ ስላንቺ የማልሆነው የለም ፣ አንቺ የእኔ ምናምን ነሽ እያለ በቃል ሊገዛሽ እና ሊሞላሽ የሚሞክር ወንድን በምንም ተዓምር ልብሽን እንዳትሰጪው ነው:: ምክንያቱም ወንዶች ሁሉ የውሸት ባህር ናቸው::"

"ታዲያ አሁን..."

"እኔ ጠንካራ ሴት ነኝ! በእኔ ቦታ ይሄን ጊዜ ሌላ ሴት ብትሆን በንዴት ወይ ሴተኛ አዳሪ ሆናለች ወይ በመጠጥ ሱስ ጠዋት እና ማታ እየተጋች በመናወዝ ራሷን አስራ ተቀምጣለች:: እኔ ግን ከዚህ በኋላ ህይወቴ ይህ ልጅ ነው በማለት ስለወሰንኩ ይህን ምንም የማያውቅ ልጅ ለማሳደግ ስራዬን በሚገባ ቀጠልኩ:: ለማንኛውም አንቺ ከወንድ ይልቅ በትምህርትሽ በርቺ! አደራ! እነዚህ የሴይጣን ቁራጭ የሆኑ ወንዶች እንዳይሸውዱሽ! በይ እኔ እዚህ ጋር ታክሲ ልይዝ ነው! በነገራችን ላይ ልቅም ያልሽ ቆንጆ ነሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ትጠብቅሽ" በማለት ምንም ሳልናገር በፍጥነት ድንቡሽቡሽ ካለው ልጇ ጋር ታክሲ ውስጥ ገቡ:: ቤት እስከምደርስ የልጅቷን ታሪክ እያውጠነጠንኩ ነበርኩ:: በጣም የገረመኝ እንዴት እናት የልጇን ባል ቀምታ ታገባለች? እንዴት ባልስ የሚስቱን እናት አግብቶ ይሄዳል? ይቺ ከንቱ ህይወት ወዴት እያመራች ነው ወይስ እውነተኛ ፍቅር የሚሉት ጉድ ይሆን? ፍቅር የሚሉት ጉድስ ይህን መሰል ድርጊት ሊከውን ይችላል? ወይስ የመጨረሻው ዘመን እየመጣ ይሆን? ወይስ 666 ምድር ላይ ስራውን ማከናወን ሙሉ ለሙሉ ጀምሮ ይሆን?

ትምህርት ቀጥሏል:: የአስራ አንደኛ ክፍል ሁለት ተማሪዎች እንዲሁም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ሁለት ተማሪዎች እኔን ጀንጅነው የራሳቸው ለማድረግ ከፍተኛ የተደራጀ ጅንጀና አከናውነውብኝ ነበር:: ሁሉንም እንደ አመጣጣቸው ሳይሆን ስሜታቸውን በማቀዝቀዝ እና ሀሳባቸውን በማስቀየር መለስኳቸው:: የተማሪዎች ከፍተኛ የተደራጀ ጅንጀና ሲገርመኝ አስረኛ ክፍል ፊዚክስ ሲያስተምረን የነበረው መምህር ሁኔታ ይበልጥ አስገረመኝ::በጣም እንደሚፈልገኝ ነግሮኝ ቢሮው ድረስ አስጠራኝ:: እኔም በምሳ ሰዓት አስተማሪው ቢሮ ሄድኩኝ::

"ይህን ጉዳይ መንገር የነበረብኝ የዛሬ ዓመት ነበር፤ ግን አስተማሪሽ በመሆኔ ከበደኝ እሁን ግን አስተማሪሽ አይደለሁም! ስላንቺ ማሰብ የጀመርኩት ገና ዘጠነኛ ክፍል እያለሽ ነበር:: አሁን የማስበው ስላንቺ ነው! ስሜቴን እንደምንም ለመቆጣጠር ብሞክርም ስላንቺ ከማሰብ ግን ልተው ከቶ አልቻልኩኝም! ካንቺ ፍቅር ይዞኛል! ማስተማር ሁሉ እያቃተኝ ነው! አፈቅርሻለሁ!" አለ::

"መምህር አዝናለሁ! በዚህን ሰዓት ሙሉ ትኩረት ማድረግ የምፈልገው በትምህርቴ ላይ ብቻ ነው፤ በዚያ ላይ አንተ የእኔ መምህር ነበርክ:: ተማሪዎች በምንም ሁኔታ በፍቅር እና በወሲብ ጉዳይ ምንም አይነት ግንኙነት ከአስተማሪዎች ጋር ማድረግ የለባቸውም የሚለውን የፀና አቋም አከተላለሁ! አንተም እውነተኛ አስተማሪ ከሆንክ ተማሪዎችህን ከችግር መጠበቅ እንጂ ችግር ውስጥ ማስገባት የለብህም" አልኩት::

"ይገባኛል ግን..." በማለት ብዙ ለፈለፈ:: አስተማሪው ደረቅ እና የራሱን ፍላጎት ለመፈፀም ብቻ ሣር እንዳየ በሬ ፊት ለፊት የሚንደረደር ህሊናውን የሸጠ ስለሆነ ከእርሱ ጋር መከራከሩ ዋጋ እንደሌለው ስለገባኝ ሀሳቡን ብቻ ሰምቼ ወጣሁ፤ ስለዚህ ጉዳይ ለማንም አልተናገርኩም:: አላመንኩም ነበር እንጂ ይህ ፊዚክስ አስተማሪ ከዚህ በፊት በውብ የጅንጀና ቃላት እና አስተማሪነቱን ተገን በማድረግ በርካታ ተማሪዎችን እያስመጣቸው የወሲብ ስሜቱ ማስተንፈሻ እንደሚያደርጋቸው ሠምቻለሁ:: እኔንም ባለተረኛዋ የወሲብ ስሜቱ ማስተንፈሻ ለማድረግ በእርግጠኝነት አቆብቅቦ እንደሚሆን እገምታለሁ... ለማንኛውም እንደዚህ ያሉ መሰናክሎችን በፅናት በማለፍ በትምህርቴ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ የዓመቱን ትምህርት እንደተለመደው በስኬት ጨረስኩት:: እነሆ ክረምት መጣ:: እንደተለመደው የፒያኖ እና የካራቴ ትምህርቴን ለመጀመር ተዘጋጀሁ:: ከዚህ በተጨማሪ በክረምቱ በርከት ያሉ መፅሐፍትን እና ከማዝናናት ባሻገር ሊያስተምሩኝ የሚችሉትን ፊልሞችን ለማየት እቅድ አስቀድሜ ነደፍኩ:: ከዚህ መሀከል አጎቴ በተለመደው ፈገግታው እየተመለከተኝ

"የእኔ ልጅ ከመስሪያ ቤት የዓመት ዕረፍት ለ22 ቀናት ወጥቻለሁ፤ ስለዚህ የፒያኖ እና የካራቴ ትምህርትሽን ከመጀመርሽ በፊት ለሰባት ቀናት ጉዞ እናደርጋለን፤ በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ጉዞዎችን ደቡብ ይሆናል:: ሻሸመኔ ፣ ላንጋኖ፣ ሀዋሳ ፣ ወንዶገነት እና የኢትዮጵያ ጠረፍ ሞያሌን እናያለን"

"የእውነትህን ነው አጎቴ?" አልኩት ባለማመን::

“ይልቅ አልባሳቶች እና የሚያስፈልጉሽን ኮተቶች በፍጥነት አዘጋጂ!”

በደስታ አጎቴን እቅፍ አደረኩት፡፡

“የእኔ ልጅ ወደፊት አገርሽን ኢትዮጵያንም ሆነ ዓለምንም እየዞርሽ ለማየት እድሉ በእጅሽ ላይ ነው፡፡ ጉዞ ገንዘብ ካለሽ አሪፍ ነገር ነው፡፡ አዕምሮሽ ዘና ይላል፡፡ በተፈጥሮ በጣም ትገረሚያለሽ! በእግዜር ጥበብ ትደነቂያለሽ! የተለያዩ ባህሎችን ታያለሽ! ብዙ ልምዶችን ታዳብሪያለሽ፡፡ አዲስ የተወለድሽ ያህል እንዲሰማሽ ያደርግሻል፤ ለማንኛውም ከሁለት ቀናት በኋላ ጉዞያችንን እንጀምራለን” አለኝ፡፡ ይህ ክረምት ለእኔ ምርጡ ክረምት እንደሚሆን ተስፋ አደረኩኝ፡፡ ገና ከአዲስ አበባ ሳልወጣ ተደሰትኩኝ፡፡

እነሆ 2005 ዓ.ም መጣ፡፡ የአስራ ሁለተኛን ክፍል ትምህርት ጀመርን፡፡ የእኔ የዓመቱ እቅድ በአሪፍ ውጤት ዩኒቨርሲቲ መግባት ስለሆነ ገና መስከረም ሳይገባ ነበር የዓመቱን እቅዴን የነደፍኩት፡፡ አብዛኛው ተማሪ ፈተና ሲደርስ ያጠናል እንጂ እንደ እኔ እንኳን የዓመት እቅድ ሊነድፍ ቀርቶ የሳምንት እቅድ እንኳ የለውም፡፡ በዚህ ጉዳይ ያቺን ፈገግታ የማይለያትን ቤተልን አንድ ጊዜ

“ለምን እቅድ አትነድፊም? አሪፍ ነገር እኮ ነው! ፈጣሪ እንኳ በእቅድ ነው ነገሮችን ተራ በተራ ይሁን እያለ የጨረሰው! ታላቁ ፈጣሪ ሰማይ እና ምድርን ለመጨረስ በፈጣሪ አቆጣጠር ሰባት ቀናት በእኛ አቆጣጠር 7000 ሺ ቀናት ፈጅቶበት ነው የጨረሰው፡፡ አየሽ ሁሉ ነገር የሚሠራው በእቅድ ነው፤ በተለይ ለተማሪ እቅድ ማውጣት እና በእቅድ መጠቀም ግዴታ ነው! አይመስልሽም?” አልኳት፡፡

“ፈጣሪ በእቅድ የሰራው እኮ ስለነገ ስለሚያውቅ ነው፡፡ እኛ የሰው ልጆች ደግሞ ስለ ነገ የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ሌላው ይቅርና እንደው በቀላሉ በእርግጠኝነት የወር አበባዬ በዚህ ቀን ይመጣል ብለሽ መናገር አትችይም! ማንም በነገ መመካት አይችልም፤ ስለዚህ ስለማላውቀው ነገ ምን ያደርግልኛልና እቅድ አወጣለሁ? ሙዴ ሲመጣ አጠናለሁ ወይም ግዴታዬ ስለሆነ ለፈተና ስል ብቻ ሙዴ ባይመጣም አጠናለሁ ፣ በዚያ ላይ እኔ እንዳንቺ ጂኒየስ ተማሪ አይደለሁም፡፡ ጀስት መካከለኛ ተማሪ ነኝ፤ ስለዚህ እቅድ ምናምን በሚለው አላምንም! አንቺ ህይወት ከንቱ ነች ትይ የለም? እና ለዚች ከንቱ ህይወት ለምን አቅዳለሁ?”

በማለት ነበር አቋሟን የነገረችኝ፤ ከዚያ ድንገተኛ ጥያቄ አነሳች

"ነፍሳቸውን ይማርና እናትሽ እና አባትሽ በመኪና አደጋ ማረፋቸውን ነግረሽኝ ነበር?" አለች ስለ እናቴና አባቴ ቤት ስትመጣ ጠይቃኝ የመለስኩላትን እያስታወሰች:: መዋሸት የግድ ስለሆነ ነበር ዋሸዋት:: በዚያ ላይ ያን የመሰለ አስቀያሚ ታሪክስ ምን ተብሎ ይወራል? አንዳንድ ታሪኮችን እኮ አይደለም ለሌላው ለራሳችን እንኳ ማውራት አስጠሊታ የሚሆንበት ጊዜ የለም ትላላችሁ?... በዚያ ላይ ቤተል ወሬ መቋጠር የማትችል ፀረ ሚስጢር ነች...

"ልክ ነሽ ነግሬሻለሁ" አልኳት::

"ከአንትሽ ጋር ስናወራ እንደተረዳሁት ሃይማኖት ያለው አይመስለኝም:: ምግብ ሲበላ ሳየው እንኳ ሳይጸልይ ነው:: የሚያምረው ቤታችሁ ውስጥ የተለጠፈ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይሁን የቅዱሳን ስዕሎች በጭራሽ አላየሁኝም:: ከአንትሽ ጋር ስናወራ ሃይማኖትህ ምንድ ነው ስለው ፍቅር ነው የሚል መልስ ፈገግ እያለ መለሰልኝና ዝም አለኝ:: የእውነት ግን የአንትሽ ሆነ የአንቺ ሃይማኖት ምንድነው ?"

"የለኝም ማለት ይቀለኛል"

"የለኝም? ታዲያ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝር ታሪኮች እንዴት አወቅሽ?"

"አንደኛ ከአንቴ ጋር እናወራለን:: ከልጅነቴ ጀምሮ አንቴ መጽሐፍ ቅዱስን እንዳነበ ታሪክ ይነግረኝ ነበር፤ በተለይ አንቴ ሆን ብሎ የሆነ የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ መተረክ ይጀምርልኝና በይ የእኔ ልጅ የቀረውን ከመፅሐፍ ቅዱስ ላይ አንብቢና ጨርሺ ይለኛል፤ በዚህ የተነሣ እኔም ስለመፅሐፍ ቅዱስ ይበልጥ ለማወቅ እና ታሪኩን ለመጨረስ አነባለሁ:: የእግዚአብሔርን ቃል እንደማንበብ ምን ደስ የሚል ነገር አለናስ?"

"የትኛውን? የፕሮቴስታንት 66 ክፍል ያለውን? የኦርቶዶክስ 81 ክፍል ያለውን ወይስ የካቶሊክን 73 ክፍል ያለውን?"

"ሁሉም ቤት አሉ:: በመሀከላቸው ያለውን ልዩነት ለማወቅ ሁሉንም ለመመርመር እና ለማንበብ እቅድ አለኝ:: አንቺ አታነቢም?"

"እኔ እባክሽ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተንተርሰው የተሰሩ ፊልሞችን ማየቱን እመርጣለሁ:: አንድ ጊዜ ግን ቤት ውስጥ ፊልም እንዳላይ መብራት ጠፍቶ ቁጭ ማለት ስለደበረኝ እስቲ ዛሬ እንኳ መፅሐፍ ቅዱስ ላንብብ አልኩልሽና ድንገት መፅሐፍ ቅዱስን ስገልጥ ያገኘሁት የኢያሱ ታሪክን ነበር:: ኢያሱ ጠላቶቹን ሙሉ ለሙሉ እያራወጣቸው

ለመደምሰስ ተቃርቦ እያለ ፀሐይ ልትጠልቅ ጥቂት ቀርቷት ነበር፤ በዚህ ጊዜ ኢያሱ ጸሐይዋ በገባኦን ላይ ጨረቃ ደግሞ በኤሌም ቆላ ላይ እንዲቆሙ አዘዛቸው:: ፀሐይና ጨረቃም ኢያሱ ሙሉ ለሙሉ ድል እስከሚቀናጅ ድረስ በያሉበት እንደቆሙለት እና አምስት ነገስታትን ባጠቃላይ በህይወት ዘመኑ ደግሞ በስድስት ዓመት ውስጥ ሠላሳ አንድ ነገሥታትን ድል እንዳደረገ አነበብኩ:: ስጨርስ በጣም ነበር የገረመኝ:: እንዴት ኢያሱ ጸሐይን ባለችበት እንድትቆም አዘዛት? እንዴት ጨረቃን ባለችበት እንድትቆም አዘዛት? እያልኩ ራሴን ጠየኩኝ:: አሁን ድረስ ድንገት ቀን ላይ ጸሐይን ስመለከት ሆነ ማታ ላይ ጨረቃን ስመለከት ትዝ የሚለኝ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያነበብኩት የኢያሱ ታሪክ ነው:: የሚገርምሽ እናቴ ግን ከመፅሐፍ ቅዱስ ውጪ ሌላ አታነብም:: ድሮ ታዋቂ ደራሲዎች መፅሐፍ አወጡ ሲባል እየፈለገች ታነብ ነበር፤ በቅርቡ ግን ያን ሁሉ ትታ የምታነበው መፅሐፍ ቅዱስን ብቻ ነው:: ያው እኔ እንደነገርኩሽ ኦርቶዶክስ እና ፕሮቴስታንት እምነት መሀከል እያደኩ ስለሆነ ኦርቶፕሮቴ እምነት ተከታይ ነኝ ለማለት እችላለሁ:: ከእናቴ ጋር ኢየሱስ ጌታ ነው እላለሁ:: ከአባቴ ጋር ስሆን ድንግል ማርያም አንቺ ተለመኚኝ እላለሁ:: ከአባቴ ጋር ስሆን ኢየሱስ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም እላለሁ:: ከእናቴ ጋር ስሆን ኢየሱስ ፈራጅ እና አማላጅም ነው እላለሁ:: አንቺ ግን ኦርቶዶክስም? ካቶሊክም? ፕሮቴስታንትም አይደለሽም? በሳይንስ ታምኚያለሽ እንዳይባል መፅሐፍ ቅዱስን ታነቢያለሽ? ምናልባት ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው ጊዜው ሲደርስ ሃይማኖት ይኖርሽ ይሆናል አይደለም?"

"ልክ ነሽ!!" በማለት ነበር የመለስኩላት:: ቤተል እቅድ የላትም:: በማቀድም አትኖርም:: ከክፍላችን ተማሪዎች ደስ የምትለኝ እርሷ ነች:: በአዲሱ ዓመት ክፍላችን ውስጥ አንዲት አዲስ ተማሪ መጣች:: ራሷን ለክፍሉ አስተዋወቀች:: ሀቁን ለመናገር በጣም የምታምር፣ ደስ የሚል ቁመና ያላት፣ ደስ የሚል የሰውነት ቅርፅ ያላት፣ ደስ የሚል ደም ግባት ያላት ቀይ ልጅ ነች:: ክልስ ቢጤ መሆኗን በቀላሉ አይቶ መናገር ይቻላል::

"የመጣሁት ከታሪካዊት ጎንደር ከተማ ነው:: ስሜ ሶስና ዱማስ እባላለሁ:: ከኢትዮጵያዊት እናት እና ከፈረንሳዊ አባት የተወለድኩ ነኝ:: አዲስ አበባ የመጣሁት ለአንድ ታዋቂ አለም አቀፍ የማስታወቂያ አሰሪ ድርጅት ለመስራት እዚህ የውክልና ቢሮ ስላላቸው ነው:: በቅርቡ የሚለቀቁ ማስታወቂያዎች አሉኝ፤ ከዚያ በተጨማሪ በቅርቡ ለገበያ የሚውል የሙዚቃ ስራዬንም ጨርሻለሁ! በማስታወቂያ እና በሙዚቃ ስራ የተወጠርኩ ብሆንም እናቴና

አባቴ በትምህርት ላይ ቀልድ ስለማያውቁ ጠንካራ ተማሪም ነኝ፤ በእርግጥ አንደኛ ወጥቼ ባላውቅም እስከ አምስተኛ ግን እወጣለሁ፤ በዚህ አጋጣሚ እናንተም ከትምህርት ጎን ለጎን የተፈጥሮ ተሰጥኦ ካላችሁ እንድትጠቀሙበት እነግራቹዋለሁ፤ በተረፈ ስላገኘዋችሁ ከልቤ አመሠግናለሁ" በማለት ተናገረች፡፡ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማውት ውብ ተሰረቅራቂ ድምጽ የዚች ሶስና የተባለች ልጅ ይመስለኛል! በጣም የሚያምር ድምፅ ነበራት! አላትም! ይህን ደግሞ ወዲያው እርግጠኛ የሆንኩት አጠገቤ በምትቀመጠው ጓደኛዬ ቤተል ጭምር ነው፡፡

"ዋው የአንቺ ድምፅ ያምራል! የዚች ልጅ ድምጽ ደግሞ ውብ ነው! ዘፋኝነት ሀጢያት ስለሆነ ይቺ ልጅ ሙዚቃ ካወጣች ይህን የመሰለ ድምጽ ይዛ ሲኦል ልትገባ እኮ ነው! አታሳዝንም? ምናልባት ፈጣሪ ይህን ውብ ድምፅ የሰጣት ለዘፋኝነት ሳይሆን እንደዳዊት ለፈጣሪ ምስጋና እንድታቀርብበት ይሆናል" አለች፡፡ በእርግጥ ሙዚቃ ሀጢያት ነው? ሙዚቃ መስማት ራሱ ሀጢያት ነው? ሙዚቃ ሀጢያት አይደለም? የሚለው ርዕስ ለዘመናት አወዛጋቢ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ስለ ሙዚቃ ሀጢያት ነው አይደለም የሚለውን ርዕስ በተመለከተ ስለሙዚቃ ከአንቴ ጋር ያወራሁትን አስቀድሜ ስለተናገርኩ በድጋሚ ይህን ሀሳብ ማንሳት ማንዛዛት ስለሚሆንብኝ እዘለዋለሁኝ...

አዲሷ ተማሪ ሶስና እንዳለችው ይህን ባለች አንድ ወር ሲሞላት ማስታወቂያዋ በተለያዩ ድህረገፆች ላይ መውጣት ያዘ፡፡ ወዲያው ወደ ሂፕ ሆፕ የሚያመዝነው ኢንግሊዘኛ ሙዚቃዋ ተለቀቀ፡፡ ተማሪዎች ሁሉ ለጉድ ሰሙት፡፡ የት/ቤታችን ቁጥር አንድ ዝነኛ ሆነች፡፡ የተለያዩ ተማሪዎች ከዚች ወጣት ባለ ውብ ድምፅ የት/ቤታችን ዝነኛ ተማሪ ጋር ጓደኛ ለመሆን ሲራወጡ አየሁኝ፤ በተለይ ወንድ ተማሪዎች ለፍቅረኝነት ሊጠብሷት ሲራወጡ አየሁኝ፡፡ አንዳንድ ሴቶች በአድናቆት ሲመለከቷት እንዲሁም በርከት ያሉ ሴቶች ደግሞ በቅናት ሲመለከቷት ታዘብኩኝ... የልጅቷ የመግባባት ክህሎት በጣም የሚደንቅ ነው፡፡ በአጭር ወር ውስጥ ከሁሉም ጋር በቀላሉ ለመግባባት ችላ ነበር፡፡ ያ የተረገመ እኔን በጅንጀና አጣድፎኝ ያልተሣካለት ቀበኛው! ፌጠኛው! እና ጉላንጁ የፊዚክስ አስተማሪ እሷንም ከፍተኛ ጅንጀና እንደፈፀመባት ተባራሪ ወሬ ወዲያው ደረሰኝ... ብቻ ይህም ያም እየተከናወነ ሳይታሰብ ቀናት ቀለጡ፡፡ የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት አለቀ፡፡ እንደተለመደው አንደኛ ወጣሁ፡፡ ሶስና እንዳለችው ዝነኝነቷ፣ ሙዚቀኛነቷ፣ ማስታወቂያ ስራነቷ አንዳችም ሳያዘናጋት

አራተኛ ወጣች:: የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ትምህርት እንደተጀመረ ግን የት/ቤቱ ተማሪዎች ሁሉ ጉድ አሉ:: ወሬው ሁሉ የሶስና ጉዳይ ሆነ! ሴቶችም ሆኑ ወንዶችም ወሬውን ለጉድ አራገቡት:: ትልቁን ሰበር ዜና ለእኔ መጀመሪያ በመምጣት ሹክ ያለችኝ ጓደኛዬ ቤተል ናት

"ሰበር ዜና"

"ምንተገኘ?"

"የት/ቤታችን ባለትልቅ ጭንቅላት ተማሪ የሆነችው ወ/ት ልዑል ታሪክ ሰራች" አለች በልዑል ላይ በማሾፍ::

"የምን ታሪክ?"

"የሶስናን እነዚያን ስንቱ የሚመኛቸውን ውብ ከንፈሮች ሳመ! ያንን ውብ ከንፈሯን ገመጠው! አሉ፤ በእርግጥ በዓይኔ አላየሁም፤ ግን ስራዬ ብዬ እከታተላቸዋለሁ! ተማሪው ሁሉ የሚያወራው ግን ይህን ነው:: ልዑል ምን ዓይነት መስተፋቅር አሰርቶባት ይሆን ያቺን የመሰለች ሴት ከዚያ ግሸጣ ላይ ልጥፍ ያለችበት? እያሉ ነው:: እኔም በጣም አስማት ሆኖብኛል"

"ምናልባት የልዑልን የጭንቅላት ውበቱን አድንቃው ይሆናል፤ በዚያ ላይ የእያንዳንዱ ሰው ፍላጎት የተለያየ ነው:: አንድ የፍቅር መፅሐፍ ላይ እንዳነበብኩት 'ፍቅር መብረቅ ነውና ይቺ ሴት ይህን ወንድ እንዴት ልትወደው ቻለች? ፍቅር የለም የሚሉትን ለማሳመን ይህን መሰል ጉድ የሚያስብል ቁርኝነት ይከስታል' ይላል:: ይህ እውነት ይሆናል፤ ምናልባት ደግሞ ሁለቱ ላይ የተፈጠረውም ይህ ክስተት ይሆን? በዚያ ላይ የሰው ልጅ ከውጫዊ ውበት ውስጣዊ ውበት አይበልጥም?" ይህን ባወራን በአራተኛው ቀን በእርግጥም የት/ቤታችን ግዙፍ ጭንቅላት ያለው ልዑል የዚያችን አዲስ የት/ቤታችንን ዝነኛ ተማሪ ውብ ከንፈር ሲገምጥ እኔና ቤተል በዓይናችን ተመለከትን:: ወይ ፍቅር... ብለን ተገረምን::

ይህ የፍቅር ወሬ ግን የት/ቤቱ አብይ የመነጋገሪያ ርዕስ በመሆን ከግንቦት አስር በላይ ሊጓዝ አልቻለም፤ ምክንያቱም ወዲያው ወሬው ሁሉ የብሔራዊ ፈተና መድረስ ሆነ:: የሶሻል ይሁን የሳይንስ ተማሪዎች ወሬ ስለ ብሔራዊ ፈተና መድረስ ብቻ ሆነ:: ለወትሮ ከፍት

የነበሩት የቤተመጽሐፍት ወንበሮች ከጠዋት እስከ ማታ ግጥም ብለው ይሞሉ ጀመር:: ትንሹም ትልቁም ተማሪ ማጥናቱን ተያያዘው

እነሆ ብዙ የተወራለት አገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ደረሰ:: ተጀመረ:: አለቀ:: በእርግጠኝነት አሪፍ ውጤት እንደማመጣ ገመትኩኝ:: የት/ቤቱ ተማሪዎች ባዘጋጁት የመለያያ ጭፈራ ላይ ግን አልተገኘሁም:: መገኘትም አልፈለኩም ነበር:: እስከዛሬም ት/ቤታችን ተዘጋጅተው በነበሩት የቀን ጭፈራ ይሁን ልዩ ልዩ በዓላትን አስመልክቶ በሚዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ አልተገኘሁም:: ይህን መሰል ኳኳታ አይመስጠኝም:: አንቴ እነዚህን መሰል ዝግጅቶች ላይ ሄደሽ ዘና በይ ይለኛል፤ እኔም እስቲ ልሞክረው በማለት አንድ ሁለት ጊዜ ለመቀላቀል ጥሬ ነበር:: ሙዚቃው፣ ጫጫታው፣ ግርግሩ፣ራስን ለመርሳት የሚደረገው ጥረት፣ አንዱ ከአንዱ ለመበላለጥ የሚደረገው ከንቱ የወጣትነት ፉክክር፣ መጀናጀኑ በተለይ የሴቶቹ ጫጫታ፣ የሴቶቹ ቁልት ማለት፣ የወንዶቹ ባዶ ጉራ... ወዘተ ሰላሜን ነሳው:: ውስጤን ረበሸኝ እናም ሁለተኛ ላለመሄድ ወሰንኩ፤ በዚህ የተነሣ የዓመቱ አጠቃላይ የመለያያ ዝግጅት ላይም አልተገኘሁም... በቦታው የነበረችው ቤተል ወሬውን እንደዘገበችልኝ ግን ብዙ ተማሪዎች ከመጠን በላይ ከባድ ከባድ መጠጦችን ጠጥተው በመስከር ተዝረከርከው እንደ ነበር... ሲሳሳሙ እንደነበር... ወሲብ ሁሉ ማንንም ሳይፈሩ በየጥጋጥጉ ቆመው ሲያደርጉ እንደነበር በሌላ በኩልም መጠጥ ጠጥተው የማያውቁ ተማሪዎች ደግሞ "ከጓደኛዬ በምን አንሳለሁ" በሚል አጉል ፈሊጥ እና "ኧረ ጠጣ! ኧረጠጪ! ለዛሬ ግድ የለም" በሚል የጓደኞቻቸው ግፊት የተነሣ ጠጥተው ሲያስታውኩ፣ መሬት ላይ ሲዝረከረኩ በተለይ አንዳንድ ባለጌወንድ ተማሪዎች ሆን ብለው ሴቶችን ከለስላሳ ጋር አልኮል ቀላቅለው በመስጠት ከሴቶቹ ጋር ወሲብ ሲያደርጉ እንደ ነበር በተጨማሪም አንዳንድ ተማሪዎች በተለይ ሴቶች ድንግልናችንን ከዩኒቨርሲቲ በፊት አስወስደን መገላገል አለብን በሚል አጉል እምነት እና የጓደኞቻቸው ግፊት የተነሣ ሆን ብለው ራቁት ቀረሽ አልባሳትን ለብሰው በመምጣት ራሳቸውን ለወሲብ አመቻምቸው ወሲብ ማድረጋቸውን የዜና ምንጬ ቤተል ነግራኛለች፤ ከዚያ የቤተል እቅድ ትዝ አለኝና በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ

"አንቺስ?" አልኳት::

"ህሳቤን ቀየርኩ"

"ማለት?"

"በእርጋታ ሳስበው ድንግልና አንድ ጊዜ ከሄደች አትመለስም:: ይቺን አንድ ጊዜ ከሄደች የማትመለስ ውድ የሴቶች ስጦታ እንዲያው በዋዛ ለማንም ሳይሆን ፍቅር ሲይዘኝ እና ልጁን በጣም ከወደድኩት ለእሱ ለመስጠት ወስኛለሁ እንጂ ለማንም መንገደኛ ድንግልናዬን አልሰጥም፤ ስለዚህ አንድ የምወደው ፍቅረኛ እስከሚኖረኝ ድንግሌን እጠብቃለሁ! ከዚያ በተረፈ እናቴ ልትነቃብኝ በማትችልበት ደረጃ በመጠኑ ጠጥቼ ነበር፤ የተወሰኑ ወንዶች በጣም ሊሸውዱኝ ከፍተኛ ሴራ አሴረውብኝ ነበር፤ ግን አልሸወዱኝም ባጠቃላይ በጣም ደስ የሚል በሌላ በኩልም በጣም የሚያስጠላ ዝግጅት ነበር ባጭሩ ይህን ይመስል ነበር" በማለት ነበር የዘገበችልኝ:: የዓመቱ የት/ቤት ህይወት በዚህ መልኩ አበቃ:: የህይስኩል ህይወትም በድጋሚ ተመልሶ ላይመጣ በዚው አለቀ:: ክረምት ላይ እንደተለመደው የፒያኖ ትምህርት እና ካራቴ ትምህርቴን ቀጠልኩ:: አንዳንዴ የአዲስ አበባ ክረምት ያስጠላል:: ዝናቡ እኛኝ ማለት ይወዳል፤ በዚህ አንጻርስ የደብረማርቆስ ክረምት ይግደለኝ...

አንድ ቅዳሜ እኝኝ በሚለው ዝናብ ዣንጥላ በመያዝ የፒያኖ ት/ት ቤት ሄጄ ስመለስ አቤት ካሉት እጅግ በርካታ የአጎቴ ከምር ቀደምት መፅሐፍት ይልቅ ምናልባት አዲስ የወጣ አሪፍ መጽሐፍ ካለ ለመግዛት የመፅሐፍ ደንበኛዬ ጋር አመራሁ:: ሠላምታ ተለዋወጥን::

"እሺ ምን አዲስ አለ?" አልኩት::

"ታዋቂ የሚባሉት በሙሉ አዲስ አላወጡም አንቺ ግጥም አትወጂም አይደለም?" አለኝ በጣም የሚያሳዝን ዓይን ያለው የመፅሐፍት ነጋዴ ደንበኛዬ::

"ይለፈኝ" አልኩት:: ከፍቅር ነክ ጉዳይ በስተቀር የአገራችን ግጥሞች አሪፍ አሪፍ ሀሳብ ስለሌላቸው ማንበብ አልወድም:: የግጥም መፅሐፍትን::

"ደቂቀ እስጢፋኖስን አንብበሸዋል?"

"ወስጃለሁ"

"አ... አዲስ ትላንት የመጣ መጽሐፍ ነው:: ይህን አንቢቢዋ" በማለት አንድ መፅሐፍ አቀበለኝ:: አነሳሁት:: ርዕሱን ሳነበው ወዲያው ትዝ ያለን አጎቴ ሰቅራጥ ነው:: ይህን ቃል ሲጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት አጎቴን ነውና:: መፅሐፉ የተዘጋጀው ሊሊ ሽመከት በምትባል ሴት ሲሆን ርዕሱ "የዝሙት ባንዲራ!" ይላል:: በቅንፍ ውስጥ "በኢትዮጵያ ምድር ላይ እየተከናወነ የሚገኝ አስደንጋጭ እውነተኛ ታሪክ" የሚል መግለጫ አለው:: ሌላ አዲስ መፅሐፍ ስላልነበረ ይህን መፅሐፍ ለማንበብ ሂሳቡን ከፍዬ ወደ ቤቴ እኝኝ በሚለው ዝናብ ውስጥ መገስገስ ያዝኩኝ::

# 3

# የገዘሙት

# ባንዲራ

## (አስቀያሚው እውነተኛ ታሪክ)

ይህ አስደንጋጭ እውነተኛ ታሪክ የእኔ የሊሊ ሽመክት ታሪክ ነው:: ተወልጄ ያደኩት ከአዲስ አበባ 114 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ወሊሶ ከተማ ነው:: የዛሬን አያድርገውና በ1948 አካባቢ የዛሬዋ ወሊሶን ንጉስ ኃይለስላሴ ጊዮን ብለዋት ነበር:: በዚያን ዘመን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ስለነበራት ዝነኛ ከተማ ነበረች፤ በዚያ ላይ የሚያምር ፍልውሃም ስላላት የቱሪስቶች መዳረሻ ነበረች:: ምን ያ ብቻ አስገራሚ የተፈጥሮ ውበት ያለው ወንጪ ሀይቅም ከወሊሶ ምድር ስለሚገኝ የደቡብ ምዕራብ ሸዋዋ የኢትዮጵያ ከተማ ወሊሶ ዝነኛ ነበረች:: በአሁኑ ወቅት ከ40 ሺ ህዝብ በላይ ያላት ወሊሶ በሃይማኖት ረገድ 63% ህዝቡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሲሆን 19% የፕሮቴስታንት ፣ 16% እስልምና እንዲሁም 0.2% ሃይማኖት የለሽ ናቸው:: በዚህ አጋጣሚ የተፈጥሮ አድናቂ የሆናችሁ አስደናቂውን እና አስፈሪውን የወንጪ ሀይቅን ሳትመለከቱ እንዳያልፋችሁ! በፍልውሃውም መንፈሳችሁን ማደስ ትችላላችሁ:: ከዚው ከወንጪ ሀይቅ ጋር በተያያዘ በአገራችን ሁለት ወደ አምልኮ የሚጠጉ እምነቶች አሉ:: በዚህ መሠረት ወንጪ ሀይቅ ከደረቀ እና ጎንደር ከተማ ከፋሲል ቤተመንግስት ፊት ለፊት የሚገኘው "ጃን ተከል ግዙፍ ዛፍ መሬት ቅርንጫፎቹ ከነኩ ኢትዮጵያ ትናወጣለች! በኢትዮጵያ ምድር የማያባራ ጦርነት ይነግሣል:: ከዚያ በኢትዮጵያ ምድር ታላቅ ደም መፍሰስ ይከሰታል" የሚል ትንቢት አለ ስለሚባል ወንጪ ሀይቅ እና ጃን ተከል ግዙፍ ዛፍ በትኩረት ይጠበቃሉ ፣ ለማንኛውም ወደ ዋናው ነጥቤ ልመለስ:: ወደ ራሴ ታሪክ:: እኔ በተወለድኩበት ቤተሰቦቼ ውስጥ በዛር የተወረሰ የቃልቻ መንፈስ ያለባቸው ፣ ራሳቸውን ለተለያዩ ኢጋንንታዊ አሠራር የሸጡ እና ለሴይጣን አምልኮ የሰጡ ናቸው:: እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ ለቃልቻ ግብር የተሰጠሁ ሴት ነበርኩ:: በግድ ደፍሮኝ ሳይሆን በከፍተኛ ልመና አግባብቶኝ የመጀመሪያ ወሲቤን ያደረኩት ለሴይጣን ቤት አሳልፎ ከሰጠኝ እውነተኛ አባቴ ጋር ነበር:: ከአባቴ በመቀጠል ከባለቃልቻው ጋር ወሲብ በተለያዩ ጊዜያት አድርጌያለሁ:: እንደ አምስተኛ ሚስቱም ስለምቆጠር ሐሙስ ሐሙስ ብቻ ከእኔ ጋር ሌላ ውብ ሴት እስከምትመጣ ድረስ ለሶስት ዓመታት ተጠቅሞብኛል:: እርግዝና የሚባል ግን አልተከሰተብኝም::

የቃልቻው ቤት ውስጥ እጅግ ብዙ ሰዎች ይመጣሉ:: ከዚህ ግቢ ውስጥ መውጣት ስለማይፈቀድልኝ ብዙ አስገራሚ ጉዶችን ለማየት ችያለሁ:: እጅግ ስመጥር አትሌቶች ፣ ዝነኛ

በለቲከኞች ፣ ነጋዴዎች፣ ቄሶች፣ ሰባኪዎች፣ ዝነኛ ሙዚቀኞች፣ አሮጊቶች ወጣቶች… ብቻ አያሌዎች በተለይ ሮዕቡ፣ አርብ እና እሁድ ሲመላለሱ አይቼያለሁ:: የጋሼ እግር ስር ሲወድቁ አይቻለሁ:: መሬት ሲልሱ አይቻለሁ! የጋሼን በረከት ሲቀበሉ አይቻለሁ! ምን ይሄ ብቻ የህግ ሰዎች፣ ዶክተሮች ፣ ሹፌሮች፣ ዘማሪዎች ፣ ፖሊሶች… ሲመጡ መምጣት ብቻ አይደለም የጋሼን እግር ሲልሱ በዓይኔ አይቻለሁ… ብቻ ለእናንተ በዝርዝር ብዙ የማይነገር ጉድም አይቻለሁ!! ልክ አስራ ሰባት ዓመት ሲሞላኝ ከምሽቱ ስንት ሰዓት እንደሆነ ሰዓት ስለሌለኝ ባላውቅም የተኛሁበት ክፍል ውስጥ መልኩን ለማየት የማልችለው ሰው ወይም የሰው ስጋ የለበሰ መንፈስ በጣም የሚያምር ውድ ሱፍ ልብስ ለብሶ መጣ:: በጣም በሚያምር እና እርጋታ ባለው ድምፅ

"ተነሺ ! ተነሺ! ተነሺ!" በማለት ሶስት ጊዜያት ጠርቶ ቀሰቀሰኝ::

"አንተ ማን ነህ?" በማለት ጠየኩት::

"አለቃሽና ጌታሽ አስማንዲዮስ ነኝ!"

"ማን ነው አስማንዲዮስ?"

"ስለማንነቴ እነግርሻለሁ"

"እና?"

"አንቺ የእኔ ነሽ! በአባትሽ በኩል አንቺ ውስጥ በወሲብ አማካኝነት ደሜን ከደምሽ ቀላቅያለሁ! መንፈሴን ከመንፈስሽ አዋህጄያለሁ! ያንቺ ነፍስ እና እስትንፋስ የእኔ ነች፤ ስለዚህ አንቺ የእኔ ንብረት ነሽ! ከእኔ ጋር ዋጅቼሻለሁ፤ ንብረቴ አድርጌሻለሁ! ከዛሬ ጀምሮ የእኔን ስራ ብቻ ትሰሪያለሽ! ከእኔ ማምለጥ አትችይም! ቀላል ስራ ትሰሪያለሽ! በመጨረሻ የክብር ስጦታሽን አበረክትልሻለሁ"

"ምንድነው ስራው?"

"እንዳልኩሽ የምጠራው አስማንዲዮስ እየተባልኩ ነው:: እኔ የጥልቁ መንፈስ አባል ስሆን በትዳር ማናጋት ላይ የተመደብኩ እና ሰዎችን በወሲብ ወጥመድ የማስር ነኝ! አንቺን ለዚህ አላማዬ በክብር መርጬሻለሁ እና ጊዜሽ ስለደረሰ ከእኔ ጋር ትሰሪያለሽ!"

"ምን?"

"ከአንድ ሺ ሰዎች ጋር ዝሙት ትፈፅሚያለሽ!"

"እህ?"

"እደግምልሻለሁ! ከአንድ ሺ ሰዎች ጋር ዝሙት ትፈፅሚያለሽ!"

"በጭራሽ ይህን ላደርግ አልችልም"

"ትችያለሽ! በአባትሽ በኩል አንቺ ውስጥ ገብቻለሁ አንቺ የእኔ ነሽ እናም ትችያለሽ"

"አላደርገውም"

"በትህትና የጠየኩሽን እንቢ ካልሽ ቀላል ቅጣት እቀጣሻለሁ"

"የምን ቅጣት"

"ይቅር በለኝ ጌታዬ አስማንዲዮስ ሆይ ብለሽ ስሜን እየደጋገምሽ በክብር እስከምትጠሪ ድረስ እቀጣሻለሁ" በማለት የእኔን ምላሽ ሳይጠብቅ ተሰወረ:: በነጋታው ይህን ነገር ከእኔ ጋር ላሉት ለአንዳቸው ለመናገር አስቤ ግን ፈርቼ ዝም አልኩ:: ይህ በሆነ ሁለተኛው ቀን ሙሉውን ቀን ሲነስረኝ ዋለ:: ይህ አልበቃሽ ብሎኝ አመሻሽ ላይ ነስሩ ሲቆም መላው ሰውነቴ በቡግር ተወረረ:: ምን ይሄ ብቻ በየአንድ ሰዓት ልዩነት ውስጥ ከብልቴ ትል መውጣት ያዘ:: በቃላት የማይገለፅ ስቃይ ፣ በቃላት የማይገለፅ ህመም፣ መከራ በዛብኝ እናም ይህን ስቃይ ጨርሶ ልቋቋም አልቻልኩኝምና ይህ በሆነ በነጋታው ያለኝን ሀይል አሰባስቤ ምሽትን ጠብቄ "ይቅር በለኝ ጌታዬ አስማንዲዮስ ሆይ" በማለት ጥሪ አሰማሁኝ:: ግን ምንም ምላሽ የለም:: በነጋታው ህመሜን መቋቋም በጣም ስላቃተኝ "እባካችሁ ሆስፒታል ውሰዱኝ!" በማለት እያለቀስኩ ለመንኩ ፣ ግን ማንም የሰማኝ አልነበረም ፣ ለነገሩ ቢሰሙኝም ደፍሮው እኔ ክፍል አይገቡም፤ ምክንያቱም አንዳች ጥፋት አጥፍቼ ቅጣት እየተቀበልኩ መሆኔ ስለሚገባቸው ለእኔ እርዳታ ቢያደርጉ በራሳቸው ላይ ጣጣ እንደሚመጣባቸው ስለሚያውቁ አንገታቸው ቢቆረጥ እንኳ እኔ ክፍል ውሃ ለመስጠት እንኳ ብቅ ከማለት እግራቸውን ቆልፈው ይቀመጣሉ:: ይህን በሚገባ እኔም ስለማውቅ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ተቀመጥኩ:: ይበልጥ ሆዴ መነፋፋት ያዘ:: መላው ሰውነቴ ሽባ መሆን ያዘ:: ምግብ የሚባል እስካሁን አልቀመስኩም:: ሰው ያለ ምግብ ስንት ቀን መቆየት ይችላል? በህመሙ ብዛት እና በምግብ እጦት ሰውነቴ ዝሏል! ውሃ ሆኗል! ከመሞቴ በፊት የመጨረሻ እድሌን ለመጠቀም እንደምንም በማለት ምሽት ላይ "ይቅር በለኝ ጌታዬ አስማንዲዮስ ሆይ! እባክህ እሺ ጌታዬ አስማንዲዮስ ሆይ!" አልኩኝ:: ይህን ካልኩ ከጥቂት ደቂቃ በኃላ ያናገረኝ ሰው መጣ:: አሁንም መልኩን ለማየት አልቻልኩም::

"ተስማማሽ?"

"ተስማምቻለሁ ግን ጌታዬ"

"ግን ምን?"

"እኔ ለዘመናት ከዚህ ግቢ ወጥቼ አላውቅም:: ትምህርት እንኳ አልተማርኩም፣ የመናገር ችሎታም የለኝም፣ ከሰዎች ጋር ማውራት እፈራለሁ፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ጌታዬ? እኔ እኮ ዓይነአፋር እና አንዲት ፈሪ ሴት ነኝ" አልኩኝ:: በጣም የድካም ስሜት ባዘለ ድምፅ::

"አትፍሪ! እኔ አንደበት እሆንሻለሁ! አንደበትሽን ከምታስቢው በላይ እከፍተዋለሁ! የፈለግሽውን ቋንቋ እንድትናገሪ አደርግሻለሁ! የተለያዩ የአገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ቋንቋዎችን እንድትናገሪ አንደበትሽን እከፍትልሻለሁ! በድፍረት እና በራስ መተማመን እሞላሻለሁ! የወንዶችን ማጥመጃ ጥበብ እሰጥሻለሁ፤ ስለዚህ ከሁለት ቀናት በኋላ ለማንም ሳትናገሪ እና ማንንም ሳታስፈቅጂ ከዚህ ለዘመናት በእስር ከታሰርሽበት ቤት ውጪ! አዲስ አበባ ሂጂ! በ098440... ስልክ ደውለሽ አወል ዋለልኝ የሚባል ወጣት ጋር ተገናኚ:: ምንም እንዳትፈሪ! እኔ ካንቺ ጋር ስለሆንኩ ሁሉን ነገር አሳካልሻለሁ! ከፊት ከፊትሽ በመቅደም መንገዱን እጠርግልሻለሁ! እመራሻለሁ! በመኝታሽ ሰዓት ከግራ እና ከቀኝሽ አባብ እና ዘንዶ ይጠብቁሽ ዘንድ አብረውሽ ስለሚተኙ ጨርሶ እንዳትሰጊ! ከአንድ ሺ ወንዶች ጋር ወሲብ አድርገሽ ስትጨርሺ ሽልማቴን ስጠኝ ጌታዬ አስማንዲዮስ ሆይ በማለት ጥሪኝ" በማለት ተሰወረ:: በነጋታው ስነሣ ሙሉ ጤነኛ ነበርኩ:: ነስር የለም! ትል ከብልቴ መውጣት የለም! የሆድ መነፋፋት የለም! ብቻ አንዳችም የበሽታም ሆነ የህመምም ስሜት አልነበረብኝም:: ቀኑን ሙሉ ከነበርኩበት ግቢ አልወጣሁም:: ከሰላምታ ባለፈ ስለሆነው ነገር ከማንም ጋር አልተነጋገርኩም:: ማንም ምን ሆነሽ ነበር ብሎ የጠየቀኝም አልነበረም:: ተኝቼ ዋልኩ:: ምሽት ላይ ራት ነገር በላሁ:: ከዚያ ተመልሼ ተኛሁ:: በጠዋት በመነሳት ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ለዘመናት በእስር ከኖርኩበት የባለቃልቻው ትልቅ ግቢ የመሳፈሪያ ገንዘብ ብቻ በመያዝ ወጣሁ:: በጣም የሚገርመው ከሶስቱ ጥበቃዎች አንዳቸው እንኳ እንደ ሌላው ጊዜ "አንቺ ተመለሽ! የት አባሽ ትሄጃለሽ?" ያለኝ አልነበረም፤ በዚህ ሁኔታ ተገረምኩ! በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእስር ተፈትቼ ነፃ አየር በመተንፈሴ እጅግ ደስ አለኝ:: አዲስ አበባ መጣሁ::

በስም ብቻ የማውቃት አዲስ አበባ እንደ ደረስኩ በቀጥታ የደወልኩት ከጌታዬ

እስማንዲዮስ የተሰጠኝ ሞባይል ቁጥር ላይ ነበር፡፡ 098840... በአንደኛው ጥሪ ነበር ሞባይሉ የተነሣው

"ሀሎ"

"ሀሎ"

"አወል ዋለልኝ ነህ? ሊሊ ሽመከት እባላለሁ ከወሊሶ ነው የመጣሁት"

"መጣሽ ሊሊ አሁን የትነሽ?"

"አውቶቢስ ተራ መናሐሪያ ውስጥ"

"በቃ እዛው ያለው ካፍቴሪያ ውስጥ ሻይ ቡና እያልሽ ጠብቂኝ አሁኑኑ እመጣለሁ"

"ስልክ የለኝም በሱቅ ስልክ ነው የደወልኩልህ"

"እሺ እስከዛ ሻይ ቡና ውሰጂና ትንሽ ቆይተሽ ከመናሐሪያ አጠገብ ያለው አዲስ ከተማ ት/ቤት በሩ ጋር ጠብቂኝ ቀይ ያሪስ መኪና ነች ፤ በፍጥነት እመጣልሻለሁ፡፡ ከላይ ቀይ ጃኬት እና ቀይ ኮፊያ አድርጌያለሁ"

"እሺ እጠብቃለሁ"

ሰዓት ስለሌለኝ በግምት ስልኩ ከተዘጋ 30 ደቂቃ በኋላ የደወልኩለት ወጣት መጣ፡፡ ቀይ... ቀይ... ቀይ... የሚል ምልክት ስለሰጠኝ ወዲያው ነበር ያወኩት፡፡

"አወል ዋለልኝ እባላለሁ" በማለት ራሱን አስተዋወቀኝ፡፡ ኢንግሊዝ ኢንባሲ ፊት ለፊት የሚገኝ ቤት ወሰደኝ፡፡ የሚያምር ግዙፍ ግቢ ነው፡፡ በድንጋይ የተሠራ፡፡ ቤቱ ውስጥ ሠራተኛ እና ጥበቃ ብቻ አሉ፡፡ አወል አዲስ አበባን ለሶስት ቀናት አሳየኝ፡፡ በህይወቴ ለመልበስ ቀርቶ አይቼ እንኳን የማላውቃቸውን እጅግ በርካታ የሚያምሩ ውድ አልባሳትን ገዛልኝ፡፡ ሌላ ሴት እንደሆንኩ ለራሴ በጣም ይታወቀኛል፡፡ ውስጤ የነበረው ያ የፍርሃት መንፈስ አሁን የለም! በኩራት እየተጀነነች የምትራመድ ወጣት ሆኛለሁ! ኢንግሊዝኛ ሲያወሩ ትርጉሙ በሚገባ ይገባኛል፡፡ ትግርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ወላይትኛ... ሁሉንም ቋንቋ ሲያወሩ ስሰማ በሚገባ ትርጉሙን እችላለሁኝ! ይህ ተዓምር አይደለምን?

በአምስተኛው ቀን አወልን ጥያቄ ጠየኩት፡፡

"አንት ስራህ ምንድ ነው?"

"የፀጉር ባለሙያ ነኝ፡፡ ጸጉር ቤት የሚመጡ ትዳር ያላቸውን ሴቶች የአባታችን መንፈስ እንዲገባባቸው እያደረኩኝ ነው፡፡ አሁን 820 ደርሻለሁ፡፡ በቅርቡ 1000 ሺ ሲሞላኝ

ትልቁ ሽልማቴን ከአባታችን አስማንዲዮስ እቀበላለሁ:: አንቺም ስራሽን ከነገ ወዲያ ትጀምሪያለሽ:: ቅድሚያ ግን ነገ ንቅሳት ቤት እወስድሻለሁ::

"ንቅሳት ቤት?"

"አዎ! ሰውነትሽ ላይ ሶስት ቦታዎች ንቅሳት ይሠራልሻል:: የአባታችን ተጨማሪ ኃይል በንቅሳቱ አማካኝነት ከደምሽ ጋር ይዋሃዳል:: ከዚያ ተጨማሪ መነቃቃት እና ጠላትን መዋጊያ ኃይል ጭምር ይሆንሻል ማለት ነው"

"ንቅሳቱን የሚሰጠው ግን ማን ነው?"

"የአባታችን አስማንዲዮስ አባላት ናቸው" አለኝ::

"ወንድም ሴትም አሉ:: ሁለቱም የአባታችን አስማንዲዮስ አባላት ናቸው" አለኝ::

ከዚያ እንዳለው በነጋታው በአዲስ አበባ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆነ አንድ ግዙፍ ህንፃ ላይ የሚገኝ ንቅሳት ቤት ወሰደኝ:: የሚያምር ወጣት እና በጣም የምታምር የተስተካከለ ቁመና እና የሰውነት ቅርፅ ያላት በዚያ የሚያምር ሰውነቷ ላይ ለጉድ ንቅሳቶች የተጥለቀለቀች ወጣት ተቀበሉን:: ከአወል ጋር ብዙ አወሩ:: የግራ እጄ ላይ እባብ... የቀኝ እጄ ላይ መስቀል... ጀርባዬ ላይ በትልቁ እኔ ራሱ እስከዛሬ ፍቺውን ያላወኩት በጣም አብስትራክት የሆነ ንቅሳት ተሰራልኝ:: ዘመናዊ ንቅሳት እጅግ በጣም ደቃቅ የሆኑ መርፌዎች ባሉት አስገራሚ ማሽን አማካኝነት የቆዳችን ውስጠኛ ክፍል በባዮሎጂ አጠራር Dermis ውስጥ የተለያዩ ቀለሞችን በማሽኑ በመርጨት የሚከናወን ስራ ነው:: በዚህ የተነሣ ውስጥ የዘለቀው ቀለም ውህድ እንደላይኛው የቆዳ ክፍል Epidermis በየጊዜው የማይፈቀፈቀውና የማይቀየረው ውስጣዊ የቆዳ ክፍላችን ቀለሙን እንደያዘ ለረጅም ዘመናት ይዘልቃል፤ ማንኛውም የንቅሳት ባለሙያ ጋር ቀርባችሁ ብትጠይቁት ምንም እንኳ ድብቁን እውነታ ቢያውቅም ለገንዘብ ሲሉ "ውይ አጉል ወሬ ነው እንጂ በንቅሳት የሚተላለፍ ምንም አይነት በሽታ ፈፅሞ የለም! ምክንያቱም የንቅሳት ማሽኑ ንጽህናውን የጠበቀ ነው! ቀለማቱም ሰውነታችን ውስጥ በመግባታቸው የሚያመጡት ችግር የለም:: እነ ዝነኛው ሜሲ፣ ኔማር፣ ቤካም፣ ዝነኛ ሙዚቀኞች፣ ዝነኛ አክተሮች፣ ዝነኛ ሰዎች ይነቀሱ የለም እንዴ? አንዳንድ ስለንቅሳት የማያውቁ ሰዎች የሚያስወሩት አሉባልታ ብቻ ነው" የሚል የአሮጊት ተረት የመሰለ የተሸመደደ ምላሽ ይሰጣቹዋል ፤ ይህ ግን ፍፁም ውሸት ነው፤ ምክንያቱም ለንቅሳት የሚውሉት ቀለማት 60% የሚሆኑት አለርጂን ይፈጥራሉ፤

ቆዳን ይሰነጣጥቃሉ ፣ ቆዳን ይልጣሉ፣ ሽፍታ እና እብጠት ያስከትላሉ፤ በተለይ በጥናት

እንደተደረሰበት ከሚነቀሱት ሰዎች ውስጥ 90% ለጉበት በሽታ ይዳረጋሉ፡፡ እንደው የሳይንስ እና የባዮሎጂ እውቀት እንኳ ባይኖራችሁ እንዴትስ ነው ቆዳችንን ዘልቀን ስንገባና ወደ ውስጠኛው የቆዳችን ክፍል ባዕድ ነገር እየጨመርን ለችግር የማንዳረገው? በሌላ በኩል እነዚህ የአባታችን የጋሼ መንፈስ የሰፈረባቸው የንቅሳት ባለሙያዎች አወል ዋለልኝ እንደ ነገረኝ ለንቅሳት ከሚመጡት ተማሪዎች፣ ሴተኛ አዳሪዎች እና ውበትን ፈላጊ ሴቶች ይሁን ወንዶች ላይ ምንም ነገር ሳያውቁ እና ሳይነገራቸው በንቅሳቱ አማካኝነት የአስማንዲዮስ መንፈስ እንደሚያጠልቁባቸው ነግሮኛል... ብቻ አወል ከወሰደኝ ዘመናዊው ህንፃ ላይ ከሚገኘው ዋነኛ አላማቸው ንቅሳት እየሠሩ ገንዘብ ማግኘት ሳይሆን ተመጣጣኝ ብር እያስከፈሉ ለንቅሳት የሚመጡት ላይ የጋሼን መንፈስ ለማስረፅ ስራቸውን በይፋ በስመንቅሳት ቤት እየሠሩ ከሚገኙት Natic tattoos ንቅሳት ጨርሼ ወጣሁ፡፡

የመጀመሪያውን ግዳዬን ለመጣል እና ስራዬን በይፋ ለመጀመር ተዘጋጀሁ፡፡ በነጋታው ከተገዙልኝ ውብ አልባሳቶች መሀከል ይበልጥ ውበቴን የሚያጎላውን እና ልዕልት የሚያስመስለኝን አልባሳት በመልበስ ወጣሁ፡፡ የመጀመሪያ ተልዕኮ ፣ የመጀመሪያ ግዳይ... ውስጤ ያለው የአባታችን አስማንዲዮስ መንፈስ እየመራ ጉርድሾላ የሚባለው ሰፈር የሚገኘው ካልዲስ ኮፊ ወሰደኝ... ገብቼ ተቀመጥኩ፡፡ የቤቱን ልዩ ጣፋጭ ቡና አዘዝኩኝ፡፡ ጨዋታው ተጀመረ፡፡ ፈረሱም ይሄው ሜዳውም ይሄው አለ የአገሬ ሰው!!

0001

የሚገርም፣ የሚደንቅ እና የማይታመን ነው፡፡ ለመሆኑ ውስጤ የነበረው ፍርሃት የት ጠፋ? ውስጤ የነበረው ሰውን ቀና ብሎ ያለማየት ፍርሃት የት ጠፋ? ያቺ ሰዎችን ቀና ብላ ማየት እንኳ የማትችል በቅቧቃ ሴት አሁን በአንድ ጊዜ እንዴት ደፋር ሆነች? አስማንዲዮስ ጨርሶ ሌላ ሴት እንዳደረገኝ በእርግጠኝነት አወኩኝ፡፡ እኔ ፍፁም ሌላ ሴት ነኝ፡፡ ሌላ ማንንም የማትፈራ፣ ደፋር፣ አንገቷን ቀና አድርጋ መንቀሳቀስ የምትችል በአንዳች አስገራሚ በራስ መተማመን መንፈስ የተሞላች ቆፍጣና ሴት! እነሆ ሴይጣን በእግሩ ስር ለወደቁት እና አንተ አባታችን ነህ ብለው አምነው ራሳቸውን አሳልፈው ለሸጡለት በሀይል ይሞላል!! ሴይጣን ከፀሐይ በታች የሆነችው ምድር የእርሱ ነችና ያልሆነውን እንድንሆን ማድረግ ይችላል፡፡ ለሴይጣን እኛን በሀይል መሙላት በጣም ተራ እና ቀላል ነገር ነው፡፡ ለሚያመልኩት መሻታቸውን ላለመስጠት ይሠጣል!! ይቺን ሀሳብ ልድገማት ሴይጣን ሀይል ይሰጣል ግን

የሚሰጣችሁ ላለመስጠት መስጠትን ነው! ይህ የሴይጣን እንቆቅልሽ ነው!!

ለማንኛውም ካፍቴሪያው ጥግ የተቀመጠ አንድ ዝንጥ ያለ ወጣት ተመለከትኩ፡፡ ከሌሎቹ ትኩረቴን እና ዓይኔን የሳበው መፅሐፍ እያነበበ ስለተመለከትኩት ነው፡፡ ስለ እርግዝና የሚያወራ መጽሐፍ ነበር የሚያነበው፡፡ የሚገርመው እኮ ከዚህ በፊት ለዘመናት በእስር የነበርኩበት ባለቃልቻው ቤት ውስጥ ቡና ከማፍላት፣ ሳር ከመነዝነዝ ፣ እጣን ከማጫጫስ እና ሐሙስ ሐሙስ ራሴን ለወሲብ ከማዘጋጀት ባለፈ ት/ቤት ሄጄ አላውቅም፡፡ ሀቁን ለመናገር የአማርኛ ፊደል ዘርን ሀ ሁ ሂ… እንኳ አላውቅም፤ ታዲያ እንዴት ማንበብ ቻልኩኝ? ይህን ቃል የገባልኝ አባታችን አስማንዲዮስ የሞላኝ ፀጋ ነው፡፡ እንኳን የአገሬን አማርኛ ቀርቶ ኢንግሊዝኛን፣ አብጠርጥሬ አነባለሁ! ሲያወሩ በሚገባ እረዳለሁ! ከኢንግሊዝኛ በተጨማሪ አረብኛ፣ መንደሪና፣ ፈረንሳይኛ፣ ስዋህሊ ቋንቋዎችን አውቃለሁ! ይህ የአባታችን አስማንዲዮስ አስገራሚ ስጦታ ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ሊታመን የማይችል ተረት ተረት ይመስላል፤ ግን በእኔ ህይወት ላይ የተከናወነ እጅግ አስገራሚ ትዕይንት ነው፤ እናም ያን የእርግዝና መፅሐፍ የሚያነብ ወጣት ተጠጋሁት

"ይቅርታ የእኔ ወንድም መቀመጥ እችላለሁ?" አልኩት፡፡ በትህትና፡፡

"ተቀመጪ!" አለኝ፡፡ በእጁ ጭምር ምልክት እያሳየኝ፡፡

"ሚስትህ እርጉዝ ናት?"

"ትክክል"

"ስንት ወር ሆናት?"

"ሶስት ወር ከ22 ቀናት"

"እሪፍ ጊዜ ላይ ነቻ! በአልትራሳውንድ ስካን ሆስፒታል ሄዳችሁ የልጃችሁን የስካን ፎቶ አያችሁ?"

"በሚገባ አይተናል"

"ፆታውስ?"

"ሴት ናት፡፡ የልጃችንን ስም ኢትዮጵያ ለማለት ወስነናል"

"ያድርግላችሁ፤ ግን በፓኪስታን ባህል ልጅ ሳይወለድ የልጅ ዕቃ መግዛት እና ላልተወለደ ልጅ ስም ማውጣት መጥፎ እድል ስለሆነ ሀጢያት ነው፤ ልክ እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ልጅ ሲወለድ ሴይጣን እንዳይጠጋው እያሉ መርፌ ፣ መርፌቁልፍ፣ ብረት ወዘተ

ከልጁ አልጋ እና ከልጁ እናት ላይ እንደሚያደርጉት ማለት ነው:: የሚገርምህ ይህን የሚያውቅ አንዱ ጅል ሀብታም ይህን ሰምቶ ሚስቱ ስትወልድ ግቢው ውስጥ ሴይጣን እንዳይገባ አንድ ሙሉ ሲኖትራክ ብረት አስገለበጠ አሉ:: ለማንኛውም እንደሳይንሱ ትንታኔ አንድ ጤነኛ ህፃን 40 ሳምንት ሲሞላው ይወለዳል:: በብዛት ለመወለድ ሲደርስ የፅንሱ ርዝመት 54 ሳሜ ርዝመት ይደርሳል:: አንዳንዴ ሴቶች 48ሳሜ ርዝመት ይኖራቸዋል:: አየህ ምድር ላይ የመጨረሻው ጉቶ የሚባለው ሰው ርዝመት ቢያንስ 56 ሳሜ ይደርሳል ማለት ነው:: ባለቤትህ አማረኝ እያለች ማስቸገር ጀመረች እንዴ?"

"ተጫወተችብኝ እንጂ ለምሳሌ መቼ ዕለት መንገድ ላይ አንድ ስልክ የሚያወራ ፌዴራል ፖሊስ አየችና እባክህ ፍቅሬ ያንን ፌዴራል ፖሊስ ስትመታው ማየት አማረኝ አለች:: ኧረ የህግ ሰው ነው እንዴት የህግሰው ይመታል? በዚያ ላይ የኢትዮጵያ ፌዴራሎች አንዳችም ቀልድ የማያውቁ እንደወረዱ ናቸው ቢገለኝስ? አልኳት በጭራሽ አልሰማህም ብላ ግግም ስትል ፌዴራል ፖሊሱ ጋር በመሄድ እባክህ የእኔ ጌታ ባለቤቴ እርጉዝ ነች አንተን እንድመታ አማረኝ ብላ አስቸገረችኝ መቼም የእርጉዝ ሴቶችን ጣጣ ታውቃለህ? እባክህ ትንሽ መታ ብቻ ላድርግህ? አልኩት፤ ከዚያ ያ ፌዴራል በቁጣ ግሎ 'ዋአይ ይቺ ወዲ ሽርሙጣ! እኔን እንዴት ምታልኝ ትልሀለች ይቺ ናይ የግንቦት ሰባት ተላላኪ' በማለት መሬት ላይ እያገላበጠ ጠብጥቦ... ጠብጥቦ... አንክቶ... አንክቶ... ለተጨማሪ ምርመራ አድራሻዬን ወስዶ ለቀቀኝ እልሻለሁ:: በነጋታው ትዝ ሲለኝ በህይወቴ እንደዚያች ስቄ አላውቅም!"

"ይቅርታ አድርግልኝና ሚስትህም ነገረኛ እና ተንኮለኛ ነች ስለ አገራችን ፌዴራል ፖሊሶች ገገማነት እያወቀች ይህን ማለት አልነበረባትም እሺ ሌላስ ምን አማረኝ አለች?"

"ጎዳናዎች የሚበሉትን ምግብ መብላት ፣ የግመል ወተት መጠጣት፣ ቀይ አፈር መብላት፣ ሞባይል መስበር፣ ሌሊት ስምንት ሰዓት ላይ ወከ ማድረግ... የመሠሉ ናቸው::"

"ትወዳታለህ?"

"የህይወቴ መሠረት ነች!"

ገራገር እና በቀላሉ ከሰው ጋር መግባባት ከሚችለው ወጣቱ ጋር አስፈላጊ ነው ብዬ ያመንኩትን ያህል አወራን፤ ከዚያ የመጀመሪያ ግዳዬን ለመጣል የወሲብ ስሜቱ ስለመጣ ይህን ሚስኪን ትኩስ ባለትዳር የአስማንዲዮስ መንፈስ አጋብቼበት የትዳር ህይወቱን ብጥብጥ ለማድረግ በጣም ስለጓጓሁ...

"ቢቃ እንውጣ?"

"የት?"

"አሪፍ ቦታ እወስድሀለሁ ብቻችንን ሆነን የምናወራበት ጭር ያለ

ቤት ውስጥ"

"ባለቤት እኮ አለችኝ"

"አውቃለሁ! ይልቅ ተነስ" በማለት እያጣደፍኩ ይዤው ወጣሁ:: በአቅራቢያው የሚገኝ ትልቅ ሆቴል ውስጥ እንደበግ እየነዳሁት አስገባሁት:: ልብሱን በፍጥነት እኔው ራሴ አወለኩለት:: ከዚያ በፍጥነት ተከመርኩበት:: ሁለታችንም ላብ በላብ ሆንን:: ከ35 ደቂቃ በኋላ ሁለተኛውን ዙር ደገምን:: አሁንም የሚገርም ወሲብ ነበር ያደረግነው:: ወጣቱ ሚስኪን እና ፈዛዛ ይመስላል እንጂ የአልጋ ላይ ንጉስ መሆኑን አውቄያለሁ:: ከሆቴሉ ጨርሰን ልንወጣ ስንል

"ስልክሽን ንገሪኝና ልመዝግበው ሌላ ጊዜም ይህን የመሰለ ጊዜ እናሳልፋለን በህይወቴ ይህን የመሰለ አስደሳች ወሲብ አድርጌ አላውቅም! አንቺ የተለየሽ ሴት ነሽ ማለት ነው!" አለኝ:: በግርምት እየተመለከተኝ::

"ያንተን ስልክ ስጠኝ እኔ እደውልልሃለሁ" በማለት የእሱን ቁጥር ተቀበልኩት:: አወል ዋለልኝ በነገረኝ ህግ ከአንድ ሰው ጋር ከአንድ ቀን በላይ ወሲብ ማድረግ በጭራሽ አይገባኝም ፤ አንድ ቀን ብቻ በማርከስ የዝሙት መንፈሱ ስለሚጋባበት ተጨማሪ ግንኙነት አስፈላጊ አይደለም ፤ እናም ይህን ስሙን እንኳ የማላውቀውን እሱም የእኔን ስም እንኳ የማያውቀውን ወጣት በፍጥነት ተለየሁት:: ሌላ ግዳይ ፍለጋ:: አወል እንደምክር እንደነገረኝ ቢያንስ በአንድ ቀን ውስጥ ሁለት ግዳይ መበከል ከቻልኩ አንድ ሺ ወንዶችን ለመበከል በትንሹ 1000/2= 500 ቀናት ያስፈልጋሉ ማለት ነው፤ እዚህ ላይ የወር አበባ ቀናት ሲቀነሱበት ቀኑ በዛ ሊል ይችላል፤ ስለዚህ ቀናቱን አጠር ለማድረግ በቀን ቢያንስ ሶስት ወንዶችን መበከል ይኖርብኛል... በዚህም ተባለ በዚያ አንድ ሺ ወንዶች ለመሙላት ከአንድ ዓመት በላይ ማስፈለጉ ግዴታ ነው:: ከዚያ ትልቁን ስጦታዬን ከአባታችን አስማንዲዮስ በክብር እቀበላለሁ!! ያቺ ቀን እስከምትደርስ ከዛሬዋ መናፈቅ ጀምሬያለሁ... እነሆ ስጦታዬ ምን ይሆን?

ታክሲ ያዝኩ:: መገናኛ ከታክሲው ወረድኩ:: በመቀጠል የአፍሪካ ትልቁ የገበያ አዳራሽ ወደሆነው መርካቶ ታክሲ በመያዝ ሂጂ አለኝ የአባታችን የአስማንዲዮስ መንፈስ፤ እናም የመርካቶን ታክሲ በመያዝ ተክለሃይማኖት ጋር ስደርስ ወረድኩ:: የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ቆምኩ፤ ወዲያው አንድ እድሜው 45 ዓመት የሚጠጋ መላጣ የሆነ ሰው ከባንክ ቤቱ ጠደፍ፣ ጠደፍ እያለ ሲወጣ አየሁት:: እኔ ጋር ሲደርስ ጠብቄ

"ይቅርታ የእኔ ወንድም የቦሌ ሚካኤል ታክሲ የት ጋር ነው የማገኘው?" አልኩት::

"የት?"

"ቦሌ ሚካኤል የሚባለው ሰፈር"

"ያጋጣሚ ሆኖ እኔም ቦሌ ሚካኤል እያመራሁ ነው:: ነይ ከእኔ ጋር ትሄጃለሽ:: የሚገርም አጋጣሚ ነው እድለኛ ነሽ ማለት ነው?" አለኝ:: በፈገግታ እየተመለከተኝ:: እኔ ከራሴ ጋር አወራሁ:: ልክ ነህ እኔ አላማዬን ለማሳካት እድለኛ ነኝ፤ አንተ ግን እኔን በማግኘትህ ከዚህ በኋላ ያለው ቀሪ ህይወትህ ጨለማ ስለሚሆን እድለቢስ ነህ! አልኩኝ:: ከራሴ ጋር አወራሁኝ:: ከዚያ ግን የውሸት ፈገግታ እየለገስኩት

"እሆናለሁ ጌታዬ ስለቀናህ ትብብርህ እጅግ አመሠግናለሁ" አልኩት:: ከባንክ ቤቱ 20 ሜትር ርቀት ላይ ያቆማት ወያኔ የምትባለው መኪና ውስጥ ገባን::

"ሙዚቃ ትወጂያለሽ?"

"እወዳለሁ" አልኩት:: ቀዝቀዝ ያለ የድሮ የትዝታ ዘፈን ከፈተ:: መኪናዋን አስነሣና ጉዞ ጀመርን::

"በነገራችን ላይ ደስ የሚል አቋም አለሽ"

"አመሠግናለሁ"

"ጥሩ ባል እንደምታገኚ እገምታለሁ"

"እየፈለኩ ነው"

"ስንት ዓመትሽ ነው? ሳትዋሺ"

"ገምት እስቲ?"

"ሴይጣን ሰውን በምን መልኩ እንደሚያጠቃ እና የሴት ልጅ እድሜ አይገመትም ይባላል፤ ምናልባት 22 ዓመትሽ ይሆን?"

"እድሜ ቁጥር ነው እኔ በቁጥር መብዛት እና ማነስ አላምንም"

"እስማማለሁ እና በሌሚካኤል ምን እግር ጣለሽ?"

"የእራት ግብዣ ቢጤ አለችብኝ"

"አሪፍ ነው"

"አንተስ?"

"እኔ ነጋዴ ነኝ፡፡ ቀን የሸቀልኩትን ገንዘብ ባንክ አስገብቼ ወደ ቤቴ እያመራሁ ነው"

"ጨዋ ነህ ማለት ነዋ? በጊዜ ቤትህ እያመራህ ነው? ባለቤትህንና ልጅህን ትወዳለህ? ያው ባለትዳር ነህ ብዬ ገምቼ ነው"

"በእርግጥ ሚስት እና ሁለት እሳት የሆኑ ልጆች አሉኝ፤ አሁን ግን በቀጥታ ቤት አልገባም፡፡ አንድ ሁለት ብዬ እገባለሁ፤ እንዴት ነሽ አንቺስ መጠጥ ቢጤ ትሞክሪያለሽ"

"አንዳንዴ"

"አንድ አሪፍ ቤት አለች ልጋብዝሽ?"

"መቼ?"

"አሁን!"

"ቀጠሮዬስ?"

"መኪና ስለያዝኩ ስንጨርስ አደርስሻለሁ? አንቺን የመሰለች ልጅ መንከባከብ አለብኝ! በደረቁ አንቺን የመሰለች ቆንጆ መሸኘት ግፍ ይሆንብኛል!"

"አመሠግናለሁ እባክህ ግን ከአንድ በላይ አንጠጣም"

"ችግር የለውም!" አለና መኪናዋን በ80 ፍጥነት ትንሽ ሄደባትና ወዲያው ፍጥነቱን በመቀየር በ100 ፍጥነት ያከንፋት ጀመር፡፡ ከዚያ በጣም የሚያምር የተዋበ ሆቴል ውስጥ ይዞኝ ገባ፡፡ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢራ ቀመስኩ፤ ሊያስታውከኝ ምንም አልቀረም ነበር፤ ግን በሚገርም ሁኔታ ወዲያው ጣፈጠኝ፡፡ ሁለት ሁለት ቢራ ከጠጣን በኋላ "የእኔ ቆንጆ የሚገርምሽ ቤት ሰሞኑን ውሃ የለችም ለአምስት ደቂቃ ብቻ ሻወር ልውሰድ? በጣም ስለሞቀኝ ነው፤ አንቺም ከሚደብርሽ ነይ እዚያው ክፍል ውስጥ ትቀመጪያለሽ"

"ኧረ እኔ..."

"የእኔ ቆንጆ ምንም የሚፈጠር ነገር የለም" አለኝ፡፡ አሁን እኮ በእርሱ ቤት እኔን እየጀነጀነ መሆኑ ነው? እኔን በፈጣን ምላሱ እርዶ ሊበላኝ እኮ ነው? በቃ እርሱ አሁን የዓለም

ምርጥ አስማጭ መሆኑ ነው? እኔን ሸውዶ አልጋ ቤት ውስጥ እያስገባኝ መሆኑ እኮ ነው? ደስ ይበለው በማለት እኔም እየተንዳሁለት ክፍል ውስጥ ገባሁ:: እውነትም ሻውር ቤት ገባ:: ታጥቦ ራቁቱን ተመለሰ:: እውን ይህ ሰው የሰው ልጅ ነው? አልያስ አህያ ? በጣም ትልቅ ብልት አለው:: እርሱ ምንም ሳይናገር በፍጥነት ተነስቼ ተከመርኩበት! አልጋው ላይ አፈረጥኩት:: እስከሚበቃኝ ዘለልኩበት... የአስማንዲዮስ መንፈስ አጋባባሁበት:: አለቀ:: ከዚህ በኋላ የእርሱ የትዳር ህይወት ውሃ ይበላዋል:: ከሚስቱ እና ልጆቹ ጋር አሲድ ይሆናል... ይፋታል... ከዚህ በኋላ ማንኛዋም ከዚህ ሰው ጋር የወሲብ ግንኙነት የምታደርግ ወጣት ወዲያው ከሰውየው ላይ እኔ ያጋባሁበትን የአስማንዲዮስ መንፈስ ትካፈላለች! ትበከላለች! ትቋደሳለች! እርሷም ከሌላ ወንድ ጋር ዝሙት ስታከናውን ያ ከእርሷ ጋር ዝሙት ያከናወነውም ወዲያው ይለከፋል እንዲህ እንዲህ እያለ መበካከሉ ይቀጥላሉ! ይህ አንዱ የአስማንዲዮስ መንፈስ በፍጥነት የሚያመራበት እና የሚራባበት ፈጣኑ ስልታዊ እና ሂሳባዊ ቀመርን የተከተለ አስገራሚ እና አስደንጋጭ መንገድ ነው::

ማታ ቤት ተመለስኩ:: የዚህ ኢንግሊዝ ኢንባሲ ፊት ለፊት የሚገኘው ውብ ቤት ነገር በጣም ገርሞኛል፤ በጣም የሚያምር ግዙፍ ቤት ነው፤ ይህን በተመለከተ የተቀበለኝን አወልን መረጃ ፈልጌ ጠየኩት::

"ለመሆኑ ይህ የሚያምር ግቢ የማን ነው?"

"እባክሽ ስለ እያንዳንዱ ነገር ለመረዳት ዝርዝር ነገር አትጠይቂ አንቺው በራስሽ ቀኑ ሲደርስ ትደርሺበታለሽ በእርግጥ እኔ ራሱ ይህ በውድ ዋጋ ሊሸጥ የሚችል ቤት የማን ነው? ይህን ሁሉ ገንዘብ እዚህ ቤት በየቀኑ በሳምሶናይት እያመጣ የሚያስቀምጠው ማን እንደሆነ አላውቅም! ማወቅም አልፈልግም!! እዚህ ቤት የዛሬ ሁለት ዓመት ከዲላ ከተማ በአባታችን ምሪት ስመጣ አቀባበል ያደረገችልኝ መክሊት አባይ የምትባል ወጣት ነበረች:: ከአባታችን የስራዋን ሽልማት ልትቀበል ወደ ሳውድ አረቢያ ስትሄድ እኔ በተራዬ ሀላፊነቱን ወሰድኩ:: እኔም አንድ ሺ ሴቶች በቅርቡ ሞልቼ ከአባታችን ሽልማት ለመቀበል የተጠራሁበት ቦታ ስሄድ አንቺ ደግሞ ሀላፊነቱን በመውሰድ እዚህ ቤት ውስጥ በመኖር እና በየቀኑ የሚመጣውን ገንዘብ በመጠቀም ትቆይና በመጨረሻ ለሌላ ከአባታችን ተመርጦ የሚመጣ ሰው አቀባበል ታደርጊለታለሽ፤ ከዚያ ሽልማትሽን ልትቀበይ ስትሄጂ በአንቺ የተተካው ሰው ተራውን ይቀጥላል፤ ስለዚህ ይህ ቤት የቅብብሎሽ ነው:: ባለቤቱ ማን ነው የሚለውን ግን አላውቅም!!"

"ሽልማታችን ምን ይሆን?"

"አላውቅም፣ ስለዚህ ነገር ማውራትም የለብንም ስለሁሉ ነገር የሚያውቀው አባታችን ብቻ ነው!!" በማለት ነበር የነገረኝ:: እያከታተልኩ በምጠይቀው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እንደሰለቸው እንዲታወቅለት የጎሪጥ እየተመለከተኝ:: ሁለቱን የመጀመሪያ ግዳዮቼን ስጨርስ ማታ እዚው አወዛጋቢ ቤት በማምራት ተኛሁ:: ምሽት ላይ በግራ እና በቀኝ እንደተባለው እባብ እና ዘንዶ እቅፍ አድርገው እያጫወቱኝ አብረን ተኛን:: እኔም ስለነገ እያሰብኩ ወዲያው እንቅልፍ ወሰደኝ::

## 0050

የጉድ ጥርቅም የሆነችውን የኢትዮጵያን ዋና ከተማ አዲስ አበባን በሚገባ ለመድኳት:: ዱከምን፣ አቃቂን፣ ደብረዘይትን፣ አስቀያሚዋን ትንሽዬ ከተማ ጫንጮን፣ ለገጣፎን፣ ሁሉንም የአዲስ አበባ አዋሳኝ ትንንሽ ከተሞችን አወኩ:: የአባታችን አስማንዲዮስ መንፈስ እግሬን የመራኝ ቦታ ሁሉ እየገሰገስኩ በመሄድ ወንዶችን አጠመድኩ:: ከወንዶች ጋር ማገጥኩ:: የአስማንዲዮስ መንፈስን አጋባሁባቸው... ዛሬም መንፈሱ እየመራኝ ወደ ቦሌ ኤድናሞል አደረሰኝ:: በ3ዲመነፅር የሚታይ አሪፍ አስፈሪ ፊልም አይቼ ወጣሁ:: የሚገርመው በዚህ የአሜሪካ ፊልም ላይ እኔ ጀርባ ላይ የተቀነስኩትን ፊልሙ ውስጥ የሚሠሩ ሁለት ዝነኛ አክተሮች ተነቅሰው ተመለከትኩ፣ በጣም አያሌ የአሜሪካ ዶላሮች ፈሰበት በአወዛጋቢው እና ዝነኛው የኢሉሚናቲዎች ዋነኛ ድርጅት ነው በሚባለው በሶኒፒክቸርስ የተሰራውን ፊልም አይቼ ኤድናሞል ዋናው በር ላይ ደርሼ ልወጣ ስል አንድ ዝንጥ ያለ፤እንደግብረሰዶማዊያን እጅግ ጥብቅብቅ ያለ ስኪኒ ሱሪ ያደረገ ወጣት ድንገት መጣና በታላቅ ራስ መተማመን በመታጀብ ስሙን አስተዋወቀኝ:: የኢትዮጵያ ፊልሞች ከንቱ ቢሆኑም አንዳንድ ጊዜ ግን ዋና ሀሳቡን ምንም እንኳ ከውጪ ፊልሞች እየተሠረቁ ከሚሠሩት የተሻሉ ናቸው በሚባሉት የኢትዮጵያ ፊልሞች ውስጥ አሻራቸውን ለማስቀመጥ ከቻሉት ከሰባት በላይ ፊልሞችን ለመስራት የቻለ እና ገንዘብም ለመሸቀል የቻለ ወጣት እንደሆነ ወዲያው የአባታችን መንፈስ ሹክ አለኝ:: እኔ ግን ምንም እንዳላወኩት በመሆን

"አወቅሽኝ" ሲለኝ

"ይቅርታ አላወኩህም" አልኩት::

"እከሌ እከሌ እባላለሁ... ለማንኛውም ከሰባት በላይ ፊልሞች አሉኝ:: አሁን

የምሰራው ስምንተኛ ፊልም አለኝ፤ የሚገርምሽ በመልከም በቁመናም ቁርጥ አንቺን የመሰለች ሴት እየፈለኩ ነበር እና ፊልም የመስራት ህልም ካለሽ እድሉን ልሰጥሽ ነበር፤ በዚያ ላይ አሪፍ ገንዘብ እከፍልሻለሁ! በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ፊልሞችም ላይ የመተወን እድል እንድታገኚ በሩን እከፍትልሻለሁ!!" አለኝ::

"ስንት?"

"ሻይ ቡና እያልን እናውራ?"

"ደስ ይለኛል" አልኩት:: ከኤድና ሞል ብዙም የማይርቀው ማፊ ሲቲ ሞል በር ላይ ያለው ካፍቴሪያ ተቀመጥን:: ስሜን ሲጠይቀኝ አፌ ላይ የመጣውን የውሸት ስም ነገርኩት:: እውነትም ይህ ሰው ታዋቂ ነው:: በተቀመጥንበት ትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ ብቻ እንኳ በርከት ያሉ ሰዎች በአክብሮትና በሞቀ ፈገግታ አሽብርቀው ሰላምታ ሲሰጡት አየሁ:: እሱም ዝነኛ በመሆኑ ጅንን እያለ አፀፋውን ይመልስላቸው ነበር::

"እንግዲህ ከተስማማሽ ፊልሙ ላይ ለ22 ደቂቃ ያህል ትሰሪያለሽ! በኢትዮጵያ የፊልም ታሪክ ለ22 ደቂቃ ወዲያው እጅግ ከፍተኛው ገንዘብ ይከፈልሻል:: ከተሳለችው ገፀባህሪ ጋር የአንቺ ሁኔታ በሁሉ ነገር ተመሳሳይ ነው:: የሚገርም ገጠመኝ ነው" አለኝ:: ከእኔ ጋር እያወራ በአይኑ ቂጥ እየሰረቀ ውብ ሴቶች በተለይ ትልቅ ቂጥ ያላቸው እና አጠር ያለች ቀሚስ ያደረጉ ሴቶች ሲመጡ ያያል... እንግዲህ አሁን እርሱ እኮ የዓለም አሪፍ ጀንጃኝ መሆኑ ነው? ፊልም ላሰራሽ! ታምሪያለሽ! የአገሪቱ ከፍተኛ ገንዘብ ይከፈልሻል! የምንፈልጋት ገፀባህሪ ቁርጥ አንቺን ትመስላለች! ለማንም ተዋናይ እስካሁን ተከፍሎት የማያውቀውን ሪከርድ የሆነ የገንዘብ መጠን ማለትም 285,000 ሺ ብር ይከፈልሻል! ቅብርጥሶ እያለ ዝነኝነቱን እየተጠቀመበት ሴቶችን በታላቅ የማይጨበጥ ጉጉት እየሞላቸው አልጋ ላይ ያጋድማቸዋል!! ወሬውን ቀባጥሮ ሲጨርስ "ለመሆኑ ብዙ ገንዘብ ለ22 ደቂቃ የሚከፈለኝ ፊልሙ የወሲብ ፊልም ነው እንዴ?" አልኩት:: ምንም እንኳ በአገራችን ኢትዮጵያ የወሲብ ፊልም እንደማይሠራ ጠንቅቄ ባውቅም እሱም ወዲያው ፈገግ እያለ "በጭራሽ የፍቅር ኮመዲ ፊልም ነው!!" አለኝ:: ወዲያው ሌላ ጥያቄ ቀጠልኩለት

"ባለቤትህ ተዋናይ ነች?"

"ማግባቴን እንዴት አወቅሽ?"

"ሞኝ ነህ እንዴ እጅህ ላይ ያለውን የጋብቻ ቀለበት አይቼ ነዋ!"

"እህ... አይደለችም፤ አየር መንገድ ሰራተኛ ነች"

"እኔ የሚገርመኝ ግን በቃ የኢትዮጵያ ፊልም ማንም እየተነሣ የሚንቦራጨቅበት ዕቃ ዕቃ ጨዋታ ሆነ ማለት ነው? ማንም ውበት ያለው? ማንም ገንዘብ ያለው እና ማንም መንገደኛ እየተነሣ የሚሰራበት ሆነ?"

"ማንም ሳይሆን ለምሳሌ እንዳንቺ ያሉ እድለኞች"

"ከዩኒቨርሲቲ በትያትር የሚመረቁትስ? ለምን ከእነርሱ ገፀባህሪ የሚወክሉልህን አትመርጥም?"

"የሚደንቀው የተማሩት ወሬ ብቻ ያነበንባሉ እንጂ ችሎታ የሚባል ነገር የላቸውም:: ከእነርሱ ጋር ስትሰሪ ይህን ስንማር እንዲህ ነው፣ ይህ እንዲህ መሆን አለበት፣ ይህ... ይህ... እያሉ ከዩኒቨርሲቲ መመረቃቸውን ብቻ ለማሳወቅ ሲቀባጥሩ እያቃጠሉሽ በከንቱ ጊዜሽን ያቃጥላሉ፤ በዚህ የተነሣ ከእነርሱ ጋር መስራት ማንም አይፈልግም፤ በዚያ ላይ የሚመረቁት ሁሉ እንዴት ተመረቁ? በቃ ኢትዮጵያ ውስጥ በትያትር መመረቅ እንዲህ ተራ ነገር ሆነ የሚያስብሉ ናቸው:: ተሰጥኦ የሚባል ነገር ጨርሶ የላቸውም"

"እህ ከአነጋገርህ ከዩኒቨርሲቲ በትያትር ለሚመረቁት ተማሪዎች ከፍተኛ ጥላቻ እና ንቀት እንዳለህ መገመት እችላለሁ አልያም የምታወራው ሀቅ ይሆናል፤ ለማንኛውም እኔ የኢትዮጵያ ፊልም ላይ መስራት አልፈልግም"

"ለምን?"

"በሁለት ምክንያቶች"

"ልትነግሪኝ ትችያለሽ"

"ጊዜህን ካልተሻማሁብህ"

"አንቺን የመሰለች ደፋር ሴት በመተዋወቄ እድለኛ ነኝ ሀሳብሽን ለመስማትም ጊዜ አለኝ"

"ይሁንልህ! የመጀመሪያው ምክንያት ታዋቂ መሆን አልፈልግም! ታዋቂ ከሆንኩ አንዱን ሀብታም አገባለሁ ወይም ከአንድ ዓመት ከሁለት ወር በላይ (425 ቀናት) ሴቶችን አጠገቡ የማያስቆየው እና ሴቶችን እንደ ቲሸርት እና ካልሲ መቀያየር የሚያረካው ልማደኛው የሀገራችን የሴቶች ቀበኛ ሼኩ ላግባሽ ሊለኝ ይችላል:: ከዚያ እኔንም ለአንድ ዓመት ሁለት ወር ያህል ይከካኝና በቀይ ካርድ ያባረኛል፤ ከዚያ ሞራሌ ይነካል:: ሁለተኛው ምክንያት

የኢትዮጵያ ፊልሞች ሁሉ ገና አምስተኛው ደቂቃ ላይ መጨረሻቸው የሚታወቅ አሰልቺ ከንቱ እና ድግግሞሽ ናቸው"

"አሰልቺ? ከንቱ? እና ድግግሞሽ?"

"አዎና! ሀሳብ እኮ የሚባል የላቸውም:: ለምሳሌ አንዲት ሴት ፍቅረኛ አላት እንደተለመደው ያ ፍቅረኛዋ እውነቱን ቀብሮ ይዋሻታል በመጨረሻ እውነቱን ታውቃለች ወይም ይነግራታል ከዚያ ይታረቃሉ ወይም ለምሳሌ አንዲት ሴት በጣም ምሁር እና ሀብታም ባል ታገባለች ያ ምሁር እና ሀብታም ባሏ ግን በስራ ብዛት ጊዜ አይሰጣትም በዚያ የተነሣ ድንገት ያቺ ሴት የሆነ ፍሪክ፣ ሰዎችን እየዘረጠጠ የሚናገር፣ ቀልደኛ፣ ስራ የሌለው ፣ ጋንግስተር ጋር ትተዋወቃለች ከዚያ ያዝናናታል! ያስቃታል! ብዙ ነገር እየቀባጠረ በቃላት ይሞላታል! ይጀነጅናታል! በቃ በእርሱ ፍቅር ትከንፋለች! ምሁር እና ሀብታም ባለቤቷን በመፍታት ያን ያሳቃትን፣ ስራ ፈት የሆነ እና ህልም የሌለውን ወንድ ታገባዋለች... ይህን የመሰሉ የተለመዱና የቸኩ ሀሳቦች እየተነሱ የኢትዮጵያ ሴቶችን ማንነት የሚያንቋሽሹ የማይረቡ ተራ ፊልሞች ላይ መሳተፍ ለእኔ ትልቅ ሀጢያት ነው"

"በሀሳብሽ እስማማለሁ የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ ግን ተመልካች እና መንግስት ናቸው"

"ማለት?"

"የሀገራችን ፊልም ተመልካች ራሱ ቅል ራስ ነው:: ማየት የሚፈልገው እና አዳራሹ ግጥም ብሎ የሚሞላው ሊያስቁ የሚችሉ ፊልሞችን፣ በስድብ የተሞሉ ፊልሞችን፣ በቧልት የተሞሉ ፊልሞችን ሲሆን ብቻ ነው፤ በሌላ በኩል መንግስት ፊልም ላይ ሳንሱር ያደርጋል:: የፈለግሽውን ፊልም መስራት አትችይም! ከፍተኛ ገንዘብ መድበሽ ድንቅ የሚባል ፊልም ብትሰሪ ፊልሙ እንዲታይልሽ ፍቃድ የሚሰጡት 'ባህልና ቱሪዝም' አይቻልም ይሉሻል:: እንደሌላው አገር የኢትዮጵያ መንግስትም ለፊልማችን ነፃነት ቢሰጥ እና ሳንሱሩን ቢያነሳ የኢትዮጵያ ፊልም በአራት ዓመት ብቻ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ ይሆን ነበር፤ ባንቺ ሀሳብ ግን እስማማለሁ፤ በተለይ ፊልሞቻችን ላይ ሴቶች ዋጋቸው የረከሰ ሆነው ይሳላሉ! ለነገሩ ከሀገራችን ሴቶች መሀከል ከአስሩ ዘጠኙ ቀፎ ጭንቅላት ያላቸው ናቸው፤ ስለዚህ የሚመጥናቸውን ፊልም እያገኙ ናቸው:: ደራሲዎቹስ የሌለውን ከየት ያምጡት?" በማለት ራሱን ነቀነቀ::

"ሀሳባችን አንድ ከሆነ ምናልባት ግን እውነተኛውን ፊልም እልጋ ላይ ስተውን በጣም አረፍ ነኝ! ቀሽም ከሆንክ ግን ጊዜዬን ማቃጠል አልፈልግም" አልኩት:: ቀና ብሎ ተመለከተኝ:: ድብን አድርጌ ጠቀስኩት :: በፈገግታ ተሞላ

"ሂሳብ ከፍለን እንውጣ?" አለኝ::

"እንውጣ ግን ያንተ ቢሮ ውስጥ ጠረጴዛህ ላይ ነው የምናደርገው"

"እሺ" አለኝ:: ከማፊ ሲቲ ሞል ካፍቴሪያ ወጥተን የያዛት ቪትስ መኪና ወሰደኝ:: ቢሮው ገባን:: ጠረጴዛው

ውስጥ ገባን:: እያከነፋት ሰሜን ሆቴል የሚባለው ሰፈር ወሰደኝ:: ቢሮው ገባን:: ጠረጴዛው ላይ በጣም የሚገርም ዝሙት ለዚያውም ያለ ኮንዶም አደረግን:: የአስማንዲዮስ መንፈስን አጋባሁበት:: ይህ ታዋቂ ሰው እንግዲህ ፊልም ላሰራሽ እያለ በርከት ያሉ ወጣት ሴቶች ጋር ወሲብ ሲያደርግ የአስማንዲዮስ መንፈስ ይተላለፍባቸዋል ማለት ነው:: ከሚስቱ ጋር በቅርቡ ይለያያል... ህይወቱ ድብልቅልቅ ያለ ይሆናል... የዝሙት ባንዲራን በየሄደበት ያውለበልባል መላህይወቱን እንደባዘነ እና እንደተቅበዘበዘ ይኖራል ማለት ነው:: የሀጢያት ብዛት ሞት ነው:: የዝሙት ብዛት ግን ሁለት ሞት ነው:: ምድራዊ እና ሰማያዊ ሞት::

* * *

ምግብ ቤት በራፍ ላይ መጥታ የቆመችው:: ይቺ እብድ እንደሌሎቹ እብዶች አይደለችም:: ይቺ እብድ እንደ ሐረር እብድ ናት:: የሐረር እብዶች ሰው አይማቱም፣ አይተናኮሉም፣ አያስፈራሩም፣ በዝምታ ይቀመጣሉ:: በዝምታ ይሄዳሉ:: በዝምታ ከራሳቸው ዓለም ውስጥ ይሰምጣሉ:: ይህ የሐረር እብዶች መለያ ባህሪያቸው ነው:: ይቺም ሴት እብድ አትናገርም አልያም ሰዎችን ለመማታት አትሞክርም! የፈጣሪ ያለህ? ይቺን ወጣት በአንድ ጊዜ ነው ያስታወሱኳት:: በእጇ ላይ ያሉት ሁለት ንቅሳቶች አይረሱም! እንዴት የአባብ እና መስቀል ንቅሳት ሊረሣ ይችላል? አዲስ አበባ ካሳንቺዝ ስለተፈጠረው ነገር ለባለቤቴ አስቀድሜ ነግሬያት ነበር:: በዚች በጣም ቆንጆ የሆነች ወጣት ላይ ስላለው አንዳች የአጋንንት አሰራር ለባለቤቴ ነግሬያት ነበር:: ታላቁ አምላካችን ይቺን ወጣት በስሜት የሚነዳውን የኢትዮጵያ ወጣት ከመጨረሷ በፊት ከታሰረችበት ረቂቅ የአጋንንት አሰራር እንዲያወጣት እና ቀንበሯን እንዲሰብረው እናስባት ነበር:: በህይወት አጋጣሚ አንኮበር አገኘናት:: አንዳችም ቃል የማትናገረዋን እና የማትጋገረዋን ወጣት በፈጣሪ እርዳታ እንደምንም ይዘናት አዲስ አበባ አመጣናት! ያሳዝናል! አንደኛዋ ኩላሊቷ ተሰርቋል:: የHIV በሽታ ሰለባ ነች... አንዳችም ቃል መናገርም ሆነ መስማትም አትችልም:: የዚችን ወጣት ህይወት ለመታደግ ምህረቱ እና ይቅር ባይነቱ የማያልቀውን የታላቁ ፈጣሪ ጸጋ ያስፈልጋል!! ይቺ ሴት በእርግጥ ሩህሩህ ናት! ምህረት የሚያስፈልጋት እና ምህረት የሚገባት ሴት! ከእስራቷ ነፃ ወጥታ ያሰረቻቸውን ሰዎች የምትፈታ ሌሎችን ለማዳን ስለ ረቂቅ አጋንንት አሰራር የምትሰብክ ሴት ፣ ብዙዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን የምትመልስ፣ ጨለማ ውስጥ ለመግባት የሚጎመጁትን ወጣቶች ያሳለፈችውን ህይወቷን በመናገር የተጠንቀቁ ደውል የምታሰማ! ህይወታችሁን በቀናው መንገድ ዋጁት እያለች መለከት የምታሰማ ሴት ናት! ወይም መሆን አለባት!!

በንፁህ ህሊና እና በተከፈተ ልብ ላመነ ሰው ደግሞ ለፈጣሪ ምን ይሳነዋል!? ሰማይና ምድርን የፈጠረ ታላቁ ፈጣሪ ከአጋንንት እስራት አንዲት ሴትን ነፃ ማውጣት በጣም ቀላል እና ተራ ነገር ነችና!... የታላቁ ፈጣሪ ምህረት እና ዓይን ከእኛ ጋር ይሁን... አሜን!!

<u>ማስታወሻ</u>

**ለውድ አንባቢያን!**

ሊሊ ሽመክት በአሁኑ ወቅት ከእብደት መንፈስ ነፃ ወጥታ ስለ አሳለፈችው እጅግ ረቂቅ የሆነው የአጋንንት እና የሴይጣን እስራት ዘመኗ እየተናገረች ትገኛለች፤ በዚህ ታሪክ ውስጥ ከሊሊ ጋር ግንኙነት የነበራቸው የሊሊ ተጠቂ የአገራችን እጅግ ዝነኛ ሰዎች ስምንም ሆነ የተማሪዎች ስምንም ለማህበራዊ ህይወት ሲባል መጥቀስ ባለመፈለጉ ተዘሏል፡፡ በተረፈ ያገባችሁም ሆነ ያላገባችሁም ወንዶች ሆናችሁ ሴቶች እባካችሁ ስሜታዊ በመሆን ማንም እንዳያስታችሁ በማስተዋል ተንቀሳቀሱ! ከዝሙት እና ከሱሶች ራሳችሁን ጠብቁ! ማንንም በማመን በፍጥነት የቅርባችሁ በማድረግ አልጋ ላይ አትዋደቁ! ከማሳጅ ቤቶች! ከንቅሳት ቤቶች! እሽኮለሌ ከሚባልባቸው ቤቶች ራሳችሁን ጠብቁ! ታላቁ ፈጣሪ በረከትን እና በማስተዋል የታጀበ እርጋታን ያበዛላችሁ ዘንድ ሥጋችሁንም ሆነ ህሊናችሁንም ጠብቁ! በተለይ በቀላሉ ከማንም ጋር የዝሙት ባንዲራን እንዳታውለበልቡ... ህይወታችሁን ከፈጣሪ ጋር ብቻ ዋጁት!! የተቀደሰ ህይወት እመኝላቹዋለሁ...! !

(ኤልያስ ያረጋል እና ሊሊ ሽመክት)

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ፡፡

# 4

# ሀዋሳ - ዩኒቨርሲቲ

(2006 እስከ 2008 ዓ.ም)

እኝኝ የሚለው ዝናብ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ቀጥሎ ነበር፡፡ የዝሙት ባንዲራ የሚለውን መፅሐፍ እስከምተኛ አነበብኩት፡፡ በጠዋት ተነስቼ የቀረውን ጨረስኩት፡፡ በእርግጥ የዝሙት ባንዲራ የሚለውን መፅሐፍ ከጨረስኩ በኋላ ሀቁን ለመናገር ጥሩ ስሜት አልተሰማኝም፤ በተለይ አባቴ የጠንቋይ አምላኪ ስለ ነበር ፈራሁ፤ በዚያ ላይ ዋናው ጠንቋይ መሪጌታም ደፍሮኝም ስለነበር ፈራሁ! ከዚያ በኋላ ቁጥራቸውን በውል የማላውቃቸውም በቦታው የነበሩ ወንዶችም ከእኔ ጋር ወሲብ አድርገው ስለነበር በሊሊ ሽመክት ታሪክ መሠረት የአጋንንት አሰራር እኔ ውስጥ ላለመግባቱ ምን ዋስትና አለኝ? ቤተሰቦች ከአጋንንት አሰራር ጋር ንኪኪ ካላቸው የእነርሱ ንኪኪ ምንም ለማያውቁት ልጆች የሚተላለፍ ከሆነ እንዴት ነፃ ልሆን እችላለሁ? እናም ውስጤ ጥርጣሬ እና ፍርሃት ነገሰ... ውስጤ በታላቅ ጥያቄ ተወጠረ፡፡ ለምን ፈጣሪያችን ሴይጣንን ፈጠረው? ለምን ፈጣሪ ሴይጣንን የሚያክል አጥማጅ አስቀምጦ የሰው ልጆች በስቃይ ሲዋትቱ ዝም ይላል? የአባት ሀጢያት ምንም ለማያውቅ ልጅ ለምን ይተላለፋል? የቤተሰቦችን ዕዳ ለምን ምንም የማያውቁት ህፃናት ይከፍላሉ? ይህ ፍትህ ነው? ይህ ተገቢ ነው? የመሰሉ ጥያቄዎች ተመላለሱብኝ፡፡ የማያልቁ እና ምላሽ የሌላቸው ጥያቄዎች!!

እንደተለመደው ፒያኖ ትምህርት ቤት ሄድኩኝ፡፡ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ካራቴ ት/ቤት በመሄድ ተማርኩኝ፡፡ ከዚያ በቀጥታ ያመራሁት ወደ ቤት ነበር፡ ትላንት ባነበብኩት ታሪክ ውስጤ ሰላም ስላጣ በቁዘማ ተቀመጥኩ፡፡ በመሀከል ቤተል ደወለች፡፡ ከቤተል ጋር ለአምስት ደቂቃ ያህል አውርተን ነገ ቤት እንደምትመጣ ነግራኝ ተለያየን፡፡ ማታ አንቴ ሲመጣ እንዲቀለኝ እና ብቸኛ አማካሪዬም ስለሆነ ሁሉን ነገር አጫወትኩት፡፡ አንቴ በፈገግታ ተሞልቶ እንደተለመደው እጄን በፍቅር ሳመኝ፡፡ ከዚያ በትኩረት እያየኝ

"የእኔ ልጅ የአጋንንት አሰራር በጣም ጥልፍልፍ ነው፡፡ ከቤተሰባችን አንደኛው የጠንቋይ አገልጋይ ከሆነ የተቀሩት ልባቸው ውስጥ እምነት እና የእ/ር ቃል ከሌለ የአጋንንት አሰራር በእርግጥ ይጫወትባቸዋል፤ እናም የአንቺ አባት የወለዳቸው ልጆች ከእ/ር ጋር የጠበቀ ህብረት የማይፈጥሩ ከሆነ አባታችሁ ከሴይጣን ጋር ቃል ኪዳን ስላለው የአባታችሁ መንፈስ

በቀኝም ይሁን በግራ ያጠቃቸዋል፡፡ የአጋንንት አሰራር በተለያዩ መንገዶች ውስጣችን ይገባል፡፡ በምናውቀውም ሆነ በማናውቀውም መንገድ እስረኛ ያደርገናል፡፡ ይህ እውነት ነው፤ ነገር ግን ትልቁ የምስራች የአንቺ ግን የተለየ ነው፡፡ አየሽ አንቺ ላይ የተሰነዘረው የአጋንንት አሰራር እንደማይሰራ አንቺን እምላክሽ እንደማይጥልሽ እና ጨለማ ውስጥ እንደማትቀሪ ታላቁ አምላክሽ ያ አስቀያሚ ድርጊት ከመፈጠሩ በፊት ግልፅ የሆነ ህልም አሳይቶሻል የመስቀሉን ህልም አስታወሽ?"

"በሚገባ አስታውሳለሁ!"

"እለቀ! አንቺን ማንም እንዳይነካሽ በፈሰሰው ደም ተከበሻል! ማንም አይነካሽም! አንድ አጋንንት አይደለም ሺ አጋንንቶች ቢሆኑ እንኳ አንቺን ሊነኩሽ አይችሉም! ካንቺ የሚጠበቀው በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደም የማዳን ሀይል ማመን እና በእምነትሽ መፅናት ብቻ ነው!! እንደ ዮሴፍ፣ እንደ እዮብ! እንደ ሩት... ጠንካራ መሆን አለብሽ! ባንቺ ላይ የአባትሽ ይሁን የጠንቋዩ ህልም እና እቅድ ጨርሶ እንደማይሰራ አስቀድሞ ተነግሮሻል! በዚህ ቅንጣት ያህል መጠራጠር የለብሽም! ወደፊትም መጠርጠር አይኖርብሽም!! አንቺ ማመን እና ፈጣሪን መጠጋት ብቻ ይጠብቅሻል፡፡ አየሽ የሰው ልጅ የአስተሳሰቡ እስረኛ ነው፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ በጣም የምወዳት አባባል As man thinks so he shall be የምትል ናት፤ ስለዚህ መቼም ቢሆን ስለ ጨለማ እንዳታስቢ! አንቺ ብርሃን ውስጥ ነው ያለሽው! ይልቅ ሁልጊዜ ማሰብ ያለብሽ ፈጣሪ ላንቺ እውቀትን፣ ማስተዋልን፣ ፈተናን ማሸነፍን ፣ ይቅር ባይነትን የሰጠሽ ካንቺም አልፎ ሌሎችንም እንድትረጂበት ነው፡፡ አየሽ ትልቅ ኃይል ሲሰጥሽ ከትልቅ ኃላፊነት ጋር ነው ስለዚህ አምላክ አንቺን በእውቀት የሞላሽ እና እውቀት የሰጠሽ ካንቺም አልፎ ምድር ላይ በምትኖሪበት ዘመናትሽ ትልቅ ነገር እንድትሰሪበት ነው፡፡ የዚያችን ሚስኪን የ13 ዓመት ልጅ የነበረችውን የአና ፍራንክን መፅሐፍ ስታነቢ አንድ ደስ የሚል አባባል ነግረሽኝ ነበር አስታወሽ?"

"አስታውሳለሁ!"

"እስቲ ድገሚልኝ!?"

"ምንም ሆነ ምንም በመሠረቱ ሰዎች ውስጣቸው ቅን ናቸው ብዬ አስባለሁ ..."

"በጣም ድንቅ አባባል! አየሽ ማንም በተፈጥሮው ተንኮለኛ፣ አጭበርባሪ፣ ደፋሪ፣ ውሸታም፣ ገንዘብ አፍቃሪ፣ ሌባ፣ ነፍሰገዳይ፣ እርኩስ፣ ጠንቋይ ቤት ተመላላሽ... እንዲሆን

ተደርጎ በዕጣ ፋንታ የሚፈጠር የለም! ባጋጣሚ፣ በማወቅና ባለማወቅ፣ በሰዎች ግፊት እና በአካባቢያዊ ተጽህኖ የተነካ ሰዎች ልባቸው ይመረዛል፣ እንዲሸፍት ይደረጋል፣ በጥላቻ ይሞላል እንጂ ሰው ሁሉ ሲፈጠር ንጹህ ህሊና እና ልብ አለው:: ለዚህ ነው ያ ሁሉ የመከራ ዝናብ ቢደርስባትም ትንሿ የ13 ዓመት ልጅ አና ፍራንክ በመሠረቱ ሰዎች ቅን ናቸው የሚል ግንዛቤ ያዳበረችው:: ይህን እውነታ በትንሽነቷ ለመረዳት የቻለች ጥበበኛ ትንሽ ልጅ ነበረች አየሽ ለሰዎች ሁሉ ይቅርታ ማድረግ አለብን! ሰዎችን ማስተማር አለብን! ሰዎችን ከጨለማ ለማውጣት መጣር አለብን! በእርግጠኝነት አባትሽ ሲፈጠር መልካም ሰው ነበር፤ ያን አስቀያሚ ድርጊት የፈጸመው አባትሽ ሳይሆን አባትሽ ውስጥ ሰርፃ የነበረው አጋንንት ነበር ይህን እውነታ በሚገባ እንደተረዳሽ እርግጠኛ ነኝ:: አንዲት ፈረንሳይ አገር በ1732 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ታትማ ዛሬ ድረስ ለጉድ እየተነበበች ያለች The heart of man የምትል ትንሽዬ መፅሐፍ አለች፤ እስጥሽና ታነቢያታለሽ:: የሰው ልጅ ልብ ሁለት ምርጫ ብቻ አለው ትላለች:: The Temple of God or The workshop of Satan የመሆን ናቸው:: ከዚያ ሰዎች ለሚሆኑበት እያንዳንዱ ምክንያት ልባቸው ውስጥ በተቀመጠው ነገር ላይ ይመሠረታል:: ልብሽን ለሴይጣን አልያም ለፈጣሪ መክፈት ትችያለሽ!! ለማንኛውም የኔ ልጅ አንቺ ላይ አንዳችም የአጋንንት አሰራር እንደማይሰራ በጣም እድለኛ ስለሆንሽ በህልምሽ በቀጥታ ተነግሮሻል ካንቺ የሚጠበቀው በመስቀሉ ላይ የፈሰሰውን የክርስቶስን ደም የማዳን ኃይል ማመን ብቻ ነው፤ ስለዚህ ቅንጣትም እንዳትጠራጠሪ! ቅንጣትም ልብሽ ውስጥ መወላወል እንዳታስገቢ! አንቺ ትልቅ ቦታ የምትደርሺ እና አገርሽ ኢትዮጵያ በጣም የምትፈልግሽ ነሽ! ይህን ማወቅ አለብሽ!"

"እመሠግናለሁ! አሁን ሙሉ ለሙሉ ተረጋግቻለሁ! አንተ ባትኖርልኝ ምን ይውጠኝ ነበር?"

"አረቦች አንዲት አባባል አለቻቸው አላህን ገንዘብ ስትጠይቀው ገንዘቡን በእጁ ሳይሆን ገንዘብ የሚሰጥህ ሰው ይልክልሃል የምትል ናት:: እኔ አጎትሽ ላንቺ መልካም ነኝ ብለሽ የምታስቢ ከሆነ አንቺም ደግሞ ለሌላ ሰው መልካም መሆን ይጠበቅብሻል:: አንቺ ሀሳብሽን ለእኔ አካፍለሽ ጭንቀትሽ ቀለል ካለልሽ ሌላሰው አንቺ ጋር መጥቶ ሀሳቡን ነግሮሽ! ጭንቀቱ ይቀለው ዘንድ ስሚኝ ካለሽ ከልብሽ ማዳመጥ አለብሽ! በህይወት ላይ ላንቺ የሚያስፈልግሽን ሁሉ ሌሎችም እንደሚያስፈልጋቸው በማወቅ መስጠት አለብሽ! በህይወት

ላይ ስትኖሪ የተፈጠርሽው ላንቺ ብቻ አይደለም! ለሌሎችም መኖር አለብሽ! ለራሱ ብቻ የሚኖር ሰው አልኖረም ማለት ነው፡፡ የእኔ ልጅ የህይወት ዋነኛው ቁም ነገር ይህ ነው"

ከአጎቴ ጋር ብዙ ነገር ተጨዋወትን፡፡ ልቤ ውስጥ የነበረው ጥርጣሬ ተወገደ፡፡ አጎቴ የሰጠኝን 32 ገልፅ ያላት ከዛሬ 280 ዓመት በፊት የተፃፈችውን The heart of man የምትል በጣም አነስተኛ መፅሐፍን አነበብኳት፡፡ ይቺ መፅሐፍ የምታብራራው ስለሰው ልጅ ልብ ነው፡፡ የሰው ልጅ ልብ ውስጥ ምንጊዜም ሁለት ተፃራሪ ሀይላት አሉ፡፡ ለምሳሌ ፍቅር/ ጥላቻ... ውሸታምነት/ እውነታምነት... የገንዘብ ፍቅር/ የገንዘብ አምልኮ... ደግነት /ክፋት... ፈጣሪን ማመን/ ፈጣሪን መካድ.. ቂመኝነት/ ይቅር ባይነት... እባብነት/ በግነት... ታታሪነት/ ልግመኝነት... ተኩላነት /እርግብነት... ልበቀናነት/ ልበጠማማነት... ልግስናነት/ ስቁንቁንነት.. አንድነት/ዘረኝነት... ብቻ ልባችን ውስጥ ከሁሉም ነገር ተፃራሪ ሀይላት አሉ፡፡ አንድ ሰው ከልቡ ውስጥ ለልቡ በብዛት የሞላው እና እንዲሞላው የፈቀደለት ነገር ይነግሣል! አሸናፊ ሆኖ ይወጣል፡፡ ለምሳሌ ልባችን ውስጥ ፍቅርም ጥላቻም ካለ እና ከሁለቱ ጥላቻን መርጠን ከሞላነው እኛነታችን የሚጎላው በጥላቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል ፍቅርን ከሞላነው እኛነታችን ጎልቶ የሚወጣው በተመሳሳይ በፍቅር ነው፤ እናም ልባችንን የእ/ርም የሴይጣንም ቤት ማድረግ እንደምንችል በተለያዩ ዘዴዎች ስለ ሰው ልብ እና በዓለም ላይ ስላሉት የሰው ልጅ ባህሪያት የምታብራራ ታሪካዊ መፅሐፍ ነች፡፡ በሌላ ቋንቋ ውስጣችሁ ያነገሳችሁት አሸናፊ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ሀሳብ የፊዚክስ ህግም ነው፡፡ ሁለት ነገር በአንድ ጊዜ አንድ ቦታ አይዝም ፤ እናም ልባችሁን እርኩስም ቅዱስም የማድረግ ስልጣን አላችሁ፡፡

በነጋታው በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ የፒያኖ እና የካራቴ ትምህርቴን ጨርሼ ቤት ተመለስኩ፡፡ ከሰዓት ባለፈገግታዋ ቤተል መጥታ ከእርሷ ጋር ስንጨዋወት ዋልን፡፡ በመሀከል ድንገት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡

"ሁሌ ፈገግታ ከፊቴ ላይ ስለማይጠፋ ደስተኛ እመስላለሁ! ሁሌ ስለምስቅ ደስተኛ እመስላለሁ! የተመቸኝ እመስላለሁ ፤ ግን ውስጤ ባዶ ነው፡፡ ውስጤ በሀዘን የተሞላ ነው! እናቴና አባቴ በመሀከላቸው ያለውን የህይማኖት ችግር ዛሬ ነገ ይፈታሉ እያልኩ ስጠብቅ ትላንት ፍቺ ሊያደርጉ እና ሀዘኔን ሲከምሩት ከማን ጋር መኖር እንደምፈልግ አይጠይቁኝ

መስለሽ? በዚህ የተነሣ ባዶነት ይሰማኛል! የወደፊቱን ህይወቴን ሳስበው እጨነቃለሁ" እያለች የውስጥ ብሶቷን ለእኔ በመናዘዝ በድጋሚ አለቀሰች:: የሴቶች ተፈጥሮ እንደ ወንዶች አይደለምና ሴቶች ጭንቀታቸውም በለቅሶ እንደሚወጣላቸው አውቃለሁና እስከ መጨረሻው ስቅስቅ ብላ እንድታለቅስ እና ውስጧ ያለውን ነገር እንድትናገር በነፃነት እና በዝምታ ፈቀድኩላት እናም እንባዋን ስትጨርስ ለማረጋጋት ጣርኩ:: "አይዞሽ ከአጠገብሽ ነኝ" በማለት ለረጅም ደቂቃዎች እቅፍ አደረኳት:: ከቤተል ሁኔታ የተረዳሁት ሁለት ቁም ነገሮች አሉ:: አንደኛው ሁልጊዜ በፈገግታ እና በሣቅ የተሞላ ሁሉ ደስተኛ ነው ማለት ሳይሆን በተቃራኒው በዚያ ሣቅ እና ፈገግታው አማካኝነት የሚደብቀው አንዳች ነገር እንዳለ:: ሁለተኛው ማንኛውም የሰው ልጅ የተባለ በሙሉ ደረጃው ይለያያል እንጂ ውስጡ ሀዘን እና ከፋት መኖሩን ናቸው:: በዚህ የተነሣ ማንም ሰው በምድር ላይ ሣለ ልቡ ውስጥ ሀዘን እና ጥያቄ የሌለበት አንዳችም እንኳ የለም፤ ሊኖርም አይችልም፤ ይህን ሀቅ ተገንዝቤያለሁ... በህይወት ውስጥ ሙሉ ደስታ፣ ሙሉ ሀዘን የሚባል ነገር የለም!! ህይወት ማለት ይቺ ናት... ህይወት ማለት የሳቅና የለቅሶ ውህድ ናት::

ክረምት ጤዛ ሆነ:: በፍጥነት አለቀ:: የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ወጣ:: ተነገረ:: ከት/ቤታችን ማንም የወደቀ የለም:: በውጤት ደረጃ ከት/ቤታችን አንደኛ እሆናለሁ በማለት ያቀድኩት ህልሜ ካሰብኩት በላይ ሆኖ አምስተኛዋ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ውጤት ያመጣች ሴት ለመሆን ችዬ ነበር:: በውጤቴ ከእኔ ይልቅ በጣም የተደሰተው አጎቴ ነበር:: ባመጣሁት ከፍተኛ ውጤት የኢንግሊዝ፣ ቤልጂየም እና ሩሲያ ነፃ የት/ት እድል እንዳለኝ ትምህርት ቤታችን ቢነግረኝም እኔ ግን በኢትዮጵያ ምድር ለመማር በመወሰን ለእኔ የመጣውን እድል ለሌላ ተማሪ እንዲሰጥ አደረኩኝ:: በዚህ ጉዳይ አጎቴ ሀሳብ አልሰጠኝም ነበር::

"የእኔ ልጅ ያንቺ ውሳኔ ነው! ብዙዎች ግን በስኮላርሺፕ እየወጡ አገራቸውን ኢትዮጵያን ከድተዋል! ገንዘብ እና ምቾትን አስቀድመው በሄዱበት አገር ቀልጠው ቀርተዋል! ገንዘብ ሰብስቤ አገሬ እመለሳለሁ ብለው በሄዱበት አገር እንደሻማ ቀልጠው ቀርተዋል፤ ስለዚህ የእኔ ልጅ አገርሽ ኢትዮጵያ እንደምትፈልግሽ መቼም እንዳትረሺ! የውስጥህን ስሜት ንገረኝ ካልሽ ግን አንዱ ብልጠት የተሞላበት ዘመናዊ ባርነት ይህ ስኮላርሺፕ የሚባለው ምርጥ

ጭንቅላት ያላቸው የአፍሪካ ልጆች አገራቸውን እንዳይጠቅሙ ለማስኮብለል የሚደረግ እና በዘዴ የተዘረጋ ስልት መሆኑን አውቃለሁ::" ነበር ያለኝ:: ለነገሩ እኔም ለጉብኝት ካልሆነ ውጪ አገር ለመማርም፣ ለመስራትም ሆነ ለመኖርም አስቤ አላውቅም፤ እናም ያለ ምንም ፀፀት በፍጥነት ነበር የውጪ ትምህርት እድሉን ለሌላ ተማሪ አሳልፌ የሰጠሁት:: የአጎቴ ሀሳብ ውስጥ እውነትነት ቢኖረውም እኔ ካልተጠቀምኩበት ሌላ ሰው በእድሉ መጠቀም አለበት፤ ምክንያቱም በተለያዩ አገራት ተምረው እየመጡ አገራቸውን በእውቀታቸው እየጠቀሙ ያሉ በርካቶች እንዳሉ ሰምቼያለሁና::

"በኦርቶዶክስ ነህ! ፕሮቴስታንት ነሽ" በሚል የሀይማኖት ልዩነት የተነሣ ቤተሰቦቿ ፍቺ የፈፀሙባት ቤተል በሀዘን ተውጣለች:: ለማረጋጋት እና ለማፅናናት የምችለውን ያህል አድርጌያለሁ:: በዩኒቨርሲቲ ትምህርቷ ላይ ትኩረት ለማድረግ እሷም ወስናለች:: የእድል ጉዳይ ሆኖ የቤተል እና የእኔ ዩኒቨርሲቲ ምርጫ አንደኛ አዲስ አበባ ፣ ሁለተኛ ሀዋሳ፣ ሶስተኛ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የመረጥን ቢሆንም ቤተል በአንደኝነት ለመማር የፈለገችው ት/ት በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሲደርሳት እኔም በአንደኝነት የመረጥኩትን ትምህርት ለመማር ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ደረሰኝ፣ እናም ከጓደኛዬ ቤተል ጋር በመንፈስ ሳይሆን በአካል ለመለያየት ግድ ሆነ... ለአጎቴ ይህን ዜና የሰማሁኝ ዕለት

"አጎቴ" አልኩት

"አቤት" አለኝ

"ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ደረሰኝ እኮ!"

"የእውነት?"

"የእውነት!"

"አሪፍ ነዋ! የሀዋሳን ንፁህ አየር እየማገሽ ማጥናት ነው:: በእርግጥ ለእኔ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብትመደቢልኝ በጣም ደስ ይለኝ ነበር:: ያው ስለምትናፍቂኝ ሀዋሳም የአምስት ሰዓት መንገድ ስለሆነች እየመጣው እጠይቅሻለሁ"

"ለብቸኝነቱ ግን አንድ አሪፍ ዘዴ አለ አጎቴ"

"ምን?"

"እስከ መቼ ብቻህን ትኖራለህ? መቼም እንድንሰማ ጆሮን የፈጠረልን አምላክ በእርግጠኝነት ይሰማል! ዓይን የፈጠረልን አምላክ መቼም ያያል! እስቲ አጎቴ ራስህን ከፍልስፍና እና ከብቸኝነት ዓለም በማውጣት ለእኔ የምትሆነውን ስጠኝ በማለት አምላክን ጠይቀው! ይህን ማድረግ ትችላለህ አጎቴ?"

"የምርሽን ነው?"

"የምሬን ነው! በእርግጥ ማግባት ምርጫ እንጂ ግዴታ አለመሆኑን አውቃለሁ! አንተ ግን ማግባት እየፈለክ የምትረዳህን እና ከእነችግርህ የምትቀበልህን ስላጣህ ተውከ ፤ ስለዚህ እስቲ ለመጨረሻ ጊዜ ፈጣሪህን የሚስት ጥያቄ ጠይቀው" አልኩት፡፡ እኔም ስርከ ሚስት እየፈለኩለት መሆኔን እና ማጣቴን ልነግረው አስቤ ተውኩት፡፡ በራሴ ድርጊት በውስጤ እየሣኩኝ፡፡

"እንግዲህ አንቺን ደስ ለማሰኘት ከእነችግሬ የምትወደኝ መልካም ሴት እፈልጋለሁ"

"እኔ ልሙት አጎቴ?"

"የእኔ ልጅ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለማንኛውም ክርስቲያን ለሆነ ግለሰብ አንድ ህግ አለ፡፡ በራሳችሁ ይሁን በማንም ስም አትማሉ! አዎ ወይም አይ በሉ የሚል ህግ አለ፤ ስለዚህ ሌላ ጊዜ ይህን አባባል እንዳትጠቀሚ! ለማንኛውም አዎ! ሚስት እፈልጋለሁ! ይህ ቃሌ ነው አንቺም በትምህርትሽ በርቺልኝ!"

"አትጠራጠር አጎቴ!" በማለት አጎቴን ከልቤ እቅፍ አደረኩት... አጎቴ ብቻውን በመፅሐፍት ተከቦ እንቅልፍ እንቢ እያለው እስከ እኩለ ሌሊት እንዲያመሽ አልፈልግም፡፡ ለአጎቴ አንዲት ህይወት ማለት ለሌሎች መኖር መሆኑን የምታውቅ መልካም ሴት ታስፈልገዋለች እናም አጎቴ ቃሉን ስለሰጠኝ ከልቤ በደስታ ተሞላሁ፡፡ ታላቁ ፈጣሪም ለአጎቴ የግራ አጥንቱን እንዲሰጠው እኔም እጸልይለታለሁ፤ ምንም አጎቴ በሰው ፀሎት ባያምንም ... አንድ ጊዜ ስለ ጸሎት ስናወራ "በፀሎት ታምናለህ በመፀለይ ግን አታምንም?" ስለው "ፈጣሪ እኔ የምፈልገውን ነገር ያጣልና ነው ፀሎት የማደርሰው?" ብሎኛል፡፡ በእርግጥ በዚህ በአጎቴ ሀሳብ እኔ በጣም አላምንበትም! ፀሎተኛ ባልሆንም ለአንድ የክርስትና እምነት ተከታይ ፀሎት ዋነኛ ቁልፍ ነገር መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ፀሎት ማድረግ ወሳኝ እና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አውቂያለሁ፡፡ ፀሎት ማድረግን አጋንንት የሚፈሩት እና የሚንቀጠቀጡት መሣሪያ መሆኑን

አውቄያለሁ:: የማይፀልይ ሰው ታላቁ እግዚአብሔርን አላወቀም:: የሚጸልይ ግን ከእ/ር ጋር መታረቅ የፈለገና የቀድሞው የሀጢያት ስራው እየታወሰው በትህትና የተሰበረ ልብ ያለው መሆኑን አውቄያለሁ:: በተለይ ከፀሎት በቀር ንስሐ መግቢያ በር አለ ብሎ የሚናገርም ሆነ የሚያምንም ሰው ቢኖር እርሱ በሴይጣን የተታለለ ግለሰብ መሆኑን አውቄያለሁ:: በተለይ ጸሎት የቃላት ኳኳታ ፣ የቃላት ድግግሞሽ ሳይሆን ከውስጥ የሚመነጭ የልብ መቃተት ነውና ቃላት ሊገልፁት አቅም ላይኖራቸው ይችላል፤ ስለምን ቢባል በተመሰጠ ልብ፤ በመንፈሳዊ ሀሳብ፣ በተሰቀለ ህሊና ወደ ፈጣሪያችን የምንነጠቅበትና ከፈጣሪያችን ጋር የምንነጋገርበት ስለሆነ እነሆ ጸሎት ከቃላት ኳኳታ በላይ መሆኑን አውቄያለሁ:: እግዚአብሔር የሚቀበለው እውነተኛ ጸሎት በንፁህና በተሰበረ ልብ የሚቀርበውን ብቻ ነው፤ ስለምን ቢባል በምሳሌ 15፡8 ላይ "የኃጢያን መስዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው ፤ የቅኖች ፀሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው" ይላልና፤ በሌላ በኩል በየቀኑ ከምድራችን ላይ ወደ ፈጣሪ ከሚቀርቡት ጸሎቶች የአብዛኛው ህዝብ ፀሎት ተቀባይነት የለውም፤ ስለምን ቢባል በኢሳ 1፡15 ላይ "እጃችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሠውራለሁ ፤ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም ፤ እጆቻችሁ በደም ተሞልተዋልና" የሚል አለና፤ እናም ሁልጊዜ ጸሎት አደርጋለሁ ፤ ግን ፀሎቴ ተሰምቶ አያውቅም፤ ስለምን ፈጣሪ የእኔን ፀሎት አልሰማኝም??" የምትሉ ሰዎች ራሳችሁን አንድ ጥያቄ ጠይቁ:: ለፀሎት የሚያበቃ ንፁህ ህሊና አላችሁ? ውስጣችሁ ከፋት፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ተንኮል፣ አላማኝነት፣ ጥርጣሬ፣ የነገር ሠረገላነት የለምን? ይህ ውስጣችሁ ካለ ጸሎታችሁ እንዴት ሊሰማ ይችላልን?? ሌላው ከፀሎት ጋር ያለ ወርቃማ ህግ በማቴ 5፡43 –46 ላይ የተቀመጠው ነው "በሠማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ ለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ" የሚለው መሆኑን በሚገባ ተረድታችኋልን? ከእናንተ የተለይ ሀይማኖት ያለውን ትወዳላችሁ? ክብር ትሰጣላችሁ? በፍቅር ትቀርባላችሁ? ወይስ የእኔ ሀይማኖት ብቻ ልክ ነው፤ ከእኔ ሀይማኖት ውጪ ያለው ሁሉ መናፍቅ ነው!! እያላችሁ ትፈርዳላችሁ... ይህን የምታደርጉ ከሆነ ጸሎታችሁ ልክ የፈሪሳዊያን ያህል ነውና ከቶ ይሰማልኛል ብላችሁ እንዳታስቡ!! ፈሪሳዊያን እንዴት እንደሚፀልዩ ግን ታውቃላችሁ??

ከአዲስ አበባ የሚያስፈልጉኝን ኮተቶች በመያዝ እና ጣጣዎችን ሁሉ በመጨረስ እነቴን በመለየት ወደ የኢትዮጵያ ቁጥር አንድ የመዝናኛ ከተማ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጉዞ ጀመርኩ:: ሐዋሳን ያኔ ሳያት ተመችታኝ ነበር፤ አሁን ይበልጥ እንደምትመቸኝ ስድስተኛው ስሜቴ ሹክ አለኝ:: ለምትፈልገኝ አገሬ ኢትዮጵያ እየደረስኩላት በመሆኑም ውስጤ በሀሴት ተሞላ::

በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ አንድ ወር እንደቀልድ ነደደች:: ሀይስኩል እያለን ብዙ የተወራለት ለእኔ ግን ከጠበኩት በታች በጣም የወረደብኝ የዩኒቨርሲቲ ህይወት እና ትምህርት ተጀመረ:: በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አንዲት መጠነኛ ፍራቻ ነበረችብኝ፤ ምናልባት ከደብረማርቆስ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የተመደቡ ያኔ አብረውኝ አንደኛ ደረጃ የተማሩ የቤተሰቦቼን ገመና የሚያውቁ ተማሪዎችን አገኛለሁ ብዬ ሰግቼ የነበረ ቢሆንም ማንንም ባለማግኘቴ ሀሳብ ቀለለልኝ:: ሀዋሳ በመጣሁ አርባኛው ቀን አመሻሽ ላይ ራሴን ከሀሳብ ነፃ ለማድረግ ወሰንኩና በቀስታ እየተራመድኩ ሳይንስ ውሃ ቀለም የለውም እያለ ቱሪውን ቢነፋም በተለምዶ ጥቁር ውሃ ከሚባለው የአዋሳ እና ሻሸመኔ አዋሳኝ ድንበር አምርቼ ጥቁር ውሃ የሚባለውን አነስ ያለች የውሃ ከምችት አይቼ በተፈጥሮ ተገርሜ ወደ ዩኒቨርሲቲ እየመጣሁ ሳለ አንድ ሁለት ወንዶች ለዚያውም የአዋሳ አራተኛ ዓመት ተማሪዎች መሆናቸውን የነገሩኝ በግድ አብረሽን ዘና ካላልሽ በማለት በቀኝ እና በግራ እጄን አጥብቀው ይዘው ጉተታ በጣም ፈጠሩብኝ:: ይባስ ብለው በግድ ሊስሙኝ ይታገሉ ጀመር፤ እናም በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የካራቴ ትምህርቴን በተግባር ለመጠቀም ግዴታ ሆነብኝ:: ሁለቱንም መሬት ላይ እንደ ኮብልስቶን አንጥፌያቸው ሄድኩኝ:: እነቴ ለምን የካራቴ ትምህርቴን እንድቀጥልበት እንዳደረገኝ አሁን በሚገባ ተገለፀልኝ:: አንደኛ ጤና ነው:: ሁለተኛ ይህን የመሰለ አስገዳጅና አላስፈላጊ ነገር ሲፈጠር ራስን መከላከያ ነው:: ከዚው ከለከፋ እና ጅንጀና ጋር በተያያዘ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ተጋግሎ እስከሚጀመር የሁለተኛ፣ የሶስተኛ እና የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች እኔን ለማጥመድ ከፍተኛ ጥረት አድርገው ነበር:: ለመጅንጀን የተቀናበሩ ሴራዎችን ዘርግተው፣ ምላሳቸውን በማር እና ሬት ለውሰው ተሽከርከረውብኝ ነበር:: አፈቀርኩሽ ማለትን እንደ ዕቃዕቃ

ቆጥረው ምንም ሳያፍሩ ገና እንዳየሁሽ አፈቀርኩሽ እያሉ ተበረጨቁብኝ... በእርግጥ ይህ ለእኔ ብርቅ አልነበረም:: እንኳን እኔን የመሰለች በተፈጥሮ አጋጣሚ ቆንጆ የምትባል ሴት ትቅርና ማንኛዋንም ሴት በተለይ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ከሆነች ድንግል ናት ተብሎ ስለሚታሰብ ድንግልናዋን ለመገርሰስ ወንዶች ከበባ ማድረግ ያልተጻፈ ህጋቸው ነው:: ይህን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አስቀያሚ የራስ ወዳድነት እና ሴቶችን ተጠቅሞ የመጣል ባህሪ ገና ሀይስኩል እያለሁ እንኳ አውቃለሁ! ተረድቻለሁ! አንዲት ጠንቃቃ ሴት የምትሄድበትን ቦታ ማወቅ አለባትና አስቀድሜ አውቄያለሁ::

ኢኮኖሚክስን ለመማር አብረውኝ በአንድ መኝታ ቤት የተመደቡት ሣራ፣ የትምወርቅ፣ ሀዊ፣ ሩት እና መከሊት እንደመልካቸው ጸባያቸውም ለየቅል ነው:: የሴቶቹን ሊደብቁት የማይችሉትን አመል እና ፀባያቸውን ለመረዳት ሁለት ሳምንት ብቻ ነበር የፈጀብኝ:: እንደሰጡኝ መረጃ ከሆነ ሩት እና ሣራ ጭሰት የጀመሩት ገና አስረኛ ክፍል እያሉ ነበር:: ይጠጣሉ ፣ ይጨፍራሉ፣ ወንዶችን ያወጣሉ:: አሁን ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ገብተው ሙሉ ለሙሉ ከቤተሰብ ቁጥጥር ነፃ በመውጣታቸው ለዚያውም የመዝናኛ ከተማ የሆነችው ሀዋሳ በመሆናቸው ለመጨስ፣ ለመጠጣት ፣ የተለያዩ ወንዶችን ለማውጣት እና ዳንኪራ ለመደለቅ ትልቅ አረንጓዴ መብራት በራላቸው፤ በዚህ ዓይነት ትምህርታቸውን እንዴት እንደሚቀጥሉ ያሰጋኛል:: የትምወርቅ እና ሀዊ ይሉኝታ የሚያጠቃቸውና ብዙም በራስ መተማመን የማይታይባቸው በህይወት መንገዳቸው ላይ ብልጥ እና ተንኮለኛ ሰው ካገኛቸው በቀላሉ የሚደለሉ መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ:: መከሊት በጣም የሚደንቅ መልካም ሥነ ሥርዓት ካለው ቤተሰብ ውስጥ እንዳደገች ያስታውቃል:: የሚገርም አስደሳች ፀባይ አላት:: የሰው ክብር አላት:: እርጋታና ማስተዋል አላት:: ስትናገር እንኳ ቃላቷ የተመረጡ እና ጨዋ ናቸው:: ይቺን ልጅ በቆይታ እንደተረዳዋት እና አስቀድሜ እንደጠረጠርኩት መልካም ሥነምግባር ካላቸው ካቶሊካዊያን ቤተሰቦች መወለዷን ነው:: አንድ ችግር ግን አለባት:: መከሊት በፈሊጣዊ አነጋገር መልኬ ጠፋኝ ነች! (ሁልጊዜ መስታወት አብዝታ የምታይ ሴት) ይህ ድርጊቷ ብቻ ቋቅ ሊያስብለኝ ይደርሳል:: በጣም ጭሰታም የሆነችው ሩት የፕሮቴስታንት

እምነት ተከታይ ከሆኑ የደሀ ቤተሰብ የተወለደች ልጅ ነች፤ ግን ጠንክራ ተምራ ራሷንም ሆነ ቤተሰቧንም ለመለወጥ አንዳችም መነሳሳት እና ተጠያቂነት የሚባል ነገር የላትም:: በሌላ በኩል የተለያዩ ሱሶች እስረኛ ሆናለች፤ አንድ ቀን አመሻሽ ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ አውርተን ነበር::

"አንቺ ግን ዛሬ እንኳ ከእኛ ጋር ጭሰት ለምን አትወጪም?" አለችኝ:: እኔም አጋጣሚውን በመጠቀም የራሷን ህይወት በሾርኔ የራሴ አድርጌ መናገር ጀመርኩ::

"ሩትዬ! እኔ የደሀ ልጅ ነኝ! በትምህርቴ ጠንክሬ ለአላማ በመማር ራሴንም ቤተሰቦቼንም መርዳት አለብኝ:: ቤተሰቦቼን እንኳ ባልረዳ ራሴን በመርዳት ሸክማቸውን ማቅለል አለብኝ:: አንቺም ሩትዬ እንደ እኔ ብታደርጊ ጥሩ አይመስልሽም? እንደ ነገርሽኝ ደግሞ አንቺም የደሀ ልጅ ነሽ፤ ሁኔታሽን ግን ሳጤነው ትምህርቷን ጠንክራ በመማር ድህነትን ለማሸነፍ የምትፍጨረጨር ዓይነት ልጅ አያስመስልሽም:: ተሳስቻለሁ ሩትዬ?" አልኳት በሚሰረስር ሁኔታ እያየዋት::

"ልክ ነሽ ግን ከገባሁበት ሱስ በቀላሉ መውጣት አልችልም፤ በዚያ ላይ ስለነገም ሆነ ስለ ቤተሰቦቼም መጨነቅ አልፈልግም:: አራት ነጥብ" በማለት ነበር ወሬውን ወዲያው የዘጋችው:: ከሩት ጋር ይህን ባወራን አምስተኛው ወይም ስድስተኛው ቀን ምሽት ላይ ሣራ እና ሩት ስክር ብለው መጡ:: እኔ ያጋጣሚ ሆኖ ከሽንት ቤት እየተመለስኩ ነበር:: ጥግ ላይ መብራት ብዙም የማይበዛበት ቦታ ተወሽቀው ከንፈር ለከንፈር ሲላላሱ በዓይኔ በብረቱ አየሁኝ:: እነሱ መሆናቸውን ይበልጥ ለማረጋገጥ ተጠግቼ አየሁኝ:: ራሳቸው ሣራ እና ሩት ናቸው:: እያዘንኩ ወደ መኝታ ቤቴ ተመለስኩ:: ይህን ነገር ለማንም አላወራሁም! የማወራት ፍላጎትም የለኝም! ከመክሊት ጋር ብዙ የሚያመሳስለን ነገር ስላለ እና ሁለታችንም ለትምህርታችን ከፍተኛ ትኩረት ስለምንሰጥ ከሁሉም ይልቅ ጓደኝነቴን ከመክሊት ጋር ለማድረግ ወሰንኩ:: ምን ይታወቃል? ምናልባት እኮ ሀይስኩል እያለች ይቺ ሩት የተባለች ወጣት የዚያች የሊሊ. ሽመክት የዝሙት ባንዲራ ተጠቂ የነበረች ይሆናል:: ምን ይታወቃል? ያቺ ሊሊ. ሽመክት የተባለች ሴት በርከት ያሉ የሀይስኩል ተማሪዎችን በዝሙት ባንዲራ ለከፋቸው የለም? እናም ይሆናል... :: ይህ የእኔ ንፁህ ግምት ነው::

ሀቁን ለመናገር የዩኒቨርሲቲ ትምህርት በጣም አስቸጋሪ አይደለም:: ቀላልም አይደለም:: መቼ? እንዴት? በምን መልኩ? የሚሉትን መመለስ እና በትኩረት ማጥናትን ይጠይቃል:: አስቸጋሪው እሳት የሆነውን የወጣትነት፣ የነጻነት ህይወት እና ከቤተሰብ ቁጥጥር ነፃ መሆንን በማመን ራስን የመግዛት ጥበብን ማወቅ ይጠይቃል ... ብቻ ዓመቱ ሳይታሰብ ነበር ያለቀው:: የመጀመሪያ ዓመት ውጤትን እኔና መክሊት አሪፍ ውጤት በማምጣት ጨረስን:: በተለይ የእኔ ውጤት ምርጥ ነበር:: ሁለቱ ጭስታሞችና የሴዚቢኒያኒዝም መንፈስ ያለባቸው ሩትና ሣራ ለትንሽ ተንጠልጥለው አለፉ:: የትምወርቅ በመካከለኛ ውጤት አለፈች:: ሀዊ ብታልፍም በቤተሰባዊ ጉዳይ በሚቀጥለው ዓመት እንደማትመጣ ነግራን ተለየችን :: ክረምቱን ከአጎቴ ጋር አሳለፍን:: ባንክ ቤት ያለውን በርካታ ሚሊዮን ብሮች ማንቀሳቀስ እንደምችል ሙሉ ለሙሉ ተረጋገጠልኝ:: በአጎቴ ምክር በሁለት ዓመት ውስጥ ትርፍ የሚገኝበት የአንድ ሚሊዮን ብር አክሲዮን በስሜ ገዛሁ:: ከአዲስ አበባ ብዙ ርቀት ላይ የማትገኘው ቡራዩ ከተማ በመሄድ ከአንድ ገበሬ ላይ በአንድ ሚሊዮን ብር መሬት በስሜ ገዛን:: እንደ አጎቴ ገለጻ ይህን መሬት ከሁለት ዓመት በኋላ ለመሸጥ ብንፈልግ ዋጋው እንደሚጨምር ነገረኝ:: ኢትዮጵያ ውስጥ የወርቅ እና የመሬት ዋጋ እየተወደደ እንደሚመጣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ ዋጋ እየረከሰ እየመጣ እንደሆነ እያዘነ ነገረኝ:: ከዚው ከመግዛት ጋር በተቀራኘ ቦሌ እና አራት ኪሎ የተመረጡ ሁለት ቦታዎች ላይ ከሚገኙ የንግድ ሱቆች በስሜ ሁለት ሱቆች ገዛን:: ለጊዜው ከሁለቱ ሱቆች እያከራየሁ ገንዘብ እንደማገኝ አጎቴ ነገረኝ:: ባጠቃላይ ባንክ ቤት ካለው በርካታ ብር አራት ሚሊዮን ብሩን በስራ ላይ እንዲውል አደረግነው:: ከዚህ በተጨማሪ በክረምቱ እማር የነበረውን የሙዚቃ እና የካራቴ ትምህርት ስለጨረስኩ ለ44 ቀናት የሚሰጥ የኢንተርፕሬነርሺፕ አጭር የስልጠና ት/ቤት በመግባት በርካታ ቁም ነገሮችን ስለንግድ እና ስለ ገንዘብ አያያዝ እንዲሁም ውስጣችን ስላለው የታመቀ ሀይል አጠቃቀም በሚገባ ለመረዳት ቻልኩኝ፤ ከዚህ በተጨማሪም ስለኢንተርፕሬነርሺፕ የሚያብራሩ ሁለት ታዋቂ መጽሐፍትን በመግዛት አነበብኩ:: አሁን በጣም የገባኝ አንድ እውነት እያንዳንዱ ግለሰብ ለዚች ምድር በቀኝም ይሁን በግራ እኩል ጠቃሚ እንደሆነ ነው:: በሌላ በኩል ገንዘብ በስራ ላይ ካልዋለ በዝምታ ባንክ ቤት ቢቀመጥ ትርጉም የሌለው መሆኑን እና ከጊዜ ጊዜ የመግዛት አቅሙ እየተዳከመ እንደሚመጣ ነው፤ ብቻ ለእኔ ከጠበኩት በላይ አሪፍ ክረምት ነበረች... ሳላስበው በፍጥነት ያለቀች ክረምት ነበረች:: ብዙ መስራት እንዳለብኝ

የተገነዘብኩባት ልዩ ክረምት ነበረች:: እያንዳንዱ ሰው የህይወት ጥሪ እንዳለው የተረዳሁባት ክረምት ነበረች:: አንድ ዶክተርም ሆነ አንዲት መሬት የምትጠርግ ሴትም ለዚች ምድር አስፈላጊነታቸው እኩል መሆኑን የተረዳሁባት ክረምት ነበረች::

የሁለተኛ ዓመት ትምህርት ተጀመረ:: ከትምህርት ክፍላችን የተወሰኑ ተማሪዎች ተጭረዋል:: በቀይ መብራት ውስጥም የተቀመጡም ተማሪዎች እንዳሉም ሠምቻለሁ:: ይህን ዓመት ጨረስኩ ማለት በሚቀጥለው ዓመት ተመራቂ ነኝ ማለት ነው:: ለካ! ዘመን በቀላሉ እንዲህ ይበራል? አብዛኛው ተማሪዎች ጠንክረው ከመማር ይልቅ ፈተና ሲደርስ ብቻ እያጠኑ መዝናናትን መርጠዋል:: ፈተና እስከሚደርስ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ሀሳዋን በታላቅ ጭፈራ፣ ዝሙት ፣ በዋልፈሰስ እና በአንቶፍንቶው ያቃጥላሉ:: ይህን ስታዘብ ለዚች ምስኪን በእያንዳንዱ ዓመት ፈተና የማያጣት ኢትዮጵያ በጣም እጨነቅላታለሁ:: ይህ በዝሙት ባንዲራ ማውለብለብ ከፉኛ የተለከፈ ትውልድ እንዴት ይቺን ኢትዮጵያን ይቀበላታል እላለሁ? ይህ በዘረኝነት ውስጡ የተሞላ ትውልድ እንዴት ኢትዮጵያን ሊቀበላት ይችላል እላለሁ? እውነተኛ የወጣትነት ትርጉም የገባቸው ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ናቸው:: የወጣትነት ፍቺው በጣም ተናግቷል:: በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለወጣትነት የተሰጠው ድፍና አራምባናቆቦ ሆኗል:: ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለእኔ የወጣልኝ ቅፅል ስም አሮጊቷ እና የድሮ ሰው የሚል መሆኑን ነግረውኛል:: ከመንገርም አልፎ ሲጠሩኝም ምንም ሳይጨንቀኝ እና ልጅ እያለሁ አጎቴ የነገረኝና ያቺን የገደል ማሚቶ ታሪክ እያስታወስኩ አቤት እላለሁ:: እንግዲህ ይህ ስም የወጣልኝ ስለማልቅም፣ ስለማላጨስ ፣ ዳንኪራ ቤት ስለማልሄድ እነርሱን ስላልመሰልኩ ነው:: አይ ከንቱነት! አይ የህይወትን ትርጉም አለማወቅ! አይ የመዝናናት ትርጉምን አለማወቅ! ለአብዛኛው ለዘመኑ ወጣት መዝናናት ማለት ዝሙት መፈጸም ፣ ጫት መቃም፣ መጠጥ መጋት፣ በስካር መናወዝ፣ እስከምሽቱ ስድስት ሰዓት ድረስ መጨፈር ፣ ራስን መርሳት ነው ብለው አብዛኞች አምነዋል:: አይ ከንቱነት! ወጣትነት ፋሽን ተከታይ ዘናጭ ተሽቀርቃሪ መሆን ማለት አይደለም! ወጣትነት ራስን በሱሶች ማጠር ማለት አይደለም! ወጣትነት በምክንያታዊነት ሳይሆን በስሜታዊነት እየተነዱ ራስንና ሌላውን አደጋ ውስጥ

መዝፈቅ ማለት አይደለም! ወጣትነት ብዙ ጃንቦ የጠጣ ጀግና ማን ነው መባባል ማለት አይደለም! ወጣትነት ብረት ገፍቶ ደረትን ማሳበጥ ማለት አይደለም! ወጣትነት ሺሻ ቤት ተቀምጦ ጭስ ማቡነን ማለት አይደለም! ወጣትነት በወሲብ ሱስ ከዚህም ከዚያችም ጋር በዝሙት ተወጥሮ መልከስከስ ማለት አይደለም! ወጣትነት በጥላቻ እና በዘረኝነት ተሞልቶ መታወር፣ መደባደብ እና መነታረክ ማለት አይደለም! ወጣትነት ተመልሶ የማይመጣውን ተፈጥሮ የሰጠችንን ታላቅ ኃይል በማይረባው ነገር ጊዜን ማቃጠል ማለት አይደለም! ወጣትነት ጊዜያዊ ስሜትን ብቻ እያዳመጡ እንደፈረስ ጋሪ መነዳት ብቻ አይደለም! ወጣትነት በሀሜት፣ በአሉባልታ፣ በወሬ ሱስ፣ በአቃቂር፣ በተንኳሽነት፣ በቧልት መሞላት ማለት አይደለም! ወጣትነት ይሄንንም ያንንም ይቺንም ያቺንም መጀንጀን መጀናጀን ማጀናጀን ማለት አይደለም! ወጣትነት በባዶ ጭንቅላት ምርጥ አልባሳትን ለብሶ አልያም ምርጥ የፀጉር ቁርጥ ተቆርጦ እየተጀነኑ በባዶ ኩራት ተወጥሮ መሬትን ለመርገጥ እየተጸየፉ መራመድ ማለት አይደለም! ወጣትነት በግዴለሽነት፣ በተስፋ መቁረጥ፣ ከነፈሰው ጋር መንፈስ ማለት አይደለም! ወጣትነት በራስ ወዳድነት መንፈስ መወጠር እና እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ማለት አይደለም! ወጣትነት በማይረባው በቀበሌኛ አመለካከት መታጠር ማለት አይደለም! ወጣትነት ቁንጫ የምታክል እውቀት በመያዝ ይቺ እውቀት ብቻ ትበቃኛለች እያሉ አጉል መመጻደቅ ማለት አይደለም... ወጣትነት ባህር ነው:: ወጣትነት ውቂያኖስ ነው:: ወጣትነት አድማስ ሰፊነት ነው:: ወጣትነት እውቀትን ለማስፋት የምንጋደልበት ሰዓት ነው:: ወጣትነት በማስተዋል ብርሃን መሞላት ነው:: ወጣትነት ችግር ፈጣሪነት ሳይሆን ችግር ፈቺነት ነው:: ወጣትነት በዘረኝነት ተሞልቶ አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ወላይታ... ቅብርጥሶ እየተባባሉ ቡድን በመስራት ስለ ቀበሌኛ አስተሳሰብ መስበክ ሳይሆን ወጣትነት ስለ ኢትዮጵያዊነት ከተቻለም ስለ አለም አቀፋዊነት እይታን ማስፋት ነው:: ወጣትነት ፍቅርን እና አንድነትን መስበክ ነው:: ወጣትነት በዝሙት ባህር መንቦራጨቅ ሳይሆን ስሜትን የመግዛት ጥበብ ማዳበር ነው:: ወጣትነት አንድን ነገር በአንድ ዓይን ሳይሆን በሶስት ዓይን የመመልከት ጥበብን ማዳበር መቻል ነው:: ወጣትነት ብርሃን ነው:: ወጣትነት ተስፋ አለመቁረጥ ነው:: ወጣትነት በቀናነት መሞላት ነው! ወጣትነት እስከመጨረሻው ጠብታ ህልምን ለማሳካት መፍጨርጨር ነው:: ወጣትነት ማንበብ ነው:: ወጣትነት መጠየቅ ነው:: ወጣትነት ስለዓለም ፣ ስለ ህይወት፣ ስለ ጥበብ፣ ስለ እውቀት ብዙ ለማወቅ መጠማት ነው:: ወጣትነት ለሌሎች መኖር

ነው:: ወጣትነት ለዚች ሚስኪን አገር ኢትዮጵያ ምን ልስራላት ብሎ ራስን መጠየቅ ነው:: ወጣትነት ስለነገ ትልቅ ህልም እና እቅድ መሰነቅ ነው:: ወጣትነት እሳት ነው:: ወጣትነት ቤንዚል ነው:: ወጣትነት ቅጠል ነው:: ወጣትነት ጤዛ ነው:: ወጣትነት ታክሲ ነው:: ወጣትነት ምርጫ ነው:: ወጣትነት ባህር ላይ ያለች ጀልባ መሆን ነው:: ወጣትነት የመቶ ሜትር ሩጫ ያህል ነው:: ወጣትነት ውስጥን ፈተናን ለማለፍ ማጀገን ነው:: ወጣትነት ከፍርሃት፣ አልችልም እና አይሳካልኝም የሚለውን እስር በጣጥሶ ማለፍ ነው:: ወጣትነት ለአንዳች ስኬት በኩራት እና በሞራል መራመድ ነው... እያየሁት እና የታዘብኩት ግን ተቃራኒውን ነው:: ፍፁም ለየቅል ነው:: ፍጹም የማይመሳሰል ነው:: ይህን ሳስብ ለዚች ፈተና የማያጣት ሚስኪን አገር ኢትዮጵያ እጨነቃለሁ! ይህ በወሲብ ፣ በጫት፣ በሺሻ፣ በተንኮል፣ በዘረኝነት የተወጠረ ወጣት እንዴት ኢትዮጵያን ይረከባታል እያልኩ እጨነቃለሁ:: ይህ ከዲሞክራሲና ከነፃነት ይልቅ ለዳቦ የሚጨነቅ ትውልድ እንዴት ኢትዮጵያን ይቀበላታል እያልኩ እሰጋለሁ! ይህ የራሱ ጥቅም ብቻ ከተሟላለት ስለሌላው ኢምንት የማይጨነቀው ራስ ወዳድነት ከፉኛ የነገሰበት ትውልድ እንዴት ይቺን ሚስኪን ኢትዮጵያን ይረከባታል እላለሁ!? ይህ በስራና በእውነት ሳይሆን በቃልና በአንደበት ብቻ የሚዋደድ ከንቱ ትውልድ! ይህ ሙቅ ሰልቅ ትውልድ! ቢከፍቱት ተልባ ትውልድ! ውሃ በላ ትውልድ! ወገበ ነጭ ትውልድ ! ሰው ጤፉ ትውልድ! ቆሽት አንድድ ትውልድ! በጨዋና ምክር ለሰጪው ቀላል ነው ባይ ትውልድ! ቧልትና ፌዝ አፍቃሪ ትውልድ! የጉማሬ ባህሪን ቁርጥ የተላበሰ ትውልድ! ጉማሬ ዘፈን ይወዳል፣ ጨዋታ ይወዳል፣ ከበሮና ነጋሪት ሲሰማ እየፈነጠዘ ከባህር ይወጣል:: ጉማሬ በበላበት አፉ ይፀዳዳል! በቃ ይህ ትውልድ ቁርጥ ጉማሬን ነው! ይህ የአሮጊት ተረት መስማት የሚወድ ትውልድ! ይህ የአድዋ ድል ቁብ የማይሰጠው ትውልድ! ይህ ምነው ጣሊያን ገዝታን በነበረ የት እንደርስ ነበር እያለ የምኞት ፈረስን የሚጋልብ የነፃነት ፍቺን ያላወቀ ግራጠመም ትውልድ! ይህ ሺ ምክንያት እና ሰበብ ደርዳሪ ትውልድ! ኢትዮጵያን ወደፊት እንዴት ሊያራምዳት ይችላል እያልኩ እቆዝማለሁ! ምንድ ነው ወጣቱን እንዲህ ያዝረከረከው? ምንድ ነው የወጣቱን ሞራል የሰለበው? ምንድነው ወጣቱን ፈሪና በቅቢቃ ያደረገው ? ምንድነው ወጣቱን በዘረኝነት የሞላው? ምንድ ነው ወጣቱን በትንሹ ቶሎ ቅስሙ እንዲሰበር ያደረገው? ምንድ ነው ወጣቱን ማስተዋሉን የሰለበው? ኢህአዴግ ነው?? ወግ አጥባቂነታችን ነው?? ፈሪሳዊነታችን ነው?? ግሎባላይዜሽን ነው?? መርገምት ነው?? እያልኩ እጠይቃለሁ::

አንዳንዴ ደግሞ ጥንታዊ አባቶቻችንን ከፍ ዝቅ አደርጋለሁ:: ድንጋይ እየጠረቡ ድንጋይ የሆነ ትውልድ ፈጠሩ እላለሁ... በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ወጣቶች መብከን እና መከሸፍ እያሰብኩ ራሴን በራስምታት እና ጭንቀት ከምወጥር ሙሉ ትኩረቴን ትምህርቴ ላይ በማድረግ እጠናለሁ:: አነባለሁ:: ያለኝን እውቀት ለማስፋት እና ይበልጥ ለማዳበር ሳልሰለች በታላቅ ትጋት መጽሐፍትን እመረምራለሁ:: እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች እንዳችም ሳልሰስት እውቀቴን አካፍላለሁ:: አንዳንዴ ሁሉ ነገር ሲደብረኝ ደግሞ ሺ ጉድ በውስጧ አቅፋ የያዘችውን ውቢት ሀዋሳን እየዞርኩ እጎበኛለሁ:: አዲስ አበባ ከሀዋሳ አንጻር በንጽህና ግም ነች:: አዲስ አበባ መንገድ ላይ የሚጸዳዳ በሽ ነው:: ሀዋሳ መንገድ ላይ የሚጸዳዳ አንድቀንም አይቼ አላውቅም:: የአዲስ አበባ ወንዶች ሲላከፉ ሙድ አላቸው:: የሀዋሳ ወንዶች ለከፋ ግን ክብርን የሚነካ ነው... ትኩስ ዓሣ ለመብላት እና አስገራሚ ትዕይንቶችን ለማየት ስፈልግ አሞራ ገደል እሰየማለሁ:: አንዳንድ ሰዎች ያልበሰለውን ዓሣ ጥሬውን ሲገምጡት አይቼ የመጀመሪያ ጊዜ ዘግንኖኝ ነበር:: አስር ብር ተከፍሎ የሚገባበትን የአሞራ ገደል የጫት ቃሚዎች ትዕይንት፣ የጠጣዎችን ትዕይንት፣ የአባ ኮዳዎችን ትዕይንት ፣ የትኩስ ፍቅረኞችን ትዕይንት ማየት ሌላው አዝናኝ ነገር ነው:: ሀዋሳን በሚገባ አጠናዋት::የተማሪዎችን መዝናኛዎች እና የሚወራላቸውን እውቅ ጭፈራ ቤቶችን አወኩኝ:: የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለወሲብ ንግድ ስልክ፣ ፎቶዋቸውን እና በአካል የሚቀመጡባቸውን ትላልቅ ሆቴሎችን በሚገባ አወኩኝ:: የሀዋሳን ውብ ሆቴሎች፣ የራቁት ጭፈራ ቤቶች፣ የዝሙት ባንዲራ ለጉድ የሚውለበለብበትን መናሐሪያን እና አስፈሪውን አይጋን በምሽት ላይ ለደህንነት በጣም አደገኛ የሆኑትን መንደሮች በሚገባ ሁሉንም ቀስ በቀስ ለየዋቸው:: የሀዋሳን እጅግ መናጢ ደሀዎች የሚኖሩባቸውን የደከረቱ ሰፈሮችንም ተመለከትኳቸው:: ቆንጆዋ ሀዋሳ የኢትዮጵያ ወጣቶችን ለማርከስ እና ህልማቸውን ለማጨናገፍ በርከት ያሉ የእብደት ቦታዎችን አዘጋጅታ ትጠብቃለች:: ስለ ሀዋሳ ሺ ጉዶች እያጠናሁ፣ ትምህርቴንም በሚገባ እያጠናሁ አንዳንዴ ስለወጣቶችም እየተብሰለሰልኩ ሳይታሰብ ጊዜው ያልቃል:: በአወዛጋቢዋ ሀዋሳ እኔ ደስተኛ ነኝ፤ በተለይ የሀዋሳ አየር ንብረት ለእኔ ተመችቶኛል:: የፍቅር ሀይቅን መመልከት ውስጤን በሀሴት ይሞላዋል:: ምናልባት የተፈጥሮ አድናቂ ስለሆንኩ ይሆናል:: ለመሆኑ ተፈጥሮን የማያደንቅ ግለሰብ የእውነት ጤነኛ ነውን??

የሁለተኛ ዓመት ትምህርቴን በስኬት አጠናቅቄ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩኝ:: አዲስ አበባ ደርሼ ሰውነቴን እንዲቀለኝ ታጥቤ አጎቴን መጠበቅ ያዝኩ:: አጎቴ ገና ሲመለከተኝ ሁሌ በማይለወጠው እውነተኛ ደማቅ ፈገግታ ተቀበለኝ:: ለአጎቴ መቼ እንደምመጣ አልነገርኩትም ነበር:: እቅፍ አድርጎ ሳመኝ:: ስለዓመቱ ትምህርት እና ስለውጤት አወራን:: ተጨዋወትን::

"እስራኤል የምትባል ሴት ነገ አስተዋውቅሻለሁ"

"እስራኤል?" አልኩት ይህን ስም ሰምቼ ስለማላውቅ

"የእኔ ልጅ ነገሩን ያልነገርኩሽ ጉዳዩን እርግጠኛ እስከምሆን ነበር፤ አሁን ግን ሙሉ ለሙሉ በሰላም እየተጓዘ ነው ፤ ስለዚህ ነገ አስተዋውቅሻለሁ:: እስራኤል የምትባል አንድ ልጅ ያላት ባለቤቷን በመኪና አደጋ ያጣች የ30 ዓመት ሴት ጠብሼ ነገሮች በሰላም እየተጓዙ ነው:: አሁን ሰባት ወር ሞላን "በማለት ፈገግ አለ:: ይህ ያላሰብኩት አስደሳች ዜና ነበርና በፍፁም ደስታ ተጠምቄ አጎቴን እቅፍ አደረኩት:: የእውነት አጎቴ ሲደሰት ማየት እፈልጋለሁ:: የአጎቴ ደስታ ማለት የእኔ ደስታ ማለት ነው:: አጎቴ በዓለም ላይ ያሉ ወንዶች ሁሉ አንድ አለመሆናቸውን በሚገባ እንድረዳ ያደረገኝ ፍፁም የማይለወጥ ፍቅር ከልጅነቴ እስከ ወጣትነቴ የሰጠኝ መልካም ሰው ነው፤ እናም የአጎቴ ደስታ የእኔ ደስታ ማለት ነውና እጅግ ደስ አለኝ::

በነጋታው አጎቴ የጠበሳትን ሴት ተዋወኳት:: የሁለት ዓመት ልጅ አላት:: ሴት ልጅ:: እርጋታ የሚነበብባት ፣ ጠየም ያለች፣ ወፍራምም ቀጭንም የማትባል ሴት ናት:: መርካቶ ውስጥ ትልቅ የሚባል የስቴሽነሪ ዕቃ መሸጫ አላት:: ምክንያቱን ባላውቀውም ይቺን ሴት እንዳየዋት ነው ስድስተኛው ስሜቴ የወደዳት:: በተለይ እርጋታዋ ይማርካል:: የአጎቴን የመውለድ ችግር አውቃ ከእነ ችግሩ አጎቴን ለመውደድ እና ለማግባት በመዘጋጀቷ ቅን ልብ እንዳላት ያሳብቅላታል:: ስለ እስራኤል ማታ ከአጎቴ ጋር ስናወራ

"እና መች ለመጋባት ወሰናችሁ?" አልኩት::

"በሚቀጥለው ዓመት ሐምሌ 15/2008 ላይ"

"ለምን ቶሎ አትጋቡም?"

"የእኔ ልጅ ጠቢቡ ሰለሞን በምሳሌ 19፡13፤21፡9 እና 27፡15 ላይ 'ጠበኛ ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት... ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመቀመጥ በውጪ በቤት ማዕዘን ላይ መቀመጥ ይሻላል... በዝናብ ቀን የሚያንጠባጥብ ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው...' ይላል፡፡ ስለዚህ ይበልጥ መተዋወቅ እና መጠናናት ይኖርብናል፤ ስለዚህ ጊዜ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁለተኛ ነገር በሚቀጥለው ዓመት አንቺ ሐምሌ ላይ ትመረቂያለሽ፤ እናም ካንቺ ደስታ ጋር ሁለት ደስታ ለማድረግ በሚቀጥለው ዓመት የተሻለ ነው"

"አሪፍ ሀሳብ ነው! ፈጣሪ ሁሉን ነገር ቀና እንደሚያደርገው ተስፋ አለኝ፡፡ ሌላው ጥሩ ነገር ምን እንደሆነ ታውቃለህ አጎቴ?"

"ንገሪኝ"

"የእስራኤል ልጅ ገና ነፍስ ያላወቀች ስለሆነች እና እውነተኛውን አባቷን ስለማታውቅ አንተን በአባትነት ለመቀበል በጣም ይቀላታል፡፡ ይህ ደግሞ አሪፍ ነገር ነው አይመስልህም?"

" ልክ ነሽ የእኔ ልጅ! ያቺ ምንም የማታውቅ ብላቴና ፍቅር የሚሰጣት አባት ያስፈልጋታል፡፡ እናትም ያስፈልጋታል፡፡ ህጻናት የሚንከባከባቸው እናትና አባት የግዴታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለህጻናት ከምግብም በላይ ዋነኛው አስፈላጊ ነገር የቤተሰብ ፍቅር ነው፡፡ እኔም እንደ ልጄ በመቁጠር ፍቅር እየሰጠዋት አሳድጋታለሁ፡፡ የእኔ ልጅ መወለድ ቋንቋ ነው፡፡ አባትነት እምነት እናትነት እውነት ነው የሚል የኤርትራዊያን ምርጥ ተረት አለች፡፡ እውነትን የያዘች ተረት"

"እርግጠኛ ነኝ መልካም አባት ትሆንላታለህ፤ በዚያ ላይ አሪፍ ስም ይኖራታል፡፡ የትንሿ ልጅ ስም ማርእሸት ስለሆነ ያው ት/ቤት ባንተ ስም ማርእሸት ሶቅራጥስ እየተባለች ትጠራለች ደስ አይልም አጎቴ ?"

"ዛሬ በእጃችን ናት! ህይወት ማለት ዛሬ ናት! ህይወት ማለት አሁን ማለት ናት! ነገ ሁልምናት! የአምላክ ፍቃድ ከሆነ እኔም በስሜ የምትጠራ ልጅ ለማሳደግ እችላለሁ ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ነገር እንደሚሆን ውስጤ እየነገረኝ ነው፡፡ ውስጣችን ሲነግረን ደግሞ ማመን ይኖርብናል፡፡ የውስጣችን እውነት ብርሃን ነው፡፡ ውስጥሽ ትንሽ ብርሃን ካለች ዓለም ላይ ያለውን ግዙፍ ድቅድቅ ጨለማ ታንበረክካለች፤ ትልቁን ፈተና ማሸነፍ ትችላለች፤ ይህን ሁልጊዜ አስታውሺ! በተረፈ በጣም ከልቤ አንቺንም አመሠግናለሁ! የእውነቴን ነው!

ምክንያቱም አንቺ ሀሳቡን ባታነሺ ኖሮ እስከ መጨረሻው ለመኖር የማስበው ብቻዬን ስራዬን እየሰራሁ እና በቀሪው ሰዓት ደግሞ በርከት ያሉ መፅሐፍትን እየመረመርኩ ለመኖር አቅጄ ነበር:: ያን እቅዴን እንድሰርዝ ስላደረግሽኝ አሁን ላይ በመሆን ሳስበው ልክ ነሽ ፤ እናም አመሠግናለሁ" ምንም ሳልናገር አጎቴን እቅፍ አደረኩት:: አጎቴ የዛሬ ዓመት በፍጥነት መጥቶ እና አግብቶ ከፍቅረኛው እና ከዚያች ትንሽዬ ልጁ ጋር ሲጫወት አሰብኩና ውስጤ ካሁኑ በደስታ ተፍነከነከች::

በጣም ደስ የሚል ክረምት ነበረች:: የመንጃ ፍቃድ ትምህርት ጀመርኩ:: ያው ከምርቃት በኋላ መኪና መግዛቴ ስለማይቀር መማር ግዴታዬ ነበር:: በጣም የሚያሳዝነው ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ት/ቤት ሄጄ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ስንወያይ እጅግ በጣም አዘንኩ:: አፈርኩ:: ተበሳጨሁኝም::

"እንኳን ወደ ድርጅታችን መጣሽ! የኔ ቆንጆ ገንዘብ ካለሽ ጊዜሽን በከንቱ ከምታቃጥይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጣጣሽን መጨረስ ትችያለሽ"

"አልገባኝም"

"መንጃ ፍቃዱን በቀላሉ ቤትሽ ድረስ ላመጣልሽ እችላለሁ"

"እንዴ! ሳልማር? ሳልሰለጥን?"

"የኔውብ መንዳቱን እኮ ቀስብለሽ ትማሪያለሽ ዋናው ነገር መንጃ ፍቃዱን መያዝ ነው:: አገራችን ውስጥ መንጃ ፍቃድ ለማግኘት ያለውን ቀላል መንገድ እየነገርኩሽ ነው:: እኔም ልተባበርሽ ዝግጁ ነኝ"

"ገባኝ ታዲያ ስንት ይጠበቅብኛል?"

"ለዚህ የሚገርም ውብትሽ ሲባል በቅናሽ 14600 ብር ይበቃሻል" አለና በግራ ዓይኑም ጠቀስ አደረገኝ::

"በጣም የምታሳዝን እና የማትረባ ከንቱ ሰው ነህ! ስንቶች በየቀኑ በመኪና አደጋ በሚያልቁባት ከተማ እና በመኪና አደጋ ከዓለም ቁጥር አንድ በመባል የተፈረጀች አስቀያሚ

ስም ባላት አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖርክ እና ካንተ በላይ መቼም ይህን አሰቃቂ ዜና የሚያውቀው እንደ ሌለ እያወክ የሰው ልጅ ህይወትን እንዲቀጠፍበት ምንም ሳትሰስት ለገንዘብ ስትል ብቻ እንዲሁ በዋዛ ምንም እውቀት እና የመንገድ ስርዓትን ለማያውቅ ግለሰብ ገንዘብ ስለከፈለ ብቻ ህጋዊ የመንጃ ፍቃድ ወረቀት መስጠት ትልቅ አሳፋሪ ሀጢያት ነው:: ፈጣሪ ከገንዘብ ይልቅ የማስተዋል በርህን ይከፈትልህ! ከእያንዳንዱ በመኪና ተገጭተው የሚሞቱ ሰዎች ስቃይ እና ህይወት ጀርባ እጅህ እንዳለበት ግን አትርሣ!!"

"እንዴ አመረርሽ? እኔ እኮ ስቀልድ ነው! ምን አይነት አስተሳሰብ እንዳለሽ ልፈትንሽ ፈልጌ እኮ ነው" ምናምን እያለ እንደ ህጻን ልጅ ሊሸውደኝ እየቀባጠረልኝ አስልችቶኝ ነበር፣ ግን የቻልኩትን ያህል ነግሬው ሌላ መኪና ማሰልጠኛ ት/ቤት ተመዘገብኩ:: በክረምቱ ሌላው ያከናወንኩት ጉዳይ በትንሽነታቸው ተደፍረው የፌስቱላ ችግር የደረሰባቸውን ህፃናት በመርዳት መልካም ስራ እየሰራ ለሚገኝ ድርጅት 300,000 ሺ ብር እንዲሁም 200,000 ሺ ብር ለአንድ ማየት የተሳናቸውን እየሰበሰበ ለሚያስለጥን ልበ ቀና ሰው ከአጎቴ ጋር በመሄድ የለገስን ሲሆን በተጨማሪ ባንክ ውስጥ ገንዘብ በዝምታ ቢቀመጥ ዋጋ ስለሌለው በሁለት ሚሊየን ብር ቡልቡላ የሚባለው ሰፈር ለንግድ አሪፍ መስቀለኛ መንገድ የሆነ ቦታ ላይ አንድ ቤት በስሜ ገዛን... ከዚህ ውጪ ከአጎቴ ጋር፣ ከአጎቴ ፍቅረኛ እና ትንሽዬ ልጁ ማርእሸት ጋር አሪፍ ክረምትን ካሳለፍኩ በኋላ የመጨረሻ ዓመት ለመመረቅ የሚያበቃኝን ትምህርት ለመማር ወደ ቆንጆዋ ሀዋሳ ከመስቀል አደባባይ በስካይ ባስ አመራሁ:: የዚህ ዓመት ተመራቂ ተማሪ መሆኔን እያሰብኩ ደስ እያለኝ እና በፈገግታ እየተሞላሁኝ:: ለአገሬ ኢትዮጵያ ደረስኩልሽ የምላት ዘመን ስለመጣ ውስጤ በደስታ እንደቅቤ እየቀለጠች ወደ ሀዋሳ ማምራት ያዝኩ:: ለአገር መድረስ ማለት ሙስናን እና ዘመዳ ዘመድ ነክ ትስስርን በመበጠስ ለእውነታ እና በቅን ልቦና ብቻ በታማኝነት መስራት ማለት ነው:: ለአገር መድረስ ማለት ሁሉንም በእኩል ማፍቀር ማለት ነው:: ለሀገር መድረስ ማለት ማንኛውንም ኢትዮጵያ ሀይማኖት እና ዘርን ሳይመርጡ በፍፁም ቅንነት ማገልገል ማለት ነው:: ለአገር መድረስ ማለት በሀላፊነት ስሜት መሞላትና ከራስ ወዳድነት መሸሽ ማለት ነው:: ለሀገር መድረስ ማለት የቃል ሳይሆን የተግባር ሰው መሆን ማለት ነው:: ይህ ነው ለአገር መድረስ ማለት!!

የተለመደው ት/ት ተጀመረ:: በአገሪቱ ያለው የቦለቲካ ውጥንቅጥ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች አንጻር እኛ ጋር ቀዝቀዝ ያለ ነው ማለት ይቀላል:: በቦለቲካ ላይ ያለኝ እይታ የሊበራል አስተሳሰብ አድናቂ ነኝ:: በአፍሪካ ወይም በኢትዮጵያ ደግሞ የስልጣን ወንበር ላይ ለመቀመጥ እውነት እና ሀቅን የያዘ ሳይሆን ምላጭ ምላስ ያለው፤ አለብላቢት ምላስ ያለው፣ ነገር የመጠምዘዝ ችሎታ ያለው፣ ብርሃንን ጨለማ ነው ጨለማን ብርሃን ነው ብሎ ቱሪውን መንዛት የሚያውቅበት ሴይጣንና የሴይጣናዊነትን ባህሪ ጠንቅቆ የሚያውቅ ፣ የሰው ልጅ ውድ ህይወትን ከዝንብ ሞት እኩል የሚቆጥር ሰው ካልሆንክና የቦለቲካን ቁማር አጨዋወት ሳታውቅ ቦለቲካ ውስጥ ጨርሶ አትግባ ይባላል እናም እኔም የቦለቲካን ቁማር አላውቅም :: የኢህአዴግን ቁማር የተቃዋሚዎችን ቁማር፣ የቦለቲከኞችን ቁማር አላውቅም:: የማውቀው ወይም ስድስተኛው ስሜቴ የሚነግረኝ ግን ሀያ አምስት ዓመታትን በስልጣን ወንበር ላይ የተዘፈዘፈው እኔ ብቻ አውቃለሁ የሚለው ኢህአዴግም ሆነ ጠንካራ ህብረት የሌላቸው በስሜት የሚነዱት ተቃዋሚዎች እውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ውስጣቸው እንደሌለ ነው፤ በተለይ ተመራቂ ተማሪ ከመሆኔ ጋር ተያይዞ ብዙ ጉድ ለመታዘብ ችያለሁ:: በርከት ያሉ ተማሪዎች ያለ አንዳች ልፋት እና ውጣውረድ ሥራ ለማግኘት የግድ አባልነትን አሁኑኑ መጠመቅ አለባችሁ ስለተባሉ ወደው ሳይሆን በግድ በፍርሃት በትር ተደቁሰው ለጥቅማቸው ሲሉ ተጠምቀዋል፤ እንግዲህ በእጅ አዙር የእኔን አባልነት እና ደጋፊነት ካልተቀላቀላችሁ ስራ የማግኘት እድላችሁ ጢኖ ነው እያለ የሚያስበካ ከንቱ መንግስት እንዴት ኢትዮጵያን ይወዳታል ማለት ይቻላል? እንዴት በየቦታው ተቃውሞ ላይነሳበት ይችላል? እንዴት ኢትዮጵያ በግለሰቦች ቁጥጥር ስር አይደለችም ማለት ይቻላል? እንዴት ለአንድ ወገን ጥብቅና ብቻ የቆመ ነው የሚባለው ውሸት ይሆናል? ከኢትዮጵያ 95 ሚሊየን ህዝብ 90 ሚሊየን ህዝብ በድህነት ባህር እየዋኘ እንዴት ኢትዮጵያ አድጋለች ማለት ይቻላል? እጅግ በርካታ ሰዎች የስራ እድል የሚያገኙት በኢትዮጵያዊነታቸው ሳይሆን በዘመዳ ዘመድ እና በቀበሌኛ ትውውቅ የሆነባት አገር ውስጥ እየኖርን እንዴት መንግስት አለን ያስብላል? ኮሽ ባለ ቁጥር እየደነገጠ በስብሰናል፣ ገምተናል፣ ተሐድሶ እናደርጋለን የሚል መንግስት እንዴት መንግስት ይባላል? የበሰበሰና የገማ ነገርስ እንዴት መታደስ ይቻለዋል? ጠያቂ ትውልድ ሲነሳበት ፀብ ያለሽ በዳቦ እያለ ጭንቅላታቸውን እየቀወረ እስር ቤት እየዶለ የሚኖር መንግስት እውን መንግስት ነውን? ... እናም ተማሪዎች ስራ ለማግኘት የአባልነት ፎርም ሲሞሉ ሳይ የእውነት

ከልቤ በኢትዮጵያ አዘንኩ። በዚህ በአገሬ ከንቱ ከንውን እና በወጣቶች መከሸፍ እየተብሰለሰልኩ ወራቱ ሳይታሰብ ይንጉዳሉ። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከመከሊት በስተቀር እውነተኛ የሴትም ሆነ የወንድም ጓደኛ የለኝም። ከተወሰኑ ሴቶች ጋር ጓደኝነት ለመቅረብ ጥሬ ነበር ፤ ግን የሴቶቹ ወሬ አይጥመኝም፣ ስለ ወንድ ፣ ስለወሲብ፣ ስለፋሽን እና መንደርኛ ወሬ ማውራት ያስጠላኛል። መስማትም ያንገሸግሸኛል። በርካታ ሴቶች ከእውቀት ይልቅ ቧልትን መርጠዋል። አዕምሮያቸውን በእውቀት ከማስዋብ ይልቅ ቆዳቸውን በቻይና ስራሽ አልባሳት እና በታይላንድ አርቴፊሻል ዊግ ማስዋብን መርጠዋል። ስለዓለም ጥበብ ከማውራት ይልቅ ስለወንዶች ፣ ስለጀነጀናቸው ወንድ፣ ስለ አደረጉት ወሲብ፣ ስለ ጭፈራ ቤት፣ ስለ ተንቀባረሩበት ወንድ... መሰል ለእኔ እጅግ ተራ ሚዛን የማይደፉ ወሬዎችን ያወራሉ፤ ይህ ለእኔ ትርጉም አልባ ነው። እናም ይህን መሰል ከንቱ ወሬ ከመስማት ብቸኝነት የከበረ ዋጋ አለውና ብቸኝነቴን መርጬያለሁ። በዚህ ደግሞ አልተከፋሁም። በሌላ በኩል ልቀርባቸው የወሰንኳቸው ወንዶች በሙሉ አልሸሹም ዞር አሉ ናቸው። አብዛኛው ኢትጵያዊያን ወንዶች እኔ እንደተገነዘብኩት የሴት ጓደኛ መያዝ አይችሉም። ጓደኛዬ ይሉና ትንሽ ቆይተው "አፈቀርኩሽ! የእኔ የልብ ትርታዬ ነሽ" ይላሉ። የጓደኝነት ድንበራቸውን በፍጥነት ይሠርዙና የወሲብ ጥያቄ እንደተራ ነገር ያነሣሉ ፤ በዚያ ላይ ልቀርባቸው እና ራሳቸውም በግድ ሊቀርቡኝ ፈልገው የቀረብኳቸው ወንዶች ወሬያቸው ራሱ ሚዛን አይደፋም። ስለ ኢንግሊዝ ኳስ፣ ስለመጠጥ ፣ ስለሺሻ፣ ስለ ጫት፣ ስለ ሴቶች ቅብርጥሶ ነው። እኔ ከወንዶችም ሆነ ከሴቶችም ጋር ማውራት የምፈልገው ስለጥበብ፣ ስለህይወት ፣ ስለፍልስፍና ፣ ስለ አላማ ያለው ህይወት፣ ስለማንነት ፣ ስለ ኢትዮጵያዊነት ፣ ስለ ስብህና ነው፤ ይህን ላገኝ አልቻልኩም፤ በዚህ የተነሣ ከወንዶቹም ጋር መመሳሰል እና ማስመሰል መቻል አቅቶኝ ሳይሆን ስላልፈለኩ መራቅን መረጥኩ። እውነቱን ለመናገር ተመሳስሎ መኖር የሚያቅተኝ አይደለሁም። ከሁሉም ጋር የእውነት እና የለበጣ ፈገግታ እየሰጠዋቸው መኖር ለእኔ በጣም ቀላል ነው፤ ግን ከዚህ ይልቅ ውስጤ ሰላም የሚያገኝበትን መንገድ መርጬ መራቅን መረጥኩ። በዚህ የተነሣ "አሮጊቷ እና የድሮ ሰው" እያሉ ሙድ ለመያዝ ይሞክራሉ። የተወሰኑት ሁልጊዜ ምክር ስለማበዛ እና ስህተታቸውን ሳልሸነግላቸው በድፍረት እና በግልጽነት እንዲያሻሽሉ ስለምነግራቸው ደግሞ ንክ ቢጤ እመስላቸዋለሁኝ። ሁሉንም የምንቃቸው አንዲት ቁልል እና ጉረኛ ሴት እመስላቸዋለሁኝ። የተወሰኑት ደግሞ ሀይስኩል

እያለሁ ሀይለኛ ፍቅር ይዞኝ የተጓዳሁ እና በዚህ የተነካ ከወንዶችም ሆነ ከሴቶችም የምርቃቸው እመስላቸዋለሁኝ... ብቻ በዚህም በዚያም እያለ የዓመቱ ትምህርት በፍጥነት መገስገስ ያዘ፡፡ የወጣቶቹን ሁኔታ ሳውጠነጥን ያ ትንቢት አገሬ ኢትዮጵያ ላይ እየሆነ ይሆን እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ? "... ሀይወት የሚገኝበትን ት/ት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልን፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደገዛ ምኞቶቻቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፡፡ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ" 2ጢሞ 4፡3-4 ያለው እየሆነ ይሆን??

በጣም ደበር ካለኝ ደግሞ በጣም የምወደው ፍቅር ሀይቅ እሄዳለሁ፡፡ ፍቅር ሀይቅ እጅግ ብዙ ትዕይንት ስላለ አዕምሮዬ ዘና ይላል፡፡ ለእኔ የፍቅር ሀይቅን ውሃ ማየት መረጋጋት እና ደስታን ይሰጠኛል፡፡ በተለይ ማታ ላይ የፍቅር ሀይቅ ላይ ጸሐይ ስትጠልቅ እና ብርሃኗን በሀይቁ ላይ ስታንጸባርቅበት የሚፈጠረውን ምስል ማየት አይ አንቺ ውብ ተፈጥሮ ያስብለኛል ከማስባልም መንፈሴን ይለውጠዋል... እናም ፍቅር ሀይቅ ለእኔ ውድ ቦታ ነች አሁንም ፍቅር ሀይቅ ከሚገኘው ፍቅር መዝናኛ ውስጥ ተቀምጬ ሐይቁ ላይ የሚከናወነውን ትዕይንት እያየሁ ሣለ ከአጠገቤ ራቅ ብለው የተቀመጡት ፍቅረኛሞች ትኩረቴን ሰረቁት፡፡ ባላውቃቸውም ከሁኔታቸው እኔ በወሬያቸው መሀከል ጣልጣል እያደረጉ ከሚያወሩት የኢንግሊዝኛ ቃላት በመነሳት እና ያለሁበት አልያም የሁለተኛው ግቢ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንደሆኑ ብዙ የሚያሳብቅባቸው ነገሮች አሉ "እንደምትይው የእውነት የምትወጂን ከሆነ ፍቅርሽን በወሲብ ግለጪልኝ! አካልሽን ከአካሌ ቁርኝነት እናስፈጥራቸው! አዳም ሔዋንን እንዳወቃት እኔም አንቺን እንዳውቅ ፍቀጂልኝ"

"እሺ ግን ያለ ኮንዶም በሚለው ሀሳብ ጨርሶ አልስማማም!!"

"በኮንዶም ወሲብ መፈፀም አፍንጫን አፍኖ የፅጌሬዳ አበባን ለማሽተት እንደመሞከር ነው ይላሉ ሩሲያዎች"

"የፈለከውን ብትል አልስማማም! ያለ ኮንዶም ወሲብ አድርጌ ራሴን ለአደጋ ማጋለጥ አልፈልግም"

"ምን ማለት ነው አደጋ?"

"እርግዝና... በሽታስ?"

"እኔን በበሽታ ትጠረጥሪኛለሽ ማለት ነው?"

"ነገር አታዞር! ከቾች ካልከ አብረን ሄደን ሆስፒታል እንመርመር፤ ከዚያ የሚሆነውን እንወስናለን"

"በቃ ይህ ነው ውሳኔሽ?"

"አበቃሁ! ሴት ነኝ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብኝ፤ በዚያ ላይ የእውነት አንተም የምትወደኝ ከሆነ የወሲብ ጥያቄህን አንሳልኝ" ወሬያቸውን ሳያስጨርሱኝ ድንገት ወንዱ ተነሣ:: ሴቷም ተነሣች:: ወንዱ ላይ ብስጭት ቢጤ ይነበባል:: እኔ ከተቀመጥኩበት አቅጣጫ በተቃራኒው ወደ መውጪያው በር እንደተዘጋጉ ማምራት ያዙ... ይህን መጨረሻውን ያላወኩትን ትዕይንት በማቆም መልሼ ዓይኔን ሀይቁ ላይ ጣልኩኝ::

ብዙም ሳይቆይ አንድ ሽማግሌ እኔ ያለሁበት ቦታ መጥተው ሊቀመጡ ሲሉ በፍጥነት ከወንበሬ በመነሳት እንዲቀመጡ መቀመጫውን አስተካከልኩላቸው:: ተቀመጡ::

"ተባረኪ የእኔ ልጅ!" አሉኝ:: በፈገግታ ብቻ ዝም አልኩኝ:: ሙሉ ፀጉራቸው ነጭ ነው:: ስንት ዓመታቸው ይሆን? የወጣትነት ዘመናቸውን እንዴት አሳልፈውት ይሆን? ዓይናቸውን ከሀይቁ ላይ ተከለዋል::

"አባባ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ?"

"እንዴ! የሚያዋራኝ ካገኘሁማ ደስ ይለኛል፤ ጠይቂ የእኔ ልጅ! ምን የዘንድሮ ወጣት ከሽማግሌ ጋር መቀመጥም ሆነ ማውራትም ደስ አይለውም! አንቺ ማስተዋል አለሽ ማለት ነው! ጠይቂ የእኔ ልጅ የሚያዋራኝ ሳገኝ ደስ ይለኛል"

"ስንት ዓመቶት ነው?"

"70 ሆነኝ"

"ከዚህ በኋላ ስንት መኖር ይፈልጋሉ?"

"የእግዜር ፍቃድ ነው! ዋናው እኔ የምፈልገው ሳልታመም ድንገት እንድሞት ነው"

"በወጣትነቶ ምን ነበሩ?"

"ሊስትሮነት ሰርቻለሁ! አሳ እያጠመድኩ እሸጥ ነበር! ዋና አስተምር ነበር፤ ከዚያ ንግድ ውስጥ አሳለፍኩ፤ ቀጥሎ የእግዚአብሔርን ቃል አስተማሪ ሆንኩ:: በተለይ ሰባኪ እሆናለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም ግን ሰባኪነት መጠራት ነው:: ጳውሎስ አሣ አጥማጅ ነበር፤ ሳወል እጅግ ነፍሰ በላ ነበር:: የአስራ ሁለቱን ሀዋሪያት የግል ህይወታቸውን ብታነቢ አንዳቸውም የወንጌል ቃል ሰባኪ እንሆናለን ብለው አስበውት አልነበረም፤ እኔም እንደዛው ነበርኩ:: አየሽ ተንኮል የሌለበትን የቃሉን ወተት መመኘትን የመሰለ ነገር የለም:: የእ/ር ቃል

መስበክን የመሰለ አስደሳች ነገር የለም፡፡ በማቴ 10፡32 ላይ በሰውፊት ለሚመሠክርልኝ ሁሉእኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሠክርለታለሁ ይላል፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ ያለው አደገኛ ነገር በሥህተት እና በረቀቀ ድንቁርና ላይ ተመስርቶ ከልብ የታመነበትን አስተሳሰብ ያህል ዐደገኛ ነገር የለም፤ ይህን ለመስበር እና በዚህ አስራት ውስጥ ያሉትን ወገኖችን የእውነት በርን ለማሳየት የቻልኩትን ያህል ጥሬያለሁ፤ በዚህ የተነሣ የመከራ አይነትን አይቻለሁ! ነፍሴን አምላከ እየታደጋት እስከዛሬ አለሁ"

"ሀይማኖቶ ምን ነበር?"

"የእኔ ሀይማኖት የወንጌሉ የቃል እውነት ነው! ስለ ወንጌል ቃል እውነት አወራ ነበር እንጂ እንደ ዘንድሮ ሰባኪዎች አልወሸከትም ነበር"

"የዘንድሮዎቹ ይወሸኪታሉ እንዴ?"

"የወንጌሉ ቃል በግልፅ ያስቀመጠው በሠማያት ያለውን የአባቴን ፍቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም ይላል፡፡ የዘንድሮ ሰባኪዎችም ሆኑ ቄሶችም የቃላት ከምር እና ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ብቻ ላይ ናቸው፤ በተለይ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስብከት ቅጥ ያጣበት ሰዓት ነው፡፡ የአገራችንን ከርስትና በተመለከተ የውጪ ዜጋዎች በዓለማችን ከከርስቶስ በፊት ከርስቲያን ሀገር እንደሆነች ጉራዋን እየቸረቸረች የምትናገር ብቸኛ ከንቱ አገር ኢትዮጵያ ናት እያሉ ያላግጡብናል፡፡ እውነታቸውን ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን ዘመናዊ ፈሪሳዊያን ነን፡፡ በወግ ማጥበቅ የምንድን ይመስለናል! እምነታችን ሁሉ የታይታ ነው፡፡ አገራችን ውስጥ ያሉት የእምነት ድርጅቶች እውነተኛውን ወንጌል ከመስበክ ይልቅ ጥቅማቸውን ቀማሪዎች በዝተዋል፡፡ ገንዘብ አፍቃሪዎች፣ የእኔ ሀይማኖት ይበልጣል ባዮች፣ የተዓምራት ነጋዴዎች፣ የጸበል ቸርቻሪዎች፣ ስለምድራዊ ቁስ እና ገንዘብ ሰባኪዎች፣ ለምዕመናን ባዶ ተስፋ መጋቢዎች፣ የእ/ርን ቃል እና ዘረኝነትን እኩል ከመስበክ አንዳችም ፍርሃት የማይዘቸው ያልተሰበኩ ሰባኪዎች፣ ስለ እውነተኛው የወንጌል ቃል ሳይሆን የራስ ሀይማኖት ድርጅትን ከፍከፍ አድራጊዎች ፣ ራሳቸው በታላቅ የሀጢያት ባህር ተውጠው ስለፅድቅ ሰባኪዎች የነገሱበት በሌላ በኩል ደግሞ ተከታዮችም አይናቸውን በጨው አጥበው ስለሚያገኙት ጥቅም እንጂ ስለ እውነተኛ ወንጌል መስማት ቋቅ የሚላቸው ሆነዋል፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ራዕይ 3፡5 ላይ የተገባቸውም ስለሆነ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ ይላል ነጭ፤ ልብስ የሚወከለው ንስሐን ነው፡፡ ከሀጢያቱ ስርየት ያገኘን ግለሰብ ነው፡፡ በሌላ በኩል እኛ አገር ያሉት የዘንድሮ ሰባኪዎች ነጭ ልብስ መልበስ ያቃታቸው፣ ስለ

ነጭ ልብስ በድፍረት የሚያወሩ ናቸው፡፡ በቅርቡ ግን አምላክ ሁሉንም በመምታት አንከርድዱን ከገለባ ያጠራዋል፡፡ አየሽ በመረጃ ወይም በእውቀት መሞላት እምነትን ሊወክል አይችልም፡፡ እውቀት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ስለበጎ ምግባራት ሁሉ የጠለቀ እውቀት ቢኖረውና ወደ ህይወቱ ቀይሮ የማይጠቀማቸው ከሆነ ምን ይጠቅመዋል? ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሐዋ 20፡35 ላይ ከሚቀበል ይልቅ የሚሠጥ ብፁህ ነው ይላል፡፡ ስለመስጠት መልካምነት ሰዎች እንዲያደርጉት እየመከርሽ አንቺ የማትሰጪ ስቁንቁን ከሆንሽ ምን ዋጋ አለው? በተግባር ያልታከለ ቃል ከንቱ ነው፡፡ ለምሳሌ እራበኝ ለሚልሽ ግለሰብ አንቺ የማትበይውን ብትሰጪው ወይም በረደኝ ለሚልሽ ሰው አንቺ የማትለብሽውን ብትሰጪው መስጠት ሳይሆን በማጣቱ ላይ መመፃደቅ እና የበላይነትሽን ማሳየት ነው፡፡ ምጽዋት ወይም መንፈሳዊ ስጦታ ማለት ያለሽን እና የምትፈልጊውን ያለ አንዳች ስስት ማካፈል ማለት ነው፡፡ ከምትበይው ማብላት፣ ከምትለብሺው ማልበስ እንጂ ትራፊሽን እና የማትፈልጊውን መስጠት ማለት አይደለም፤ ይህን እንኳ በቅጡ የማያስተምሩ ሰባኪዎች ነው ያሉን"

"ህይወት ግን ለእርሶ ምንድናት?"

"እህ ወጣት እያለሁ ህይወት ማለት ነገ ሳትሆን ዛሬ ናት፤ እኛ የሰው ልጆች በጣም የሚያረካን በተቃራኒው ስለዛሬ ሳይሆን ስለ ነገ ማውጠንጠን ነው፡፡ ስለማናውቀው ነገ! ስለማይጨበጠው ነገ... ህይወትን ህይወት ያስባላት ይህ ባህሪያችን ነው፡፡ ስለ ነገ ማሰብ ባይኖር ምን ይውጠን ነበር?? እያልኩ አውጠነጥን ነበር፡፡ በመጨረሻ የገባኝ ግን ህይወት ማለት የቃሉን እውነት ማወቅ እና የእግዚሐብሔርን የፍቅር ብዛት መረዳት መሆኑን አውቄያለሁ"

"ለምሳሌ ከቤተሰቤ የወረስኩት ገንዘብ ቢኖረኝ ምን ማድረግ አለብኝ?"

"መፅሐፍ ቅዱስ ላይ 'ደግ ሰው ለልጅ ልጆቹ ውርስ ትቶ ያልፋል... የኃጢአተኞች ሀብት ግን ለፃድቃን ይከማቻል' ይላል፤ ብዙዎች ከፈጣሪ ጋር የተቆራረጡት፣ ብዙዎች ሀጢያት እየሠሩ የሚገኙት በገንዘብ ጉዳይ ነው፡፡ የገንዘብ አምላኪነት የሀጢያት ስር ነው፡፡ ገንዘብ ራሱን የቻለ አምላክ ነው፡፡ ዓለም ላይ በቂ ሀብት አለ፡፡ ይህ ሀብት ለእያንዳንዱ ሰው ይበቃል፡፡ ይህ ሀብት ግን ለእያንዳንዱ ስግብግብ ሰው አይበቃውም፡፡ አሳሳቹ ሴይጣን ደግሞ ሰዎችን በስግብግብነት መንፈስ ይሞላቸዋል፡፡ ታላቁ መፅሐፍ ቅዱስ ሥጋ ሁሉ እንደሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና ሣሩ ይጠወልጋል፤ አበባውም ይረግፋል ይላል፡፡

የዓለምን ሀብት ይሁን ቅራቅንቦ እዚው ጥለነው እንሄዳለን:: በእርግጥ ሀብታም መሆን ሀጢያት አይደለም:: በንፁህና እና በንፁህ ላብ የመጣ የሀቅ ገንዘብ ችግር የለውም:: በረከት ነው:: ለምሳሌ ከቤተሰብሽ የወረሽው ብዙ ብር አለሽ ማለት ያ ገንዘብ ያንቺ ነው ማለት አይደለም :: ብዙ መልካም ነገር እንድትሰሪበት እና ያን ገንዘብ በአግባቡ እንድታስተዳድሪው ትልቅ ሀላፊነት ብቻ ተሰጠሽ ማለት ነው:: እውነታው ይህ ነው:: በዚህ ምድር ላይ የእኔ የምትይው ነገር የለም:: ራቁት ትመጫለሽ! ራቁት ትመለሻለሽ! የምትረግጪው መሬት የእግዜር ነው! የምትተነፍሺው አየር የእግዜር ነው! የምትጠጪው ውሃ የእግዜር ነው! የእኔ የሚባል ነገር የለም! የእኔ እያልን በእኔነት እንድንታወር የሚያደርገን የክፉ መንፈስ ባለቤት የሆነው ሴይጣን ብቻ ነው"

የእውነት የፍቅር ሀይቅ ጋር ድንገት መጥተው አጠገቤ የተቀመጡት ሽማግሌ ከህይወት ልምዳቸው በመነሳት እጅግ ውድ ምክሮችን ሰጡኝ:: በመጨረሻ መርቀውኝ እና በወጣትነት ዘመኔ የእግዚሐብሔርን ቃል በሚገባ ማንበብ እንዳለብኝ አበክረው መከረውኝ እኔም አመስግኜያቸው በፍቅር ሀይቅ ላይ ፀሐይ ስትጠልቅ ያለውን ግሩም ድባብ አይቼ ባጃጅ በመያዝ ወደ ዩኒቨርሲቲው ተመለስኩ::

ህይወት በሀዋሳ ቀጥላለች:: ትምህርት እያለቀ ነው:: በተለይ ወንድ ተመራቂ ተማሪዎች ተመራቂ ነን ለማለት ይህን የፈረደበት ሱፍ ለብሰው መንጎራደድ ጀምረዋል:: የእውነት ግን ተመርቀዋል? የእውነት በቂ ሥነምግባር ፣ በቂ እውቀት ፣ በቂ በራስ መተማመን፣ በቂ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ፣ በቂ የስራ ኃላፊነትን የመሸከም ሞራል፣ በቂ የአዕምሮ ዝግጅት አድርገዋል? አይመስለኝም:: የኢትዮጵያ እና ህንድ ዩኒቨርሲቲዎች ዋነኛ ጥረታቸው ቁጥር ላይ ብቻ ነው:: ይህን ያክል ተማሪ ተመረቀ ለማስባል ብቻ እንጂ ከሚመረቁት ተማሪዎች የማይመረቁት ይበዛሉ:: አብዛኛው ተማሪ የሚመረቀው ላለመመረቅ ነው:: የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች እኔ አማራ፣ እኔ ትግሬ፣ እኔ ኦሮሞ ፣ እኔ ወላይታ... እኔ ቅብርጥሶ እያለ ዘር እየቆጠረ እንደጋርዮሽ ዘመን ድንጋይ እያነሣ የሚቧቀሰውን ወጣት አዕምሮ ሞርደው እንኳ መች በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ቀርፀውት ማስመረቅ ቻሉ? ለቁጥር ፣

ለወሬ፣ ለቦለቲካ ቁማር ብቻ ይህን ያህል ተማሪ ተመረቀ ለማስባል ብቻ እንጂ ከሚመረቁት ተማሪዎች የማይመረቁት ይበዛሉ:: አብዛኛው ተማሪ የሚመረቀው ላለመመረቅ ነው:: የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች እኔ ለቦለቲካ ቁማር ብቻ ይህን ያህል ተማሪ ተመረቀ! ይህን ያህል ዩኒቨርሲቲ ተከፈተ! እየተባለ ነጋሪት መጎሰም እንዴት ያበሳጫል!? በቀላሉ ሞራላቸው እንክት የሚል፣ ስለተመረቁበት ትምህርት እንኳ በተገቢው ማስረዳት ተራራ የሚሆንባቸው፣ በራስ መተማመን የሌላቸው፣ በቅቧቃ ተማሪዎችን ብቁ ናችሁ ተብሎ ለቦለቲካ ቁማር ብቻ ማስመረቅ እንዴት በንዴት ያጨሳል? በዚህ ሁኔታ እርር፣ ቅጥል ፣ ድብን እያልኩ በአገሬ ኢትዮጵያ እያዘንኩ የምርቃት ቀኔ ደረሰ::

የምርቃቴ ቀን አጎቴ ደስ እንዲለው በፈገግታ ተሞልቼ ለመታየት ሞከርኩ:: የመመረቂያ ልብሴን አድርጌ አጎቴ ሲመለከተኝ አቤት ያየሁበት የደስታ ብዛት! አቤት እንዴት እቅፍ አድርጎ እንደሳመኝ! አቤት በደስታ እንዴት እንደ ህፃን ልጅ  እንደቦረቀ!... የምርቃቴ ቀን ማታ ህዋሳ በሚገኘው አጎቴ አስቀድሞ አልጋ የያዘበት ኢንጆሪ የተሰኘው መልካም መስተንግዶ ያላቸው ሆቴል ውስጥ እራት እየበላን

"የእኔ ልጅ እንደዛሬ ደስ ብሎኝ አያውቅም! ተመረቅሽልኝ! አሁን ለአገርሽ ኢትዮጵያ አገልግሎት የምትሰጪበት ዘመን ደረሰ ማለት ነው:: እውነተኛ፣ ታማኝ ፣ ሁሉንም በቅን የምታስተናግድ፣ ሙስና የማታውቅ ሰራተኛ ትሆኛለሽ ማለት ነው! የእውነት በጣም ነው ያኮራሽኝ!!" አጎቴ ገና አኮራሃለሁ! ቀን ቀን እየሰራው በማታው ክፍለ ጊዜ ሁለተኛ ዲግሪዬን ለመማር ወስኛለሁ:: በትምህርት አለም አለቀ የሚባል ነገር አለመኖሩን መቼም ታውቃለህ?"

"በሚገባ የእኔ ልጅ!!" በማለት አሁንም በፈገግታ ተሞልቶ እየተመለከተኝ

"የእኔ ልጅ አገርሽ ኢትዮጵያ ላይ ተፅህኖ መፍጠር የምትችይ አንዲት ጠንካራ ሴት እንደምትሆኚ ተስፋ አደርጋለሁ!!"

"እኔም ውስጤ የሚለኝ ያንን ነው:: አጎቴ በተለይ ስለ አገሬ ኢትዮጵያ ችግር ማውራት ሳይሆን ቢያንስ ከኢትዮጵያ ችግሮች አንዱን መፍታት እና መፍትሔ መስጠት የምትችል ችግር ፈቺ ሴት መሆን እፈልጋለሁ! መፈለግ ብቻ አይደለም እንደማደርገውም

አርግጠኛ ነኝ! እጎቴ ገና እንደ ንስር በከፍታ እበራለሁ! ለአገሬ ጠቃሚ ነገሮችን እሰራለሁ! ስኬታማ እሆናለሁ! ውስጤ የሚለኝ ይህን ነው"

እጎቴ ከተቀመጠበት በመነሳት ግንባሬን ሳመኝ ፤ ከዚያ መልሶ ተቀመጠ፡፡ በትኩረት እያየኝ

"ኀበዝ የእኔ ልጅ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያን ችግሮች የሚያወራ ሳይሆን ቢያንስ የቻለውን አንድ ችግር ለመፍታት ጥረት የሚያደርግ ነው፡፡ አየሽ አባቶቻችን በነፃነት እንድንኖር በእደዋ ላይ ደም እና አጥንት ከስከሰው ይቺን አገር አስረከበውናል እኛም ለሚቀጥለው ትውልድ የምትመች ኢትዮጵያን ሰርተንላቸው ማለፍ ይኖርብናል፤ ስለዚህ የእኔ ልጅ የአገርሽን ችግር ለመፍታት እንደንስር በከፍታ ብረሪ! እውነተኛ ኢትዮጵያዊት ሴት ሁኚ! እምላክም ከልበ ቅኖች ጋር ስለሆነ ይረዳሻል"

ከእጎቴ ጋር ምግባችንን መብላት ቀጠልን፡፡ ከሚያምረው ሆቴል ውስጥ በዝቅተኛ ድምፅ ሙዚቃ ተከፍቷል፡፡ የቴዲ አፍሮ ሙዚቃ... ምግቢን እየበላሁኝ ሙዚቃውንም ማጣጣም ያዘኩኝ፡፡ ህይወት ራሷ ማጣጣም አይደለችም??

... እግር ይዞ እንዴት አይሄድም
ሰው ወደፊት አይራመድም
እፈር ይዞ ውስጡ እረንጓዴ
ለምን ይሆን የራበው ሆዴ?"

# ድ
# ህ
# ረ
# ታሪክ

(ከ2009 ዓ.ም እስከ...)

እያንዳንዱ ነገር የጊዜ እስረኛ ነው፡፡ እነሆ በተያዘው እቅድ እና ቀን መሠረት ከሀዋሳ ጣጣዬን ጨርሼ ስመለስ ሁካታ እና ግርግር ባልበዛበት በጣም ደስ በሚል የሠርግ ሥነ ሥርዓት አንቴ ፍቅረኛውን ከአነ ልጁ አገባት፡፡ ቤታችን በሣቅ እና ፌሽታ ደመቀ፡፡ እኔም በተመረኩበት ሙያ አገሬ ኢትዮጵያን በትጋት እየሰራሁ ለማገልገል በመወሰን ባለኝ ምርጥ ውጤት የተነሣ በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ስራ ጀመርኩ፡፡ በዚያው ጎንለጎን ስራ ለሌላቸው ቢያንስ አስር ሰዎች ስራ የሚያገኙበትን የራሴን የግል ድርጅት ለመክፈት የገበያ እና የቦታ ጥናት ማከናወን ጀመርኩ፡፡ አንዲት ስኬታማ እና ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ሴት ለመሆን ወሰንኩ፡፡

በመጨረሻ አንድ እውነት ውስጤ ሰረፀ፡፡ ያን እውነት ማብላላት ያዝኩ፡፡ ከራሴ ጋር ክርክር ገጠምኩ፡፡ እኔ ሳልሆን እውነት አሸነፈ፡፡ ያ እውነት በውስጤ ገዘፈ፡፡ ያ እውነት በውስጤ ነገሰ፡፡ ያ እውነት በልቤ አበራ፡፡ እነሆ ብዙ ገንዘብ ማሰባሰብ ሀጢያት አይደለም ግን ከንቱ ነው፡፡ ምድራዊ ነው፡፡ የሚወዱትን የልብ አፍቃሪ በደማቅ ሠርግ ማግባት ደስ ይላል ግን ከንቱ ነው፡፡ ቤተሰብ ማፍራት እና ትውልድን መቀጠል ደስ ይላል፡፡ ግን ከንቱ ነው፡፡ ትኩስ እንቅልፍ በሚነሳ እውነተኛ ትኩስ ፍቅር መያዝ ደስ ይላል፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ ማለቂያ ስለሌላት አስደናቂዋ ዓለማችን በእውቀት ማሰብ ደስ ይላል፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ ከሚወዱት የራስ ሰው ጋር በፍቅር ቀልጦ ጊዜን ማሳለፍ ደስ ይላል፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ በአለም ዝነኛ መሆን ደስ ይላል ፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ከዓመታት ልፋት በኋላ በአሪፍ ውጤት መመረቅ ደስ ይላል፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ በአሪፍ ደሞዝ ስራ መቀጠር ደስ ይላል፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያዊነትም ሆነ ዓለም አቀፋዊነትም ማውራት ደስ ይላል ግን ከንቱ ነው፡፡ ስለ ፍልስፍና ፣ ስለ ጥበብ፣ ስለ ህይወት፣ ስለ ህይማኖት ማውራት ደስ ይላል፤ ግን ከንቱ ነው፡፡ ሁሉ ነገር ደስ የሚል ከንቱ ነው፡፡ ሁሉ ነገር በሣቅ የሚሞላ ከንቱ ነው፡፡ ሁሉ ነገር ህያው የመሰለ ግዑዝ ነው፡፡ ሁሉ ነገር ዘላቂ የመሰለ ጤዛ ነው፡፡ ሁሉ ነገር እውነት የመሰለ ህልም ነው፡፡ ሁሉ ነገር የሚጨበጥ የሚመስል የማይጨበጥ ነው፡፡ ሁሉ ነገር ብርሃን የሚመስል የማይጨበጥ ነው፡፡ ሁሉ ነገር ብርሃን የመሠለ ጨለማ ነው...

የከንቱ ... የከንቱ ከንቱ... ምድራዊ ነው:: ሀዘንም ከንቱ ነው:: ደስታም ከንቱ ነው:: ልጅ መውለድ ከንቱ ነው:: መካንነትም ከንቱ ነው:: ቤተመንግስት ውስጥ መኖር ከንቱ ነው:: በቆሻሻ ከምር ቆሼ መንደር መኖርም ከንቱ ነው:: ማግኘትም ከንቱ ነው:: ማጣትም ከንቱ ነው የበዛ አዋቂነትም ከንቱ ነው:: የበዛ አላዋቂነትም ከንቱ ነው:: ህይወትም ከንቱ ነው:: መሞትም ከንቱ ነው:: ዝነኛ መሆን ከንቱ ነው:: በማንም አለመታወቅም ከንቱ ነው:: እናያለን ግን አናይም ይህም ከንቱ ነው:: እያየን ብናይም አልያም ሳናይሳናይም ከንቱ ነው:: እየሰማን ግን አንሰማም ይህም ከንቱ ነው:: እየሰማንም ባንሰማም ከንቱ ነው:: እየሣቅን አንስቅም ለነገሩ እየሣቅን ብንስቅም ከንቱ ነው:: ያለን ይመስለናል ግን የለንም፤ ይህም ከንቱ ነው:: በቃላት ኳኳታ ተሞልተናል ይህም ከንቱ ነው:: ጨዋነን ይህም ከንቱ ነው:: ባለጌ ነን ይህም ከንቱ ነው ... አንዳችም ከንቱ ያልሆነ በምድር ላይ የለም:: ምድራዊ ፍቅር ሳይሆን ሰማያዊ ፍቅር ግን ከንቱ አይደለም:: እኔ ህይወት፣ ብርሃን ፣ መንገድ፣ እውነትም ነኝ ያለው ግን ከንቱ አይደለም፤ ስለዚህ በመሬት ላይ ሳላችሁ አስቀድማችሁ ከንቱ የሆኑትን ነገሮች ከማግበስበሳችሁ እና ከመሰብሰባችሁ በፊት ከንቱ ያልሆነውን ነገር ሰብስቡ! ይህን ማድረግ ከቻላችሁ የአለምን ጥበብ አወቃችሁ ማለት ነው:: አንዳንዶች በህይወት ይሠክራሉ አንዳንዶች ግን ህይወትን ያሰክራሉ!! የሚለውን ቀመር ዋጃችሁት ማለት ነው:: ከዚያ እንደ ንስር መብረር ትችላላችሁ!!

እ

ነ

ሆ

ውድ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቼና እህቶቼ! ከንቱ ያልሆነውን ልባችሁ ትሻ እና ትዋጅ ዘንድ! ዘንድ! ለሰዎች ይቅርታ ማድረግን ትዋጁ ዘንድ! የልባችሁን ስብራት ትጠግኑ ዘንድ! ለራሳችሁም ለሌሎችም ቅን ትሆኑ ዘንድ! ከተስፋመቁረጥ እና ግራ መጋባት ማዕበል ትወጡ ዘንድ! ህይወትን ታሰክሯት ዘንድ! በተግባር የምትዋጁትን ፍቅርን ልባችሁ ላይ ትሞሉ ዘንድ! የእውነት ብርሃን እንዲመጣላችሁ እመኝላቹዋለሁ!! በማስተዋል ፀጋ እና በፍቅር ፀጋ ተሞልታችሁ ዋጋ ያላችሁ እንድትሆኑ እመኝላቹዋለሁ!! እዚህ ጋር ከእኔ ጋር እንሰናበት:: ይህ የእኔ የእሊኒ ፍቅር ታሪክ ነው:: በሀሳብ የተወለደ ምናባዊ ፈጠራ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ የተከናወነ እውነተኛ ታሪክ... ዛሬ አንዲት ሌላ ወጣት ስለሆንኩኝ እና ልቤ በፍቅር ስለተሞላች

በውስጤ የነበረውን የተደበቀ በገዛ አባቴ እና በብዙ ወንዶች በመደፈሬ የተነሣ የሰረፀብኝን ፍራቻ እና ጥላቻን ቀርፌ አይኑን በድጋሚ አላየውም ያልኩትን የአባቴን መልክ ቁርጥ የሆነውን የአባቴን ልጅ ትልቁ ወንድሜን እና ሌሎቹንም በእህትነት ቀርቤያቸዋለሁኝ፡፡ ለበርካቶችም እንደ እኔ የመደፈር አደጋ እና ሰለባ ለሆኑ እህቶቼ ምናልባት ይቺ የግል ታሪኬ የልባቸውን ስብራት ለመጠገን ጠብታ ትሆን ዘንድ እና ምንም ይሁን ምንም ሺ ምክንያት ከመደርደር ማለትም ህይወቴ የተበላሸው ስለተደፈርኩ ነው! ባልደፈር ኖሮ ይህን ህይወት አልኖርም ነበር... ባልደፈር ኖሮ ይቺን የመሰለች ህይወት ምስቅልቅል ያለባት ሴት አልሆንም ነበር... ባልደፈር ኖሮ ስብራት አይኖርብኝም ነበር... ኖሮ ... ኖሮ... ከማለት ይልቅ በቆራጥነት ስለ አሸናፊነት ያስቡ ዘንድ ታሪኬን አቋድሻለሁ፡፡ በተረፈ ማንም የቆመ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ እያልኩኝ ለአገሬ ኢትዮጵያ መልካም በመመኘት ልጨርስ ፤ ፍቅር እና አንድነት ለአገራችን ኢትዮጵያ ይሁን፡፡ አሜን! አምላካችን እግዚሐብሔር የተሰፋይቷን ምድር ይባርካት፡፡ አሜን! ለህዝቦቿም የማይናወጥ ሰላምን ያንግስባቸው፡፡ አሜን! ጥላቻን! ትዕቢትን! ዘረኝነትን! ራስ ወዳድነትን! ከኢትዮጵያ የእግዚሐብሔር ጣት ይሰውራቸው... አሜን!!

እሌኒ ፍቅር

አዲስ አበባ—አበበ ቢቂላ ስታዲዮም

ኢትዮጵያ፡፡

__ማሳሰቢያ፡-__ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን የጥንቁልና እና አጋንንት መጥሪያ ቃላትን እንዳይጠቀሙ! ቃላቱ ተቆራርጠው የተፃፉ ቢሆንም አጋንንት እና እርኩስ መንፈስ መጥሪያዎች ናቸው፡፡


ኢያሪኮ 777
ኢያሪኮ 999
FM 66.6
በኢያሪኮ ከተማ
ለሚስቴ
ፍለጋ